# ሽብርተኞች

እውነተኛ የወንጀል ታሪኮች



# ስድስቱ

# ወንጀለኞች

( እውነተኛ የወንጀል ታሪኮች )

**The World's Great Detectives and Their Most Famous Cases**


አዘጋጂዎች፡-

ብሩስ ሄንደርሰንና ሳም ሱመርሊን

*By Bruce Henderson and Sam Summerlin*

ትርጉም

ጌታቸው መኩንን ሐሰን ( ሌ/ኰሎኔል )



አ ዲ ስ አ በ ባ

ግንቦት 1981

የተርጓሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው ።

የሽፋን ሥዕል ፥ ሉቃስ አማረ

አከፋፋይ ፡—

ስ. ቁ.—44—19—29

# ማውጫ

ራም ከመከላት በፊት
ገጽ 12
* * *

የሻይ ሲኒዎችና የጉብኝት ካርዶች
ገጽ 33
* * *

የኦፔራ አደራሹ ግድያ
ገጽ 61
* * *

በቺካጉ "የክፍለ ዘመኑ ወንጀል"
ገጽ 99
* * *

ባለቤቱ እንኳ የማታውቀው ጉድ !
ገጽ 144
* * *

ወደር የለሹ አገባቢ !
ገጽ 181
* * *

## ምስጋናና ማስታወሻ

በጉ አሳቢዎች ለሀገርም ሆነ ለወገን የሚበጀውን ያበረታታሉ ፣ ይደግፋሉ ፣ በዚህም ለትውልድ ቁም ነገር ጥለው ያልፋሉ ። የኒህ ተቃራኒያን ግን በአስመሳይነት በታጀለው ካባቸው የታታሪዎችንና የበጉ አሳቢዎችን ጥረት ያኮላሻሉ ፣ ወይም ያፍናሉ ፣ ወይም ያንኳስሳሉ ከዚህ የበለጠ የሚያደርጉት የለምና ። ለመሆኑ ከዚህ የከፋ ወንጀል አለመኖሩን እንደት ማወቅ ተሳናቸው? ። ለዚህና ለተከታዩ የትርጉም ሥራ ውጤት ብዙ ጥረቶች በደካሞች ቢሰናከሉም በበጉ አሳቢዎች ጥረት ከዚህ ደርሷል ። በዚህም ቀና መንፈስ የዕውቁ ደራሲ የማሞ ውድነህንና የጓድ ሥምረት ክፍለየሱስን የቅርብ ክትትልና ድጋፍ አመሰግናለሁ ።

* * *

ይህንና በተከታታይ የሚቀርበውን የምርጥ መርማሪዎች አስደናቂ ውጤቶች ለአንባቢያን ለማቅረብ በሚያስችል ሁኔታ መሠረታዊ ገንዛቤን ያስጨበጠኝን የኢትዮጵያን ፖሊስ ኮሌጅ ልዘነጋው ስለማልችል ማስታዎሻነቱ ለኢትዮጵያ ፖሊስ ኮሌጅ ነው ።

247

## የአዘጋጁ መልዕክት

የመጀመሪያ የወንጀል ልብ - ወለድ "ግድያ በሩምርግ" የተባለው የኤድጋር አላንፖ መጸሐፍ ከታተመበተ ጀምር ከአንድ ምዕተ ዓመት በላይ የአንባቢያንን መንፈስ ፡ መስጦ ቆይቷል ።

ለምሳሌ በፓሪሱ መርማሪ የተሳለው አውግስት ዱፒን አስደንጋጭ የሩምርግ የግድያ ምስጢርን ሲፈታ ወይም ደግሞ የማርቲን ቤክ የፈጠራ መርማሪዎች ወንጀለኛውን ሲያድኑ የሚተርኩት መፃሕፍት የብዙዎችን አንባቢያን መንፈስ እየሳቡ የፈጠራ መርማሪዎችን ሥራ አድናቂዎች አድርገዋቸዋል።በአንፃሩ ግን ስለእውነተኛው የምርመራ ሥራና ክትትል እምብዛም ትኩረት አልተሰጠበትም ።

አደገኛ ወንጀለኞች 'ታዋቂ' እየሆኑ እነሱን ይዞ በወንጀለኛነታቸው ለሕብረተሰቡ በማጋለጥ እንዲታወቁ የሚያደረገው መርማሪ ግን ማንነቱ ከታሪክ በስተጀርባ የውኃ ሽታ ሆኖዋል ። ይህ ለምን ሆነ? ለሚለው ጥያቄ አንድ ታዋቂ ዐቃቤ ሕግ ሲያስረዱ "አንድ ትንሽ ስህተት ከፖሊስ ከተገኘ ተገልጋዩ ሕዝብ ጋራ አሳክሎ በማጋነን ፖሊሱ ምንም የማይሰራ ዓይነት አድርገው በወሬ ያወኩትል ። በአንፃሩ የፖሊስ ክፍል ውጤት ያለው ተግባር እንዲያከናውን የሚበጀውን በማገገዝ በኩል ግን የሚደረግ ምንም የለም ፣ ቢባል ከውነት የራቀ አይደለም ።" ሲሉ በተገልጋዩ ሕዝብና በፖሊሱ መሐከል ያለው ግንኙነት ለሥራው ወሳኝ መሆኑን አስረድተዋል ። አስተያየታቸውንም በመቀጠል ሲናገሩ "እንዲያውም ፖሊስ እኛ የማንወደውን አስልቺ ሥራ ለመስራት የቆመ አድርገን የወሰድን ብዙ ነን ።" ብለዋል ።

ይህ አባባል በአሁኑ የወንጀል ድርጊት መብዛት አኳያ ሲታይ ሐቅነቱ የጉላ ነው።ወደ ተነሳንበተ ታሪካችን እንመለስና በዚሁ የፈጠራ ወንጀል ትረካ ዋና የታሪኩ ባለቤት ሆነው በሚቀርቡት እንደየኒውዮርኩ መርማሪ ሊዲ ሊጋንና እንደ ተባባሪው ፍራንክ ሰርፒኮ በዓለማችን ዙሪያ በግልጽ የሚፈጸሙትን ወንጀሎች በመከታተል ምስጢራቸውን

በማውጣት ገላጭ ከሆኑ ጽሑፎች ጉን ድርጊቱን በፊልም የሚተር
ኩ ሥራዎች እንደለሸን ፈልተዋል ።

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ እስከ ለሁን በተመሳሳይ ከተፃፉት መጽሐ
ፍት በታዋቂነታቸውና በአስደናቂነታቸው ለንባቢያንን የሳቡትን
በመምረጥ በውስጣቸውም ያለውን የወንጀል ታሪክ ለሁን ከለ
ለንበት ዘመን የወንጀል ድርጊት ጋር በማዛመድ ሕብረተሰቡ ሊገ
ድበው ያልቻለውን የወንጀል ጉርፍ የሚገድብበትንም መንገድ
አብሮ እንዲያየው ለማድረግ ነው ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ድንቀ መርማሪዎች በስማቸው
ክብደት ሉቻ የማይገኙላቸው መርማሪዎች ሆነው እንዲቀርቡ የተሰ
ጣቸው ስም ሪድ ፤ ሸኒቨር ፡ ለጊ ፡ ኩሶ ፡ ኖቭል ፤ ሀንሰን ፡ ሊ. ኮክ
እና የመሳሰሉትን መሆኑን ማስረዳት እንወዳለን ።

በመጽሐፉ የቡድን ሥራና አዳዲስ የቴክኖሎጂ የሥራ
ውጤቶችን መጠቀም በሊላው የሕይወት መስክ አስፈላጊ እንደ
ሆነው ሁሉ በፖሊስ ሥራም አስፈላጊና ወሳኙነት እንዳለው
ለመመልከት ይቻላል ።

በአገር ውስጥም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ በጣም ጥራት ባ
ለው በድምጽ ምዝገባ ብቻ የሰውን ማንነትን ከሚገልጹ መሣሪያዎች
እስከ የውሸት መመርመሪያ ድረስ ባለው መሣሪያ በመጠቀም የፖ
ሊስ ተግባር ይከናወናል ። ይህም ሲሆን ከልምድ የዳበረው የጥንት
የአመራመር ዘዴ አስፈላጊ አይደለም ማለት አይሆንም። በዚህ መጽ
ሐፍ ውስጥ አንድ መርማሪ የሚጫወተው ሚና ቁልጭ ብሎ
ቀርቧል ፡ ወንጀሉ ድንበር ዘለል ከሆነ መርማሪዎች በሚያደርጉት
ሕብረት ወንጀለኛው እንደት እንደሚታደን እንማርበታለን ።
በዚህም

ከኒውዮርክ እስከ ኒስ ወይም እስኮትላንድያርድ ወይም እስከ
ፈረንሳይ ሱሬት ፡ ከቶኪዮ እስከ ቴልአቪቭ መርማሪዎች በአንድ ልብ
በመነሳት ወንጀለኛውን አጥምደው ይይዛሉ ።

መርማሪዎች ለምንድነው በየጉራንጉሩ ገብተው ሕብረተሰቡ
የተፋቸውን ማጅራት መቾዎች ፣ ሕገ ወጥ የፍትወተ ሥጋ ፈፃሚዎችን፣
አጉራ ዘለሉችን፣ ቤት ሰርሳሪዎችን ፣ ሴተኛ አዳሪዎችን፣ የአእምሮ ሕመ
ምተኞችንና የመሳሰሉትን የሚያድኑት ? ምክንያቱን በጽሑፍ ውስጥ



ቀየት ብሉ በዝርዝር ብናገኘውም ለአሁኑ ግን አንድ በኒውዮርኩ
ብሮንክ ነዋሪ የሆነ ነባር ፖሊስ የሰጠውን አስተያየት እናቀርብላ
ችሁ ፡ “ ብዙዎቹ መርማሪዎች ጊዜ የማያመጣው ምንም ነገር
እንደሊለ ለመገንዘብ ይሳናቸዋል ። ለምሳሌ ወንጀሉ በራሱ
በመርማሪው ቤተዘመድ ላይ ሊፈጸም ይችላል ፤ በማንኛውም ጊዜ
ቢሆን አንድ መርማሪ አንድ ወንጀል ሲከታተል በራሱ ላይ እንደ
ተፈጸመ አድርጉ ትኩረት መስጠት አለበት ። በመሆኑም በማንም
ላይና የትም ክትትልና ምርመራ ማድረግ የግድ ነው ” በማለት
ምክሩን አካፍሏል ።

የፖሊስ ተግባር በአሁኑ ጊዜ በአሜሪካ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም
አገሮች ከበሬታ እያገኘ ነው ። የተቀጣላቸውን መርማሪዎች የሚከነ
ክነን አንድ ጥያቄ አለ ፤ ይኸውም በአለማችን ላይ ማነው ቀልጣፋ መር
ማሪ ? እንዴትስ ነው ሥራውን የሚያከናውነው ? የሚሉት ሲሆኑ
የዚህ መጽሐፍም ዓላማ ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት ያተኩ
ራል ።

መጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱት ቀናትና ድርጊቶች ሁሉ እው
ነተኛ ናቸው ፡ አንዳንድ ስሞች ተተተዋል ወይም በሊላ ተተክ
ተዋል ፤ ይህም የተደረገው ጥፋተኛ ያልሆኑ ከታሪኩ ጋር ግንኙነት
የነበራቸውን ሰዎች መብት ላለመንካት ተብሎ ነው ።

# መግቢያ

የፖሊስ ምርመራ፣ ታማኝነትን፣ አስተዋይነትን፣ ልባዊ የሙያ ዝንባሌን፣ ጠንቃቃነትን፣ ምስጢር ጠባቂነትን፣ ቆራጥነትን፣ የምርመራ ጥበብ ችሎታንና ሰብአዊነትን የሚ ጠይቅ ነው ። ረጅም ዘመናትን ባሳለፈው የፖሊስ ታሪክ እንደሚታወቀው ፖሊስ በተለያዩ ሀገሮች በተለያዩ ነገሮ ችና ፍጥረታት ተመስሏል ። " ፖሊስ እንደ እርግብ የሠ ላም ምልክት ነው " የሚሉም አሉ ። ያም ሆነ ይህ በተ ለይ የፖሊስ የምርመራ ሥራ ከላይ የተጠቀሱትን ለማሟ ላት መቻል አለበት ።

የዚህ መጽሐፍ ተርጓሚ ከልጅነት አንስቶ በነበረ ውና አሁንም ባለው ልባዊ የሙያው ፍቅር በርካታ የፖሊስ የምርመራ ውጤት ማኅደሮችን አገላብጧል ። በመላው ዓለም ድንቅ ናቸው የተባለላቸውን የፖሊስ ምርመራ ውጤ ቶችንም ለመቃኘት ሞክሮአል ፤ በሙያውም በመማር ፣ በመሥራትና በማስተማር ግንዛቤ ለመውሰድ ችሏል ። ከዚህ ሁሉ የተገነዘበው ጥቂት ነገር ቢኖር የፖሊስ የም ርመራ ውጤቶች በአዝናኝ ፣ በአሳዋቂነትና በአስተማ ሪነት ባህሪያቸው በልብ ወለድና በእውነተኛ ታሪክ መልክ እየቀረቡ በመላው ዓለም ተነባቢነትን ሲያ ገኙ በሀገራችን መጠነኛ እንኳን ሙከራ ያለ መደረጉን ነው ። ተርጓሚው የፖሊስ ምርመራ ውጤቶችን የማቀ ናበር ልምድ የአብዮታዊ ፖሊስ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ በነ በረበት ጊዜ የፖሊሶች ምርጥ ምርመራ ውጤት አምድ ላይ

በተለይ የሀገር ውጭ የምርመራ ውጤቶችን ሲያዘጋጅ ለማዳበር ቢቻለውም በዚህ የመጀመሪያ የትርጉም መጽሐፍ ግን ልምዱን በተቻለው ሁኔታ ተጠቅሟል ።

የፖሊስ የምርመራ ውጤቶችን ለመተርጐም መጠነኛም ቢሆን የሙያው ግንዛቤ ወሣኝነት ያለው ሲሆን ለሀገራችን አንባቢያን በአመቺ ሁኔታ ለማቅረብ ግን ጥቂት ጥረትን በተጨማሪ መጠየቁ አይቀርም ። በመሆኑም ተርጓሚው ከጉዳዩ ዋና ጭብጥና ተከታታይ ሁኔታዎች ሳይዘል አንባቢያን ያለችግር ሊገነዘቡት በሚችሉት መልክ ለመተርጐም ሞክሯል ።

የፖሊስን ዕውቅ መርማሪዎች ልዩ የሚያደርጓቸው ባህሪያት አሏቸው ። አንዳንዶቹ በሳይንሣዊና ቴክኒካዊ ምርመራ ላይ ልዩ ትኩረት ሳይሰጡ ወንጀለኛውን በማያወላዳ ማስረጃ ያጋልጣሉ ፤ ሌሎች በምርመራ ታክቲክ በመጠቀም የበለጠ ውጤት ለማግኘት ሲችሉ የማግባባትና መስሎ የመቅረብ ጥበብ ያላቸውም መርማሪዎች ውጤታማ ናቸው ። የዚህ የመጀመሪያ ክፍል 6 የምርመራ ውጤቶችም የ6 ታዋቂ የፖሊስ መርማሪዎችን ልዩ የምርመራ ችሎታና ባህሪይ ሊያስነብቡ ይችሉ ዘንድ ተመርጠው ተተርጉመዋል ። ዋናው መጽሐፍ በ2 ክፍል የተከፈለ በመሆኑ በ2ተኛው መጽሐፍ የሚቀርቡትም ሌሎች 7 ዕውቅ መርማሪዎችና ድንቅ ውጤቶቻቸው እንዲሁ 7 ዓይነት ልዩ ችሎታና ባህሪያትን ያንፀባርቃሉ ። በተቻለ መጠን ተስማሚውን ባህሪ የመውረሱ ጉዳይ ግን አዋቂነት ነው ። በዚህ አጋጣሚ የመርማሪዎቹን የኋላ አጭር ታሪክ እንደ ወንጀለኞቹ መጠቀሱ መርማሪ ከምን ዓይነት ዝንባሌና ችሎታ ሊፈልቅ እንደሚችልም ያስረዳል ።



በዚህ መጽሐፍ የቀረቡት የምርመራ ውጤቶች በአብዛኛው በሰለጠነው ዓለም ያሉት ፖሊሶች የምርመራ ውጤት ሲሆኑ ወንጀሎቹም በብዛት ሊከሰቱ የሚችሉት በዚያው በሰለጠነው ዓለም ነው ። ይህም ሲባል በታዳጊ ሀገሮች መሰል ወንጀሎችና ተመሳሳይ ክስተቶች አይኖሩም ማለት አለመሆኑም መታወቅ ይኖርበታል ። በምርመራ ጥበብ ረገድም ታዳጊ ሀገሮች ባላቸው የፖሊስ አቋም የሚስተካከሉ የምርመራ ውጤቶችን አስገኝተዋል።

ሆኖም አንዱ ከሌላው የሚቀስመው የተሻለ አሠራር መኖር ስላለበት የምርመራው ሥራና ውጤት በዚህ መንፈስ ሊወሰድ ይገባል ።

ተርጓሚው የተመሰጠበት ዋና ጉዳይ በሰለጠነው ዓለም የመርማሪዎች ደረጃ ከፍተኛ መሆኑንና ለዚህ ጉዳይ ኃላፊነት የሚሰጣቸው ደግሞ በሳልና በተለይ በሙያው አዋቂዎች በመሆናቸው ሁኔታ ነው ።

አንባቢያን ከወንጀሉ መንስኤና አፈጻጸም እንዲሁም ከመርማሪዎቹ ልዩ ጥበብና ችሎታ ላይ የሚኖራቸውን ትኩረት ያለመሰልቸት ለመጠበቅና ከቁምነገሩ ላይ ልብ እንዲሉ ለማድረግ አንዳንድ አስፈላጊ ያልሆኑ ዝርዝር የግለሰብና የቦታ ስሞች ፤ አገላለጾች ወዘተ . . . እንዳሉ ተትተዋል ወይም በከፊል ተገልፀዋል ፤ ወይም ግልጽ ሊሆን በሚችል ሁኔታ ቀርበዋል ። ዓምተ ምህረቱ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ነው ።

ሌ/ኰሎኔል ጌታቸው መኰንን

አዲስ አበባ 1981

# ራም "ከመከላት በፊት"

ዕለቱ ሰኔ 8,1949—ምሽት ላይ ነው ። በፓሪስ ከተማ
ቦስኩዌት ተብሎ በሚታወቀው አውራጐዳና ዳርቻ ላይ
ከሚገኘው እንድ የተንጣለለና የታወቀ ምግብ ቤት ሦስ
ት ሰዎች ፍጹም በተመስጦና ነገር ዓለሙን ሁሉ ረስ
ተው በግል ጨዋታና ጉዳያቸው ላይ ያተኮሩ በመሰለ
ሁኔታ ራታቸውን ይመገቡ ነበር ። ከነዚያው ፍጹም
በተረጋጋና በወዳጅነት ስሜት ተዝናኝዎች መካከል አን
ደኛው ባለ ጥቁር ሉጫ ጠጉር ቀጫጫና ዓይነቀዝቃዛ የመ
ሆኑ ሁኔታ ከሌሎች ጓደኞቹ ለየት የሚያደርገው ከመሆኑ
በስተቀር በጋራ ጉዳይና ስሜት ላይ በአንድ ልብ የመወያዩ
ታቸው ጉዳይ አጠራጣሪ አልነበረም።የሆነ ሆኖ ያው ዓይነ
ቀዝቃዛ ሰው ኤሚል ቡሶን በመባል የሚታወቀው አደገኛ
ወሮበላ ነበር ። ኤሚል በፈረንሣይ አገር በወሮበላነት ተግ
ባሩ የለየለትና የታወቀ በተለይ ከፍተኛ አደጋ ፈጽሞ ፈጥኖ
የመሰወር ልዩ ችሎታ የነበረውና የሰላማዊ ሰው ጠር ነበር።
ሁለተኛው ሰው የኮርሲካው ተወላጅ ኦርሶኒ በመባል
የሚታወቀው ሲሆን ፡ ሦስተኛው ደግሞ በቡሶን የወሮበላ
ቡድን በጀሌነት ይሠራ የነበረው ዬዜሬ ፖሌድሪ ነበር ።
የሚገርመው ጉዳይ ቢኖር የብዙ ዘመን የኤሚል ጓደኛ
የነበረው ፖሌድሪ ይቀምሳት የነበረችው እራት የሕይ
ወቱ የመጨረሻ ጽዋ መሆኗን ቅንጣትም ያህል ለመ
ገንዘብ ወይም ለማጤን ያለመቻሉ ነበር ። ኤሚልም
ቢሆን ከፖሌድሪ ጋር ያሳለፈው የረጅም ዘመናት የወ
ዳጅነት ጊዜያትና ጓደኝነቱ በዚያን ጊዜ ዋጋ ሊኖረው



አልቻለም ። ይህ ሁሉ ግን ያለምንም ምክንያት አልነበረም።
የኤሚል አንጀት እንደዚያ ሊጨክንና ሊቆርጥ የቻለበት
ራሱን የቻለ ምክንያት ነበረው ። ይኸውም ፖሌድሪ ሞ
ሪስ ዩቬስ "ዓሣ አጥማጅ" በሚል ቅጽል ስም የሚታወቀ
ውን ጓደኛውን በስለት እንዲገደል በማድረጉ ኤሚል የልብ
ቂም ስለያዘበት ነበር። ኤሚል በዚያ ቂም ሳቢያ ፖሌድሪን
ለማጥፋት ከወሰነበት ቀን ጀምሮ አንዳችም ጥርጣሬ ሳያ
ሳድር ለመግደል ደፈጣ ካደረገ ውሎ አድሯል ። የግድያ
ድርጊቱን ለመፈጸም የሚያስችሉትንም ሁኔታዎች እንዲሁ
ካመቻቸ ብዙ ቀናት አልፈውታል ። በረጅም ጊዜ እቅዱም
በዚያን ዕለት ልክ ከምሽቱ 4 ሰዓት ሁለት ሌላ የወንጀሉ
ተባባሪዎች ሊስመልጡት ይችሉ ዘንድ በዋናው አውራጐዳና
በመኪና እንዲደርሱ ቅድሚያ ዝግጅት አድርጐ ነበር ።
ከሚችም ጋር ለብዙ ጊዜ ለመተያዩት ያለመቻላቸውን እን
ደምክንያት አድርጐ የራቱን ግብዣ ያቀነባበረው ኤሚል
ወደ ምሽቱ ሦስት ሰዓት ተኩል ሲሆን የመጨረሻዋን ኮኛ
ካችንን እናንሳ በማለትና ለፖሌድሪ የረጅም ዕድሜ መል
ካም ምኞቱን እገልጻለሁ ብሎ ብርጭቆውን አነሳ ። ሁሉም
በዚያው የመልካም ምኞት ሥርዓት መግለጫ በፈገግታና
በደስታ ብርጭቆዎቻቸውን እንስተው ስለተደረገውም መ
ስተንግዶ የተሰማቸውን ደስታ ገለጹ ። ኤሚልም የሚ
ፈለግበትን ሂሣብ ካጠናቀቀ በኋላ ወደሠፈራቸው ለመ
ሄድ የሚያስችላቸውን አውራ ጐዳና እንዲይዙና እግራቸ
ውን እያፍታቱ ሊጓዙ የሚችሉ በማስመሰል በጨለማ ወደ
ወጥመድዋ መንገድ ይመራቸው ጀመር ። በድንገትም ወደ
ነሱ አቅጣጫ የምትመጣ የመኪና ድምፅ ሰሙ ። ኤሚልም
እጅግ በቀለጠፈ ፍጥነትና ፋታ በሌለው ሁኔታ ሽጉጡን
መዞ ጥይቱን በፖሌድሪ አካል ላይ ላካት ። ኦርሶኒ
በዚያ ድንገተኛና አስቃቂ ሁኔታ በመሸበር እግሬ አው
ጪኝ ብሎ ሲሮጥ ኤሚል ወደመጣችለት መኪና መሮጥ

ጀመረ ፤ ወዲያውም በቅድሚያ ከተቀነባበረው እቅዱ
ውጭ በግል ስሜቱ ኃይል ተገፋፍቶ ገዳይ ጥይቱን ወደላ
ከበት ወደፖሌድሪ ተመልሶ የተዘረረውን የጓደኛውን ሬሣ
አገላብጦ አፉን ከከፈተ በኋላ ዳግመኛ እንዳይናገር የመ
ጨረሻ ማስጠንቀቂያ በማለት በምላሱ ላይ ተኮሰበት ።
በዚህም የቁጭት ጥማቱን ተወጥቶ በተዘጋጀችለት ተሽከ
ርካሪ ተሳፍሮ እንደተለመደው በፍጥነት ተሰወረ ።

በጓደኛው ላይ የፈጸመው አሰቃቂ የወንጀል ድርጊት
ኤሚል ከፈጸማቸው ወንጀሎች መሀከል የተለየ ዓይነት
በመሆኑ በፖሊስ የወንጀል ታሪክ ውስጥ የፈረንሳይ
አል—ኩፖን የሚለውን ደረጃ አስጥቶታል ። በዘመ
ኑም በፈረንሳይ የታጠቁ ወረበሎች እንደልብ እተየ
ዘዋወሩ ይህን መሰሉን ወንጀል የሚፈጽሙ ቢሆንም በኤ
ሚል ቡሶን የሚመራውን የወሮበላ ቡድን ያህል የሚፈራ
ግን አልነበረም ። በተለይም ኤሚል ልዩ ጥበብ በተሞላው
ተሽሎክሉኮ የማምለጥ ዘዴው የፈረንሳይን ፖሊሶች ይ
ጫወትባቸው ስለነበር “ የማይማረክ ” የሚል ቅጽል ስም
ና ታዋቂነትን አግኝቷል ። እንዲያውም በሱ ምክንያት በየ
አውራ ጐዳናና በየመንደሩ የውንብድና ፣ የዝርፊያና የግድ
ያ ወንጀል በመጧጧፉ ሰው ሁሉ በሰላም አምሽቶ የመ
መለሱን ጉዳይ ይጠራጠር ነበር ።

በርግጥ የኤሚል የሰውነት አቋም ይህን ያህል የሚያ
ሸብርና የሚያስደነግጥ ዓይነት አልነበረም ። ሆኖም የፈጣ
ንነቱንና የጨካኝ ቀዝቃዛ ዓይኖቹን ሁኔታ እንዴ ያዩ ሁሉ
የሚረሳው ዓይነት አልነበረም ። ሌላው ልዩ ጥበቡ ወይም
ብልሃቱ የማምለጫ ዘዴውን የሚቀይሰው ተውኔታዊ ሽፋ
ኖችን በመጠቀም የመሆኑ ጉዳይ ሲሆን በዚህም ጉዳት
ካደረሰባቸው ቦታዎች ሳይታሰብ በፍጥነት የማምለጥ ችሎ
ታው የትንግርት ነበር ። ተውኔታዊ ዘዴዎችንና የራሱ





በፈረንሳይ ሕይወት “ ኢንስፔክተር ማይግሬት ” የፈረንሳዩ መርማሪ
ቻርልስ ሽኒሸር ፣ በፓሪስ ሌፍት ባንክ በሚገኘው ቢሮው ። አሁን ከፈረ
ንሳይ ሱሬቴ ናሽናሌ በጡረታ ተገሏል ። ታዋቂ መርማሪነቱ ግን አሁንም
የጉላ ነው ። በግል የቢሮው ግርግዳ የሙራል የመካከለኛው የፈረን
ሣይ ዘመን ምስል ይታያል ። /ብሩስ ሄንደርሰን/

ጥበብን በማዳበር ጉዳት ለማድረስ ካሰበበት አካባቢና ሁኔታ ለመመሳሰል የማያደርገው ዝግጅትና የማይፈጥረው ዘዴም አልነበረም። በሌላ በኩል ደግሞ ይህንኑ አደገኛ ምሽግ ለመናድ ግንባር ቀደም ኃላፊነት የተጣለው በስመ ጥሩውና በዝነኛው የወንጀለኞች ፣ ተከታታይና መርማሪ "ኢንስፔክተር ማግሬት" በመባል በቅጽል ስሙ በሚታወቀው በመርማሪ ቻርልስ ሸኒቨር በመሆኑ ጉዳዩንና ሁኔታውን የተለዩ መልክ ሰጥቶታል ።

ሁለቱ ታዳኞችና አዳኝ ሲነፃፀሩ አንደኛው የአውሬነት ፣ የፈጣንነትና የጨካኝነት ሁኔታ ሲንፀባረቅበት ሌላኛው ደግሞ የትዕግሥተኝነትና የቆራጥነት መንፈስና ሁኔታ ይታይበታል ። ያም ሆነ ይህ በመካከላቸው የተፈጠረው የአዳኝነትና የታዳኝነት ትግል ከአሥር ዓመታት በላይ ሆኖታል ። ራሱ ቻርልስ ሸኒቨር ይህንን ሁኔታ ሲገልጽ "የዕውነተኛውና የእልክ አስጨራሹ የቁማር ጨዋታ ሥራ" ይለው ነበር ።

ኤሚል ይህን መሰሉን ባህሪይ እንዲሁ በቀላሉ የወረሰው አይመስልም ፣ የሕጻንነት ዘመኑና የሕይወት አቅጣጫው ይህንኑ ባህሪይ ሳይጠቁም አላለፈም ። የኤሚል ወላጆች ከሱ ጋር አሥር ልጆችን አፍርተዋል ፣ ከነዚያም መካከል አምስቱ ገና ለአቅመ አዳም ሳይደርሱ በጨቅላ ዕድሜያቸው ተቀጭተዋል ። በዚያ ሁኔታም አእምሮአቸውን የሳቱት የኤሚል እናት በአእምሮ በሽተኞች ሆስፒታል ገብተው እንዳሉ ሕይወታቸው አልፏል ። በመሆኑም የቀሩት ልጆች የነበራቸው አማራጭ ዝርፊያና ስርቆት ብቻ ነበር ። ኤሚልም እሥር ቤትን የሚያውቀው ዘጠኝ ዓመት ከሞላው ጀምሮ ሲሆን በዚያን ጊዜም ሊታሰር የቻለው አንዲት የ15 ዓመት ኮረዳን ከዕቃ ማከማቻ መጋዘን ድረስ



በማጅብ በፋክቱርዋ ተጠቅሞ የማጭበርበር ወንጀል ለመፈጸም በመሞከሩ ነበር ።

በዚያን ጊዜ በፈጸመው ወንጀል የልጅነቱ ሁኔታ ታይቶ በምክር ተለቀቀ። ከሁለት ዓመታት በኋላም እንዲሁ ሌላ ወንጀል ፈጽሞ የወጣት ጥፋተኞች ማረሚያ ፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ በዕድሜው ማነስ ምክንያት እንደገና በምክር ተለቀቀ ። በዚያ መካከልም ቤተሰቡ ከነበረበት ከተማ ወደሌላ ትልቅ ከተማ ሲንቀሳቀስ እርሱም ከተማውን ለቀቀ ። በአዲሱ ከተማም ከታላቅ ወንድሙ ጋር በመሆን በፈጸመው ወንጀል ለፍርድ ቀረበ ፣ በዚያን ጊዜ **16** ዓመት ሞልቶት ስለነበር የመጀመሪያው ፍርድ ተፈረደበት ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም አያሌ የወንጀል ሪኮርዶችን አስመዝግቧል ። ኤሚል ከነወንድሙ በወጣትነቱ የእስር ቤትን አሰቃቂ ሕይወት የተጋፈጠ ሲሆን ከእስር ቤት በማምለጥና በመያዝ በኩልም ልዩ ታሪክ አለው። እንዲያውም ከነወንድሙ ከፈረንሳይ አምልጠው ወደሻንጋይ በመርከብ ከተሻገሩ በኋላ በተለያዩ የቅጥፈት ወንጀሎች ተሳትፋችኋል ተብለው ከሁለት ዓመታት በኋላ በዓለም የፖሊስ ድርጅት አማካይነት ወደ ፈረንሳይ በእሥር ተመልሰዋል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ኤሚልን ልዩ የሚያደርገው ሁኔታ ሲኖር ፣ ያም ከጨካኝነቱና ከማይገታ የውንብድና ተግባሩ ሌላ ፈጽሞ የማይታሰብና ቁጥር ስፍር የሌለው የደግነት ሥራ ለዘመዶቹ መሥራቱ ሆኗል ። በተለይ እህቱ በገንዘብ እንዳትቸገር ሲል ያለውን አራግፎ የመላኩ ሁኔታ ከደግነቱ አንደኛው ባህሪይ ነበር ። በሌላም በኩል በሕጻናት ላይ ልዩ የፍቅር ምልክትም አሳይቷል ።

ኤሚል በማርሰሊስ ከአንዲት ሴትኛ አዳሪ ጋር በፈጠረው ወዳጅነት ለብዙ ጊዜያት አብሯት ይኖር ነበር ። በዚያም ግንኙነት ሴት ልጅ አስወልዷል ። ከብዙ የእሥራት ቅጣት በኋላም የልጇን እናት በሕግና በሥነ ሥርዓት አገባት ። ልጁ ግን ለረጅም ጊዜያት ከነርሶች መዳፍ ሳትወጣ በመንጋጋ ቆልምም በሽታ ምክንያት ሕይወቷ አለፈ ፤ ባለቤቱም የሳንባ በሽታ ሕመምተኛ ስለነበረች በአጭር ጊዜ ውስጥ የልጅዋን መቃብር ተከትላ ተለየችው ። ኤሚል የቤተሰቡ ሁኔታ ክፉኛ መንፈሱን ረብሾታል ። እንዲያውም ከአደገኛና ተደጋጋሚ የወንጀል ድርጊት ለምን ሊገታ እንዳልቻለ ጥያቄ በቀረበለት ቁጥር "ሟች ልጄ በሕይወት ኖራ ቢሆን ኖሮ ከማደርገው ድርጊት እታረም ነበር" በማለት መልስ ይሰጥ ነበር ። የኋላ ኋላም በሕጻናትና በልጆች ላይ የነበረውን ፍቅር ወደእንስሳት አስተላልፎ ነበር ። የሰውን ሕይወት ለማጥፋት ቅንጣት ያህል ስሜት የማይሰጠው ኤሚል እንስሳ ሲሰቃይ ባየ ቁጥር ከፍተኛ ጭንቀት ይሰማው ጀመር ። አንድ ጊዜ ጂሌዎቹን ይዞ በገጠር አካባቢ ሲዘዋወር የአንድ ዓሳማ የጣር ድምጽ በአንድ ቄበሬ ማሳ ውስጥ ይሰማል፤የዓሳማውን አራጅ እንደወንጀለኛ የስድብ ናዳ አውርዶበት ሽጉጡን አውጥቶ በአሳማው እናት ላይአንድ ጥይት ተኩሶ ከገደለ በኋላ "....ይህን እንስሳ ለመግደል ይህን ያህል ማሰቃዩት አይኖርብህም ነበር!" በማለት ከቦታው ተሰወረ ። ያም ድርጊት በፍጥነት በአካባቢው በመዛመቱ የዛኑለት ቡድኑ ከቦታው ለመሸሽ ተገደደ ። የአካባቢው ፖሊሶችም የዓሳማውን ነዳይ ለማግኘት ያደረጉት አስሳም ሳይሳካ ቀረ ።

በሌላ በኩል ደግሞ በሕግ ሊደረስበት የሚችለውን ችግር ከወዲሁ በጥበቡ የመከላከል ዘዴው የሚናቅ



አልነበረም ። አንድ ጊዜ በአንድ ቡና ቤት በምሽት ቁማር ሲጫወት በመሸነፉ ከቡና ቤቱ በራፍ የቆመች አንዲት አውቶሞቢል የኔናት ብሎ በ250,000 ፍራንክ ለአንድ በመኪናዋ ለተመሰጠ ሰው ለመሸጥ ተስማማ ፤ አውቶሞቢሏም የተሰረቀች ስለነበረች የግዢውን ገንዘብ እንዲቀበል ሲጠየቅ እጁ ተሰብሯል ብሎ በርሱ ምትክ ሌላ ሰው ፈርሞ እንዲቀበልለት ያደርጋል ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የመኪናዋ ገዢ የተሰረቀች መኪና ሲነዳ በመያዙ ይታሰራል ። ኤሚልም በተደረገበት ጥቆማ መሠረት "የተሰረቀ አውቶሞቢል ሸጠሃል" የሚል ክስ ቀርቦበት በፍ/ቤት ይጠየቃል ፤ ሆኖም ምንም ተጨባጭ የሆነ የጽሑፍ ማስረጃ ስላልነበረ ስለመኪናዋ የሚያውቀው ጉዳይ እንዳልነበረ ሽምጥጦ ካደ ። ስለሆነም መኪናዋን በማድነቅ ብቻ ጉዳዩን ሳያጣራ የገዛት ግለሰብ በሌብነት የ6 ወራት እሥራት ሲከናነብ ኤሚል ግን ነጻ ወጣ ።

የተለያዩ አደገኛና አሰቃቂ ወንጀሎች በመፈጸም የታወቀው ኤሚል በመሳሪያ ዘረፋ ሳይቀር ተወንጅሎ የፈረንሳይ ፍ/ቤት የዕድሜ ይፍታህ እሥራትና ከባድ ሥራ ፈርዶበትም ነበር ። አንድ ጊዜ በቪክቶሪያ ዋና ከተማ አውራጎዳና በተፈጸመው ግድያ ወደአንድ የፓሪስእሥር ቤት ለጥያቄ ሲዛወር ዕብድ በመምሰል ያሳየው ትርዕይት "የአካዳሚ የኒሻን ሽልማት" የሚያጐናጽፍ ተግባር ይመስል ነበር ። የወንጀሉን ድርጊት ለመመርመር በፖሊሶች የምርመራ መቅድም ከተከፈተበት ጊዜ አንስቶ ራሱን የከባድ አእምሮ በሽተኛ ለማስመሰል በታሰረበት ክፍል ውስጥ ላይና ታች በመቁነጥነጥ ፤ በመብስከስከና የአእምሮ በሽተኛ በትክክል ሊያሳይ የሚችለውን ሁኔታ ሁሉ

በማሳዮት ለመስሎቹም ሆነ ለዘቦቹ ፋታ የማይሰጥ የራስ
ምታት ሆኖባቸዋል ። በዚያው አድራጐቱ ሁኔታውን
በቅርብ ለመከታተልና ለመታዘብ ሲባል በእስርቤቱ
ክሊኒክ ቢያስቀምጡትም የሕክምና ምርመራ የሚያደር
ጉለትን ሐኪሞች እንኳ ሳይቀር ፋታ በማይሰጠው የመ
ቁነጥነጥና የመብሰክሰክ ሁኔታው አሽብሮ ሊያታልላ
ቸው ችሏል ። በመጨረሻም በአእምሮ ሐኪም ምክር
ወደአንድ የአእምሮ ሆስፒታል ተላለፈ ። ከዚያ ሆስፒ
ታል እንደገባም ምንም እንኳን ጥብቅ ጥበቃና ቁጥጥር
ቢደረግበትም በወንድሙና በ3ት አበሮቹ በመረዳት በገ
መድ በተሰራ መሰላል ከአእምሮ በሽተኞች ሆስፒታል አደ
ገኛ የግንብ አጥር ተንጠልጥሎ አመለጠ ።

ኤሚል ከአእምሮ በሽተኞች ሆስፒታል ካመለጠ
በኋላ የውንብድና ሕይወቱ ከፍተኛ ደረጃ ደረሰ ። ለ3
ተከታታይ ዓመታት በፓሪስ አውራጐዳናዎች ሳይቀር
በፈጸማቸው የዝርፊያ ፡ የስርቆትና የግድያ ወንጀሎችም
ስሙ እየጐላና አቻ ቢስ እየሆነ ሄደ ። በጣም የሚያ
ስገርመው ጉዳይ ቢኖር ደግሞ ከሆስፒታሉ ካመለጠበት
ዕለት ጀምሮ ለሦስት ተከታታይ ወራት ባብዛኛው
ከፓሪስና ከአከባቢዋ ያለመለዮቱ ነበር ። ያም ሊሆን
የቻለበት ምክንያት ይከታተሉት የነበሩትን የፖሊሶች
ቡድን ለማምለጥ በሚቀይሰው ስልት ረቂቅነትና የማስመ
ሰል ጥበቡ ነበር ። የፈረንሳይ ፖሊስና ፍርድ ቤትም
በወቅቱ " ኤሚል የፈረንሳይ አንድ ቁጥር ጠላት ነው ።"
በማለት በይፋ ለማሳወቅ ተገደዋል ።

በሌላ አቅጣጫ ደግሞ የኤሚል አደገኛ ሥራዎች
የመርማሪ ቻርልስ ሽኒቨርን የምርመራ ጫና የመጨረሻና
ከባድ አድርጐታል ።



የቻርልስ ሽኒቨር አባት የጦር ሙያተኛ የነበሩ ሲሆን፤
ቻርልስ ከልጅነት ዘመኑ ጀምሮ የፖሊስ ጋዜጦችን በጉ
ጉት ተከታትሏል ። ቤተሰቦቹ ግን ያን ስለማይወዱለት
ጋዜጦቹን በደብተሮቹ መሃል በመወሸቅ ለማንበብ ይገ
ደድ ነበር ። ከፖሊስ ጋዜጦች ካነበባቸው መካከል ከት
ዝታው የማይጠፋውና ሊፋቅ ያልቻለው በአንድ የቀድሞ
ወንጀለኛና የፖሊስ ተከታታይ መካከል የተካሄደው ፍል
ሚያና በተከሱም የሁለቱም ሕይወት በአንድ ጊዜ
የማለፉ ሁኔታ ነበር ።

ቻርልስ በፓሪስ የከፍተኛ ትምህርቱን ካጠናቀቀ
በኋላ በጋዜጠኝነት ሥራ በመሳተፍ ጽሑፎችና ሪፖርቶ
ችን በአንድ ብሔራዊ ጋዜጣ ላይ አቅርቧል ። ያ ሁሉ
ሆኖ ግን በፖሊስ ሙያ መመስጡ አልቀረም ። በፖሊስ
ሙያ ከፍተኛ ዝንባሌና ተመስጦ ባደረበት ዘመንም የፈረ
ንሳይ ባለሥልጣኖች የባቡር ላይ ዘራፊዎችንና ነፍሰ ገዳ
ይዎችን ለማጥፋት የሚያስችል ዘመቻ ጀመሩ ። በዚያም
ሳቢያ ልዩ የፖሊስ ግብረኃይል ተቋቁሞ የባቡሩን ደህ
ንነት ለመቆጣጠር ተወሰነ ። ለዚያም ተግባር ብቁ
የሚሆኑ ሰዎችን ለመመልመል በተሰጠው ፈተና ሽኒ
ቨር ተወዳድሮ ባገኘው አርኪ ውጤት ተቀባይነትን
አገኘ ። በመሆኑም በየካቲት 1/1925 ለብዙ ዘመናት ሲመ
ኘው የነበረውን የፖሊስ ሥራ በአንድ ልዩ የባቡር ጣቢያ
መስመር ተመድቦ ተያያዘው ።

ሽኒቨር ዝነኛነቱንና ታዋቂነቱን ያጠናከረው ለመ
ጀመሪያ ጊዜ የተሰጠውን ግዳጅ (ሥራ) በሚያስገርም
ሁኔታ በ2 ሰዓት ጊዜ ውስጥ አጠናቆ ለማቅረብ በመቻሉ
ሲሆን ሥራውና የሥራውም ውጤት የሚከተለው ነበር ።
አንድ የእንግሊዝ ተወላጅ ኮቱ ተሰርቆበት ለፖሊስ ያመ
ለክታል ፤ ያንንም እንዲከታተልና ውጤት እንዲያስ

ገኝ ሸኒቨር ይታዘዛል ፤ በከፍተኛ ዝንባሌውና በረጅም ጊዜ የወንጀል ታሪኮች ንባብ ራሱን ያዳበረው ሸኒቨር የዚያ መሰሉ ወንጀል ፈጻሚዎች ሊገኙ የሚችሉባቸውን አካባቢዎችንና ቡና ቤቶችን በማሰስ ሌባውን ለአንድ ደላላ ሲሸጥ በድንገት ደርሶ እጅ ከፍንጅ ይይዘዋል ፤ ከዚያ በኋላም ለእንግሊዛዊው ከአንድ ምቹ ሆቴል ቤት ተዝናንቶ ከተቀመጠበት ድረስ በመሄድ በድንገት የኮቱን መገኘት አበሰረው ። እንግሊዛዊውም በፍጥነቱና በጥበቡ በመደነቅ “ አንተስ ከእስኮትላንድያርድ ፖሊሶች ሳትሻል የምትቀር አይመስለኝም” ፤ በማለት አድናቆቱን ገለጸለት ።

ከሦስት ዓመታት የባቡር መስመር ጥበቃ ሥራ በኋላም ሸኒቨር የአደገኛ ወረበሎች ተከታታይ እንዲሆን ተመደበ ፤ የዚያም ምደባና ግዳጅ ከአደገኛው ወሮበላ ከኤሚል ጋር እንዲፋጠጥ አደረገው ። በሚያዝያ 1938 በሚያስገርምና በልዩ ፖሊሳዊ ጥበቡ በኤሚል የሚመራውን አደገኛ ቡድን በባንክ ዘረፋ ወንጀል ምክንያት በቁጥጥር ስር አዋለ ። ያን ከባድ የባንክ ዘረፋ ወንጀል ሸኒቨር ሊያጋልጠው የቻለው በኤሚል ውሽማ አማካይነት ሲሆን ጉዳዩም እንዲህ ነበር ። ኤሚል ከባንክ ዘረፋ ድርሻው ለውሽማው ለጄን ቡና ቤት ገዝቶላት ስለነበር ለመዝናናት ጄን ቡና ቤት ይሄዳል ፣ እዚያም ሸኒቨር አግኝቶት በቁጥጥር ሥር አዋለው ።

ሸኒቨርም ባደረገው ምርመራ ኤሚል ፍጹም ሸምጥጦ ስለካደውና ይህም ወደ ፍርድ ቢቀርብ ዞሮ ዞሮ ያለ ተጨባጭ ማስረጃ ተቀባይነት ስለማይኖረው ሸኒቨርንም የባሰ ችግር ላይ ሊጥለው ስለሚችል በቡና ቤቱ ያለችውን ክፍል ለማሰስ ወሰነ ። በዚያም መሠረት ከኤ



ሚል ጋር ተያይዘው በመሄድ አሰሳ ሲያደርግ በክፍሉ አንድ የሴት ጃንጥላ ተገኘ። በጃንጥላው ውስጥም ምናልባት የተቀመጠ ነገር ሊኖር ይችላል በሚል ግምት ሲዘረጋው የ100 ፍራንክ ኖት እንደዝናብ ተዘርግፎ ወለሉን አጥለቀለቀው ። ማስረጃ በማጥፋት ረገድ ከፍተኛ ጥበብ የነበረው ኤሚል በዚያ ሁኔታ በመደናገጥ አፉን ከፍቶና ዓይኑን አፍጥጦ ቀረ ።

ምንም እንኳን ሁኔታው ኤሚልን ለጊዜው ክፉኛ ቢያስደነግጠውም ገንዘቡ በጃንጥላው የተከማቸበት ምስጢር ፈጽሞ ለሱ እንግዳ ነበር ። ለካስ የኤሚል ውሽማ ጄን ከፍቅረኛዋ ጋር ባደረች ቁጥር ከኪሱ በማያውቅበት ሁኔታ ገንዘብ እያወጣች በጃንጥላው ውስጥ እየደበቀች ታጠራቅም ኖሯል ። በተለይ ለኤሚል እጅግ አደገኛና መጥፎ አጋጣሚ የሆነበት ከተዘረገፉት የገንዘብ ኖቶች የጥቂቶቹ ቁጥር ከባንክ ከተዘረፉትና ከተመዘገቡት የባንክ ኖቶች መካከል ተመሳሳይ መሆናቸው ነበር ። በዚያም ታላቅ የወንጀል ተግባሩና በተገኘበት ተጨባጭ ማስረጃ ኤሚል ታሰረ ። የሆነ ሆኖ አሁንም እንደተለመደው በአበሮቹ አማካኝነት ከእሥር ቤት ሊያመልጥ ቻለ ።

ከዚያም በኋላ ሸኒቨር አልተኛለትም ነበር ፡ ኤሚል ካመለጠ በኋላ ከሚፈጸሙት ወንጀሎች ልዩ ሁኔታና ከወንጀለኛው ባህሪይ በመነሳት ያንኑ የለየለት ወንበዴ በግንቦት 1941 ለሁለተኛ ጊዜ በአንድ አደገኛ የወንጀል ድርጊት ወህኒ እንዲወርድ አድርጎታል ። የሆነ ሆኖ የዕድሜ ይፍታህና የከባድ ሥራ ፍርድን ያከናነቡት በግንቦት 1943 ነበር ። በዛው ዘመን ሸኒቨር በአንድ “ ጃክ አ. ኤስ.ኤስ” በሚባል ፈረንሳዮች በሚመሩት የአሜሪካኖች ህቡእ ድርጅት ውስጥ አባል ሆኖ በመገኘቱ ወደ ናዚዎች ካምፕ በግ

ዞትንት ወረደ ። ከጦርነቱ በኋላም የኤሚልና የሸኒቨር የድ መትና የአይጥ ጨዋታ ተጀመረ ። ኤሚል በ1947 ከእብ ዶች ሆስፒታል ሲያመልጥ ፣ ሸኒቨር ደግሞ ከጦርነቱ በፊት ጀምሮ በፈረንሣይ በብሔራዊ ደረጃ ተጧጥፎ የነ በረውን የወረበሎች ፣ የነፍስገዳዮችና የዘራፊዎችን ቡድን ለማጥፋት በተቋቋመው ግብረ ኃይል የበላይ ኃላፊ በመ ሆን ተሾመ ። በመሆኑም የሁለቱ መንገድ እንደገና ይጠ ላለፍ ጀመር ።

ከእስር ቤት ካመለጠበት ጊዜ ጀምሮ በሕይወቱ ያካ በተውን የወንጀል አሰራር ስልትና ልምድ ለኑሮው ማደሻ እንዲሆነው ያታን የማይለይና ወንጀለኞችን ያሰባሰበ በዘረፋም የተካነ ህቡእ ድርጅት በፓሪስ አደራጀ ። ለዚህ ድርጅት የሃሳቡ ንድፍ አውጪ ከመሆኑም በላይ አልፎ አልፎም በዝርፊያው ፕሮግራም ውስጥ ገብቶ ከፍተኛ ሚና ይጫወት ነበር።ኤሚል የዝርፊያ ወንጀሉን ከፈጸመ በኋላም እንደጉድ ፈጥኖ የመሰወሩን ጥበብ ያዳብረው ጀመር ። በዚ ያም ምክንያት በኤሚል የተመራው የወሮበላ ቡድን ከ1 947 እስከ 1950 በነበሩት ጥቂት ዓመታት እንኳ 24 ከፍ ተኛ የዝርፊያ ፣ የአፈናና ሌሎች አደገኛ ወንጀሎችን ፈጽ ሟል ። ይህም በገንዘብ ሲተመን 60 ሚሊዮን ፍራንክ ደርሷል ። በሌላ በኩል ደግሞ በተደራጀ ጥበቡና ከእ ሥር ቤት የማምለጥ ዘዴው ከሦስት ጊዜ በላይ ከእሥር ቤት በሚያስደንቅና በተደራጀ መልኩ አምልጧል ። በግ ድያም ረገድ ከደርዘን ያላነሰ ሕይወት በሚዘገንንና በሚ ያስቅቅ ሁኔታ ቀጭቷል ። አፋቸው አምልጧቸው በርሱ ላይ የምስክርነት ቃል ሰጡ የተባሉ ቀርቶ የቅርብ ጓደኞ ቹና ተከታይዎቹ እንኳ እጅግ ምስጢራዊ በሆነ ዘዴ እየ ተፈጁ ሬሳቸው የሚካና የአሞራ ሲሳይ ሆኖ ቀርቷል ።



ያን አደገኛ ወሮበላ እስከመጨረሻው የማደን ኃላ ፊነት የተጣለበት ሸኒቨርም በዚያ ደረጃና ሁኔታ ላይ ያለ የሌለውን ፖሊሳዊ ጥበብ በመጠቀም ጉዳዩን እልባት ለማስያዝ የመጨረሻውን ፖሊሳዊ ስልት ተያያዘው ። በተለይ ዋና ዘዴ አድርጐ የተያያዘው በኤሚል ዙሪያ የነ በሩትን ወንበዴዎች በማጥፋት ብቻውን ማስቀረት ስለ ነበር ቀስ በቀስ የቅርብ ተባባሪዎቹንና ቀንደኛ ጀሌ ዎቹን አድፍጦ እያሳደደ የማሠርና የማጥፋት ዘመቻውን አጧጧፈ ። የዚያ ዘመቻ ከንዋኔ ጥቂት ቀናት ያስቆጠረና አድካሚ ቢሆንም በውጤቱ ረገድ ግን የታሰበውን ያህል ተከናውኗል ። ስለሆነም ኤሚል ካለምንም ተከታይና ደጋፊ እርቃኑን ሊቀር በመቻሉና የከተማው ወሮበላዎች ስላመ ጹብት በቦሎኝ ጫካ ውስጥ እየተደበቀ ማደር ጀመረ ።

በዚያው አንፃርም የኤሚል ተከታታይዎች የደፈጣ እንቅቅልሽ እየላላ ሙሄድ ጀመረ ። ሸኒቨርና ረዳት ፖሊ ሶቹ “ . . . ይህን አደገኛ ወሮበላ ርቃኑን ስላስቀረነው የል ፋታችን ውጤት በቅርቡ በተጨባጭ ይታያል ” እያሉ ሲዝቱ ፣ ኤሚል በሌላ በኩል ደግሞ ሙሉ በሙሉ በፖ ሊሶች ክትትልና ዓይነቁራኛ ስር መውደቁን በቅድሚያ ለመገንዘብ በመቻሉ “ ደፈጣቸው ይከሽፋል ” እያለ መዛቱ አልቀረም ። ኤሚል በጣም ተንኮለኛ ፣ ደፋርና ንቁ በመሆኑ ለትንሿ ኮሽታና ክትትል ከባድ ግምት በመ ውሰድና ለሁሉም ነገር ጊዜ ባለ መስጠት በወሰደው ርም ጃም ከዓይናቸው ሥር ሁሉ እየተሰወረ ለ33 ወራት ያህል ሳይጨበጥላቸው ቀረ ።

ሸኒቨር የኤሚልን የማምለጥና የመሸለኩለክ ጥበብና ስልት በአድናቆት ሲያትት “. . . . ጓደኞቹና ተከታይዎቹ እንዳሉ አልቀዋል ፣ ወይንም አካለ ጐደሎዎች ሆነዋል ፣ ወይንም ታስረዋል ። የርሱ ይህን ያህል ሳይያዝ ለመዳን

መቻል ከጓደኞቹ በድፍረቱ ፣ በብልሃቱና በፍጥነቱ የመምጠቁን ሁኔታ ያረጋግጣል ። በሌላ በኩል ግን የፈለገውን ያህል ራሱን ለመደበቅ ቢሞክርም ዘላለማዊ ባለመሆኑ በቁጥጥር ሥር ከመዋል አይድንም ፣ በተለይም ገንዘብ በሚያስፈልገው ጊዜ የዘረፋው ጥም ስለሚቀሰቀስበት በቀላሉ በአደገኛ የዘረፋ ወንጀል ላይ እንዳለ እጅ ከፈንጅ ለመያዝ ሙሉ ዝግጅት በመደረጉ እንደሚያዝ ርግጠኛ ነኝ ” ብሏል ። በተጨማሪም ሸኒቨር በቅርብ መከታተሉ አማራጭ የሌለውና አስፈላጊ መሆኑን ይናገርም ነበር ፣ ለዚያም እንደ ትሮጃን ፈረስ የማጥመጃ ዘዴ መፈለግ አለበት ብሎ ስለ አመነ ለኤሚል መፈናፈኛ የሚያሳጣ ወጥመድ ማዘጋጀት ጀመረ ። በመርዝ እንደምትቀሰቀስ ተባይ ከደፈጠበት ተሳክሮ ሲወጣ ሊጋለጥ ይችል ዘንድም የክትትሉ ጥብቅነት ፣ የመጋለጡ ጊዜ እየተቃረበ የመሄዱ ሁኔታ ፣ የተደረገው ትኩረት ሁሉ በተከታዮዎቹ አማካይነት እንዲዛመት ተደረገ ። ይህ ለየት ያለ ፖሊሳዊ ዘዴ ከኤሚል አደገኛ ወንጀል ፣ ፈጥሮ የማምለጥ ስትልና ብልሃት አኳያ በውልና በጥበብ የተቀናጀ ነበር ። ኤሚል ወሬውንም ከዋናው ተከታታይ ወይም ከፖሊሶች ሳይሆን ከሌሎች እንዲሰማና ከተዘረጋበት ወጥመድ እንደልማዱ በፍጥነት ለማምለጥ ሲሹለከለክ ያለብዙ ቀናት ደፈጣ በወጥመዱ እንዲገባ ተወጠነ ።

ፖሊሶች ኤሚልን ለማጥመድ እንደትሮጃን ፈረስ የተጠቀሙበትም ሰው ታስሮበት በነበረበት እስር ቤት ውስጥ አብሮት የነበረውን አንድ ነጻ የወጣ እሥረኛ ነበር። በዚያ መሠረት ኤሚል በስልት በተዘጋጀው የፖሊሶች ወጥመድ በግንቦት 1950 ለመጀመሪያ ጊዜ ገባ ፣ ይኸውም ከዚያው ሰው ጋር አንድ ውል በመዋዋሉ ነበር ። ኤሚል ለአንድ መኪናና ሽጉጥ ዋጋ ለሰውየው በርካታ ገንዘብ ለመስጠት ተዋዋለ ፤ በዚያ ውላቸው መሠረትም “ በትሮጃን ፈረስ ሆድ ያደፈጠው ” የጥንቱ የእሥር ቤት ጓደኛው የጠየቀውን ሁሉ ለመፈጸም ዝግጁና በተግባር ማዋል እንደሚችል አረጋገጠለት ። ሸኒቨርም በዚያ ረገድ ስለነበረው አጠቃላይ ሁኔታ ሙሉ መረጃ እንደደረሰው “ . . . እንዲህ በድካም ያንከራተተን አደገኛው ወሮበላ ኤሚል የተላከለትን መርዝ ጉርሷል ። ሆኖም አሁንም ልዩ ብልሃት ይጠይቀናል ” ብሏል ። በዚያም ዋናው ተከታታዩ ነገሮቹ ተጣድፈው “የትሮጃን ፈረስ” ወጥመድ እንዳይፈርስበት ሶስት ቀናት ሆን ብሎ እንዲያልፉ አደረገ ። በመጨረሻም መርማሪው የመጨረሻውን ዕድል መውሰድ ፈለገ ።

በዚያን የተጧጧፈ የአይጥና ድመት ዘመቻም ያልታሰበ ሁኔታ ተከሰተ ። ይኸውም አደገኛው ወሮበላ ከፓሪስ ከተማ ዳርቻ ወደምትገኘው ሆቴል በመሄድ ለመዝናናት ማቀዱንና ወደዚያችም ቦታ ጓደኛው በመኪና እንዲወስደው በመወሰኑ ነበር። ሸኒቨር ይህኑ መረጃ በተጨባጭ እንዳገኘ በራሱ ወጪ አንድ መኪና ተከራይቶ ለኤሚል የእሥር ቤት ጓደኛ የጉረሰና የተቀባበለ ሽጉጥ አስታጥቆ ከነመኪናዋ አስረከበው ።

በሌላ በኩል ደግሞ ተከታታይ ፖሊሶችን ሰብስቦ “ የተጣለብንን ግዳጅ ለመወጣት እንበቃ ዘንድ ተገቢው ፖሊሳዊ ቅንብር ተከናውኗል ፣ በፖሊሳዊ ጥበባችን አኳያ ካሁን ወዲያ የተተወው ኃላፊነት ለናንተ ብቻ ነው ፤ በመሆኑም በመንገድ ኤሚልና ጓደኛው ብቅ ሲሉ የምታደርጉትንና የምትወስዱትን ጥንቃቄ አስቡበት ” በማለት ተገቢውን መመሪያ ሰጥቶ አሰናበታቸው ።

ሸኒቨር በተለይ የጠመደውን ወጥመድ ለቅርብ የሥራ ባልደረባው ለጊላርድ ሲነግረው እንዴት መኪናና መሳሪያ ለአደገኛ ወንጀለኛ ለመስጠት በመወሰኑ ተገር ሞ ፡ ይህንንም ለመፈጸም ሕሊናው እንዴት እንደፈቀደ ለት ጠይቆታል ። ሸኒቨር በበኩሉ ለሥራ ባልደረባውና ለፖሊሶቹ ሲያስረዳ "የካርታ ጨዋታ ታዲያ ምኑላይ ነው? የጨዋታውን ጥበብ ያወቀበት ሰጥቶ መረከብ አይደለ ምን ? እንዲያውም ባይገርማችሁ የመዝናኛ ወጪውን ሁሉ የምከፍለው እኔ ነኝ " በማለት አቋሙን ነገራቸው። በተጨማሪም በካርታው ጨዋታ የመጨረሻዋ ካርታ ብትቀርም እንኳ አዝማሚያው የሚያበረታታ መሆኑን አረጋገጠላቸው ።

የክትትሉና የተወሰደው ርምጃ ሁኔታ የፖሊሶቹን ልብ እንዳንጠላጠለ ሰኔ 3 ቀን ከጧቱ አሥራ አንድ ሰዓት ላይ ርምጃው በተፈለገውና በታቀደው መሠረት በሰ ላም የመከናወኑ ሙሉ መረጃ ለሸኒቨር ደረሰ ።

ሸኒቨር የሥራ ባልደረቦቹን ሰብስቦ " . . . ደጋ ግሜ ነግሬያችሁ ነበር ፤ የኛ ሥራ ዞሮ ዞሮ የካርታ ጨዋታ መሆኑ አይቀርለትም ፡ ኤሚልን በጃችን ለማስ ገባት ይህን መሰል አስጊ ሁኔታ ውስጥ መግባት የግድ ነው ። በካርታም ጨዋታ የሚገኘው ድል ከዚህ መሰል አስጊ ሁኔታ ነው ። ያም ሆነ ይህ የደከመው ወንጀለኛ ወደተዘጋጀለት የመጠለያ ቦታ መድረሱ ደርሶኛል ።" በማለት የተንጠለጠለውን ልባቸውን በአብሳሪ መረጃ አረጋጋው ።

ሸኒቨር የግርግርና የችኮላ መንፈስ ያለማሳደሩ ሊደ ርስ የሚችል ብዙ የእልክና የእልሞት ባይ ተጋዳይን ጥፋት ለማዳን ሲል ነበር ። በተለይ በዚያ ረገድ የተጠቀመው



ዘዴ እንደ አንድ የጃዝ ባንድ ቅንብርና ቲያትር ጥበብ የረ ቀቀ ነበር ። ትንሽ ልዩነት ቢኖረው በሸኒቨር ጥበብ ላይ ጥቂት ስህተት ቢፈጸም የደም መፋሰስና ዕልቂት የሚያስ ከትል የመሆኑ ሁኔታ ነበር ።

ያም ሆነ ይህ ወደተጠመደለት ወጥመድ የተጓዘውን አደገኛ ወንጀለኛ ኤሚልን በቁጥጥር ሥር ለማዋል ዋና መርማሪውና ረዳቶቹ ኤሚል ወደተጓዘባት የፓሪስ ዳርቻ ሆቴል ጉዞ አደረጉ ። ሰኔ 10 ወደንጋቱ ላይ ኤሚል ካረፈ በት ሆቴል 3 ኪሎሜትር ወደ ዱቪል ወደሚያመራው መን ገድ ላይ መኪናውን አቁሞ በእግሩ ጥቅጥቅ ወዳለው ጫካ በመግባት የበላይ ኃላፊውን መጠባበቅ ያዘ ። ያ በእ ንዲያ እንዳለ ጊላርድ (በወቅቱ የዋና ኮሚሽነር ማዕረግ የነበረው ) ባለቤቱንና የኢንስፔክተሮቹን ጄኔራል በመ ያዝ በወቅቱ አለች በሚባልላት ዓይን ማራኪ አውቶ ሞቢል በመሆን ወደማረፊያዋ ሆቴል ገቡ ። የኤሚልን ዓይን ላለመሳብና ጥርጣሬ ላይ ላለማሳደር ሶስቱም እንግ ዶች የእስፖርት ልብስ ሲለብሱ ሁለቱ ግን ምንም ዓይ ነት ትጥቅ አልታጠቁም ነበር ።

የክትትሉ መረብና ወጥመድ በፖሊሶች በኩል በዚያ መልኩ ሲዘረጋ ኤሚል ደግሞ በተለመደችው ጠረጴዛ ላይ ተቀምጦ ይዝናና ነበር ።

በርግጥ ኤሚል ወደማረፊያው ሆቴል የመጡትን እን ግዶች አስተውሏቸዋል ፡ ነገር ግን በዘመናዊና ውብ መኪና ላይ ልዩ ፍቅር ስለነበረው ልቡ የተንጠለጠለውና ዓይኑ የተወረወረው ደስ በምትለው መኪና ላይ ነበር ። እርሱም ፖሊሶች በምንም ዓይነት የዚያችን ዓይነት መኪና ሊይዙ አይችሉም ፡ መሆን የሚችሉት እገር ጐብኝዎች ብቻ ናቸ ው ። እያለ ያሰላስል ነበር ። ወደኋላ ግን ከመኪናዋ ላይ የነ

በረውን ትኩረት ነቅሎ የሶስቱን ሰዎች ሁኔታ መከታተ
ልና የሚጫወቱትንም ጨዋታ በተመስጦ ማዳመጥ ጀመረ።

ከሶስቱ አንደኛው ማለትም ጀኔራል ቦርንቼ በዱቪል
በሚገኘው አንድ ማረፊያ ሆቴል በቅድሚያ ስለተያዘለት
የማረፊያ ክፍል ለማረጋገጥ የሆቴሉ አስተናጋጅ የሚመለ
ከተውን እንዲያገናኘው ጠየቀው ፡፡ ከሁለት ደቂቃዎች በኋ
ላም መሥመር ተገኘለት ፡፡ ቦርንቼ ከተቀመጠበት ተነ
ስቶ ኤሚል በተቀመጠበት ቦታ ታኮ አለፈ ፤ ቴሌፎኑ
ንም በማንሳት የማስተናገጃ ክፍል ሠራተኛው መሆኑን
ካረጋገጠ በኋላ ዶክተር አንድሬ ከፓሪስ መሆኑን በመ
ግለጽ ለባለቤቱና ለራሱ ቦታ መያዝና አለመያዙን
ይጠይቃል ፡፡ ቀጥሎም በዚያኑ ሌሊት ሊደርስ እንደ
ሚችልና ማረፊያውንም ለአንድ ሣምንት ያህል እንደ
ሚፈልገው ያረጋግጣል ፡፡ በዚያ ምልልስ ከደዋዩ ወገን
የሚሰማው ድምጽ ግን“ . . . እስቲ አንድዬ ይጠብቁኝ ”
የሚል ብቻ ነበር ፡፡ ወትሮውንም ይህ ስልት የኤሚልን
ጥርጣሬ ለማስቀየር የተጠነሰሰ ስለነበር “ ዶክተር አን
ድሬ ” ግን “ ደህና ! ደህና ! ለመሆኑ ለአንድ ክፍል ከነባ
ኞው ምን ያህል ታስከፍላላችሁ ? ” በማለት ተከታታይ
ጥያቄዎችን ያጐርፍ ጀመር፡፡ የማስተናገጃው ጸሐፊ በበኩሉ
በዚያው በስልክ “ . . . ጌቶች በመጀመሪያ ደረጃ
በስምዎ የተያዘለዎት ምንም ክፍል የለም ! ” ሲል ፡ አን
ድሬ የጸሐፊውን ንግግር በማቋረጥ ” . . . . ደህና ሞንስ
የርና ማዳም ፎርስትየር የሚባሉ ጓደኞቻችንንም አብረን
ይዘን ስለምንመጣ ለመሆኑ ለነሱም ቦታ ትይዙላችዋላችሁ
ወይ ? “ በማለት በማይገጥምና በተደጋጋሚ ጥያቄ አጣደ
ፈው ፡፡ የሆቴሉ ጸሐፊም ባልተያያዙ ጥያቄዎች መኾርጐድ
ጐድ በመገረም “ . . . እባክዎትን ጌቶች ለሚሉት ሁሉ
አይሆንም . . . ” በማለት ንግግሩን ሳይጨርስ “ . . . ልክ



ነው የእንግዶቹ አልጋ ከኛ ቀጥሎ መሆን አለበት ፡፡” ይለ
ዋል ፡፡ ሞንስየር ፎርስየር (ጊላርድ መሆኑ ነው) በበኩ
በኩል በማለፍ “ ዶክተር . . . ክፍል እንዲያዝልን አደረግ
ክልን ? ” በማለት ይጠይቀዋል ፡፡ በዚያ ሁኔታ ኤሚል ተደ
ናግሮ በመገለማመጥ ላይ እንዳለ ዘለው ተጠመጠሙበት ፡፡
ወሮበላውና አደገኛ ወንጀለኛው ኤሚል ተቀላጥፎ ሽጉጡን
ለማውጣት ፋታ ሊያገኝ አልቻለም ፡፡ ውቢትዋ ማዳም ቦር
ንቼ በሰከነ መንፈስ ጉዳዩን ትከታተል ስለነበር ከቦር
ሳዋ ፊሽካ አውጥታ ነፋች ፡፡ ዋናው የኤሚል ተከታታይና
ብዙ ድካምና ጥረት ያደረገው ሽኒቨር በምልክቱ በመጠቀም
ከየት መጣ ሳይባል ፈጥኖ ደርሶ የእጅ ካቴናውን በኤሚ
ል እጅ ውስጥ አስገብቶ ቆለፈባቸው ፡፡ በሁኔታው ግራ
የተጋባውና የተደናገጠው ኤሚል በመጨረሻ መውጫ
መግቢያ ያሳጣውን ጥብቅ ተከታታዩን ሽኒቨርን በማየቱ
እጅግ በመደነቅ “ ... ለካ ይህን ሁሉ የምታደርገው አንተ
ኑረሃል ? ” በማለት ተናግሮ ሊታለል በማይገባው ሁኔታ
እንደተታለለና እንዳለቀለት አወቀ ፡፡ ሽኒቨርም ሰዓቱን
ተመልክቶ ” . . . አሁን ሰዓቱ ልክ ከምሽቱ አንድ ሰዓት
ከ47 ደቂቃ ሆኗል ፤ ካሰብኩት ስብሰባ በሁለት ደቂቃዎች
በመዘግየቱ ከፍተኛ ይቅርታ እጠይቃለሁ ፡፡ ” በማለት
ደስታውን ገለጸ ፡፡

በመጨረሻም ሽኒቨር ምሳውን እንዳልበላና የጫካው
ውስጥ የሥራ ሽርሽር ረሀቡን እንዳባባሰው በመግለጽ
በአንድነት ምሳቸውን እንዲመገቡ ጠየቀ ፡፡ ወደ ኤሚ
ልም አመልክቶ አንድ ወንበር ሳብ ካደረገ በኋላ “ . . .
ኤሚል እባክህን ከመሄድህ በፊት ቁጭ በልና ቡናና ኮ
ኛክ እናስጐንጭህ . . . ” በማለት ጠየቀው ፡፡ ኤሚልም
“ለምን ራም አይሆንም ” (በፈረንሣይ በተለምዶ የሞት

ፍርድ የሚፈረድበት የሚጠጣው ራም ነው ) በማለት በን
ዴት ተናገረ ።

ኤሚል ሽኒሽርን በጥላቻ አትኩሮ እየተመለከተው
ሳለ ሌሎቹ ግን በተከፈተ ከፍተኛ የምግብ ፍላጐት ከድል
በኋላ የተገኘውን ራት ተዝናንተው ይጐስጉሱት ጀመር ።
በተለይም የቀረበላቸውን እንጆሪ ከመጠን በላይ በማድነቅ
" እነህን እንጆሪዎች ከንር የለቀምኳቸው እንዳጋጣሚ
ራሴ ነበርኩ"ሲል ፤ ኤሚልም "ይህን አውቄ ቢሆን ኖሮ በእ
ንጆሪዎቹ ላይ የእይጥ መርዝ እደርግባቸው ነበር " በማለት
ቁጭቱንና ጥላቻውን ምንም ሳይደብቅ አፍረጠረጠው ።

ሽኒሽር በበኩሉ " . . . . ለመሆኑ እንዴት ልትታ
ለል ቻልክ?" ብሎ ቢጠይቀው የመኪናዋ ውበት የበስተ
ጀርባ ፖሊሶችን እንዳጋረደው አረጋገጠለት። በመጨረሻም
ሽኒሽር ከመቀመጫው ብድግ በማለት " . . . በል ኤሚል
ወደ ነገሩ ብናስብ ይሻላል " ብሎ በተያዘው መሰረት
ጉዞውን ወደእሥር ቤት እንዲያመራ አዘዘው ። ኤሚል
ከዛች የገጠር ሆቴል ከመንቀሳቀሱ በፊት ኮኛኩን ለመጨ
ለጥ የመረጠው በመጋቢት 28/1956 በጥዋቱ እንገቱን በጉ
ሊትን (እንገት መቁረጫ) በሚቆርጥበት የሳንቴን እሥር
ቤት የራምን ድርሻ ለመቆጠብ ነበር ።



# የሻይ ስኒዎችና የጉብኝት ካርዶች

ጥር 26, 1948 ወደ ዘጠኝ ሰዓት ተኩል ላይ
በቶክዮ ከተማ ፍንጣቂ በረዶዎችን ያዘለ ከፍተኛ ዝናብ
ይወርድ ጀመር ። በዚያ በረዶ ቀላቅሎ በሚጥልበት
ሁኔታና ወቅት ቀኑ ጨለምለም ብሎ ውሏል ። በዚያም ወ
ቅት የቴኮኩ ባንክ ሊዘጋ ጥቂት ሲቀረው አንድ በመካከለኛ
ዕድሜ የሚገኝ ሰው በድንገት ይደርስና ትሕትና በተሞላ
በት አቀራረብ " ትላንትና በተነጋገረው መሠረት ከጤና ጥ
በቃ ተልኬ የመጣሁ የጤና ጥበቃ ሠራተኛ ነኝ " በማለት
በባንኩ ከነበረ አንድ ጸሐፊ ጋር ይነጋገራል ።— ሰውየው
በጃፓን ቶኪዮ የጤና ጥበቃ ሠራተኞች በተለይም በመስክ አ
ገልግሎት ሥራቸው የሚያጠልቋቸውን መጫሚያዎችና ል
ብሶች አሚልቷል ፤ በዚያም መሠረት ነጭ ልብስና ቀይ የላስ
ቲክ ቦቴ ከመልበሱም ሌላ እነስ ያለች ጥቁር ቦርሳም ይዟል።

የባንክ ጸሐፊው በነበረው ኃላፊነት ወደ ባንክ
የመጡትን እንግዶችና የመጡበትን ምክንያት በሚገባ
አጣርቶ ከተቀበለ በኋላ ሊገናኙ ወደሚገባቸው የባንክ
ሠራተኞች ወይም ኃላፊዎች የማስተላለፍ ኃላፊነት ነበ
ረበት ። የጤና ጥበቃ ሠራተኛ ነኝ ያለውም ሰውዬ በልብ
ሶቹ ከሚታወቅበት ሁኔታ ሌላ የጉብኝት ካርድ ስለሰጠው
ይህንንም በሚገባ ሳያጣራ ወደ ዋናው ሥራ አስኪያጅ ቢሮ
አስተላለፈው ። በወቅቱም ዋናው ሥራ አስኪያጅ ስላልነ
በሩ ከተጠባባቂ ዋና ሥራ አስኪያጅ ከዮሺዳ ጋር በመገና
ኘት የጉብኝት ካርዶች ልውውጥ ካደረጉ በኋላ የአመ
ጣጡን ዋና ዓላማና ተልዕኮ በዝርዝር ያስረዳል ፤ በዚ

ያም መሠረት ከጀኔራል ዳግላስ ማክአርተርስ ዋና መ/ቤት ተልኮ የመጣ መሆኑንና በአካባቢው አንድ የሕዝብ የውሃ ጉድጓድ በመበከሉ የባንኩ ሠራተኞች አካባቢውን በበከለው የተቅማጥ በሽታ መያዛቸውን ሁሉ ይገልፃል ፣ ስለሆነም ለተቅማጡ በሽታ የመከላከያ መድኃኒት ለመስጠትና በተለይም ለዚህ ጉዳይ ኃላፊነት ካለበት መ/ቤት የሕክምና ቡድንና አስፈጻሚ ፖሊስ በመኪናቸው እስከሚደርሱ ድረስ ቅድመ ዝግጅት እንደሚያደርግና እንደሚያመቻች ያብራራለታል ። ተጠባባቂው ሥራ አስኪያጅም በተጨባጭ ባየው ሁኔታና በሰውዬው አቀራረብና አነጋገር ተልኮውን አምኖ ተቀበለው ። ይህም የሆነበት ራሱን የቻለ ምክንያት ነበረው ፤ ዋናው ምክንያት በጥዋቱ ዋናው ሥራ አስኪያጅ በሆድ ቁርጠት ተሰቃይቶ ሥራውን ለርሱ ጥሎለት ወደ ቤቱ በመሄዱና እንዲሁም አንደኛው የባንክ ደንበኛ የተቅማጥ በሽታ እንደያዘው በማረጋገጡ ነበር ።

ተጠባባቂ ሥራ አስኪያጁ ስለችግሩ በሚገባ ሊረዳ ቢችልም የአሜሪካኑ ድርጅት በዚያ ረገድ የልብ እንደማያደረስ ስለሚያውቅ ባልተለመደው ቅልጥፍናቸው ከመጠን በላይ መደነቁ አልቀረም ። እንዲያውም አሜሪካኖች የአስተዳደር ኃላፊነት በነበራቸው ዘመን እንኳን ያን ድርጅት ለአገልግሎት የሚጠይቅ ምንም ሰው እንዳልነበር በማስታወስ በዚያን ዕለት ግን ሳይጠየቅ ቶሎ ለመድረስ መቻሉ አስገርሞታል ። የሆነ ሆኖ የተቅማጥ በሽታው መሠራጨት አጠራጣሪ ሆኖ ባለመገኘቱ የባንኩ ሠራተኞችና በቅርብ የተገኘው የባንኩ ተላላኪ ከነቤተሰቦቻቸው የሻይ ስኒዎቻቸውን እየያዙ ለተቅማጥ በሽታ መከላከያ መድኃኒት ሊወስዱ ይችሉ ዘንድ ሰልፍ ይዘው ተራቸውን እንዲጠባበቁ ከአደረገ በኋላ እንግዳው የመከላከያ መድኃኒቱን እንዲሰጣቸው ጋበዘው ።



እንግዳውም ሁለት ጠርሙሶችን በማውጣት በየሲኒዎቻቸው ላይ ካደረገ በኋላ መድኃኒቱ ኃይለኛ በመሆኑ ጥርሳቸውን ሳያስነኩ እንዲጨልጡት ነገራቸው ፤ ያም አልበቃ ብሎ ስኒዎቻቸውን ለሁለተኛ ዙር መድኃኒት እያጠቡ እንዲያዘጋጁ አዘዘ ። ሆኖም የመጀመሪያው ዙር መድኃኒት የአንዳንዶቹን ጉሮሮ እያቃጠለ ስላሳለቻው ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ጠየቁት ፤ እንግዳውም “ እይዟችሁ ሁለተኛው ዙር ይህንንም ያሽላችኋል ስለዚህ ለሁለተኛው ዙር ተዘጋጁ ።” በማለት እንዲዘጋጁ አበረታታ ። ከባንኩ ሠራተኞች አንደኛው ደግሞ “ እንደዚህ ጠንካራ የሆነውን መድኃኒት በውኃ ብንጉመጠመጠው አይሻልምን?” ብሎ ሲጠይቅ እንግዳው በአንገት የአዎንታ ምልክት አሳየ ፡ በዚያን ጊዜ ሁሉም መድኃኒቱ ስለአቃጠላቸው ውኃ ለማግኘት ተሰለፉ ፤ በዚያ ሰልፍ ላይ ከወይዘሪት ማሳኮ ሙራታ ፊት በመሆን ውኃ ለማግኘት ሰልፉን ሲጠባበቅ የነበረው ጉረምሳ ጥቅልል ብሎ ሲወድቅ ተመለከተች ፣ ርሷም በጣም በመደናገጥና በመጨነቅ ዕርዳታ ሊሰጠው ይችል ዘንድ ወደዋናው ሥራ አስኪያጅ ቢሮ ስትሮጥ ሌሎችም እንደዚሁ በያሉበት ወድቀው ሲንፈራፈሩ ታገኛቸዋለች ፤ ሙራታም እኡእኡታዋን እያቀለጠች ገና ወደ ሥራ አስኪያጁ ቢሮ ሳትደርስ ርሷም በወለሉ ላይ ተዘረረች ።

እንግዳው “ኃኪም” በጣም በቁረጋጋ መንፈስ ሁኔታውን ሲመለከት ከቆየና ሁሉም ሠራተኞች ሊንቀሳቀሱ እንደማይችሉ ካረጋገጠ በኋላ ወደ ባንኩ ካዝና በማምራት በጥሬ ገንዘብ 164,000 በባንኩ ቼክ ደግሞ 17,405 የን በመውሰድ በእርጋታ ቀጥ ብሎ በባንኩ መውጫ በር በመውጣት ተሰወረ ።

እእምሮዋን ስታ የነበረችውም ወይዘሪት ከአንድ ሰዓት በኋላ ቀስ በቀስ ራሷን እያወቀችና እየነቃች ሄደች ።

ግራና ቀኝ ስትመለከትም የሥራ ባልደረቦቿና እንደርሷው መድኃኒቱን የወሰዱት በስቃይ ተኮራምተውና ሰውነታቸውም ተዘርሮ ስለአየቻቸው ፤ እንደምንም ብላ በሻከረ ድምፅ ዕርዳታ ለማግኘት መጮህ ጀመረች ፤ በዚያም ጩኸት በባንኩ አጠገብ በሚገኘው አውራጎዳና ሲያልፉ የነበሩ ሁለት ሴቶች ደርሰው ሁኔታውን ከተመለከቱ በኋላ ለፖሊስ በአስቸኳይ አሳወቁ ።

ፖሊሶችም ደርሰው በባንኩ የተከሰተውን ድንገተኛና አሰቃቂ ሁኔታ ሲመለከቱ የከፊሉ ሕይወት አልፎአል፤ እንዳንዱ ጣረሞት ይዞት ያጣጥራል ፤ እንዳንዱ ደግሞ እንደምንም ቴሌፎኑን በመተናነቅ ለፖሊስ ሪፖርት ለማድረግ ይታገላል ። እንቡላንስም ደርሶ ሁኔታው ሲጣራ ከ10ሩ ሠራተኞች መካከል አራቱ ብቻ የተረፉ ሲሆን ከተረፉትም መካከል እንደአጋጣሚ ተጠባባቂ ዋና ሥራ አስኪያጁና ወይዘሪት ሙራታ ይገኙበታል ።

ከዚያም በኋላ መድኃኒቱን የጠጡባቸው ሲኒዎች ተሰባስበው በሲኒዎቹ ውስጥ ሊገኙ የተቻሉት የመድኃኒቱ ጠብታዎች ተጠራቀሙ ። ቀጥሎም የተቅማጥ መድኃኒት የተባለው ምናልባት መርዝ እንዳይሆን በሚል ጥርጣሬ ለምርመራ ተላከ ። በሌላ በኩል ደግሞ የወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ በዚህ ረገድ ሌላ ተፅዕኖ ማሳደሩ አልቀረም ፤ ይኸውም በተለይ ከጦርነቱ በፊት በጃፓን አገር ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ ፣ የማኅበራዊና የምጣኔ ሀብት ምስቅልቅልና ግርግር ስለነበር የተመረዘ ምግብ እየተበላ በባንክ ሠራተኞች ዓይነት ችግር መሰቃየት የተለመደ ነበር ፤ ስለሆነም ተመሳሳይ ሁኔታ ሊሆን ይችላል በሚል ግምት ስለምርመራውም ሆነ ውጤቱ ግድ የሰጠውና የተቻኮለም አልነበረም ።

ያም ሆነ ይህ የሻይ ስኒው ድግስ ከተከናወነበት ከ3 ሰዓታት በኋላ በሆስፒታሉ የተደረገው የምርመራ ሪፖ



ርት ተላከ ። በዚያ ሪፖርት መሠረትም የደረሰው አደጋ በምግብ መመረዝ ምክንያት አለመሆኑ ተረጋገጠ ። ሐኪሞቹ ከተረፉት ሠራተኞች ሆድዕቃ ጭምር የተወሰደውን መድኃኒት በማውጣት የፖታሲየም ሲናይድ መርዝ መሆኑን ደረሱበት ።

ያ ! በቴኮክ ባንክ የተካሄደው የጅምላ የሕይወት ፍጅትና ዝርፍያም ዓይነት ከጦርነቱ በኋላ በሀገሪቱ ግዛት ያለአንዳች ርኅራኄ የሚካሄድ ድርጊትና የተለመደ የወንጀል ሁኔታ እየሆነ መጣ ።

በሌላ በኩል ደግሞ ያን የመሰለ አሰቃቂ ወንጀል ፈጽሞ ያመለጠውን አሳዶ የመያዙ ጉዳይ ሊታለፍ የማይገባው ሆኖ ተገኘ ። በዚያም መሠረት ያንኑ ሰው በቁጥጥር ሥር ለማዋል የ7 ወራት ጊዜ ፈጀ ።

ለ7 ወራት ከፍተኛ ነቀርሳ ሆኖ የሰነበተውን ወንጀለኛ በመከታተል ይዞ ለማቅረብ በመጀመሪያ ኃላፊነት የተሰጠው የቶኪዮ ከተማ ፖሊስ ዋና መምሪያ የነፍስ ግድያ መርማሪ ቡድን ኃላፊ ለነበረው ለኢንስፔክተር ሺጌኪ ሆሪዛኪ ነበር ። ያም የሆነበት ዋና ምክንያት በአሜሪካኖች ቁጥጥር ሥር ሆኖ የጃፓናውያንን አዲስ ሕግ የማደስና የማጠናከሩን ተግባር ለማረጋገጥ ሲባል ነበር ። ከሆሪዛኪም ጉን በመሆን እንዲያግዘው ወይም እንዲረዳው የሕዝቡ ጠበቃ ኡሜዞ ታካጊ ተመድቦለት ነበር ።

በወንጀሉ የክትትል ተግባር የቡድን ሥራ አስፈላጊና ጠቃሚ ቢሆንም ጉዳዩን እስከመጨረሻው ተከታትሎ ሊያፈርጣት የሚችለው ግን አንድ ሰው ብቻ መሆኑ ይታወቃል ። በዚያም መሠረት የዚያ የአደገኛ ወንጀል ጉዳይ በመ/አለቃ ታሜጉሮ አጊ እጅ ተጣለ ፣ መ/አለቃ ነገሮችን አስፈላጊ ባልሆኑ ቦታዎች የማይበትንና ከፍተኛና የረጋ አስ

ተዋይ በመሆኑ ያንን ኃላፊነት የመሸከም ብቃቱ ተረጋግጦለታል ።

በተደረገው ክትትል መሠረት የዚያ ሁሉ ጉድ በትክክል ሊጋለጥ የቻለው በዚያኑ ዕለት ከእኩለ ለሊት በኋላ ላይ ነበር ። የሚገርመው ጉዳይ ወይም ዋና ነገር ቢኖር ፖሊሶቹ የወንጀለኛውን የጣት አሻራ በስኒዎቹ ወይም በጉብኝት ካርዶቹ ላይ ለማግኘት ያለመቻላቸው ነበር ።

በክትትሉና በምርመራው ረገድ ግን የተቀነባበረና ጥብቅ ቅንጅት ተፈጥሯል ። በዚያም መሠረት ሆሪዛኪ የክትትሉ ቡድኑ መሪ በመሆን በሥሩ 6 ታዋቂ ተከታታይዎች እንዲኖሩትና ከዐቃቤ ህጉ(ከህዝቡ ጠበቃ) ጋርም በቅርብ በመገናኘትና በመተጋገዝ ተግባሩን እንዲያከናውን ሲደረግ ማዕከሉም በዋናው መ/ቤት እንዲሆን ተደረገ ። በዚያንም ወቅት ምንም ዓይነት ችሎታ ሊኖረው ቢችልም አንድ ተከታታይ ያን መሰሉን ወንጀል በተናጠል እንዲከታተል አይፈቀድም ነበር ።

ቡድኑ በስፋትና ጠለቅ ባለ ሁኔታ ተግባሩን በማከናወን ላይ እንዳለ ከ3 ወራት በፊት በቶኪዮ ዳርቻ አካባቢ በሚገኘው በያሱዳ ባንክ (የኢባራ ቅርንጫፍ) ተመሳሳይ የባንክ ዝርፍያ ወንጀል ተፈጽሞ እንደ ነበር ተደረሰበት ። ቀደም ሲል ሲነገርም ከነበረው የባንክ ዘረፋ ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር ልዩነት አለው ተብሎ የተመዘገበው ለአስተናጋጁ የተነገረው ሥም "ዶክተር ሼጌሩ ማቱሲ" የሚለው የተለዬ ሥም መሆኑ ብቻ ሲሆን በሌሎች ሁኔታዎች ግን ከሞላ ጐደል ተመሳሳይነት እንዳለው ታወቀ ። ቢሆንም ከቲኮኩ የባንክ ዘረፋ በኋላ እየቀዘቀዘ ለመሄድ ችሏል ።

በሌላ በኩል ደግሞ በተካሄደው ክትትልና ምርመራ የባንኩ ሠራተኞች የሻይ ስኒዎቹ ከመበከላቸው 7 ቀናት



ቀደም ብሎ ተከስቶ የነበረው ሁኔታ የተከታታይዎቹን ትኩረት ስቧል ። ያም ጉዳይ የተከሰተው በሚትሱቢሺ ባንክ ነበር ። በዚያ ባንክ አንድ "ዶክተር ጂሮ ያማጉቺ" ለመሆኑ የጉብኝት ካርድ ያቀረበ ሰው የማኅበራዊ ደህንነት ባልደረባና የቴክኒክ ልዩ ሙያተኛ ነኝ በማለት ከቀረበ በኋላ ሕጋዊ ሠነዶችን ሲጠየቅ ሹልክ ብሎ ወጥቶ ማምለጡ ነበር።

ያ ሁኔታ ምንም እንኳን የባንኩን ሠራተኞች ትንሽ ግራ ቢያጋባም ለፖሊስ ጣቢያ ሪፖርት ባለመደረጉ የፖሊስን ክትትል የተዳከመ አድርጐታል ።

ከዚያም ሁሉ ሌላ ተጨባጭነት ያለው ፍንጭ ተከስቷል፤ያም የሻይ ስኒዎቹ የመርዝ ብክላ ከተከናወነ ከአንድ ቀን በኋላ ሲሆን የተሰረቀውን የ17405 የን ቼክ ለመመንዘር አንድ ማንነቱ ያልታወቀ ሰው ወደ ባንኩ ገብቶ በአንድ ጥንቃቄ በጐደለው የባንኩ ሠራተኛ ምክንያት ሰውዬው ሊያዝ አለመቻሉ ነበር ። በርግጥ የተጭበረበረው ቼክ ከባንኩ ሥራ አስኪያጅ ድረስ ደርሶ እስኪመረመርና እስኪታይ ድረስ የተጭበረበረ ለመሆኑ አልተደረሰበትም ።

ተከታታይ ፖሊሶቹም የተለያዩ መረጃዎች በማሰባሰብ ረገድ የማይናቁ ውጤቶችን ያገኙ ሲሆን በሌላ በኩል ግን የካርዶቹን ሁኔታ በማሰባሰብና በመመርመሩ ረገድ የተለዬ ትኩረት በመስጠት የወንጀለኛውን ማንነት ለመለየት እንደሚቻል ተገነዘቡ ። ሆሪዛኪም በካርዶቹ አማካይነት ክትትሉ አንድ እቅጣጫ ሊይዝለት እንደሚችል አመነ ! በዚያም በተደረገው ስምምነት መሠረት ተገቢው ክትትል ተደርጐ በሦስቱም ቦታዎች የተሰጡት ካርዶች ምንም እንኳን ስማቸው የተለያየ ሊሆን ቢችልም የአንድ ሰው የማጭበርበሪያ ስልት ወይም ጥበብ እንደሆኑ ተደረሰበት ። ከዚያም በኋላ ፖሊሶች የተገኙትን የጉብኝት ካርዶች የታተሙበ



የጃፓኑ ከፍተኛ ተከታታይ ታሜጎሮ አጊ፣ በቶክዮ ከተማ የፖሊስ መምሪያ በሺ የሚቆጠሩ መረጃዎችን በማሰባሰብ የደከመና እርቲስቱ ሂራስዋ እንዲጋለጥ ያደረገ ነው ። (ኤስ. ኪሙራ)



ትን ማተሚያ ቤት በቅድሚያ ለማግኘት መቻሉ የክትት ላቸውን መሠረት እንደሚጥለው በማጤን በዚያ ረገድ ልዩ ትኩረትና ክትትል ተደርጐ የሚከተለው ውጤት ተገኘ ።

ዶክተር ጂሮ ያማጉቺ በሚል ስም የታተመው የጉ ብኝት ካርድ በቶኪዮ ውስጥ ጊንዛ አጠገብ ከምትገኝ አነስተኛ ማተሚያ ሱቅ ሲሆን ካርዱን ያሳተመውን ግለ ሰብ ማንነት ግን ለማወቅ አልተቻለም ።

በሌላ በኩል ደግሞ በዶክተር ሼጌሩ ማቱሳ ስም የታ ተመው ካርድ ጉዳይ ነው ። ዶክተር ሼጌሩ በመሠረቱ በሲ ንዳይ የሚኖሩ ዕውቅ ሐኪም የነበሩ ሲሆን ክትትሉ በመ ካሄድ ላይ እንዳለ በያሱዳ ባንክ የተሰጠው ካርድ የሳቸው ለመሆኑ ቶኪዮ ወደ ሚገኘው አንድ ፖሊስ ጣቢያ በመደ ወል በራሳቸው ፍላጐት አረጋግጠዋል ። የሆነ ሆኖ እኒ ያው ታዋቂ ግለሰብ የቴኮኩ ባንክ ሠራተኞች የመርዝ ፍጅት ሲካሄድ በባንኩ አካባቢም ሆነ ውስጥ ዝር ያለማ ለታቸው በሚገባ ተረጋግጧል ። በጃፓኖች ወግና የረጅም ዘመናት ባህላዊ ልምድ እንደሚታወቀው በታወቁ ጠበብ ትና ነጋዴዎች መካከል ትውውቅ ሲደረግ ‘‘ ሜሺ ’’ በመ ባል የሚታወቀውን የካርድ ልውውጥ ማድረግና ካርዱንም በክብር በማስታወሻነቱ ማስቀመጥ የተለመደና የረዥም ጊዜ የወግ ውጤት ነው ። ስለሆነም እኒያው ሐኪም አንድ ጊዜ አንድ የሐኪሞች ስብሰባ ለመሳተፍ ሲዘጋጁ 100 ካር ዶች እንዲታተሙላቸው አድርገው ዘጠና ስድስቱን ካደሉ በኋላ አራት ካርዶች ሳይታደሉ እንደተረፉአቸው አረጋግ ጠዋል ።

የካርዱ ሁኔታ በአንድ በኩል ከላይ እንደተጠቀሰው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ዶክተር ያማጉቺና ዶክተር ማ ቱሳ በማለት ራሱን በተለያዩ ስሞች ያስተዋወቀው ሰው አንድ ሰው ለመሆኑ በአካባቢው በቀረቡት ማስረጃዎችና

ምስክሮች መሠረት በሚገባ ሊረጋገጥ ችሏል።የዚያው ሰው
አጠቃላይ ገጽታና ሁኔታም ከምስክሮች በሚገባ በዝርዝር
ታውቋል ። በዚያም መሠረት የሰውየው በግራ በኩል
ያሉት ጥርሶቹ የወለቁ ፣ ጉንጩ ላይ ትልቅ ጠባሳ የነበረ
ውና በዕድሜውም የገፋ ሆኖ ተገኝቷል ። በዚያም የአቋ
ምና የሰውነት ገለጻና ትንታኔ መሠረት በጃፓን ዋና ዋና
ከተሞች የማፈላለጊያ ምስል ተቀርጾ ተላላፈ ። ሆሪዛኪና
ረዳት ተከታታይዎቹም ከሕዝብና ከፖሊሶች የሚላከላቸ
ውን ጥቆማና መረጃ በመከታተልና በመጠበቅ ሳምንታት
ካሳለፉ በኋላ እውነተኛው ዶክተር ማቱሳ ከላይ ስለተጠቀ
ሰው ሁኔታ በዝርዝር በመረጃ መልክ ለመ/አለቃ አጊ አሳ
ወቁ ።

መ/አለቃ አጊ በዛን ጊዜ 43 ዓመት የሞላው ጉል
ማሳ ነበር ። አጊ ምንም እንኳን ለቶኪዮ ፖሊስ ዋና
መምሪያ አዲስ ተቀጣሪ የነበረ ቢሆንም በካርዶቹ ምር
መራና ጉዳይ ላይ በሰል ያለ ዕውቀት የነበረው ነበር ። በሌላ
በኩል ደግሞ የሥራ ባልደረቦቹ (ጓደኞቹ) በሙያው ላይ
የነበረውን የዐቃቤ ሕግ አቋም ይቃወሙትና እንዲያውም
ስሙን ከማጥፋት አልፈው ይወነጅሉትም ነበር ።

አጊ የፖሊስን ሙያ የመረጥኩት ድብቅ ወንጀሎችን
በማውጣት ኅብረተሰቡን የማገልገል ከፍተኛ ዝንባሌ ስለ
ነበረኝ ነው ባይ ነው ። በፖሊስነት ሙያ በተግባር እንደ
ሚታየው ግን የጀመረውን ሥራ ዳር ሳያደርስ በመሰልቸት
የሙተው አዝማሚያ ታይቶበታል ። የኋለ ኋላ ግን የፖሊስ
ዝንባሌው ከፍተኛ እየሆነ በመምጣቱ ለሰከነ ሥራ የተመ
ቻቸም ሆኖ ነበር ። ቢሆንም በአጊም ሆነ በሌሎች
ብርቱ የፖሊስ ተከታታይዎች የተደረጉት ጥረቶች እስከአ
ሁን እመርቂ ውጤት አላስገኙም ።



ፖሊሶቹም በየአቅጣጫው ከአደረጉአቸው ክትትሎችና
ምርመራዎች በተጨማሪ በሻይ ስኒዎቹ የደረሰውን የፍጆት
ሚስጥር ለማውጣት 8 ሺህ ሰዎችን ለጥያቄ ማቅረብ ተገደው
ነበር ። ዶክተር ማቱሳንም እንደገና ጠርተው ስለገሙበኝት
ካርዶቹ ሊያስተውሱ የሚችሉአቸውን ነጥቦች በሙሉ እን
ዲነግሩአቸውና በልውውጥም ያገኟቸውን ካርዶች ሊያስ
ታውሷቸው ይችሉ ዘንድ ከፍተኛ ግፊት አደረጉ ። በዚያም
ልዩ ቁረት ዶክተሩ በልውውጥ ካገኟቸው ካርዶች መካከል
‘‘ሳዳሚቺ ሂራስዎ’’ የሚባል የአንድ አርቲስት ሰዓሊ ስም
ተገኘ ። የዚያ ሰዓሊ የመኖሪያ አድራሻ በካርዱ ላይ የተጻፈ
ሲሆን ስሙም አታሩ ሆካይዶ በሚል ተመዝግቧል ።

ዶክተር ማቱሳ ሆካይዶን የተዋወቁትና የተገነዘ
ቡት እንደ የአንድ የአርቲስት ሰዓሊያን ማኅበራት ሊቀ
መንበር አድርገው ነበር ፣ ሆኖም የተገለጸውን ያህል
ታዋቂነት አልነበረውም ።

ከዚያም ሰዓሊ ጋር ለመተዋወቅ የቻሉትም በአ
ንድ አነስተኛ ጀልባ ጉዞ ላይ እንዳሉ መሆኑን አስታውሰው
ርሳቸውም በሰዓሊው ሁኔታ መሳባቸውንና በወቅቱ “ጸደይ
ተቃርቧል ” የሚል ጽሑፍ በአንድ ቦርድ ላይ ስሎ ያንኑ
ሥራ ለቶኪዮው አልጋወራሽ በስጦታ መልክ ሊያቀርበው
ማዘጋጀቱን የነገራቸው መሆኑን አስታውሰዋል ።

በዚያም መሠረት የተባለውን ሰዓሊ ካለበት መኖሪያ
ቤት ድረስ በመሄድ ማንነቱን ማረጋገጥና ማወቅ አስፈላጊ
ሆኖ በመገኘቱ ፖሊሶች ተላኩ ። ፖሊሶቹም ይዘውት በመ
ጡት መረጃ መሠረት የተባለው አርቲስት የ50 ዓመት ዕድ
ሜ የነበረው ዓይነ አፋር የሆነና ቀደም ሲል ከቀረበው የም
ስክሮች ማረጋገጫ መግለጫ ጋር በምንም ዓይነት የማይ

መሳሰል መሆኑን አረጋግጠው ሪፖርታቸውን አስተላል ፈዋል ።

የክትትሉና የምርመራው ጉዳይ ውሎ ባደረ ቁጥር እየቀዘቀዘና የኤሊ. ጉዞ መልክ እየያዘ መጣ ። እንዲያውም እያደረ በሄደ ቁጥር ውኃ ከማይገባው አለት ላይ የሚፈስ ውሃ ይመስል ጀመር ። ያም በመሆኑ በቶኪዮ የሚገኙ እውቅ እንስፔክተሮች ተሰባስበው ጉዳዩን አንድ እልባት ለማስያዝ የሚያስችላቸውን ጥናት ተያያዙት ። በዚያም መሠረት የቀረቡት መረጃዎች ሁሉ አንድ በአንድ በጥልቀት እንዲመረመሩ ተደረገ ፡ ቀደም ብለው ተዳስው የታለፉት ጥቆማዎችና መረጃዎችም እንደገና የመታየታቸውና የመጠናታቸው ጉዳይ አማራጭ የሌለው ሆኖ በመገኘቱ በተለይ ቀደም ሲል የተጠቆመው ሰዓሊ ለዳግመኛ ምርመራ እንዲጠራ ተደርጐ ፡ ምርመራውን ያካሄዱት ፖሊሶች ከደሙ ንጹህ መሆኑን በድጋሚ አረጋገጡ ። በዚያ ደረጃ የአብዛኛዎቹ መርማሪዎችና ተከታታዮች ትዕግሥት በመሟጠጡ ምርመራውና ክትትሉ እንዲቆም መጉትጐታቸው አልቀረም ።

ከላይ ታሪኩ በመጠኑ የተገለጸለት መ/አለቃ አጊም ጉዳዩን በበለጠ ትዕግሥትና ፖሊሳዊ ጥበብ ያለመሰል ቸት ግብ ለማድረስ ታጥቆ መነሳቱን አሳወቀ ፡ በዚያም ቆራጥ ሐሳቡ ምንም ዓይነት ተቃውሞ አልደረሰበትም ።

አጊ በፍጹም ቆራጥነትና ትዕግሥት ደብዛው እየጠፋ የመጣውን የሻይ ስኒ መርዝ ፍጅት ምርመራ ለመቀጠል በተነሳበት ወቅት ስለጉዳዩ በቅድሚያ ዝርዝር ጥናት ወስዷል ። በጁዶ ትምህርት ለውጤት አስተዋይነትና ትዕግሥትን የተማረው አጊ በቅድሚያ ተደጋጋሚ



ትኩረት የተደረገበትን ሰዓሊ በማውጣጣት ተጨባጭነት ያለው ፍንጭ ለማግኘት ቆርጦ ተነሳ ።

ሰኔ 3 ቀን መ/አለቃ አጊ በእጅ ሻንጣው የባንኩን የመርዝ ግድያ መረጃዎችን በማመቅ ወደሰሚን ጉዞውን ቀጠለ ። ጉዞውን ያደረገው በለሊት በሚጓዘው ባቡር በመሳፈር ስለነበር በእንቅልፍ ላይ እንዳለ መረጃዎቹ እንዳይሰረቁበት በመስጋት የእጅ ቦርሳውን ከእግሩ ላይ አስሮት ተጉዟል ።

በእርግጥ አጊ ሰዓሊው ከጥርጣሬ ዝርዝር ውስጥ ነጻ ሊሆን እንደሚችል ገብቶታል ፡ ሆኖም በዚያ ረገድ የሚኖረውን ጥርጣሬ ከአእምሮው ፍጹም ነጻ ለማድረግ ይቻለው ዘንድ ውል ያለው ፍተሻና ምርመራ ማድረግ ስለሚገባው ሰዓሊውን ከማየቱ በፊት ስለጓደኞቹ ፡ አዘጋጅቶ ስለአወጣው የጉብኝት ካርዶችና ሌሎች ሁኔታዎች በቅድሚያ አጠና ።

በዚያው ጥናት ካገኛቸው ፍንጮች መካከልም ያው ሰዓሊ በአንድ ወቅት በካርድ ሥራ በአደረገው ሥርዓት አልባ ተግባር ተከሶ ለምርመራ የቀረበ የመሆኑ ሁኔታ ስሚቱን ስለነካውና ስለቆረቆረው መላ ምት ጥበቡን (ስልቱን) ከመጠቀም ራሱን በመቆጣጠር ሊገታ ያልቻለ መሆኑን በኋላ ሲተርክ አውስቷል ።

አጊ ሰዓሊው ጋር የመጀመሪያውን የትውውቅ ቀጠሮ የወሰደው የአንድ የከብት ዕርባታ ሥራ ያካሄድ በነበረ በሰዓሊው ወንድም አማካኝነት ነበር ። ስለ ሰዓሊው የሥራ ውጥረት ሁኔታም ጠይቆ ምንም ሥራ እንደሌለው ስለአረጋገጠለት ከሰዓሊው ቤት ተያይዘው ደረሱ ። ከቤቱ እንደደረሱ ወንድምየው ሰአሊውን አነጋግሮት

እስኪመለስ ድረስ እጊን እንዲጠብቀው አድርጐ ቤቱ ውስጥ ከገባ በኋላ ተመልሶ በመምጣት ሰዓሊው ከወላጆቹ ጋር ሆኖ ወደሚጫወትበት ወደ ላይኛው ክፍል ወሰደው ።

በትውውቁ ወቅትም እጊ ሁለት ነገሮች ከመሥመር ውጭ ሆነው አገኛቸው ። እነዚህም አንደኛው ቀደም ሲል የሰዓሊው ወላጆች በጠና ታመው እንደነበር የደረሰው መረጃ ሐሰት ሆኖ የሁለቱም ወላጆቹ ጤና በጣም የተጠበቀ ሆኖ ማግኘቱ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሰዓሊው ሥራ እንደሌለበትና እንዳልያዘ የተነገረው መረጃ ሁኔታ ነበረ ። እጊ ከሰዓሊውም ቤት ውስጥ የአንዱ ክፍል በር ገርበብ ብላ ለማየት እንደቻለው የሰዓሊው የስዕል ዕቃ ዎች ተበታትነውና በሥራ ላይ እንዳሉ ሆነው አግኝቷቸ ዋል ። በመሆኑም እጊ ከላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ረገድ ለምን ለማስመሰል ሙከራ ሊያደርግ እንደቻለ ማሰላሰልና ማጤን ጀመረ ። የሰዓሊውን ገጽታ እጊ በትኩረት ሲመለከት ቀደም ብሎ በምስክሮች የተረጋ ገጠውና በፖሊስ የተላለፈው መግለጫ ትዝ አለው ። በፖሊስ የተላለፉት ምልክቶች ያለአንዳች ጥርጥር በሰ ዓሊው ገጽታ ላይ ይነበባሉ ።

ከሰዓሊው ጋርም እጊ ባካሄዳቸው ረጋ ያሉ ወንድ ማዊ ውይይቶች ከግድያው ጉዳይ ጋር በቀጥታም ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ግንኙነት ያላቸውን ወጐች አ ነሳ ። በዚያም መሰረት በባንኩ በሻይ ስኒ መርዝ ግድያ ይካሄድ በነበረበት ወቅት በአንድ በተባበሩት መንግ ሥታትና በጃፓን በጐ አድራጊዎች ኅብረት ይታይ በነበረ አንድ የውሃ ቅብ ስዕል ኤግዚቭሽን አዳራሽ



ከጥር 21 እስከ ጥር 28 ባሉት ቀናት በየዕለቱ ይሄድ እን ደነበር አውስቷል ።

ሰዓሊው ከላይ ከተጠቀሱት ቀናት መካከል በተለ ይም ጥር 26 ቀንን ሆን ብሎ በማንሳት በዚያን ዕለት ከአ ማቹ ኡዙ ያማጉቺ ጋር ከእኩለ ቀን በኋላ የነበረውን ቀጠሮ ለማክበር ከቀትር በፊት የስእሉን ኤግዚቭሽን መጐብኘቱንና ወደ ቤቱ ከተመለሰ በኋላ በባንኩ ቤት የተካሄደውን አሰቃቂ ግድያ በሬድዮ መስማቱን አረጋ ግጦለታል ። የሰዓሊው የዚያ ዙሪያ ጥምጥም ወግና ጥረት የባንኩ ወንጀል በተፈጸመበት ዕለት በአካባቢው ያለመድረሱን ለማስተባበል ሆን ብሎ ያደረገው መስሎ ታይቷል ።

እጊ ምንም እንኳን በሰዓሊው ረገድ ከላይ የተጠ ቀሱትን መረጃዎች ለማገኘት ቢችልም የአካባቢው ፖሊ ሶች ሰዓሊውን ከጥርጣሪያቸው ፍጹም ነጻ አውጥተውት ስለነበር ከነርሱ ጋር ያልታሰበ ግጭት ላለመፍጠርና ላለማስቀየም ሲል የሚያቀርባቸውን ጥያቄዎች በመ ቆጠብ ሌላውን የክትትል ዘዴውን ተያያዘው ። በዚ ያም ረገድ ጉዞውን ወደ ሆካይዶ ቀጠለ ። ሰኔ 12ትም ወደቶኪዮ ከመመለሱ በፊት በተንጠለጠለ መረጃ ልቡን መስቀል ባለመፈለጉ ሰዓሊውን እንደገና መልሶ ጐበኘው ። እጊ ያን ሁኔታ በሚመለከት እንደ ተናገረው “ በእጄ ለመጨበጥ የፈለኩትን ነገር ስላላገኘሁ ከመጠን በላይ ይከነክነኝ ነበር ። በመሆኑም መላልሼ ሰዓሊውን ለመጐ ብኘት መነሳቴ የግድ ሆኖብኛል ” ብሏል ።

ሁኔታው በዚያ ደረጃ ላይ እንዳለ በተለይ በጃፓ ኖውያኑ ተከታታይዎችና በተጠርጣሪው ሰዓሊ መካከል

የተደረሰው መንቃቃት ተፈጥሮአዊ ያልሆነ ትሁትናንና
መከባበርን ሁሉ እየፈጠረ ይሄድ ጀመር ።

አጊ በዚየ መስል ግንኙነት ለሰዓሊው የዕለት ግብኘ
ማድረግ ሁሉ ጀመረ። በዚየው ወግና ወዳጃዊ መስል
ግንኙነት ሰዓሊው ፎቶግራፉን በማስታወሻነት እንዲ
ሰጠውም ጠይቆት ለጊዜው ያልነበረው መሆኑን ገልጾለታ
ል።ከዚየ በኋላ ግን አጊ ሰዓሊውን ፎቶግራፍ አንስቶ በስ
ጦታ መልክ አበርክቶለታል ። በደራ ጨዋታቸውም አጊ
ስለዶክተር ማቱሳ አውስቶለት ሰዓሊው በአንድ አነስተኛ
የመጓጓዣ መርከብ ላይ እንደተገናኙ ማስታወሱንና
ዶክተሩ በካርዱ ላይ አድራሻ ለመጻፍ ሲሉ ብዕሩን
ወስደው እንዳስቀሩበት አወጋው ። አጊም ካርዱን እንዲየሳ
የው ሲጠይቀው የተባለው ካርድ 211 000 የን ኪያዘ
የገንዘብ ቦርሳው ጋር በቶኪዮ ኪስ አውላቂዎች ከጥቂት
ቀናት በፊት እንደ ተሰረቀበት ነገረው ።

አጊ በተከታታይ ያጠራቀማቸውን መረጃዎች በመ
ያዝ ወደቶኪዮ በመመለስ ላይ እንዳለ እግረ መንገዱን
ወደ ዶክተር ማቱሳ ቤት ጐራ በማለት ስለብዕሩና በካ
ርዱ ላይ ስለተጻፈው ጉዳይ በዝርዝር ሊያጫውቱት
ይችሉ ዘንድ ጥያቄዎችን አነሳ ። ዶክተሩም ለጊዜው
በመገረምና በመደናገጥ ብዕር የመያዝ ልምድ የሌላቸው
መሆኑን አረጋግጠውለታል ።

መ/አለቃ አጊን ያስደነቀውና ትኩረቱን ያሰባሰ
በው ሌላው ጠቃሚ ነጥብ ሰዓሊው ስለኬሚካል የነበ
ረው ጥልቅ ግንዛቤና ዕውቀት ነበር ። አጊ ከሰዓሊው
ጋር ባደረጋቸው ውይይቶች በአብዛኛው ስለፖታሲየም



ሲናይድ በብዛት ይጠቅስለት ነበር ። በዚያም ሰዓሊው
ስዕል መሳል ከሚያስፈልገው በላይ ስለኬሚካሎች ቅመ
ራ (ቅመማ) ማወቁ የሚያስደነግጥና የሚያስገርም ሆኖ
አግኝቶታል ።

አጊ ወደቶኪዮ ተመልሶ ከላይ ተከታትለው የተጠቀሱ
ትን መረጃዎች አቀናጅቶ ሪፖርት ለማድረግ በመቻሉ
ሰዓሊው ሂራስዋ በጥርጣሬ ዝርዝር ውስጥ እንደገና እን
ዲገባ ወይም እንዲመዘገብ ተደረገ ። በመሠረቱ በሻይ
ስኒ መርዝ ፍጅት ወንጀል ከ2000 ያላነሱ ተጨማሪ
ሰዎች በመታሰራቸው በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ሂስ ይካ
ሄድባቸው ነበር ። ይህ ሁኔታ እንዳለ ሆኖ በሰዓሊው ፎቶ
ግራፍ ረገድ በአጊና በመርማሪዎቹ መካከል ከፍተኛ
የሃሳብ ልዩነት ተፈጠረ ። በዚያ የሃሳብ ልዩነት መሰረ
ረትም መርማሪዎቹ የሚፈለገው ሰው ምስል አጊ ካቀ
ረበው ጋር አይመሳሰልም በማለት ተስፋ በመቁረጥ
ከጉዳዩ እጃቸውን ለማውጣት ወሰኑ ። ሆኖም የአጊ አለ
ቆች የተሻለ ተጨባጭና አሳማኝ ፍንጭ ካገኘ ጉዳዩን
እንደ ገና ሊያንቀሳቅሱት እንደሚችሉ ቃል ገብተው
ለት ጥረቱ በዚያ ደረጃ ተገቶ ተሰናበተ ።

ቢሆንም አጊ የተሰጠውን ተስፋ በመቀበልና የጀመ
ረው ክትትል ትክክለኛ መስመሩን የያዘለት መሆኑን በራሱ
በመተማመን እንደልቡ መንቀሳቀሻ የሚሆን ገንዘብ ለማ
ግኘት ቤቱን በ350 000 የን (በጊዜው ብዙ ዋጋ ነበር) ለመ
ሸጥ ወሰነ ። ሆኖም የፖሊስ ዋና ጽ/ቤት አጊ በወሰነው ው
ሳኔና በተነሳበት ቆራጥ ርምጃ በመደነቅ ቤቱን እንዳይሸጥና
በዚያ ምትክ ግን ለ70 ቀናት የሚያንቀሳቅሰው የ70,000
የን አበል ተሰጠው ፤ አጊ በዚያ ደረጃ በራሱ ርምጃ የሚ
ንቀሳቀስ በመሆኑ በቅድሚያ በዋናው መ/ቤት በመሆን
ዘርዘር ያሉ ጥናቶችን በማካሄድ አጣራ ። ከፍተኛ ትኩ

ረት ያደረገበትን ሰዓሊ በቶኪዮ ተቀምጦ የአኗኗሩን ሁኔታ በቅርብ ማጥናትና መከታተልም ጀመረ ። ከዚያም አልፎ የሰዓሊውን ጓደኞችና አኗኗር እንዲሁም የግንኙነት ሁኔታ ሁሉ በማጠያየቅ በዝርዝር ማጥናቱን ተያያዘው ። ሌላው ቀርቶ የሰዓሊውን ባለቤትና ሴት ልጅ እንኳን ሳይቀር በቅርብ በመገናኘት ነገሮችን መንጥሮ ለማውጣት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ጀመረ ።

የሰዓሊውን የእጅ ጽሁፍም ከተለያዩ ካርዶችና ከሌሎችም በመውሰድ ከተመነዘሩት ቼኮች ጽሁፍ ጋር የማገጣጠምና የማመዛዘን ሥራውንም ጀመረ ። በዚያም ረገድ ተጨባጭነት ያለው ውጤት ለማግኘት ችሏል ።

ከላይ የተጠቀሱትን ተጨማሪ መረጃዎቹን ካሰባሰበ በኋላ አጊ ኢንስፔክተር ሆሪዛኪ ጋር በመቅረብ ጉዳዩን ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማስረዳት የእስር ማዘዣ ወጥቶ ሰዓሊው በቁጥጥር ሥር እንዲውል ሪፖርት አቀረበ ። አጊ በዚያ ሪፖርቱ ሁለት መሠረታዊና ጠቃሚ ጉዳዮችን ለፖሊስ ለማስጨበጥ ችሏል ። እነዚያም

1ኛ. በየካቲት 9 የሰዓሊው ባለቤት 44,500 የን በባለቤቷ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ባንክ ማስገባቷ ፤ ሆኖም ከተባለው ሁለት ቀናት በፊት ሰዓሊው 150 የን የሚያወጣ ወጭ ለመክፈል መቸገሩና ለሰዓሊዎች ማኅበር የሚከፍለውን ክፍያ በችግር ምክንያት ማሳለፉ ታውቋል። ከዚያም ሌላ ለባለቤቱ 3 ጊዜ በመመላለስ የሰጣት ድምር 69,000 የን መሆኑን አረጋግጧል ።

2ኛ. ሰዓሊው ሁለት ውሽሞች እንደነበሩትና በገንዘብ በኩል ያስቸግሩት እንደነበርም ተረጋግጧል ።



በመሆኑም አጊ ያጣራውና የለፋበት ጉዳይ ከሰባት ወር በኋላ ተሳክቶለት በነሐሴ 20 በሰዓሊው እጅ ላይ ሰንሰለትዋ እንድትጠልቅ አስደረገ ።

አጊ የሰዓሊውን በድንገት የመታሰር ዜና በቅጽበት እንዳይሰራጭ ተገቢውን ቅድመ ዝግጅትና ጥንቃቄ ለማድረግ ሞክሮአል ። በዚያም መሰረት እጆቹን የከረቻማቸው ይህን ጉዳይ እንዲያከናውኑ ግዳጅ ከተሰጡት ሌሎች ሁለት ተከታታይዎች እጆች ጋር ነበር ፤ የዚያም ሁኔታ ማንኛቸው እንደታሰሩ የማሳሳቻ መንገድ (ዘዴ) ይሆናል የሚል ግምት በተመልካቹ ልቦና ላይ አሳድሯል ። ያም ሆነ ይህ ወሬው ከመቅጽበት ሾልኮ በብዙኃኑ መገናኛ ተበተነ ። የዜናውም ሁኔታ ተዳፍኖ የነበረውን ወይም እንዲቀር የተደረገውን የሰብአዊ መብት ረገጣ ጉዳይ እንደገና ቀስቅሷል የሚል ሮሮ አስከተለ ። በተለይ ሰዓሊው ጥፋቱ ታውቆ ሳይፈረድበትና ተጨባጭ ማስረጃዎች ሳይሰበሰቡበት በእጅ ሰንሰለት ታስሮ ወደ ወህኒ መውረዱ አጠያያቂ ጉዳይ ሆኖ ቀረበ ። አጊ ግን እጁን በሰንሰለት ለመከርቸም የተገደደው ተጠርጣሪው እንዳያመልጠውና ቶኪዮ ድረስ በሰላም ለማድረስ በመፈለጉ መሆኑን አረጋግጧል ።

የስኒ መርዝ ፍጅቱ ጉዳይ መላውን የጃፓን ሕዝብ በወቅቱ ያነጋገረና ያበሳጨ ጉዳይ ስለነበረ በወንጀሉ ተጠርጥሮ የተያዘውን ሂራሳዋን ለማየት ሥፍር ቁጥር የሌለው ሕዝብ ተይዞ በተጓጓዘበት ባቡር ጣቢያ ተኮልኩሎ ጠብቋል ። ከሕዝቡ የተለያዩ አስተያየትና የቅሬታ ስሜት በወቅቱም በባቡሩ ጣቢያ አካባቢ የተደመጠ ሲሆን አንዳንዶቹም እንዲህ ዓይነቱ ሰው ያለአግባብ ተወንጅሎ ሰብአዊ መብቱ እንዴት ሊገፈፍ ይገባዋል ? በማለት ያጉረመርሙ ነበር ።

በሌላ በኩል ግን የሰዓሊውን ወንጀል በተሻለና በበለጠ ሁኔታ የሚያረጋግጡ መረጃዎች መሰብሰባቸው አልቀረም ። በተለይም ቶኪዮ የሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ሲፈተሽ በወቅቱ ወንጀሉን ፈጽሞ የተሰወረው ነፍሰ ገዳይ ለብሷቸው የነበረውን የሚመስሉ ቡናማ ሙሉ ልብስና ከላይ የሚጠለቅ ነጭ ልቅ ልብስ እንዲሁም ገዳዩ ይዞት ነበር ተብሎ የተመሰከረው ትንሽ ጥቁር የቆዳ ቦርሳ ተገኙ ። ከዚህም ሁሉ በላይ ሁለቱ ከሞት አፋፍ የተረፉት የባንክ ሠራተኞች በአንደኛ ደረጃ አስረጅነትና ምስክርነት ቁመው የስኒውን መርዝ ፍጅት ያስከተለው ራሱ መሆኑን አረጋገጡ ። ይህ ሁሉ ማስረጃ ቢጠናከረበትና ቢመስከረበትም ሰዓሊው ፈጽሞ በተባለው ወንጀል አለመሳተፉንና ከደሙ ነፃ መሆኑን ለፖሊስ ምርመራ በተደጋጋሚ በመቅረብ ጠንካራ የክህደት አቋም ወሰደ ።

አጊም ቀደም ሲል ያልነበረውን ያን ያህል ገንዘብ ባጭር ጊዜ ውስጥ እንዴት ሊያገኝ እንደቻለ ጠየቀው ። ሰዓሊውም አንድ ዶክተር ኡዞ የሚባል የኢኖ ኢንዱስትሪ ኩባንያ ፕሬዚዳንት የነበረ በጥቅምት ወር (ከግድያው3 ወር ቀደም ሲል) የሰጠው መሆኑን ተናገረ ፤ አጊ ግን ማስታወሻውን ከኪሱ ሳብ አድርጐ የተባለው ሰው የሞተው በነሐሴ መሆኑን በመግለጽ ዓይን ያወጣ ውሸት እንደነገረው ደብተሩን ከፊቱ በመወርወር አረጋገጠለት ። ሰዓሊውም ያን የቀን መዛባት ጥያቄ ጉዳይ ለማስተናገድ የሚሳነው መሆኑን በማረጋገጡ ፊቱ በድንገት ፍም መሰለ፡ ውስጣዊ የመንፈስ መረበሹን የሚያረጋግጡበት ምልክቶችም በገጽታው ተባብረው አጋለጡት ።

ሂራስዋ ወህኒ እንዳለ የኋላ ኋላ ስለአጊ ሲገልጽ “ አጊ እንደድመት አድፋጭ ፤ ተንኮለኛና ሰይጣን የሆነ



ተከታታይ ነው ” ብሎታል ። በእስር ቤት እንዳለም ራሱን ለማጥፋት ከአንድም ሶስት ጊዜ ተደጋጋሚ ሙከራዎችን አድርጐ ነበር ። እንዲያውም አንድ ጊዜ ከመጠን በላይ መድኃኒት በመዋጥ ራሱን ለመግደል ሞክሮ በሕክምና ሲፈወስ ከአንድ የወህኒ ቤት ዘበኛ ደረት ላይ እርሳስ በመንተፍ የእጁን ሥር ለመቁረጥ አስቦም ሳይሳካለት ቀርቷል ።

በመጨረሻ የቶኪዮን ፖሊሶችና በተለይም አጊን ያስመረረው ክህደቱ ተለወጠ ። ሰዓሊው በወህኒ እንዳለ ኑዛዜውን አቀረበ ፤ በኑዛዜውም የሙታኑ መናፍስት ለሊት እንቅልፍ እንደነሱት ገልጾ ራሱ አዘጋጅቶ በሰጣቸው መርዝ የተፈጁ በመሆናቸው የሞት ፍርድ እንዲፈረድበት ጠየቀ ። በዚያም መሠረት ጥቅምት 12, 1948 ሂራስዋ በዘረፋ ፡ በግድያ ፡ ማጎተሞችን አስመስሎ በመሥራትና ለመግደል በመዶለት ወንጀል ክስ ተመስርቶበት ከሰጠው የእምነት ቃል ጋር ሌሎችን የተሰበሰቡ ማስረጃዎች ሁሉ በማጠናከር ለፍርድ ቀረበ ። ቢሆንም ራሱ ሰዓሊው የገዛው ጠበቃ በመድኃኒትና በመንፈስ ስቃይ ብዛት የመጣበት ሐሳብ ነው በሚል ተሟገተ ። የዚያም ሙግት ሁኔታ የተለዩ መልክ ይዞ ቀረበ ።

በመሠረቱ ፖሊስ ያን ጉዳይ ለመከታተል ያወጣው ወጪ ሲተመን 17,000 የአሜሪካን ዶላር ደርሷል ። በዚያው አስቃቂና አደገኛ ወንጀል ሳቢያም በጥርጣሬ 8,796 ሰዎች ተይዘዋል ፤ ያም ሆኖ በተለይ በተጨማሪ የተያዙት ሰዎች በሰዓሊው መያዝ ምክንያት መለቀቅ እንደሚገባቸው ፖሊስ በማመኑ ሊለቀቁ ይችሉ ዘንድ ለፍርድ ቤቱ ጥያቄ አቅርቧል ።

ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ቀርቦ ክርክር የተጀመረው ከሕዝብ ተመርጠው ፍርድ ቤት የሚቀመጡ ታዛቢዎች በሌ

ሉበት በእንዴት ሦስት ዳኞች በሚያካሂዷት በቶኪዮ በምትገኝ ፍ/ቤት ነበር ። ከፍ/ ቤቱዋም ክስ ቀርቦ ክርክር እየተደረገና ማስረጃ እየተደመጠ የመጨረሻውን ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ 15 ወራትን ፈጅቷል ። ወንጀለኛ ተብሎ የታሰረውና ለፍርድ የቀረበውም ሰዓሊ ወንጀለኛ አለመሆኑን የሚያረጋግጡለት መከላከያዎችን በመደርደር ከነጠበቃው ሽንጡን ገትሮ እንደገና ተጋተረ ። ቀደም ሲል የተናዘዘውም ፖሊስ በርሱ ላይ ባካሄደበት አግባብ የሌለው ምርመራ ከመሆኑም በላይ አንዳንድ አንጐል የሚያስትና የሚያቀውስ የምርመራ ዘዴ ተጠቅመውብኛል በማለትም ተከራከረ ።

ጠበቃውም እንደገና ሰዓሊው በ1925 በተወጋው የዕብድ ውሻ መድኃኒት ምክንያት ጤናው የቀወሰ ሰው ምልክት ይታይበታልና ወደ አእምሮ ሐኪም እንዲሄድለት ጠይቆ በዚያው መሠረት ከተፈጸመ በኋላ ጤነኛ ሰው መሆኑ ተረጋገጠ ።

ዐቃቤ ሕጉም በበኩሉ እንዴት አድርጐ ሂራስዋ ለባንክ ሠራተኞች መድኃኒቱን በሻይ ስኒ እንዳጠጣ በፊልም ቀርጾና አስደግፎ በማስረጃነት ለፍርድ ቤቱ አቀረበ ። ያው አቃቤ ሕግም በጉዳዩ በጥልቀት በመመስጥ የዚያ ዓይነት ወንጀል ተሰምቶም ተደርጐም የማይታወቅ የጭካኔ ውጤት በመሆኑ እንደዚያ ዓይነት ሰው ይቅርታ ሊደረግለት እንደማይገባ ለዳኞች በማሳመን አቀረበ ። በዚያም ሐሳብ መሠረት አራት ቀናትን የፈጀ የማጣሪያ ሥራ ከተካሄደ በኋላ ዐቃቤ ሕጉ ያቀረባቸው መረጃዎች ተቀባይነት አገኙ ።

በሌላ በኩልም ደግሞ ሂራስዋ በባህሪውም ሆነ በሞራሉ የዚያን መሰል የጭካኔ ተግባር ለመፈጸም የማይችል



በጣም ሰብአዊነት የሚያጠቃውና ሰዎችን የማያፈቅር በመሆኑ የተባለውን ወንጀል ፈጽሞ ለመፈጸም ችሎታም ሞራልም የሌለው መሆኑን በማጋለጥ ጠበቃው ተሟግቶለታል ። በዚያው የመከላከያ ሙግት ሰዓሊው እናቱና አባቱን በጠቅላላው ቤተሰቡንና ወዳጆቹን አፍቃሪና አሳቢ ከመሆኑም በላይ ከስዕል ሥራው በስተቀር ሌላ ነገር ስሜት የማይሰጠው በጣም ትሁት የ57 ዓመት አዛውንት መሆኑን በማስረዳት የቀረበበትን ወንጀል አስተባብሎለታል ።

ለዚያ የግድያ ወንጀል ወይ መጨረሻ የመዝጊያ ቁልፍ ሆኖ የተገኘው መድኃኒት በትክክል በወንጀለኛው እጅ ለመግባቱ የሚያረጋግጥ መረጃ ስላልቀረበበትና በተለይም የእጅ ጽሑፉ በፖሊስ ላቦራቶሪ በሳይንሳዊ መንገድ ሊታወቅ ባለመቻሉ ሲሆን መርማሪውንም ተፈታትኗል።

ያ ሁሉ ክርክር ይካሄድ በነበረበት ወቅት ተከሳሹ ሰዓሊ በብሔራዊ ጦርነት ጊዜ የሚለበስ ባሕላዊ ልብስ ለብሶ በመዝናናትና ፍጹም ተስፋ በቆረጠ ስሜትና መንፈስ ይከታተል ነበር ። በመጨረሻው የፍርድ ዕለት ግን በሀገራቱ እጅግ የተከበረና የተለዩ ልብስ ከላይ እስከታች ለብሶ ቀረበ ። የሆነ ሆኖ ያ ሁሉ የማስመሰል ሁኔታ ከወንጀሉ ነፃ ሊያደርጉት አልቻሉም ፤ ፍርድ ቤቱ ወንጀለኛነቱን ስለአረጋገጠበት በስቅላት የሞት ቅጣት እንዲቀጣ በየነበት ።

የሞት ፍርዱም ብያኔ ሲነበብ ወንጀለኛው "ትልቅ ወንጀል ተፈጽሞኛል ፤ ያለበቂ መረጃና ያለአግባብ ተፈረደብኝ" በማለት በመዝለልና ውሳኔውን ለመስማት በተሰበሰበው ሕዝብና የፍርድ ቤት ሠራተኞች መሀል በመጮህ የተለየ አስደንጋጭ ሁኔታ ፈጠረ ። በዚያም ራሱን የመረበሽና የአ



የጃፓኑ ሰዓሊ ሳዳሚቺ ሂራስዋ ፣ በእጅ ሰንሰለት ታስሮ ፣ የበዓል ብሔራዊ ልብስ አጥልቆ ፣ በሻይ ስኒ የመርዝ ድግስ ደግሶ የ12 ሰዎች ግድያና የባንክ ዘረፋ በመፈጸሙ የመጨረሻውን ፍርድ ለመቀበል ወደ ቶክዮ ፍርድ ቤት ሲሄድ/ አሻሂ ሺምቡን /



ሪታ ሁከት ዓይኑ ተጉልጉሎ ፊቱም ከፉኛ ተለዋወጠ ።

በመሠረቱ በሰዓሊው ላይ የተፈረደው ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በዝርዝር በንባብ ተሰምቷል ፤ በዚያው መሠረት ዳኛ ሪጉቺ በንባብ ባሰሙት 150 የውሳኔ ጽሑፍ ላይ ሂራስዋ በሰዓሊነት በአንድ ወቅት ታዋቂነትን ያተረፈ ለመሆኑ በሚገባ አትተውና ጠቅሰው በውሻ በሽታ ለሕክምና በ1925 መድኃኒት ከተወጋ ጀምሮ ግን ሰዎችንና ራሱን የማታተል ባህሪይ እንደወረሰና የስዕል ሥራዎቹም ደንበኛ እያጡ በመጡ ቁጥር ያው ባህሪይ እየባሰበት ከመሄዱም በላይ ለቤተሰቡና ለሁለቱ ቅምጦቹ ሥራ አሰሪ ማጣቱን በመንገር የተግበሰበሰ የገቢ ምንጩን አመጣጥ ይደብቃቸው እንደ ነበር ተረጋግጧል ። ጉዳዩን በዝርዝር ሲያትቱም የዶክተር ሽጌሩ ማቱሳን ካርድ በመቀበል የመጀመርያ ሙከራውን ሲያደርግ እንደከሸፈበት ሆኖም በተከታታይ ሙከራውን በመቀጠል ምንም እንኳን 4 ሰዎች በሕይወት ለመትረፍ ቢበቁም የ12 ምስኪንና ሰላማዊ ሰዎች ሕይወት በራሱ ተንኮል በአሰቃቂ ሁኔታ በመረፍረፉ የፈጸማቸው የወንጀል ድርጊቶች የቀረቡ በመሆኑ ከፍርዱ ነፃ የሚሆንበት አንዳችም መንገድ አልተገኘም ።

ሂራስዋ ከተፈረደበት የሞት ቅጣት ራሱን ነፃ ለማውጣት ያለማቋረጥና ያለመሰልቸት እስከ መስከረም 29/1951 ለቶኪዮ የበላይ ፍ/ቤት ይግባኙን ያኾርጉደጉደው ጀመር። ቢሆንም ተቀባይነት ሊያገኝ አልቻለም ። በመጨረሻም 71,200 ገጽ የያዘው የምርመራ መዝገቡና ማስረጃዎቹ ከተመረመሩ በኋላ የጃፓን የመጨረሻው ጠቅላይ ፍ/ቤት በመጋቢት 6/1955 የይግባኙን ጥያቄ ውድቅ አደረገ ።

የሆነ ሆኖ በውል ባልታወቀ ምክንያት የሂራስዋ የሞት ፍርድ ትዕዛዝ ሳይፈጸም 20 ዓመታትን አሳልፏል ። በዚያ ሁኔታ ሰዓሊው በእስር ቤት በመማቀቅ ከመገኘቱም በላይ ዕርጅና ከፉኛ ተጫጭኖት የ80 ዓመት አዛውንት ሆነ ።

በዓለም አስደናቂና አስገራሚ ሪኮርዶችንና ሁኔታዎችን በመመዝገብ ረገድ የታወቀው የጂኒየስ መጽሐፍ ስለ ግድያው አጠቃላይ ሁኔታ የገለጸ ሲሆን ይህን ወንጀል ባጭሩ “ የዓለም የመጨረሻው ዝግ ያለ ወይም የሰመመን የጭፍጨፋ ስልት ” ብሎታል ።

ሰዓሊው በእሥር ቤት ጊዜውን የሚያሳልፈው ግጥሞችን በመጻፍና አንዳንድ ስዕሎችንም በመቅረጽ ነበር ። በዚያም ጥረት ሥራዎቹ ከጳውሎስ ሴዛኔ ሥራዎች በጥራት መወዳደር ጀመሩ ። 850 ሥራዎችንም በመቅረጽ “ ሂራሰዋን እድኑ ” የሚል የቅጽል ስም ወጥቶለት በእስር ቤት ግቢ ለትርኢት ይዞር ነበር ። የርሱም ሃይማኖት ቡድሃ ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብን ይወድ ነበር ። ከዚያም ሌላ ያለአግባብ ተፈርዶብኛል በማለት መወትወት የዕለት ተግባሩ አድርጎ በመወሰድ በነፃ መለቀቅ ይችል ዘንድ በአገኘው ቀዳዳ ሁሉ ሙግቱን ሊያቋርጥ አልቻለም ። እንዲያውም እንደማንም በፖርላማ የበላይ አካል ምርጫ ላይ ተሳታፊ በመሆን ካሸነፈ በኋላ እንደሱ ለተፈረደባቸው ሁሉ ለመታገል እንደሚፈልግ ከፍተኛ ምኞትና ተስፋ እንደነበረውም ይናገር ነበር ።

በሌላ በኩል ደግሞ ከአራቱ በሕይወት ከተረፋት ሰዎች መካከል የሻይ ስኒ መርዝ ፍጅቱን ጉድ እንዲጋለጥ ያደረገችው ሴት ሄራስዋ ባንክ ውስጥ ገብቶ ፍጅቱን የፈጸመው ሰው እንዳልሆነ ለአንድ ሐኪም መስሎ የተኛች



በት ሆስፒታል ድረስ ላሚወታት ጋዜጠኛ ተናግራለች ። እንዳጋጣሚ ያቺው ሴት ከ3 ዓመታት በኋላ ያንኑ ጋዜጠኛ አግብታለች ።

የሂራስዋን ጉዳይ ያለመሰልቸት በከፍተኛ ትዕግሥትና ስሜት በመከታተል ግብ ያደረሰው አጊ ም ከመ/አቅነት ማዕረግ ወደ ኢንስፔክተርነት ማዕርግ አድጐ በመጋቢት 1949 ወደ አኪጋሚ ጣቢያ ተዛውሮ ሲሰራ ከቆየ በኋላ በሚያዝያ 20/1964 በጡረታ ከሥራ ተገለለ ። አጊ ስለሂራስዋ ወንጀለኝነት ቅንጣት ጥርጣሬ የለውም ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ካጋጠሙት አያሌ ምርመራዎች የሰዓሊው ጉዳይ ከባድና አስቸጋሪ መሆኑንም ይመሰክራል ፣ ከባድ የሆነበትንም ምክንያት ሲያስረዳ በየአቅጣጫው በተመርማሪው ላይ በነበረው ሁኔታና አመለካከት ልዩነት መሆኑን አስረድቶ ፣ በአንድ በኩል አለቆቹ ቸልተኝነትን ማሳደራቸውና ከሥራ ጓደኞቹ ጋር መቃቃር መፈጠሩ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በራሱ እምነት ላይ ርግጠኛ ለመሆን የተቸገረበት ጊዜም እንደነበረ አልደበቀም ።

አጊ ስለሂራስዋ በተጨማሪ ሲመሰክር ቀላል ሰው እንዳልነበረ በአጠቃላይ አረጋግጦ በጣም ብልህና የሁሉንም እንቅስቃሴ በቅርብ የሚከታተል እንደነበርም ተናግሯል ። ስለራሱም ሲያወራ በራሱ የሚተማመንና ሐቀኛ መሆኑን ገልጾ እንዲህ ዓይነት ችሎታ ደግሞ በሳይንሳዊ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ እስካልተደገፈና እስካልተጠናከረ ድረስ በፖሊስ በኩል አድካሚና ዋጋ እንዳልነበረው አጋልጧል ። በአጊ ልዩ የክትትልና የምርመራ ዝንባሌና ጥበብ የፖሊስ መ/ቤት በጡረታ ከተገለለበት በየጊዜው እንዲያማክርና አንዳንድ የሥራ ድጋፍ በመስጠት እንዲረዳ ይጠራ ነበር ። እንዲያውም የሥልጠና ፕሮ

ግራም በማዘጋጀት ለወጣት ፖሊሶች ትምህርት በመስጠትና ጽሑፎችን በማዘጋጀት ከፍተኛ ተሳትፎ ያደርግ ነበር ።

እገ. በፖሊስ ክትትልና ምርመራ ሥራ ዋና መርህ አድርጐ የያዘው በምንም ዓይነት አንድ ተጠርጣሪ ወይም ማንኛውም ሰው የተናገረውን ነገር እንዳለ ዝም ብሎ በመውሰድ ዕምነት መጣል አስፈላጊ ያለመሆኑንና እውነተኛውን ነገር ለማግኘት ከተፈለገ በቆራጥነትና በትዕግስት የግል ጥረት ማድረግ ወሳኝነት ያለው መሆኑን ነው ። እገ. በዚያ ረገድ የሂራስዋን ጉዳይ ሲናገር በመጀመሪያ ሲያየው በፍጹም ገዳይ ይሆናል ብሎ እንዳልተጠራጠረ ተናግሯል ። በመጨረሻም በሌላ ወቅት ገዳይነቱን ለማውጣጣት ወንጀለኛ ላያደርጉት የሚችሉትን መረጃዎች ሲያሰባስብ ያለጥርጥር ወንጀለኛነቱን እንዲያደርስበት የረዳው መሆኑን አረጋግጧል ።

ሌሎች ኢንስፔክተሮች ደግሞ ሂራስዋ ሰዓሊ በመሆኑ ስለመርዝ ያለው ዕውቀት የተወሰነ መስሎአቸው ተታለው እንደነበር ከሰዓሊው አነጋገር እንደደረሱበትና በኬሚካል ላይ የነበረው ዕውቀት ደግሞ ከፍተኛ መሆኑን መገንዘባቸውን አረጋግጠዋል ።

በመጨረሻም ሂራስዋ ላደረገው ፍጅት ቅንጣት የማይጠራጠር መሆኑን እገ. በጠንካራ አቋሙ አረጋግጧል ።



# የኦፔራ አዳራሹ ግድያ

ወቅቱ መጋቢት 12,1963 ከቀትር በኋላ ረፋዱ ላይ ነበር ። በቭየና ከመላው አውሮፓ ወደር የለሽ ከሚባል በትና ከተሽቆጠቆጠው የቭየና ስቴት ኦፔራ አዳራሽ ከ10 ሰዓት በኋላ ታላቁ የመድረክ አዳራሽ ሙሉ ተመልካችን ለማስተናገድ ተከፈተ ። የምሽቱ ትርኢት ዲ ዋልኩር ተብሎ የተሰየመውና በዋግነር የተዘጋጀው የሙዚቃ ድራማ ነበር ። አሥራ አንድ ሰዓት ከአምስት ደቂቃ ላይ የኦፔራው ተካፋይ ኮረዳዎችን ጸጉር የምትሰራው የ22 ዓመት ወጣት ጌርትሩድ ጋሊ በሴቶች መታጠቢያ ክፍል መደበኛ የቆንጃጅት ጸጉር ሥራዋን ለማካሄድ ዘው ብላ ገባች ። ክፍሉ ከቲያትር ቤቱ አዳራሽ ከላይኛው ፎቅ ራቅ ባለ አካባቢ ላይ የሚገኝ ከመሆኑም በላይ በዛው አካባቢም የሙዚቀኞችና የዳንኪራ ረጋጭዎች የመለማመጃና የማሰልጠኛ አዳራሾች ይገኛሉ ። ዲ ዋልኩር ተብሎ የታወቀው ኦፔራ የጦፈ ዳንስ የሚጠይቅ ትርኢት ስላልሆነ የተለመደው የዳንኪረኞች ግርግር በዚያን ዕለት አልነበረም ። በመሆኑም አካባቢው ጭር ብሎ ነበር ።

ያ ፀጥታ የተሞላበት አካባቢ በመድረኩ ከነበረው ግርግር ጋር ሲወዳደር ፈጽሞ የተገላቢጦሽ ነበር ። ወይዘሪት ጋሊም በሚያስደነግጥና ልብ በሚሰልብ ትርኢት ከነበረችበት ክፍል ወደ መታጠቢያው ክፍል ማምራት ጀመረች፣ በዚያ ጉዞዋ አንድ እጅግ ልዩ የሆነ ክስተት በፊቷ ድንቅር አለ ። በመተጣጠቢያው የጓዳ ክፍል ወለል ላይ የአንዲት



ትንሽዋ ዳግማር ፋሪኽ የባሌት ተማሪ እና የቭየና ስቴት ኦፔራ አዳ ራሽ አሰቃቂ ግድያ ተጠቂ ።



እምቡጥ ልጃገረድ እርቃን አካል በደም ተበክሎ ተዘርሯል። ፀጉር ሰሪዋ ያየችውን ሁኔታ ለሥራ ባልደረባዋና ለተላላ ኪው በመንገርዋ የኦፔራው አዳራሽ ሐኪም ተጠርተው በመምጣት የሕክምና ምርመራ ካካሄዱ በኋላ ታዳጊዋ ወ ጣት በደረሰባት የመወጋት አደጋ መሞቷን አረጋገጡ ።

በዚያ መልክ በአውስትሪያ ታሪክ ውስጥ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ አሰቃቂ ግድያ ደረሰ ። የዚያም ሁኔታ በመላው ዓለም በመዛመቱ የአካባቢውንና የዓለምን ስሜት ቀሰቀሰ ።

አደጋ የደረሰባት ታዳጊ ወጣት ማንነት ሲመረመር ዳግማር ፋሪኽ ሆና ተገኘች። ፋሪኽ የባሌት ተማሪ ስትሆን ዕድሜዋም 10 ዓመት ነበር ። የኦፔራው ባልደረባ ሆና ለ2 ዓመታት አገልግላለች ፣ ቀጠን ያለች የደስ ደስ የነበራት ረጅ ም ነጭ ጸጉር በጀርባዋ ትነሰንስ የነበረውችው ፋሪኽ ከእና ቷና 16 ዓመት ዕድሜ ከነበራት ከእህቷ ከሲልቭያ ጋር ትኖ ር ነበር ። እናትና አባቷ ሠራተኛ የነበሩ ሲሆን አባቷ ግን በሥራ ፀባይ የተነሳ የሚኖሩት ራቅ ብለው ነበር ።

ፋሪኽ በዚያች አሰቃቂ የሰዓት በኋላ ጊዜ ከቤትዋ በመ ነሳት የባሌት ዳንስ ወደምትደንስበት አዳራሽ ለመድረስ የፈ ለገችው ልትደርስበት ባልቻለችበት በ11 ሰዓት ላይነበር ።

በቭየና በተለይ ሙዚቃ በኅብረተሰቡ ዘንድ እጅግ ተወዳጅ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛውን ደረጃ የያዘ ስለነ በር ተመልካች ቦታው ሳይያዝበት አዳራሹን ከአፍ እስከ ጢሙ የሞላውና ያጥለቀለቀው ገና የትርኢቱ ሰዓት ሳይደ ርስ ነበር። የዲ ዋልኩር ትርዒት መንፈስ የሚረብሽና ገዳይ እማልዕክትን የሚያሳይ ቢሆንም በአዳራሹ ውስጥ ትርዒ ቱን ለመመልከት ተመቻችቶ የተቀመጠው ሕዝብ ከመድ ረክ በስተጀርባ እውነተኛ ግድያ ተፈጽሞ በድኑም ያልተ ነሳና ገዳዩም በአጣዳፊ ምርመራ ላይ እንደሚገኝ በፍጹም አልተገነዘበም ።

ኦፔራው እየተካሄደና ተመልካቹም በተመስጦ እየ
ተከታተለ ሳለ ከመጋረጃው በስተጀርባ ደግሞ የጦሬ የፖ
ሊስ የምርመራ ትርኢት መካሄድ ጀምሮአል ። በቅድሚያ
ወንጀል በተፈጸመበት ቦታ የደረሰው ዶክተር ፍሬድ
ሪክ ኩሶ ነበር ፣ ኩሶ ቁመቱ ዘለግ ያለ ብራማ ጸጉር ፣
ግርማ ሞገስ ያለው አቋም የነበረውና ዲፕሎማት ይመ
ስላል ። ሆኖም ከፕሮቶኮል ሥራ ይልቅ ወደ ተጨባጭ
የምርመራ ውጤት የሚያተኩር በመሆኑ የቬየና ስቴት
የደኅንነት ኃላፊና በተጨማሪም ታዋቂ መርማሪ ነበር ።

ከመካከለኛ የኅብረተሰብ መደብ ቤተሰብ የተገኘው
ኩሶ በ1917 በቬየና ተወልዶ አንደኛና መለስተኛ
ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ በቬየና ዩኒቨርስቲ በመግባት
የሕግና የመንግስት አስተዳደር ሳይንስ ተማሪ ሆኖ
ነበር ። በዚያም መሰረት የሕግ ዲግሪውን አግኝቷል ።
በኦውስትሪያ ውስጥ የክብር መጠሪያውንም " የፍርድ
ቤት አማካሪ " አድርጉት ነበር ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በሐምሌ 1943
በም/መቶ አልቅና ከሮሜል የአፍሪካ ኃይ ጋር በመሆን
በሰሜን አፍሪካ አገልግሎት አበርክቷል ። በዚያን ጊዜም
ኩሶ በአሜሪካኖች ስር ምርኮኛ በመሆን በተለያዩ ካም
ፖዎች በኮንኮርድያ ፣ ካንሳስና ኢንዲያና ታስሯል። በኮንኮ
ርድያ ካምፕ በነበረበት ወቅት ኩሶ በአጠቃላይ የሕግና
ፍትሕ ስሜት ስላሳደሩበት የፌዴራል ቢሮ ምርመራ
መዛግብትና መጽሐፍቶች በሰፊው ማንበብ ያዘ ። በዚ
ያም ማንዛቢው በአንግሎ ሳክሰን ባሕላዊ የሕግና የፍርድ
አመራር ሁኔታ በጣም ስለተመሰጠ በዚያ ጉዳይ አን
ዷት አጭር ምንባብ ጽፎ አቅርቧል ። በትውስት አግ
ኝቶ ያነባቸው ከነበሩት መጻሕፍት " ያልተረጋጋ የፍ



ርድ አሰጣጥ በአንግሎ አሜሪካን ሕግ " በሚል ርዕስ
ከቀረበው ጽሑፍ " አንድን እሥረኛ በሥራ እንዲጠመድ
ማድረግ በጣም ከባድ ጸጋ ነው ፤ ለፍትህና ለህግ ሟች
ለመሆን ዝግጁ ነበርኩ " የሚለውን ሐረግ ያስታውሳል ።
ያችው ጽሁፍ የኋላ ኋላ በቬየና ዩንቨርስቲ ተቀባይ
ነት በማግኘቷ በአሁን ጊዜ በዩንቨርስቲው ቤተ መጽ
ሐፍት በመካከለኛው አውሮፓ በወንጀል ሥራዎች ምር
መራ ከሚሠሩት ከፕሮፌሰር ዶክተር ሮላንድ ግራስ በርገር
የጠበብት ሥራዎች ጐን ተሰልፋለች ።

ኩሶ ወደቬየና በ1946 እንደተመለሰ የአውራጃው
ጠበቃ ለመሆን ምኞት ነበረው ። የሆነ ሆኖ በቬየና ስቴት
ፍ/ቤት ለአንድ ዓመት ያህል የወንጀልን ጉዳይ በመከታ
ተል ከሰራ በኋላ ሌላ የተለዩ ውሳኔ ላይ ደረሰ ። ያም ውሳኔ
የተያዘን ወንጀለኛ ጉዳይ መደበኛ በሆነ መንገድ ከማ
ዩት ይልቅ ለተሰራው ወንጀል መፍትሔ ማስገኘት በይ
በልጥ የሚያስደስት በመሆኑ በዚሁ መቀጠል ነበር ።
ኩሶ ምኞቱን በማከታተል እንደገለጸው " ገና ባልተደ
ረሰባቸው ወንጀሎች ላይ በመነሳት በምርመራ ጠልቄ
ለማወቅ የምፈልገው ለፖሊስ ግንባር ቀደም ለመሆን
ስል ነው ፡ ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ በመገኘት አጥ
ፊም ይሁን አይሁን ከሚመለከተው ማናቸውንም ሰው
ጋር መሥራት በጣም እጓጓለሁ " ብሏል ።

ኩሶ ሚስት ባገባበት ዓመት ማለትም በ1947 በአው
ስትሪያ የወንጀል ማዕከል በነበረው የቬየና ስቴት ደኅ
ንነት ቢሮ የፖሊስ ኮሚሽነር በመሆን ተመደበ ። ኩሶ
በትኩስና በአፍላ የሥራ ዘመኑ ከፈጸማቸው ተግባራት
መካከል ሲያስታውስ "ከባድ የወንጀል ሥራዎችን ያጣራ
ሁበትና ብዙም ውጤትና ድል ያገኘሁበት ጊዜም ነበር ።
ያለፍላጐቴ በ1955 በቬየና የአንድ ትልቅ የፖሊሶች

ምርመራ ኃላፊ አድርገውኝ ነበር ። ነገር ግን በ1959 በነበረኝ ተሰጥኦ (ዶክተር ኩሶ ለዝቅተኛነት ያልተጋለጠ ነበር ) ወደ ነበርኩት ወደ ደኅንነት ቢሮ በኃላፊነት እንድመለስና እንድሰራ ተደረግሁ ” ይላል ። ኩሶ ቀደም ሲል በተገለጸው ዝንባሌና ችሎታ በመነሳሳት አንድ ከባድ ወንጀል በሚያስተናግድ ቅርንጫፍ የምርመራ ቢሮ በመሆኑ ነገሮችን ሁሉ ሊያፈነዳቸው ችሏል ። ያም ሁሉ ሆኖ ግን በቭየና ስቴት የኦፔራ አዳራሽ በዳግማር ፋሪኽ ላይ የተፈጸመውን የግድያ ወንጀል ያህል አሰቃቂና ተወዳዳሪ የሆነ ወንጀል አልገጠመውም ።

ኩሶ ስለዚያ አሰቃቂ የታዳጊ ወጣት ግድያ ጉዳይ ሲናገር “ በመጀመሪያ ይህ ወንጀል የተፈጸመው የአውስትሪያ በጣም ትላልቅ ኪነታዊ ሥራዎች በሚካሄድበት ማዕከል ውስጥ ነው ። ቀጥሎም ወንጀል የተፈጸመባት ልጃገረድ ከመሆኗም በላይ ገና የ10 ዓመት ታዳጊ ወጣት ናት ፣ ከዚህ ሁሉም በላይ በግድያው ጊዜ በወጣቷ ላይ የተፈጸመው ጭፍጨፋ የሚዘገንን በመሆኑ እንደ እሳት ነው ያቃጠለኝ ። በተጨማሪም የወንጀሉ አፈጻጸም ሁኔታ በመላው የአውስትሪያ ሕዝብ ዘንድ ልዩና ከፍተኛ ሐዘን ፈጥሯል ። ይህ ደግሞ የመጨረሻና የማያዳግም ነው ለማለት አይቻልም ። የቭየና የወንጀል ምርመራ ፖሊስ ደግሞ ይህን ወንጀል ፈልቅቆ ማግኘት ታላቅ ክብርና ዝና ሊያስጠው ይችላል ። ” ብሏል ።

ከዚያ ጥንታዊ መልክ የያዘ ወንጀል ጋር የወቅቱ የፖሊስ መርማሪዎች ፊት ለፊት ተፋጠጡ ፤ ዶክተር ኩሶ የታዳጊ ሕጻኗን በደም የመበከልና በአሰቃቂ ሁኔታ የመወጋት ሁኔታ ሲገልጽ “ ገዳዩ የሰውን ልጅ አእምሮ ያልያዘ ከእንስሳ የተሻለ ኃላፊነት የማይሰማው አረመኔ መሆን አለበት ” ብሏል ።





ዶክ/ ፍሪድሪክ ኩሶ ፤ የአውስትሪያ ታዋቂ መርማሪ የተወሳሰበውን የ10 ዓመትዋን የዳግማር ፋሪኽ ገዳይ ኑዛዜ ያፍታታ ፣ በቭየና በቬልቨደሬ ቤተመንግሥት ደረጃዎች ላይ ቆሞ ።

የልጅቷ በድን አካል በጀርባው ተዘርሮ እግሯ ወደ ላይ ተዘርግቷል ፤ ግራ እጅዋ ወደውጭ ተዘርሯል ፤ በግራ እጅዋ የቢጫ ብረት ማሠሪያ ያላት ሰዓት አድርጋለች ። ሰዓቷ ግን እንደርሷ በድን አልሆነችም ፤ ትሠራ ነበር ። የቀኝ እጅዋ ከግራ እጅዋ ጋር ተቆላልፈዋል ። ከደረቷ በላይ በሚያንጸባርቁ ደማቅ ሰማያዊ ቁልፎች ያሸበረቀ ሸሚዝና ቀይ ቀለም ያለው ውስጥ ልብስ ለብሳ ነበር ። ሁለቱም ወደ ላይ ተጐትተው በደም ተለውሰዋል ። ከወገቧ በታች ለብሳ የነበረቻቸው ነጭ ሙታንታ ፤ ጥቁር የሚገተር የውስጥ ልብስ (ቡፋንቴ) የፈካ ቡናማ መታጠቂያ ፤ አመዳማ የእግር ሹራብ ስለወለቁ እርቃኗን ነበረች። ሌሎች የማላበሻ ልብሶችና ባርኔጣ ከሰውነትዋ በስተጐን በኩል ተጥሎ ነበር ። ቡናማ የአንገት ፊር ያለው ግራጫ የዝናብ ልብስ በማንጠልጠሊያው ላይ ተንጠልጥሏል ። በኮቱ ኪስ ውስጥ የከተማ አውቶቡስ ቴኬትና አንድ ቁልፍ ተገኘ ። ከላስቲክ ከተሠራው የእጅ ቦርሳዋ ውስጥ ለሰላሳ ብስኩት በእጅ ጓንቲዎቿ ተገኙ ።

አነስተኛዋ የመተላለፊያ ቦታ በደም ተጥለቅልቃለች ፤ በአንድ ጐን በተደረደሩት የቤት ማሞቂያዎችም ጥቁር የረጋ ደም ተቋጥሯል ። በአቅራቢያው በተገኘው አግዳሚ ወንበር ባለው ግድግዳ አምስት የደም ምልክቶች ይታዩበታል ፤ በውስጥ መሸንጉሪያው ከመብራት ማብሪያው ቀጥሎ ባለው ግድግዳ ላይ የደም ጥራጊ ሲገኝ ከሬሳው በታች ደግሞ የደም ግግር ይታያል ።

በግራ በኩል ባለው ታዳጊ ወጣት ደረት ላይ አሥራ ሰባት ጊዜ ከልቧ አልፎ ተወግቷል ። ከነዚያ ውጐች መካከል 13ቱ ልብዋንና የግራ ሳንባዋን ነክተዋል ። የውጐቹ አቀማመጥ በጣም የተቀራረቡ ነበሩ ። ገዳዩ በሚወጋበት ጊዜ እስከታች ዘልቆ ካላስገባ የወጋበትን መሣሪያ እንደማያወጣው ለማወቅ የሚያስችሉ ብዙ ምልክቶች ሲኖሩ ከነ



ዚያም መካከል ከአሥራሰባቱ ውጐች አሥሩ የልጅቷን ጀርባ በስተው ልብሷን ቀደው መውጣታቸው በቂ ማረጋገጫ ሆነዋል ። ሰባቱ ደግሞ የባሰውኑ የልጅቷን ሰውነት አልፈው ወለሉን በሳስተውታል ። ከሬሳ ምርመራው ውጤት ለማረጋገጥ እንደተቻለው 17ቱንም አሰቃቂ የመወጋት መጥፎ ሰጣ ስትቀበል በሕይወትዋ ነበረች ። በግራ ሰውነትዋም በኩል አምስት ጊዜ በቢላዋ ተቆራርጣለች ። ስለቱ የራስ ቅሏን ፤ ፊትዋንና አንገቷን ነክቷል ። የአምስቱ በቢላዋ የመቆረጥ ሁኔታ ምናልባት ልጅቷ ከሞተች በኋላ የተፈጸመ ይመስላል ።

በብልቷ አካባቢም አሥራ አንድ ቦታ ተወግታለች ፤ ሁለቱም ሆድዋ ላይ ሲሆን ፤ አንዱ ግን የሽንት ቧንቧዋን ከፍቶታል ። ከዚያ ሁሉና በተለይም ከማንባሯና ከማህጸኗ አካባቢ ከተገኘው የውጋ ምልክት ለመገመት እንደተቻለው መሣሪያው ረጅምና በጣም ስለት ያለው የአደን ቢላዋ እንደነበር አላጠራጠረም ።

ፋሪኸ ላይ የግዳጅ ፍትወተ ሥጋ ያልተፈጸመና በዚያም በኩል ያልተጐሳቆለች መሆኑ ታውቋል ። በሌላ በኩል ደግሞ በቭየና ዩኒቨርስቲ የሕግ ሕክምና ተቋም በተካሄደው የሬሳ ምርመራ ደሙ በብዛት የፈሰሰው ከደረትዋ አካባቢ ላይ በብዛት በቢላዋ በመሽቅሸቋ መሆኑን አመልክቷዋል ። አደገኛው ቁስልና ለሕልፈት ሞት ያበቃት ግን የመታነቋና በከባድ ኃይል ፊትዋ ላይና ራስዋ ላይ የደረሰው ድብደባ ነበር ።

የዚያ ሁሉ ሁኔታ የሚያረጋግጠው ነገር ቢኖር ገዳዩ የአእምሮ መታወክ ሊኖረው የሚችል መሆኑን ነበር ። ለመሆኑ ገዳዩን እንዴት ማግኘት ይቻላል ? በወንጀለኞች አደና ሥራ ይህ ጥያቄ በጣም አስልቺና ከባድ ነበር ።

ኩሶ የገዳዩን አንገብጋቢነትና አሳሳቢነት ከመጠን በላይ ተረድቶታል ፤ ያው ያልታወቀ ወንጀለኛ ከሕግ

ተፈጥሮ ውጭ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ የደም ማፍሰስ ተግባሩን ካረካ በኋላ እንደጤነኛ ሰው ከሕዝብ ጋር ተቀላቅሎና ሰላማዊ ሰው መስሎ መሄድም እንደሚችል ተገንዝቧል ። የዚህን መሰል ወንጀል ፈጻሚዎች በሌላ በኩል ደግሞ በግድያው ተግባር ከረኩ በኋላ ጉልህ የቅሬታ ስሜቶች ወይንም ጉራ የመንፋት ስሜት እንደሚታይባቸው ታውቋል ። የቅጥር ገዳይ ከሆነ ግን አብዛኛውን ጊዜ ውስጥ ለውስጥ ሊደረስበትና ሊጋለጥ ይችላል ። በእንጻሩ ደግሞ ከሕግ ተፈጥሮ ውጭ ወንጀል ፈጻሚዎች ወይም ንክ ወንጀለኞች ባብዛኛው ጊዜ በቀላሉ ሊታወቅ የሚቻል እጥጋቢ ምክንያት የላቸውም ።

ኩሶ ከወንጀል ፈጻሚው አድራጐት በመነሳት የተመዘገቡትን ጉዳዮች በማቀናጀት የምርመራውን ርምጃ ጀመረ ። ሌላው ቀርቶ በፍጥነት የኩሶ የደህንነት ቢሮና የሕግ ሕክምና ተቋም ጠበብት ከመድረኩ በስተጀርባ የምርመራ ማቢያቸውን አቋቋሙ ። ነፍስ ገዳዩ ምንም ዓይነት አሻራ በቦታው አልተወም ። ነገር ግን አንዳንድ አስደናቂ የሆኑ ረቂቅ ምልክቶችንና ማስረጃዎችን በማያያዝ ሰበሰቡ ። እኒየም ወደ በስተኋላ ጠቅመዋቸዋል ።

በወለሉ ላይ የጉማ ዱካ የሚመስል ነገር ተገኘ ። ያው ተመሳሳይ ምልክትም በመታጠቢያው ክፍልም ተዩ ፤ የደሙ ምልክት በሁለቱ ታጣፊ በር ላይና በዋናው የኦፔራ አዳራሹ ወለል ላይ እንዲሁም ወደ ካርን ጐዳና ወደሚያወጣው በመስተዋት የተሰራ በር ላይ ተገኘ ። ተጨማሪ መረጃ ሊገኝ ይችል ዘንድም ኩሶ በአንድ የደህንነት ቡድን የኦፔራ አዳራሹን በሙሉ በውሾች አስዳሰሰ ፤ አሰሳው አንድ ቀን ሙሉ ቢፈጅም የተገኘ ውጤት ግን አልነበረም ። የኦፔራ አዳራሹ መውጫዎች በጥበቃ ስር ዋሉ ። በኦፔራው አዳራሽ ምርመራው በመጧጧፍ ላይ እንዳለ በቫየና ለሚገኙት የፖሊስ ማቢያዎችና ለሁ



ሉም በአውስትሪያ የነፍስ ግድያ መቆጣጠሪያ ቢሮዎች መልዕክቶችና ቴሌግራሞች ይጉርፉ ጀመር ። ግድያው በተፈጸመበት ሌሊት የሚች እቻ የምትሆን ሱዛን ፊቸትን ባው የምትባለው ሌላ የ11 ዓመት ዕድሜ ያላት የባሌት ተማሪ ተጠይቃ ነበር ። እሷም ከኦፔራው አዳራሽ የላይኛው ፎቅ በአስር ሰዓት ከሩብ እንደወጣች በመስኮቱ በኩል በተሰራው በር አንድ ሰው ማየቷንና ሰላምታ እንደሰጠችውም አስታወሰች ። ሰውየው ወደርሷ እያዘገመ በመምጣት ሰላምታዋን መልሶላታል ፡ ከእርሷም ጋር ደረጃዎቹን አብሮ ወርዷል ። አቋርጣውም ስታልፍ በደንብ ተመልክታው ነበር ፡ በመሆኑም ሰውየው የተደናገጠ ይመስል እንደ ነበር አረጋግጣለች ። ከዚያም ያንኑ ሰው እንደገና ወደ ላይ ተመልሶ ሲወጣ አይታዋለች ፡ ስለ ሰውየው ስትገልጽም ቁመቱ አንድ ከሰባ ሁለት ሜትር ፡ በጣም ጥቁርና ወደኋላ የተበጠረ የሚያንጸባርቅ ጸጉር ያለው ፡ ፊቱ የዕንቁላል ቅርጽ ፡ አንዳንድ ምልክቶች በፊቱ ላይ ያሉበት መሆኑን ተናግራለች ። ግራጫ ልብስ መልበሱንና አንድ ጥቁር የእጅ ቦርሳ በእጁ ማንጠልጠሉንም አልረሳችም ። ያው ሰው የቢሮ ሠራተኛም መስሏት ነበር ።

በተደጋጋሚም በርካታ ሰዎች ግድያው በተፈጸመበት ሰዓት አካባቢ በካርንት ጐዳና መውጫ በኩል አንድ ሰው ሲወጣ ማዬታቸውን ለፖሊሶች አሳውቀዋል ። ስለ ሰውየውም ከተሰጡት መግለጫዎች ሁሉ ደላላው ሉድዊግ ኮቫክስ ያቀረበው ሪፖርት የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል ። ርሱም እንደተናገረው በዚያኑ ዕለት አሥራ አንድ ሰዓት ከሩብ ገደማ (በትክክል ሰዓቱን መናገር አልቻለም) በኦፔራው አዳራሽ በስተጀርባ በማሽከርከር ላይ እንዳለ አንድ ወጣት ሰው እንደእብድ መንገዱን ለማቋረጥ ይበር እንደነበርና ሰውዬውም አጭር ፡ ቀጭን ፡ ሙሉ ልብስ የለበሰና ካፖርት ያልደረበ ፡ ያጉረጠረጠ ዓይኖች ያሉት ፡ ሆኖ

የትራፊኩን ትርምስ ሁኔታ ለመቆጣጠር ካለመቻሉ
የተነሳ ከአንዷት ታክሲ ጋር ሊላተም ሲል ለጥቂት እን
ደተረፈ አረጋግጧል ።

ኩሶና ረዳት መርማሪዎቹም የወጣቷን የመጨረሻ
እንቅስቃሴ ለማቀናጀት ጥረት አደረጉ ።

በሚች ኮት ኪስ ውስጥ ያተገኘው የ6 ቁጥር አውቶቡስ
ቲኬት በአሥር ሰዓት ከሩብ ተሳፍራ መሄዷንና በግ
ምት አሥር ሰዓት ከ31 ደቂቃ በካርን ጉዳና መግቢያ ልትደ
ርስ እንደምትችል ተገምቷል ። የኩሶ የደህንነት ቢሮ እኩ
ያዋ የሆነችዋም ልጅ የሚችን እንቅስቃሴ እንድታካሂድ
በማድረግ ድርጊቱንም ቀርጾውታል ፤ በዚያም ካደረጉት
ጥልቅ ምርመራ ፋሪሽ ገዳይዋን በ10 ሰዓት ከ38 ደቂቃ
አካባቢ ማግኘት አለባት ከሚል ግምት ላይ ደረሱ። የኮትዋ
በማንጠልጠልያው ላይ መገኘት ፥ የልብሶችዋ ዚፕ ያለ
መጉዳቱና ያለመቀደዱ ፥ የእጅ ቦርሳዋ በአካባቢው ከነ
በረው አግዳሚ ወንበር ላይ መገኘት ልብሶችዋን ስታወ
ላልቅ በተጽዕኖ እንዳልነበረና በፍላጐቷ እንዳወለቀች
ለመገመት ቻሉ ። በዚያም መሰረት ሚች ከተጨፈ
ጨፈችበት ክፍል ውስጥ ምናልባት ገዳይዋን ተከትላ
ገብታ ይሆናል የሚልም ግምት ተነሳ ። በመጨረሻም
ገዳይ ግድያ የተፈጸመበትን አካባቢ ጠንቅቆ ሊያ
ውቅ እንደሚችል ኩሶ ገምቷል ። በዚያም መሠረት
ገዳይ የኦፔራው ኩባንያ ባልደረባ ወይንም የውጭ
ሰው ሆኖ ስለኦፔራው የውስጥ ድርጅትና ሁኔታ ጠን
ቅቆ ሊያውቅ የሚችል መሆን አለበት ተባለ ። በሌ
ላም በኩል ከጥያቄ ብዛት ሊደረስበት እንደተቻለው
የመግቢያና የመውጫያው በሮች በቂ ቁጥጥር ስለ
ማይደረግባቸው ሰዎች በቀጥታ ወደውስጥ ለመግባት



የማያዳግታቸው መሆኑ ታወቀ ። እንደ አጋጣሚም
በወቅቱ በኦፔራው አዳራሽ የቡድን ጉብኝት ተደርጐ ነበር።
ቡድኑ በአንደኛው መግቢያ በኩል ጉብኝቱን በመጀመር
ጉዞውን ወደ ላይኛው ፎቅ በማድረግ ሁለተኛ ደረጃ ላይ
ከደረሰ በኋላ ግድያው የተፈጸመበትን ቦታ በማለፍ በአ
ካባቢው ያሉትን ክፍሎች ጉብኝቶ በመጨረሻ በካርን
ጉዳና መውጫ በኩል በማምራት ጉብኝቱን ሲያጠቃ
ልል ምንም ችግር ያላገጠመው መሆኑ ተገለጸ ። ስለዚህ
እንደዚያ የመሳሳለ የውጭ ሰዎችን የሚጋብዝ ሁኔታ
ስለነበር ጥርጣሬው በኦፔራው ሠራተኞች ላይ ብቻ
መሆን እንደሌለበት ማስጠንቀቂያ ተገኘ ። የኦፔራው
አዳራሽ ሠራተኞች በበኩላቸው እንዳመለከቱት ቀደም
ተብሎ ለፖሊስ ሪፖርት ያላደረጉት ሁኔታ ቢኖር ወንዶች
ከጓደኞቻቸው እየተነጠሉ ሴቶች ተዋንያንን ሰርቆ ለማ
የት በመታጠቢያው ፥ በመጸዳጃውና በየመልበሻ ክፍሎ
ቻቸው ውስጥ ብቅ ጥልቅ ይሉ የነበረውን ነው ።

የስቴት ኦፔራው አዳራሽ ሠራተኛ ብዛት 1,900 ሲሆን
ኩሶና የሥራ ባልደረቦቹ ሠራተኞቹን አንድ በአንድ በማ
ግኘት ምርመራቸውን አካሂደዋል ። ሠራተኞቹን ለመመ
ርመር በማደራጀት ረገድ የተጠቀሙበትም ስልት በቅድ
ሚያ ዘፋኞቹን ፥ መዘምራኑን ፥ ባሌት ተጫዋቾችን ፥
ዳንኪራ ረጋጮችን ፥ ሙዚቀኞችን ቀጥሎ የቴክኒክ ዕር
ዳታ ሰጪ ሠራተኞችን የመድረክ ዝግጅት የሚያከናው
ኑትን ፥ አልባሾችን፥ የቁንጅና ሳሎን ሠራተኞችን ፥ የፊት
ገጽ ውበት አሸሞንሚኝዎችን፥ ጠበብትን ፥ ተራ ሠራተኞ
ችንና ቲኬት ቆራጮችን በመጨረሻም የአስተዳደር ክፍል
ሠራተኞችን የሚያጠቃልል ነበር ። የኦፔራው አዳራሽ ዕ
ድሳት ሲደረግለትም ተሳታፊ የነበሩት ተመርምረዋል ።

ግድያው በተካሄደበት ወቅት በሆነ ጉዳይ በአካባቢው ተሳታፊ የነበሩ የሌላ ድርጅት ሠራተኞችም ከምርመራው ውስጥ እንዲታከሉ ተደርጐ ተጠይቀዋል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ምርመራው በጾታ የተለዩ ልክፍት ወይም በሽታ ያለባቸውን ሰዎች ማለትም የሴት አፋኞችን ፣ ሌሎችን በሰው ስቃይ የሚደሰቱ የአእምሮ በሽተኞችን ፣ በቁመና ዘራፊዎችን ፣ አዚመኞችን ከአካባቢው በማፈላለግ ልዩ ምርመራም አድርገዋል ። ሌላ የማጣራት ዘመቻ የተካሄደው ደግሞ ከዕብዶች ሆስፒታልና የእንጐል መታወክ ያለባቸውን ሰዎች ከሚያስተናግዱ ተቋማት በቅርብ የለቀቁአቸው ወይም አጥር ጥሰው ያመለጡአቸው እንዳሉ በማጠያየቅና በመፈለግም ነበር ። ከዚያም በዓለም አቀፍ የፖሊስ ድርጅት ( ኢንተርፖል ) በኩል በውጭ ሀገርም ክትትል እንዲደረግ የተገኘው መረጃ ተላልፎአል ። በደረቁ ልብስ የሚያጥቡ ድርጅቶችም (ላውንደሪዎች) በደም የተበከለ ልብስ በቅርቡ አጥበው እንደ ሆነ ተጠየቁ ፣ ብረት ቀጥቋጮችም በሕጻኗ ሰውነት የተሰገሰገውን ቢላዋ ቅርጽና ቁመት ከቁስሉ ጥልቀትና ስፋት አኳያ እንዲገምቱ ተጠየቁ ። ከሕዝቡም የሚቀርቡት ጥቆማዎች እንዲመረምሩ ተደረገ ። ሁሉም ሲሰባሰብ ኩሶና ተከታዮቹ 14000 ተጠያቂዎችን በዚያ ጉዳይ ላይ ብቻ በቁጥጥራቸው ስር አድርገዋ ። ( ያንመሰሉ ከባድ የምርመራ ሥራ በሚከናወነበት ወቅት ሩዶልፍ ሮትማየር የሚባል አንድ የኢንስፔክተሮች ኃላፊ ዐረፈ። በአሟሟቱ ረገድ እንደሚባለው ከሆነ በጉዳዩ አሳሳቢነት በተፈጠረው የሥራ ውጥረት የደም ብዛቱ ስለተነሳበት ነው የሚል ግምት ነበር ፣ በርግጥ ሕመሙ ሲነሳበት አንዳንድ ምርመራዎችን እንዲያቋርጥ ሲጠየቅ አሻፈረኝ ብሏል። ያ ሁሉ ሆኖ ግን የሟች ወጣት ጉዳይ ሕልም ሆኖ ቀረ ።



የኩሶ የደህንነት ቢሮ የሥነ ልቦናና የነፍስ ግድያ ጉዳይች ጠበብት ከገዳዩ ድርጊት በመነሳት የገዳዩን ጸባይ ሊያውቁበት የሚችሉበትን ዘዴ እንዲያብራሩላቸው ምክር ከመጠየቅ አልተቆጠቡም ።

የቭየና የአንድ የአእምሮ በሽታ ተቋም ኃላፊ ከሆኑት ከፕሮፌሰር ዶክተር ሄርበርት ሬስነርና የአእምሮ በሽታ ክሊኒክ ዩኒቨርሲቲ ሊቀመንበር ከፕሮፌሰር ዶክተር ሃንስ ሆፍ ጋር በመገናኘት በሥነ ልቦና አመለካከት የገዳዩን የግል ጠባይና ሁኔታ በዝርዝር ለማግኘት ተሞክሯል ። በተጨማሪ ከሁለቱም ተቋማት በዚያ ጥርጣሬ ሥር ሊወድቁ ይችላሉ የሚባሉ በሽተኞችን ዝርዝር ሰበሰቡ ።

ኩሶ ከቭየናው ዩኒቨርስቲ የወንጀል ምርመራ ተቋም ሊቀመንበር ከሆኑት ከፕሮፌሰር ዶክተር ግራስበርግ ጋር በርከት ያሉ የሐሳብ ልውውጦችን አድርጓል ። ፕሮፌሰር ግራስበርግ አስተያዩታቸውን ሲገልጹ “ የአእምሮ ሁከት ያለበትን ነፍሰ ገዳይ ለማደን የሚደረገው ጥረት በወንጀል ምርመራ ተግባር በጣም ከባድና ተስፋ አስቆራጭ መሆኑን አረጋግጣለሁ ” ብለው ነበር ። ያን ጠንካራ አቋማቸውን በሚያረጋግጡበት ወቅት በጀርመን ሶስት ቦታዎች የተከሰቱ ታዋቂ ድርጊቶችን ጠቅሰዋል ። ግራስበርግ እንደ ሚዘረዝሩት “እነኝህ ጉደኞች ከመታሰራቸው በፊት በርከት ያሉ ግድያዎችን የመፈጸም ባህሪይ ነበራቸው ” ብለዋል ። ሊያዙ ስለሚችሉበት ሁኔታም ሲናገሩ የዚህ መሰሉ ልክፍተኞች ሊያዙ የሚችሉት በድንገትና በአጋጣሚ ብቻ መሆኑን አረጋግጠዋል ። የእነኩሶ የደህንነት ቢሮ በዚያ ሐሳብ ትንሽ ተስፋ መቁረጡ አልቀረም ። ሆኖም ወንጀለኛው ሌላ ተመሳሳይ ጉድ የሚፈጽም መሆንና አለመሆኑን በልዩ ትኩረት ይጠባበቁ ጀመር ። በሌላ በኩል ደግሞ ገዳዩ የሄደበት መንገድ ጫፍ ቢገኝም ቀጥሎ የነበረው ርምጃ አሸዋ

ውስጥ የገባ ዱካ ይመስል ጠፋ ። እስከመጨረሻ የተገኙትም መረጃዎች ቆሬጥ ውሳኔ የሚያስወስዱ ሆነው አልተገኙም ። ምንም እንኳን መርማሪዎቹ በምርመራቸው ላይ ተስፋ ባይቆርጡም ግራስበርግ ባቀረቡት አስተያየት ዕውነተኛነት አልተጠራጠሩም ። በዚያም ሁኔታ የስቴት ኦፔራዋ ልጃገረድ ገዳይ እንደገና ሌላ ወንጀል ካልፈጸመ በስተቀር የሚደረስበት አይመስልም ነበር ። ያም ለኩሶና ለጓደኞቹ ጥሩ ዕድል አልነበረም ፣ ያም ሆነ ይህ ብዙ ሳይቆዩ ሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጠረ ።

ሰኔ 17,1963 በግምት ከምሽቱ 12 ሰዓት ላይ ዋልትራውት ብሩነር የምትባል የ26 ዓመት ተማሪ ከጓደኛዋ ሲሲሎት ፍሬመት ጋር በቭየና ግራበን በሚገኘው አንድ ሲኒማ ቤት ይሄዳሉ ። ሁለቱ ወደጨለመው የሲኒማ ቤት ሲገቡ ወይዘሪት ብሩነር አንድ ሰው በአጠገቧ ሲያልፍ መቀመጫዋ ላይ አንድ ከባድ ምት ተሰማት ። በጨለማው የሲኒማ ተመልካቾችን ስታስተናግድ የነበረችውም ሰውየው ልጅቷን የገፋት በድንገት ሳያስብ መስሏት ነበር ። ኋላ ግን ሥራዬ ብሎ የፈጸመው መሆኑን በመረዳቷ ለመያዝ ብታሳድደውም አመለጣት፤ ልጅቷም ከነጓደኛዋ ቦታ ከያዙ በኋላ ልብሷ በሙሉ በደም መበከሉን አስተዋለችው ። በዚያም የድንገተኛ እርዳ አንቡላንስ ተጠርቶ ሲታይ 1.5 ሳንቲሜትር ጥልቀት ያለው ቁስል በልጅቷ ታፋ ላይ ተገኘ ። ተጐጂዋ ድርጊት ፈጻሚው ቁመቱ 1.75 ሜትር ሊሆን የሚችል መሆኑን ተናግራለች ። የሲኒማ ቤቱ አስተናጋጅ ደግሞ ሰውዬው 1.65 ሜትር ቁመት እንዳለው ፣ ደልዳላና ጥቁር የሚያንጸባርቅ ጸጉር ያለው መሆኑን ገልጻለች ፣ የለበሰውን ልብስ በሚመለከትም ስትገልጽ ጥቁር ጃኬትና ጥቁር ሱሪ እንደነበር አስታውሳለች ። ወቅቱ በአውስትሪያ የበጋ ጊዜ



ስለነበረ ካለባበሱ የቭየና ከተማ ወረበሎች ዓይነት እንደሆነ ገልጻለች ።

በነሐሴ 30-1963 ከሰዓት በኋላ በ9 ሰዓት ከ40 ደቂቃ ይላ ቨርጂንያ ሽይፎ በመባል የምትታወቅ የ20 ዓመት ዕድሜ ያላት በቭየና ለዕረፍት የመጣች የአሜሪካ ተማሪ የቅዱስ አውጉስታይንን ቤተክርስትያን ለመጐብኘት ወደ አውጉስትትነር መንገድ አመራች ፣ በሳሊስበርግ ወደ ቭየና መጥታ የነበረችው ከአንድ ቀን በፊት ሲሆን የምትኖረውም ከአንድ በኃላፊነት ከሚያስተናግዱት የወጣቶች መዝናኛ ሆቴል ውስጥ ነበር ። ከአንድ መጸለያ በስተጀርባ ቁጭ ብላ ሳለ አንድ ሰው ከቤተመቅደሱ አካባቢ ወደ እርሷዋ ሲመጣ ታያለች ፣ ወዲያው ከርሷ ጋር ደርሶ ጡትዋን በመጨበጥ ቀኝ ዓይኗ ላይ በአንድ ነገር ሲወጋት መነጽርዋ መሬት ላይ ወደቀ ፤ ከመሬት መነጽሯን አንስቶ ከወረወረባት በኋላም ወደመውጫው በረረ ።የተደናገጠችውም ወጣት ወደ ቤተክርስትያኑ ውስጥ ሸሸች ። ከዚያም እንደገና ተመልሶ ከመጣ በኋላ እፈፍ አድርጐ ይዞ አንድ ቃል ሳያናገራት በተደጋጋሚ በቢላዋ ወግቷት ተሰወረ ።

ወጣቷም በአሰማችው ጩኸት የቁረስቶች እስጐብኚው ያቆብ ቨላንድት እና እንዲት ሴት ለእርዳታ ሮጠው ደረሱ ። ሴትየዋ የቆሰለችውን ልጅ ተመልክተው ፖሊስ ፍለጋ ወደ ውጭ ሲሮጡ አጥቂው አሁንም አመለጠ ። ወይዘሪቷ ወደ ቁጥር 1 የድንገተኛ ሕክምና ጣቢያ ተወሰደች ። ኩሶም ሁኔታውን በአስቸኳይ እንዲያውቀው ተደረገ ። በኩሶም የደህንነት ቢሮ ጥያቄ በቭየና ዩኒቨርሲቲ የወንጀል ሕክምና ተቋም ሊቀመንበር የሆኑት ፕሮፌሰር ዶክተር ሊዮናርዶ ብሪያትኔከር ባስቸኳይ ወደ ድንገተኛ ክፍሉ መጥተው የተወጋችውን ወጣት እንዲያዩዋት ተደ

ረገ ። ሐኪሙ ከመድረሳቸው በፊት ተገቢው የፍጥነት
ርምጃ ሁሉ ተወስዷል ። በምርመራውም የደረሰው አደጋ
በጣም ከባድ መሆኑ ተደረሰበት ። ከቀኝ አይኗ ላይ ከፉኛ
ተመታ ነበር ፤ የቀኝ ጆሮዋ በረኸሙ ተቆርጧል ። በቀኝ
የማጅራትዋ አጥንት ላይ ተወግታለች ፤ በግራ ደረቷ
ላይም እንዲሁ ተወግታለች ፤ ሁለት ጊዜ ጀርባዋ ላይ
የተወጋች ሲሆን አንደኛው ውግ ለትንሽ ልቧን ስቶታል ።

አሁንም ይህን አደጋ የፈጸመውን ለመያዝ ሩጫ
ተጀመረ ፤ ወጣቷ አጥቂዋን እንደ ገለጸችው ዕድሜው ከ28
እስከ 30 ፤ ቁመቱ 1.75 ሜትር በወታደር ቁርጥ ጸጉሩን
የተስተካከለና ወደኋላ የተበጠረ ፤ የፊቱም ቆዳ በጸሐይ
የበሰለ የሚመስል መሆኑን ተናገረች ። ይህ ሁሉ ሲሆን
በፖሊስ በኩል የሚደረገው ምርመራ አላቋረጠም ። ሆኖም
አሁንም ሌላ ተመሳሳይ አደጋ በአንዲት ሴት ላይ ተፈጸመ ።

ሐምሌ 2 ፤ 1963 (ጥቃቶች እየተቀራረቡ መምጣት
ጀመሩ /ወይዘሮ ማርያ ብራነር የምትባል የ42 ዓመት
ዕድሜ ያላት አሻሻጭ በፕራተር ጐዳና የትምባሆ ማስታወ
ቂያ ሳጥን ከዘረጋች በኋላ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ ወደ
መኖሪያ ቤቷ በጊዜ ለመግባት እያዘገመች ሳለ በብቸና
መናፈሻ በጣም ደስ በሚል አረንጓዴ ክልል መንፈ
ሷን ለማረጋጋትና ለማደስ አረፍ አለች ። ከመናፈ
ሻው የተቀመጠችው ቢበዛ ለ45 ደቂቃዎች ነበር ።
ሳታስበው በአንገቷ በኩል አንድ ምት ይሰማታል ።
በጨለማ ውስጥ አንድ ነገር የመታት መሰላት ፤ ከዚያ
በኋላ ትንሽ ቆይታ ወደመናፈሻው መውጫ ትራመድ
ጀመር ። ተቀምጣ ከነበረችበት አግዳሚ ወንበር አጠገብ
የተቀመጡት ሴት በእርሷ በኩል ስታልፍ አስቁመው እየደ
ማች መሆንዋን ነገሩአት ። ሴትየዋ 73 ዓመት ዕድሜ



የነበራቸው ወይዘሮ ሮዝ ቱርኮፍ የተባሉት ሲሆኑ ሰውየ
ው ከቦታው ብዙ ሳይርቅ እንዳዩትና ወደ ዊህቡርካስ እን
ዳመ... ጠቁመዋል ። ወ/ሮ ብራነርም መወጋቷን ያወ
ቀችው ሴትየዋ ከነገሯት በኋላ ነበር ። ከዚያም ወደ ከተ
ማው አጠቃላይ ሆስፒታል ተወሰደች ። የቁስሉ ጥልቀት
18 ሴንት ሜትር ለመሆኑና ከአንገቷ ቀኝ በኩል አልፎ
ሳንባዋን መንካቱን ዶክተሮች አረጋገጡ ። ከመናፈሻው
ሲወጣ የታየው ሰውም ምልክቶች ሲተነተኑ የ25 ዓመት አካ
ባቢ ዕድሜ የነበረው በግምት 1.72 ሜትር ቁመት ፣ ቀጭን ፤
ወደኋላ የተበጠረ ፀጉር የነበረው ፤ የለበሰው ደማቅ ሙሉ
ልብስ ፣ አረንጓዴ ሸሚዝ ከደብዛዛ ከረባት ጋር ነበር ። ኩሶ
አደጋው መድረሱን እንደሰማ ተከታታይዎችን ወደ ቦታው
በመኪናው በመውሰድ አካባቢውን አስፈተሸ ። ሆኖም
አሁንም ስውር የሆነው የቢላዋው ገዳይ ደብዛው ጠፋ ።

በነዚህ ሁኔታዎች ከተማው በአስፈሪና አስደንጋጭ
ወሬ ተፈታ ። ከዚያ ቀጥሎ ወጊው ሌላውን ሰው
የሚቆራርጠው ማንንና የት ነው ? የሚለው ስ
ጋት አነጋጋሪ ሆነ ። በተለይ ሴቶች በአስጨናቂ ስጋት
ተዋጡ ። በመንገድ የሚራመዱት ተንቀጥቅጠው ሆ
ነ ፣ ፀጉረ ልውጥ ሰው ከጐናቸው ሲያልፍ አትኩረው
መመልከት ሁሉ ጀመሩ ። የደህንነቱ ኃላፊ ኩሶ በበ
ኩሉ በመናፈሻዎች ያለው ጥበቃ በዓይነቁራኛ ጭም
ር እንዲጠናከር አዘዘ ። በጾታቸው የተለዩ ሁኔታ በሚ
ያሳዩት ላይም የጀመረውን ምርመራ በፍጥነት ማጠ
ናከር ያዘ ። አሁንም በነፃ በከተማው ገዳዩ ይዋ
ልል ጀመር ። ሆኖም ልክ ኩሶ እንደጠበቀው ገዳዩ
በራሱ ግድያ ይጠላለፋል ። የገዳዩ የድብብቆሽ ጉድ

ሊጋለጥ የቻለው በእንዴት በጣም ተጠራጣሪ አሮጊት ሴትዮ ነበር ።

ሐምሌ 6 ፡ 1963 በግምት አሥር ሰዓት ከ50 ደቂቃ ላይ በጡረታ የተገለሉ የ64 ዓመት ዕድሜ የነበራቸው ወይዘሮ ኤማላኽ እቤታቸው አጠገብ እንደደረሱ ወደቤታቸው የሚያስኬደውን መተላለፊያ ይዘው በራቸውን ለመክፈት ቦርሳቸውን አውጥተው ቁልፍ በመፈለግ ላይ እንዳሉ ሳያስቡት አንድ እጅ ከኋላቸው ደርሶ ከጨበጣቸው በኋላ አፋቸውን አፈናቸው ። ወዲያው አንገታቸው ላይ አንድ ስሜት ተሰማቸው ፡ ሆኖም አፋቸውን ለማላቀቅ ዞረው ከሰውየው ጋር ግብግብ ገጠሙ ። ሰውየውም የምግብ ሹካ ወድሮባቸው ያዩታል ፡ እርሱም “ ገንዘብ ! ” ብሎ የተገላቢጦሽ ጮኸ ፤ ወይዘሮዋ ከእርጅና ዕድሜያቸው በማይጠበቅ ሁኔታ ተናንቀው እሪታቸውን አቀለጡት ፤ ሰውየውም በሴትየዋ መፈራገጥና ጨኸት ተደናበረ ፤ የሚይዝና የሚጨበጠውንም አጣ ። ወዲያውም እየተደናበረ ሸሸ ፤ ወይዘሮዋ ግን አሁንም በሚያስገርም ሁኔታ እያሯሯጡ ይከተሉት ጀመር ፤ ከዚያም አጠገባቸው ካለው ቁጥር 5 ክፍል ውስጥ ሲገባ አዩት ። እሪታውን ሰምተው ለደረሱት ሰዎች ስለነገሩም እንደኛው ሮጦ በመንገድ ላይ ላለ የትራፊክ ፖሊስ ይናገራል ። የትራፊክ ፖሊሱም ወደ ፎቁ ውስጥ በገባ በሁለት ደቂቃዎች ውስጥ በሦስተኛው ፎቅ ላይ አንድ በድንጋጤና በላብ የሰመጠ ሰው ያገጥመዋል ፤ ላቀረበለት ጥያቄም አጠራጣሪ መልስ ስለሰጠው ተይዞ ወደ ማረፊያ ቤት ከሄደ በኋላ ቃሉን እንዲሰጥ ተደረገ ።

ሰውየው ዮሴፍ ቬንቡር ይባላል ፡ ተወላጅነቱም አውስትሪያ ሆኖ የተወለደው በሀውግስድሮፍ መስከረም 16 ፡ 1930 ነበር ። በዚያ መሰረት ዕድሜው 33 ዓመት





ዮሴፍ ቬንቡር በመሃከል ፡ የ64 ዕድሜ ያላትን የቪየና ሴት በሹካ በመውጋቱና ሌሎች ሴቶችን በቢላዋ በማጥቃት ወንጀል በመጠርጠሩ ታስሮ ወደ ጣቢያ ሲወሰድ ። በመርማሪ ኩሶ በተደረገው ረጅምና የተደጋገመ ጥያቄዎች ቬንቡርም ዳግማር ፋሪኽን ማረዱን ተናዟል ። (ዋይድ ዎርልድ/

ነው ማለትነው ። የሚተዳደረውም በእሻሻጭነት መሆኑን ራሱው አረጋግጧል ። ይኸው በሹካ የደም ጥማቱን ለመ ወጣት ሹካ የደገነው ሰው በቢላዋ ከሚያጠቃው ጋር ተመሳሳይ ያለው ይመስላል ። ሆኖም የትንሽዋ ዳግማር ፋሬኽ ገዳይ ይሁን አይሁን እስካሁን የታወቀ የለም ፣ በወ ንጀል አፈጻጸምና በጥቃቱ ሁኔታ ረገድ በሁሉም ላይ ተመሳሳይነት ይታያል ፣ ሆኖም ኩሶ በዚህ ላይ ብቻ ተመ ስርቶ ከመደምደሚያው ላይ ከመድረሱ በፊት ብዙ ጥን ቃቄን መውሰድ ጀመረ ። በሌላም በኩል ቬንቩር ገዳይ አይደለም የሚሉ ወገኖችም ተነሱ ። ኩሶም ሆነ ቡድኑ ከአንድ እልባት ለመድረስ እስቾጋሪውንና ውስብስቡን የቬንቩርን የልጅነት ታሪክ ለማወቅ ተገቢውን ጥረት አደረጉ ፤ በጥያቄውና በመልሱ ላይም በጣም የሚገር ሙና የተወሳሰቡ ነገሮች ገጥመዋል ።

ቬንቩር በእርግጥ እንዳለው ሥራፈት ነበር ፤ ማረ ፊያ ጐጆም አልነበረውም ፣ ትዳር ያልመሠረተና ቀደም ሲል በወንጀል የተፈረደበትና ሪኮርድ የነበረው ሰው ነበር። ወላጆቹ ከአውስትሪያ የታችኛው ግዛት ማለትም ከሀው ግስደርፍ የመጡ ሲሆን ከወንድሞቹ አንዱ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ተገድሎበታል ። ሌላኛው ወንድሙ በመንግሥት ሠራተኛነት ይተዳደራል ፣ ሁለቱ እህቶቹ ደግሞ በትዳር የሚኖሩ ነበሩ ። ቬንቩር የአንደኛና መለ ስተኛ ደረጃ ትምህርቱን በሀውግ ስዶርፍ ከአጠናቀቀ በኋላ በጦርነቱ ወቅት ይጣል በነበረው የቦንብ ናዳ ምክንያት ለልጆች ካምፕ ተብሎ ወደ ተዘጋጀው ምሥራቅ ታይሮል ተልኮ እስከ ጦርነቱ መጨረሻ ድረስ ተቀመጠ ። ቤተሰ ቦቹም ከሀውግስዶርፍ ወደ ቭየና ተዛውረው የምግብ መሸጫ ሱቅ በማቋቋም መኖር ጀመሩ ። ወጣቱ ዮሴፍ ቬንቩርም በተለማማጅነት ደረጃ በቤተሰቡ ሱቅ መሥ



ራት ጀመረ ፣ ቀስ በቀስ ከሰዎች ጋር የመስማማት ጸባይ ይታይበት ጀመር ፣ ከጦርነት በኋላ ከሱቅ ዕቃ እየሰረቀ በአውስትሪያ በወቅቱ ተጧጡፎ በነበረው የጥቁር ገበያ በመሸጥ በአንዲት ሴት አገናኝነት በወዳጅዋ በኩል አንድ ሽጉጥ ገዛ ።

መጋቢት 21 ፡ 1947 በአንድ የሴቶች ትምህርት ቤት በሚገኝ የሂሳብ ቢሮ የምግብ ቴምብር እንዲያመጣ ይላ ካል ። ከተላከበት የሴቶች ትምህርት ቤት ውስጥ አንዷን ልጅ በማስፈራራት በአንድ መጸዳጃ ቤት ውስጥ አስገብቶ ልብሷን እንድታወልቅ የስገድዳታል ። ርሷም ኡኡ ታዋን ስታቀልጠው ተደናግጦ አመልጣለሁ ሲል ከነመሣሪያው ከትምህርት ቤቱ አጥር ግቢ አጠገብ እጅ ከፍንጅ ተያዘ ። በዕለቱ በአእምሮ ሕመምተኛ ምክንያት በዚያን ጊዜ ጥፋቱ በወንጀል መዝገብ ላይ በጥፋት መልክ አልተመዘ ገበበትም ነበር ። ከዚያም በኋላ ተመልሶ ከቤተሰቦቹ ሱቅ ውስጥ መሥራት ጀመረ ። ሆኖም በርሱና በቤተሰቡ መካ ከል ግጭት ተፈጠረ ። የግጭቱም መንስኤ ወላጆቹ እንዲ ማር በላኩት የንግድ ትምህርት ቤት ትምህርቱን ባለመከ ታተሉ ነበር። ከአባትና ከእናቱ ጋር በፈጠረው ግጭትና አለ መግባባትም ምክንያት ወደ ወላጆቹ ቤት እንደወትሮው ከመግባት ተቆጠበ ። በዚያም በየአውራ ጐዳናውና በየ በረንዳው በመንከራተት በረንዳ አዳሪ ሆነ ፣ በዚያ ዓይነት የእንክርት ሕይወት ላይ እንዳለ ጥር 22 ፣ 1949 አንዷን ሴት ለመዝረፍ ሞክሮ በመቀስ ጡቷን ወጋት፣እርሷም በመ ጣባት ድንገተኛ አደገኛ ውግ ተደናግጣ እሪታዋን ስታቀ ልጠው ተደናግጦ አሁንም ሩጦ አመለጠ፤ሆኖም ምንም ያ ህል ሳይርቅ እሪታውን የሰማው ሕዝብ አሯሩጦ ይይዘዋል ። በዚያም ሳቢያ በቭየና ፍርድ ቤት ቀርቦ ሌላ የአእምሮ ሕክ ምና ምርመራ ተደረገለት ፤ ዳግመኛም ላይረገው ጥፋት

ተጠያቂ እንዳልሆን ተወሰነለት፣ ሆኖም ወደበኋላ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ተደረገ ። በየካቲት 29 ፣ 1950 ከፍርድ ቤት ውሳኔ በኋላ የተቋሙ እንክብካቤ ስላላስፈለገው በነፃ ተለቅቆ ወደ ቤተሰቡ ተመለሰ ።

ኩሶ ቀደም ሲል የተጠቀሱት ድርጊቶች ሊቀሰቀሱና ሊከናወኑ የሚችሉት በጾታ ውጥንቅጥና ችግር ሳቢያ ሊሆን ይችላል የሚልም ግምት ለመውሰድ ተገዷል ። የፍርድ ቤቱም የውሳኔ ሐተታዎች የቬንቹር መጥፎ ድርጊቶች መንስዔ ጾታም ሊሆን እንደሚችል አትቷል ። በወንጀል ፋይሉ ላይም የተመዘገበው በዝርፊያ ወንጀል መሰማራቱን እንጂ ስለ ጾታ ጉዳይ የሚጠቅስ ምንም ነገር ባለመኖሩ ሁኔታው የልጅነቱን መጥፎ ባህሪይ በማባባስ ረገድ ከፍተኛ ተጽዕኖ አድርጓል ። ፋይሉ እንደሚመሰክረው ሰባት ጊዜ በሌብነት ተግባር ተይዞ ከፉኛ ተተችቷል ። 3 ጊዜም በመናኛ የሌብነት ተግባር በመሰማራቱ ተወንጅሎ ተለቋል ።

ጥር 22/1953 በቭየና ግዛት ውስጥ 82 ጊዜ የስርቆት ወንጀል ፈጽመሃል ተብሎ በፖሊስ ከታደነ በኋላ ታሰረ ፤ በዚያ ወንጀልም ከከባድ ሥራ ጋር የአራት ዓመታት እሥራት ተፈረደበት ፤ ጥቅምት 5/1955 ፍርዱን ጨርሶ ከስቴት እሥር ቤት ተለቀቀ ። ሁለት ወር ሳይቆይ ኅዳር 22-1955 እንደገና በስርቆት ወንጀል ተይዞ ለአራት ዓመታት ከከባድ ሥራ ጋር ተፈረደበት ። አሁንም እሥራቱን ጨርሶ ይፈታል ፤ ሆኖም ነጻነቱን ካገኘ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ የካቲት 18/1961 እንደገና በስርቆት ተወንጅሎ ይታሠራል ፤ እንደተለመደው መጋቢት 5/1963 ከእሥር ቤት በነፃ ተለቀቀ ፤ በእሥር ቤት እንደነበረም ወላጅ አባቱ በሞት ተለይተዋል ። እናቱ ደግሞ በእድጋ ምክንያት እግራቸው ተቆርጧል ። በዚያም ሳቢያ እናቱ ግሮሰሪውን ለማንቀሳቀስ ባለ



መቻላቸው ሥራውን በማቆም ከቫሕሪንግ ወደ ቭየና ሄዱ ። ከመንቀሳቀሳቸው በፊትም ለ20 ደቂቃ ያህል ከእሥር ቤት ወጥቶ አነጋግሯቸዋል ፤ ከዚያች ጊዜ በኋላ ግን ስለርሱ የሚያውቁትና የሰሙት ምንም ነገር አልነበረም ። እህቱ ጀርትሩድ ሩፕ ግን አልፎ አልፎ በገንዘብ ድጐማ ትረዳው ነበር ። ወደ ኋላ ግን በባልዋ ምክንያት የነበራትን ግንኙነት አቋርጣለች ።

ኩሶ የቬንቹርን የወንጀል ሪኮርድ አገላብጦ ሲመለከት ፖሊሶች የዳግማር ግደያ ዜና እንደደረሳቸው የዚሁ ሰው ጥቆማም ደርሶአቸው ፍሊጋ ሄደው ካገኙት በኋላ ከእጃቸው በድንገት እንዳመለጣቸው ተገነዘበ ። በወቅቱ ከተላለፉት የሕዝብ ጥቆማዎችም ሁለቱ ከጐሌርዶርፍ እስር ቤት የመጡ ነበሩ ። አንደኛው ጥቆማ ባለቤቷ ዘብ ከነበረና ከሞተው የተገኘ ሲሆን ሌላው የእሥር ቤቱ የበላይ ተቆጣጣሪ ከነበረው ከጆአን ሁቤን ነበር ። ሁለቱም መረጃዎች ከሞላ ጐደል ተመሳሳይነት ነበራቸው ፤ መረጃውም እንዲህ ይል ነበር " እሥረኛው ዮሴፍ ቬንቹር በመጋቢት 5/1963 ሲለቀቅ ቀደም ሲል ወደ እሥር ቤት ሲመጣ ይዟቸው የነበሩት ሁለት ቢላዋዎች ተሰጥተውታል " እሱም ከቢላዎቹ ውስጥ አንደኛው በፖሊሶች የተገለጸው ዓይነት መምሰሉንም አረጋገጠ ። በሌላም በኩል በኩርየር ጋዜጣ የገዳዩ መሳሪያ መግለጫና ፎቶ ተሰራጭቶ ነበር ፤ ኩሶም በመዝገቡ ላይ " የጃክ ቢላዋ ለባለቤቱ ተሰጥቷል " የሚል አገኘ ፤

የቬንቹር እናትም ስለልጃቸው የሚያውቁትን እንዲያስረዱ ተጠየቁ ፣ ርሳቸው ግን ስለርሱ የነበራቸው መረጃ በጣም ውስን ሆኖ ተገኘ ። ልጃቸው ከእሥር ቤት እንደወጣ በጣም ለጭር ጊዜ (ከ3ና ከ4 ቀናት ላልበለጠ) ብቻ እንደተቀመጠና በአንድ የኖራ ማምረቻ እንደተቀጠረ ፣ ሥራ

ውንም ወዲያውኑን እንደተወው ቆየት ብሎም ወደ ቤታ
ቸው መምጣቱን ጨርሶ እንዳቆመና ያለበትምን እንደማ
ያውቁ ተናገሩ ። ከቤት ወጥቶ የመቅረቱ ጉዳይ ያላስጨነቃ
ቸውና ያላሳሰባቸውም ከቤት ወጥቶ የመጥፋት ልምዱ ከፍ
ተኛ በመሆኑ የተነሳ መሆኑንም በተጨማሪ ተናግረዋል ።

በመጨረሻም ከእናቱ አፓርታማ ጨርሶ ከለቀቀ በኋላ
የአውስትሪያን ሕግ በማክበር ሌላ ቦታ ተመዝግቦ እንደ
ሆነ በማለት በሠላማዊ ኑዋሪዎች መዝገብ ቢመረመር ጭ
ራሽ ሊገኝ አልቻለም ። በመሆኑም ይህን አስመልክቶ ከኀ
ብረተሰቡ አንዳንድ ጥቆማዎች ይደርሳሉ የሚል ግምት
ስለነበረ በነኩሶ የተጀመረው ምርመራ በዚያም ደረጃ
አልተገባደደም ነበር ።

እሮጊቷን ሹካ ይዞ ሊወጋ የነበረው አፋኝ ከእሥር
ቤት ያንን ቢላዋ ይዞ በወጣ በሰባተኛው ቀኑ ልጅቷ በ
መገደሏ ዶክተር ኩሶ በዮሴፍ ቬንቡርም ላይ የበለጠና
ከፍተኛ ጥርጣሬ አደረበት ።

ኩሶ የዮሴፍን የሕይወት ታሪክ በጥልቀት በመመር
መሩ አንዳንድ በጣም አስደናቂ ጉዳይዎችን በእሥር ቤት
ከተካሄዱት ሂደቶች አግኝቷል ። በተለይም ከቀድሞው ፍ
ርድ ቤት መዛግብት የዮሴፍን ዝርፊያ ጉዳይ በሚመለከት
የተገኙት መረጃዎች እንዳረጋገጡት በመላበሻና በመፈተሻ
ክፍሎች ዝርፊያ የማካሄድ አመል እንደነበረው ተረጋግ
ጧል ።

ዝርፊያ ካካሄደባቸው መካከል ጥቂቶቹን ለመጥ
ቀስ ያህል በስኬቲንግ ክለብ ፡ በሎቪንገር ትያትር ቤት
የአርቲስቶች የመላበሻ ክፍሎች ፡ በጐሰርቪየር ክሊኒክ
የመፈተሻ ክፍል ፤ በሲኒማ ቤት የፍተሻ ክፍል ፡ በሠራ
ተኞች መላበሻ ክፍል ፡ በብስኩት መስሪያ ሱቅ ፤ በአንድ



ት/ቤት የሥራ አስኪያጅ ክፍል የተከናወኑት ይገኙበታ
ል ።

ሁለቱ መሠረታዊ የሆኑ ጠቃሚ የምርመራ ፍንጮች
(ቢላዋ በመያዝና በየመላበሻና ፍተሻ ቦታ የማጥቃቱ) ኩሶ
ን በባሌት ተጨዋችዋ ልጅ ላይ የተፈጸመው አረመኒያዊ
ግድያ ቬንቡር ላይ እንዲያተኩርበት አስገደደው ፤ ሆኖ
ም ባልበሰለ ሁኔታ የተጠናቀረው ጉዳይ ማለቂያው እንዳይ
በላሸበት በመጠንቀቅ መርማሪዎቹ ቬንቡርን በምርመራ
መቅድም ጥያቂያቸው ላይና በምርመራ ጅማሪያቸው ላይ
የኦፔራውን ግድያ ጉዳይ እንዳያነሱ አስጠነቀቀ ። ባንጻሩ
ግን ከዚያ በኋላ በተደረጉት የሴቶች ማጥቃት ላይ እንዲያ
ተኩሩና እንዲያጠናክሩ አዘዘ ። በቅርቡ ከፈጸማቸው ጥቃ
ቶችም መካከል በወይዘሮ ኤማላኸ ላይ በሹካ የፈጸመውን
ወንጀል ሸምጥጦ ካደ ። ለማንኛውም አንድ የርሱ የሆነ
ጥቁር ሹራብ ክፍል 5 ውስጥ በመገኘቱ ያንን ለብሶ እን
ዲቀርብና እንዲታይ ሲደረግ አሮጊቷ ያጠቃቸው ሰው
መሆኑን ያለመጠራጠር አረጋገጡ ።

በሌላ በኩል ደግሞ ሐምሌ ሰባት ጥቃት ካደረሰ
ከአንድ ቀን በኋላ ተጠቂዋ አሜሪካዊት ታዳጊ ወጣት ከሆ
ስፒታል ወጣች።እርሷዋንም አጥቅተዋል ተብለው የተጠረ
ጠሩት እንዲሰለፉ ተደርጎ እንድትመርጥ ሲደረግ አንድ
በአንድ ተመልክታ ከመካከላቸው እንደሌለ ተናገረች ።በር
ካጥ ርሱ እነሱ ሰልፍ ውስጥ እንዲገባ አልተደረገም ። በፖ
ሊስ ጣቢያው ቢሮ የተሰበሰሰቡትን ፎቶግራፎችንም አገ
ላብጣ ተመለከተች ። ውጤት አልባ ሆነባት ። በሁለተ
ኛው ቀን ሌላ የተጠርጣሪ ሰልፈኞች (ርሱ ያለበት) ተደር
ድረው እንድትመለከት ተደረገ ፤ ያለአንዳች ጥርጥር ያጠ
ቃት ቬንቡር መሆኑን አረጋገጠችላቸው ። ሌላይቱን
ምስክር ማሪያ ብራነርን ወግቶ ከቭየና ከተማ መናፈሻ

ሲወጣ ያየችው ሴትዮ በመሆኗ ርሷም ከተደረደረበት መንጥራ እውነቱን አረጋግጣለች ። የሲኒማ ቤቱም አስተና ጋጅ ሄርታ ቬንድለር አንዲት ተማሪ በቢላዋ ሲያጠቃ አይታ ያሳደደችው ሰው ለመሆኑ አረጋገጠች ። ሆኖም ያ ሁሉ ምስክርነት እየተሰጠበትና እየተጠቆመ አንዳቸውንም ወንጀል አልፈጸምኩም በማለት ሽምጥጥ አርጎ ከመካድ ፈቀቅ አላለም ። ቬንቩርም በሌላ በኩል ከአንዲት ስምዋን ለመንገር ካልፈለገች ሴት ጋር ይኖር እንደነበርና ከርሷም ጋር ለመኖሩ ለፖሊስ ማስመዝገቡን ይናገራል ። ከጐሉርዶርፍ እሥር ቤት ከወጣ በኋላ የሄደበትን ለማሳወቅ ግን ፈጽሞ አልፈለገም ።

በዚያ የክህደት ሁኔታው ልክ እንድ አዳኝ በከፍተኛ ደፈጣ እንዳለ ሆኖ የሚያድነውን ለመያዝ እንደሚያቁነጠንጠው ኩሶም በዮሴፍ ቬንቩርም ላይ ያለውን ትኩረት አጠነከረበት ። በፍርድ ቤት ማዘዣና ፈቃድ መሠረትም በዮሴፍ ላይ በበዓላትና ዕረፍት ቀናት ሳይቀር ምርመራ እንዲካሄድበት ተደረገ ። አሁንም ይህ ሁሉ እየሆነ ክህደቱ አላቋረጠም ፣ ዝርዝር መረጃ ለመስጠትም ፈጽሞ ፈቃደኛ ሆኖ አልተገኘም ። ኩሶ በመገናኛ ብዙኃን በመጠቀም ጭምር የሕዝቡን ድጋፍ ጠይቋል ፡ ራሱም በብሔራዊ ቴሌቪዥን በመቅረብ ያለውን ጭብጥ አስረድቶ ስለጉዳዩ ተጨማሪ ተጨባጭ መረጃ ካለ ሕዝቡ እንዲያቀርብለት አሳስቧል ። የቀረበው ጥያቄ ግን ውጤት አላገኘም ። ሁለት የቡና ቤት ሠራተኞች የገዳዩን ፎቶግራፍ በጋዜጣ ካዩና ካረጋገጡ በኋላ የቴሌቪዥን ተመልካች ደንበኛቸው መሆኑን በመግለጽ ብዙ ጊዜ አብረው እንደሚውሉ ተናግረዋል ። በተለይ አንደኛው የቡና ቤት ሠራተኛ ጓደኛው 55 ዓመት ዕድሜ ያለው አዛውንትና የግብረሰዶም ወንጀሉ የተከሰተበት ነበር ። ኩሶም ለጥያቄ በመጥራት ዝርዝር መረጃ እን



ዲሰጠው ጠየቀው ፤ ርሱም ባለፈው ፋሲካ ቬንቩር በፖሊስ ሳይመዘገብ ከርሱ ጋር ይኖር እንደነበር አስረዳ ። በመጨረሻም ምርመራ ላይ ሁለቱ በግብረሰዶም ግንኙነት ይኖሩ እንደነበር ተረጋገጠ ።

የቡና ቤቱ ሠራተኛ ራሱም ቢሆን አንዲት ክፍል ከሰው ተከራይቶ ነዋሪ ስለነበረ በነበረችው አንድ አልጋ ላይ ገዳዩን ለ4 ወራት ሲያስተናግደው አከራይዋ ቤት በፍጹም የማታውቅ መሆኑንም አረጋገጠ ። ቬንቩርም በአከራይዋም የድብብቆሽ ጨዋታ ተጫውቶባታል ፤ ሴትየዋ መደበኛ ሥራ ስለነበራት ከቤት የሚወጣው ወደ ሥራዋ ስትሄድ ሲሆን ወደ ቤት የሚገባውም መተኛቷን ካረጋገጠ በኋላ ነበር ። ለጓደኛውም ለአንድ ጅምላ ሺያጭ ድርጅት የድለላ ሥራ እንደሚያካሄድ የነገረው ሲሆን የኋላ ኋላ ግን ውሸት ሆኖ አግኝቶታል ፤ ለምን ለፖሊስ ከርሱ ጋር መኖሩን እንዳልተናገር ሲጠየቅ በጓደኛው መታሰር በጣም ከባድ ድንጋጤ ላይ ስለወደቀ ማሳወቅ እንደነበረበት መዘንጋቱንና ሌሊቱን ሳይተኛ እንዳደረ ተናግሯል ። በተጨማሪም ጓደኛው እንደማያሳጣው ስለተማመነበት በፍላጐቱ መጥቶ አለመግለጹን አምኗል ። ለፖሊስ ሳያስመዘግብ አብሮት በማስተኛቱም የ60 ቀናት እሥራት ተፈርዶበታል ።

ከብዙ ተከታታይ ምርመራዎች በኋላ ቬንቩር ከእሥር ቤት እንደወጣ በአንድ የኖራ ማቅለሚ ጣቢያ ለመሥራት መቀጠሩን ከዚያም ሥራውን በቆዳ በሽታ ምክንያት የተወ መሆኑን ይገልጣል ። መጋቢት 12-1963 የኦፔሪው አዳራሽ ግድያ በተካሄደበት ዕለት ከሰዓት በኋላም አዲስ ሕይወት ለመጀመር በሳሊስበር አድርጎ ወደ ጀርመኒ መሔዱን ተናግሯል ።

ኩሶ በኦውስትሪያ የድንበር ተቆጣጣሪነት ይሠሩ የነ
በሩትንና በዚህ ሥራ በቂ ልምድ ያላቸውን መርማሪዎች
አሰማራ ። በተባለው ዕለትም ቬንቩር ሊሳፈርባቸው  የሚ
ችሉ 3 የባቡር መስመሮች ነበሩ ፤ እኒያም አንደኛ አሪየ
ንት ኤክስፕሬስ (ቪየናን የለቀቀው በ8 ሰዓት ከሰዓት በኋላ)
ሁለተኛው ሮትሽይስ ኩሪየር (ቭየናን የለቀቀው በ9 ሰዓት
ከ ሰዓት በኋላ) ሶስተኛው ቫይነር ዋልዘር ( ቭየናን የለቀቀ
በ8 ሰዓት ከሰዓት በኋላ) ነበሩ ። በመጋቢት 12
ቫይነር ቫልዘር ሳልሰበርግ የደረሰው (10 ደቂቃ ዘግይቶ
ነበር ) በመሆኑም ከምሽቱ አምስት ሰዓት ከአምሳ አምስት
ደቂቃ እንደሚደርስ ገመቱ ። በሳሊስበርግ ከአረፈበት ኤ
ልም ሆቴል መዝገብ ውስጥም በተደረገው ምርመራ ከግ
ማሽ ሌሊት በኋላ እንደተመዘገበ ተረጋግጧል ።

ቬንቩርም በተደጋጋሚ ጥቃት ያደረሰባቸውን ሴቶች
ከዷል ። ኩሶ በጥያቄዎቹ መሀል የኦፔራውን ግድያ በመ
ደባለቅ ሲጠይቅ ፈጽሞ ሊያምን አልፈለገም ። ቀንና ሌሊ
ትም የማይሰለችና የማይደከመውን ድርቅ ብሎ የመካድ
ፈሊጡን ገፋበት ።

ኩሶም ገዳዩን ከዕውነታው ጋር የሚያገናኝበት ሁኔ
ታና ጊዜ እየተመቻቸለት ሄደ ፤ የሳሊስበርግ ውጤትና ሌ
ሎች የተጋጩ ኑዛዜዎቹ ተቀነባብረው ቀረቡለት ፤ ውጤቱ
ተውኔታዊ ነበር ። ቬንቩርም በሚታይ መልክ ተንቀጠቀ
ጠ ፤ በመጨረሻም "የአእምሮ ሕመምተኛ በመሆኔ ሳላስ
ታውሰው በፈጸምኩት ወንጀል ምስክሮች መስክረውብ
ኛል" በሚል ሌላ ዘዴ ለማምለጥ በመፈለጉ ከራሱ ጋር
ለመነጋገርና ራሱን ለማስተካከል ይቻለው ዘንድ የማሰ
ቢያ ጊዜ እንዲሰጠው ጠየቀ ።



ሐምሌ 27-1963ም ከአንዱ ከተግባባው መርማሪ ጋር
በምስጢር እንዲገናኝ እንዲፈቀድለት ጠየቀ ። ለዚያው
መርማሪም በሴቶች ላይ ያደረጋቸውን ጥቃቶችና የዳግማር
ፋሪኽ ግድያንም ጭምር አንድ በአንድ ተናዘዘለት ።

ኩሶ በቬንቩርም ላይ ያካሄደው አስቸጋሪ የምርመራ
ሥራ ራሱን በቻለ መልክ በራሱ በገዳዩ ስሜትና ፍላጐት
በመጠናቀቁ በምርመራ ሥራ አግባብነት የነበረው የእ
ምነት ሂደት ነበር ። ከልምድ እንደዚህ መሰሎቹ ኑዛዜ
ዎች ተደጋግመው ስለሚከሰቱ አንድ ምሽት በድንገት ኑዛ
ዜውን ለመስጠት በመፈለጉ የእሥር ቤቱ መኪና ከግሬይ
ሐውስ ( የቭየና የከተማ እስር ቤት ስም) ወደ ኩሶ የደህን
ነት ቢሮ መልዕክቷን ለማድረስ በረረች ።

ዮሴፍ ቬንቩርም የድካምና የመጠወላለግ ስሜትና መ
ልክ ከማሳየቱም በላይ ኩሶ የዘረጋለትን የገመድ ጫፍ ለመ
ቀበልና ያሚቀርቡለትን ጥያቄዎች ለመመለስ ወሰነ ። በዚ
ያው ቀንና ሌሊት በመምጣት ማለቂያ የሌለውን ጥያ
ቄና የማይበገር መልሱን የሰጠው በዚያቹ ክፍል ነበር ።
ፖሊሶች የዮሴፍን ቁርጥ ሐሳብ እንደሰሙ ወደ ቴሌፎ
ንና ወደ ብዙኃን መገናኛዎች ይናወጡ ጀመር ። በዛች ማከ
ሰኞ ምሽት የ10 ዓመቷን የባሌት ተጫዋች ታዳጊ ወጣት
መግደሉን አመነ ።

በእስጥ አገባ ሙግት መልክ የነበረው ፍጥጫ በኩሶ
ስልትና ዘዴ እልባት አገኘ ፤ ያም ውጤት ለኩሶ የምርመራ
ቡድን ትልቅ ዝናንና ልምድን አስገኝቷል ።

ቬንቩርም ከሌሎች መርማሪዎች ይበልጥ ብላስኮን
የሚያቀርበውን ጥያቄ እንደሚያዳምጠው አረጋገጠለት ።
ገዳዩም " እንደነበረ አድርጐ ለመተንፈስ " በማለት እስ

ተያየቱን ከገለጸ በኋላ ቅንጣት ነገር ሳትቀረው ኑዛዜውን
ተርትርታል ።

ኩሶ ለመርማሪው በሰጠው መመሪያ መሠረት ቬን
ሹርም በራሱ መንገድና እንደበት እንዲናዘዝ ሆነ ፣ መርማ
ሪዎቹ የሚያቋርጡት አንዳንድ መረጃዎችን ለማረጋገጥ
ሲፈልጉ ብቻ ነበር ። እርሱም የፈጸመውን ግድያ በሚያ
ውቀው መንገድ ብቻ በዝርዝር ነገራቸው ። ቢታወቀና በተ
ረጋገጠው ሪፖርቱ የተጓደሉትን ሁሉ በማሟላት ጠቅላላ
ድርጊቱን የተሟላ አድርጎታል ።

እንደሌሎች ገዳይዎች ሁሉ አንድም ሳይቀረው የተ
ናዘዘው ከኀሊና ወቀሳ ራሱን ነጻ ለማድረግና ነፍሱንም እን
ዲቀላት መሆኑን ተናግሯል ። ኑዛዜውን መተርተር ከጀ
መረበት ጊዜ ጀምሮ በጣም የመዝናናት ስሜት ከማሳየቱም
በላይ እንደልቡ መለፍለፍም ጀመረ ። በኑዛዜውም ፖሊ
ሶች ያልደረሱበትንና ያላሰቡትን ሁሉ በዝርዝር ከገለጸላ
ቸው በኋላ ወደ ኦፔራ ቤቱ የግድያ አፈጻጸም አዘገመ ። ቬን
ሹርም በኦፔራ አዳራሽ ግድያ ከማካሄዱ 4 ቀናት በፊት በአ
ንድ የቴያትር መልበሻ ክፍል በመሽሎክሎክ ገብቶ መጋ
ቢት 8 ከአንድ የመዝምራን መሪ ቦርሳ 40 ሺሊንግ መሥ
ረቁን ገልጿል ።

መጋቢት 11 ቀን ሌሊት በቭየና በካራጋን በሚገኘው
በእናቱ አፓርታማ ውስጥ አደረ ። በማግሥቱ በጣም ከተጻ
ከመችው እናቱ ጋር ከባድ ጭቅጭቅ ነበራቸው ። የጭቅ
ጭቁም መነሻ ያው እናቱ ዘወትር የሚመኙለት የተከበረ
ሥራ ይዞ በወግ በማዕረግ እንዲኖር በማሳሰባቸው ነበር ።
ርሱም ያ ጭቅጭቅ በሴቶች ላይ ያለውን ጥላቻ ሊያባብስ
በት ቻለ ። በዚያም ምክንያት የቁጭት ጥማቱን ለመወጣት
ሲል አንድ ሴት ለመግደል ወሰነ ። የትኛዋም ዕደለቢስ
ሴት ብትሆን ለርሱ ምንም ልዩነት አያመጣበትም ።



ከዚያም በኋላ ከእናቱ ጋር ባደረገው የጭቅጭቅ መጋ
ጋል ጭሶ ወደ ኦፔራው አዳራሽ አመራ ። ከጥቂት ቀናት
በፊት የስርቆቱን ፕሮግራም ለማከናወን እዚሁ አካባቢ
ብቅ ብሎ ስለነበር ብዙ እንግዳ አልሆነበትም ። ከኦፔራው
አዳራሽም እንደገባ በጣም ጭር ያለበት ቦታ በመሄድ የጠ
ነሰሰውን የሴት መግደል ዓላማውን የሚፈጽምበት ቦታ
እንዳለ ካጠና በኋላ የሚያገኛትን ሴት ለማጥመድ ተዘጋጀ።

ቆየት ብሎ ወደ ኦፔራ ቤቱ ተመለሰ ። በዚያን ጊዜ
ግን ለመግደል ጽኑ ውሳኔ አደረበት ። ነገር ግን ቢላዋውን
ቤቱ ረስቶ እንደመጣ ስለታወቀው ወደ እናቱ አፓርታማ
ተመልሶ የጃክ ቢላዋውን ይዞ ወዲያው ተመለሰ ። እንደተ
ለመደው ለሶስተኛ ጊዜ በዚያች ዕለት ወደ ስቴት ኦፔራው
ሹልክ ብሎ ገባ ። አንድ ሴት ይዞ ለማጥቃት አድፍጦ በመ
ጠባበቅ ላይ እንዳለ አንድ ሴት ወደ መጸዳጃ ቤት ስትገባ ያያ
ል። ወዲያው ግን አንድ ግራጫ ኮት የለበሰ ግዙፍ ሰው ስለ
መጣበት ዓላማው ከሸፈበት ። በመተላለፊያው ቢለዋውን
ይዞ ቢቆምም ሰውዬው ግን ስላላስተዋለው ከጉዱ ተረፈ ። ት
ንሽ እንደቆየም አንድ ትንሽ ልጅ ስትመጣ ያያል ። እርሷም
ሱዛን ፊቼትንባው ነበረች ። ቬንሹርም ላሰበው ተግባር
ትውልልኛለች ብሎ ያሰባት ይህች ነበረች ። ነገር
ግን የሕይወቷን መጠናቀቂያ ዕድል የሚያድን አንድ ጉድ
ተፈጠረ ። ርሱም ከታች ሌሎች ልጃገረዶች እየተንጫጩ
ስለመጡ ከዓላማው ተቆጠበ ። ልጅቷ ቀደም ሲል በደንብ
አድርጋ የዚህን ሰው ገጽታ ልትናገር የቻለው ልጅ ናት።

ከ10 ደቂቃዎች በኋላ የ10 ዓመትዋ ወጣት ዳግማር
ፋሪኽ ብቻዋን ወደ ፎቅ ስትወጣ ተመለከተ ። ገዳዩም

ራሱን ሐኪም እንደሆነ አድርጐ አጅቦ ወደ መታጠቢያው ቤት በመምራት አስገባት ። በተረጋጋ መንፈስም ዛሬ የባ ሌት ልጆች ልብሶቻቸውን ሌላ ቦታ እንዲቀይሩ ታዟል። ብሎ በመንገር በሕይወቷ ዳግመኛ ተመልሳ ወደ ማትመ ጣበት በር ልብሷን እንድትቀይይር መርቶ አስገባት ። በ መታጠቢያው ቤት እንዳስገባትም ተመርምራ እንደሆነና እንዳልሆነ ይጠይቃታል ። በሚቀጥለው እርምጃው ደግሞ በጣም አስፈሪ የሆነውን የማጥቃትና የግድያ ሥራውን እን ዳካሄደ ይገልጻል ። በስንት ችግር ተሊቃቅመው የተ ገጣጠሙት መረጃዎች አሁን ኩሶ ያጣብቃቸው ጀመር ። ከግድያው በኋላ ልክ ፖሊሶቹ እንደገጣጠሙት ሁሉ ገዳዩ ከገደለ በኋላ ወደታችኛው ፎቅ በመውረድ በረጅሙ የእም ድር ቤቱ የኦፔራ መተላለፊያ በማቋረጥ ወደ ካርን ጐዳና አቅጣጫውን በመምራት ሄደ ። የደም ነጠብጣቦች በበሩ መስተዋትና በመውጫው በር ሊኖር የቻለበት ለምን እን ደሆነም ከገዳዩ ኑዛዜ መርማሪዎቹ አረጋግጠዋል ።

በግድያው ምርመራ ወቅት በፖሊሶች የተጠሩ ምስክ ሮች የሰጡት መልስ በቬንቡርም ኑዛዜዎች ተሰምተዋል ። የዚያም የታክሲው ግጭት በኑዛዜው ውስጥ ተጠቃሎ ተገ ልጾ ነበር ። እንደተናገረው በፈጸመው ድርጊት በጣም ተረ ብሾ ወደ አቅራቢያ መንገድ ለማቋረጥ በደም የበሰበሰው ን ኮቱን ተሸክሞ ሲሮጥ አንድ ባለታክሲ ሊገጨው ነበር። በዚያ መንገድ ነበር የባለመኪናውን ምስክርነት ለማረጋ ገጥ የተቻለው ።

ገዳዩ ሩጫውን በፋሪስ ጐዳና አድርጐ ከቀጠለ በኋ ላ አንድ ቦታ ቆም ብሎ ቡና ጠጥቷል ፣ ቀጥሎም ቀስ ብሎ በመራመድ ወደ ሽቬዘር በርና ወደ ሆፍሽ ርግ ተጓዘ ። ከዚያም ቀስ በማለት ወደ ቀድሞው ቤተ መንግሥት በመግባት በደም የተዘፈቀውን ኮትና የእጅ ጓን



ቲውን ሸጉጦአቸዋል ። ያንንም ተከትለው ፖሊሶች ሲፈ ትሹ የተባለው ርግጠኛ ሆኖ ተገኝቷል ። ያ ድርጊትና መረጃ በኦፔራ አዳራሹ ካደረገው ግድያ ጋር በተጨባጭ የሚያገናኘው ሆኖ ተገኝቷል ። ኮቱን በዚያ መልክ ካስ ቀመጠ በኋላ ወደ ባቡር ጣቢያ በመሄድ ከምዕራብ የባቡር ጣቢያ ወደ ሳሊስበርግ የምትሄደውን የኤክስፕሬስ ባቡር በመያዝ ተጓዘ ። በሚቀጥለው ቀን ለጉዞው የሸርሽር ትኬት በማስቆረጥ ወደ ሙንሂን ቀጠለ ። እዚያም የጃክ ቢላውንና የመታወቂያ ወረቀቶቹን በመጣል በአካባቢው ፖሊስ በሌላ ስም ራሱን አስመዘገበ ። በዚያን ጊዜ ነው ፖሊሶች የኦፔራ ቤቱን ገዳይ ለማግኘት ይጥሩ የነበረው ።

ለምን ያንን አሰቃቂ ግድያ እንደፈጸመ ሲጠየቅ “በሁ ሉም ሴቶች ላይ ያንን የመሰለ ወንጀል የፈጸምኩት በሴቶች ላይ ውስጣዊ ጥላቻ ስላለብኝ ነው” በማለት በድጋሚ መል ሶላቸዋል ። በአእምሮ ሕክምና የምርመራ ውጤት ረገድ የተደረሰበት ነገር እንዳለም በተደረገው ማጣራት ቬንቡ ር ያን መሰሉን ጥላቻ በሴቶች ላይ ያደረሰው በትንሽነቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድዋ ልጅ ላይ ባደረገው የጥቃት ሙከራ ስላስደነገጡት በሴቶች ላይ ጥላቻ እንዲያድርበት ምክንያት ሆኗል የሚል ሲሆን ርሱም ሲናገር “ሴቶችን መጥላት የጀመርኩት የ15 ዓመት ዕድሜ በነበርኩበት ጊዜ ነው ። ለምን እንደሆነ ግን አላውቅም” ብሏል ።

ቢላዋውን በሚመለከት የወጣውን ጋዜጣዊ መግለጫ እንዷት ሴትዮ እንብባ ወደ ፖሊስ ጣቢያ በመምጣት የተ ባለውን ቢላዋ አስረከባ ነበር ፤ ሴትዮዋም ያገኘችው ገዳዩ በጠቀሰው ቦታ እንደሆነ አረጋግጣላቸዋለች ።

ዶክተር ኩሶ በመጨረሻ ሲያጠቃልል “ በደህንነት ቢሮ አማካይነት ከተደረጉት ምርመራዎች የዮሴፍ ቬንቹርም ወንጀሎች ሊጋለጡና እርሱ እንደፈጸማቸውም በአስተማማኝ ደረጃ ላይ ደርሰዋል ። ምናልባት ቆየት ብሎ ኑዛዜውን የሚያመሰቃቅልበት ጉድ ወይም ሁኔታ ቢፈጠር የደህንነቱን ቢሮ መረጃዎቹን ሊለውጣቸው አይቻለውም ” በማለት የቬንቹርን ኑዛዜ በምስማር ከእውነታው ጋር አጣብቆታል ።

የኦፔራውን ቤት ግድያ ዶክተር ኩሶ ሲያስታውስ ባለመጠራጠር “ ይህ ግድያ ከማንኛውም ወንጀል በበለጠ ሁኔታ ናላየን አዞሮት ነበር ” በማለት ጸጸቱን ገልጿል ። ኩሶም “በኔ ኃላፊነት የሚገኝ የነፍስ ገዳይ ወንጀለኛ መርማሪ ትላልቅ ጉዳዮች ማስተናገድ ይኖርበታል ። በመታደል አብዛኛዎቹ መፍትሔ ተሰጥቷቸዋል ። አንዳንዶቹ ግን በቀላሉ የሚፈቱ አይደሉም ። ” ብሏል ።

የኦፔራው አዳራሽ ግድያ ትላልቆቹ ግድያዎች ጐን የሚቆጠር ነበር ። ምንም እንኳን የትንሽዋ ዳግማሪ ፋሪሽ ጉዳይ መፍትሔ ቢያገኝም ድርጊቱን በሕይወቱ እስካሊ በሙሉ ሲታወሰው እንደሚኖር ገልጿል ። ምክንያቱም በአንድ መርማሪ ሕይወት ውስጥ እንደዚህ ዓይነት ከባድ ሁኔታ የሚያጋጥመው ከስንት ጊዜ አንደዬ ሊሆን ስለሚችል ነው ፤ ስለ ምርመራ ዘዴውም በተመለከተ ዶክተር ኩሶ ያስተዋለውን ሁኔታ ሲናገር “ ለአንድ መርማሪ በጣም ከፍተኛ ሥራ የሚሆነው ሰው ሰራሽ ድልድይ ከተጠርጣሪው ጋር በመገንባት ይሆናል ። አንድ ሰው ተጠርጥሮ ቢታሰር ከመናዘዙ በፊት መርማሪውን እንደ ጠላት ቢመለከተው ጥሩ አይሆንም ። ዞሮ ዞሮ በምርመራ በተቻለ መጠን በነቃ መንገድ የመግባባትና ለሰውየው ልዩ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል ፡ መርማሪዎችና የአእምሮ



ሐኪሞች የሰውን ልጅ ምስጢርና አስተሳሰብ በጥልቀት ገብተው የመመርመር ችሎታቸው ቀላል አይደለም ” ብሏል። ኩሶ ለነፍስ ገዳይዎች ይቅርታ ባያደርግላቸውም አንድ ነፍስ ገዳይ ወንጀሉን የፈጸመበትን ምክንያት ለማገናዘብ ይሞክራል ።

በሌላም በኩል ኩሶ በሚያደርገው ትምህርታዊ ገለጻ የሚደጋግመው ነገር አለው ። ይኸውም “ የመርማሪዎች ሥራ በኑዛዜ ላይ ተወስኖ አይቀርም፣ ይቀጥላል “ብሎ መጀመሩ ነው ። ለዚህም የሚሰጠው ምክንያት ኑዛዜን በመረጃዎች የተደገፈ ለማድረግና ለማሟላት ሲባል ነው ”። ብሏል።ኩሶ ሌላው የምርመራ ባህሪይ በምንም ዓይነት መንገድ ተመርማሪን በኃይል በመያዝ ለማውጣጣት ያለመሞከሩ ሲሆን የኩሶ ትልቁ ቁም ነገር ምስጢር መጠበቁና ከበታቾቹ ጋር ያለው መልካም ግንኙነት ነበር። ሁሉም በአንድነት ስለ ወንጀለኛው ማድረግ የሚኖርባቸውን ያዳምጡታል፤ መረጃዎችን ያፈልቃሉ፤እንዲሁም መረጃ ሰብሳቢዎችን ይከተኩታሉ ። ወንጀለኞች በእሥር ቤታቸው እንዳሉ በቅርብ በመሆን ይጠይቁአቸዋል ። ይኸውም ከተፈቱ በኋላ ለሌላ የወንጀል ምርመራ ሥራ ሊረዱአቸው ስለሚችሉ ነው ። በእያንዳንዱ ወንፆል ምርመራ ኩሶ ያለው ትኩረት በጣም ጠንካራ ነው ። በዚያ ምክንያት ኩሶ የወንጀለኛውን የግድያ ምክንያቶችን ማወቅ ብቻ ሳይሆን የወንጀለኛውንም ዘዴ ያጠናል ።

ኩሶ ራሱን ደንበኛ የወንጀል ጠቢብ እንደሆነ አድርጎ ይቆጥራል ። በሪፖርቱ ላይ ነገሮችን ችላ አይልም ። በጣም በተንጸባረቁና በጥሩ ፎቶግራፎች የታጀቡ ሪፖርቶች ስሜቱን እንደማይገዙት ይናገራል ። በመሆኑም ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ በመሄድ የራሱን ግንዛቤና አስተያየት መቅረጽ ይወዳል ። አንድ ወንጀል ከተፈጸመ በኋላ

ኩሶ የማያቋርጥ መረጃ እንዲያደርሰው ስለሚያደርግ በደን
ገት ለሚፈጠሩ ለውጦች ቶሎ የመደንገጥ ወይም በቀላሉ
የመደነቅ ባህሪ የለውም ።

ኩሶ የእውስትሪያ ታዋቂ መርማሪዎች በማስታወሻ
ቸው ላይ ስለእውነተኛ ሕይወት በይፋ ሲገለጽ " ብቸኛ
መርማሪ በስርኩናን ዶይል እንደታየው የሻርሎክ ሆልም
ሁኔታ የልብ ወለድ ባህሪይ ይሰጠዋል ። ነገር ግን ዕውነተ
ኛው የፖሊስ የወንጀለኛ ምርመራ ሥራ የሚሠራው በአንድ
ሰው ሳይሆን በደንብ ልምድ ባካበቱ ቡድን ነው።ጥሩ ጥሩ
ሃሳቦችን ማመንጨት ከማዕረግ ጋር የተያያዘ አይደለም ።

የኔ ባልደረቦች ደፋሮችና ችሎታም ያላቸው ሰዎች
ናቸው ። በዓለም በምንም ዓይነት አንድ ሰው ብቻውን በተ
ከታታይ ወንጀልን ለመፍታት አይችልም ። ስለዚህ በጣም
አስፈላጊ የሆኑ ጥሩ ረዳቶችን መያዝ ነው ፣ የውሳኔው ኃላ
ፊነት የመሪ ስለሆነ ለድል ሆነ ለውድቀት ኃላፊነቱን የም
ሸከመው ራሴው ነኝ " በማለት ደምድሟል ።



# በቺካጎ " የክፍለ ዘመኑ ወንጀል "

የሴትዮዋ ጩኸት እንደቃጭል ድምጽ የቀጠነና ጆሮ
የሚበጥስ ነበር ። በደቡብ ቺካጐ በተለይም በሁካታና ሥር
ዓት አልባ አካባቢነቱ በታወቀው በዊንዲ ሲቲ አካባቢ
ያ ! እንደደማቅ ቃጭል ጆሮ ሰንጣቂ ድምጽ የተለመደ አል
ነበረም ።

የሚወብቅ አየር በነበረበት በዚያን ቀን ማለዳ ላይ
የተሰማው ያልተለመደ ድምጽና እሪታ ተጨናንቀው
በተሰሩት የከተማ መኖሪያ ሠፈር የነበሩትን የጉረቤት
ሰዎች አደናገጠ ። ሁሉም በያሉበት የምን እሪታ ነው እያሉ
በመነጋገር ላይ እንዳሉና ሁኔታውን ተረድቶ ለእርዳታ
ለመድረስ አንድም ሰው ሳይመጣ እሪታው ግልጽ እየሆነ
በተደጋጋሚ ይሰማ ጀመር ።

" እርዱኝ የነፍስ ያለህ ! ሁሉም አለቁ ! " የሚለውን
እጅግ የሚያሳዝንና ሆድ የሚረብሽ ድምጽ ወደ መጨረሻ
የሰሙት የቤት እመቤት የሆኑት ወ/ሮ አልፍሬድ ዊንድ
ሚለርና ነርሷ ወ/ት ጁዲ ዲክቶን አሳዛኙና አስደንጋጩ
የእሪታ ጩኸት ከተሰማበት ማዶ ከሚገኘው ቤት እየተ
ሯሯጡ ደረሱ ።

እነርሱም "እግዚኦ ፈጣሪ!ሁሉም አልቀዋል ... ሁሉ
ንም ገድሎአቸዋል . . " አሉ ። እኚሁ ሴቶች በደቡብ ቺ
ካጐ የሕዝብ ሆስፒታል አጠገብ ለነርሶች መኖሪያ በሚያ

ገለግለው ሕንጻ መስኮት ውጭ በሁለተኛው ፎቅ ግድግዳ
ላይ በአደገኛ ሁኔታ እንዷት ዞማ ጥቁር ጸጉር ያላት ቀጭን
ወጣት ልጅ ተንጠልጥላ አዩ ። ወ/ት ዲክቶን በጭንቀት
ላይ የነበረችውን የዚችኑ ልጅ ማንነት ለመለየት ጊዜ አል
ወሰደባትም ። የ23 ዓመቷ ወጣት ኮራዞን ፒይዞ አሙራወ
ነበረች ። ወጪቷም ለወ/ት ዲክቶን ባለችበት የጭንቀት
ሁኔታና ቦታ ላይ እንዳለች “ ሁሉም አልቋል ! . . . በሕይ
ወት ያለሁት እኔ ብቻ ነኝ ! . . . ” በማለት በድንጋጤ በተ
ረበሸ አንደበቷ አሰማች ።

ወ/ሮ ዊንድሚለርም ልጅቷ በጭንቀት ተንጠልጥላ
ወዳለችበት አደገኛ ጠርዝ እየተሯሯጡ “ እንዳትዘሊ . . .
ወደ ውስጥ ግቢና በደረጃው ተጠቅመሽ ነይ ! . . . “ በማ
ለት ጮሁ ። ወ/ት አሙራወ ግን ባለችበት ግድግዳ ላይ እን
ዳለች ” በድን ሆና ቀረች ።

በዚሁ ሁኔታ ላይ ወ/ት ዲክቶን በሕንጻው ምድር ቤት
በሚገኝ አንድ መኖሪያ ክፍል መስኮት አድርጋ ለመግባት
አንገቷን ብቅ አደረገች ። ባየችውም የሚዘገንን ሁኔታ ሰው
ነቷ ተረበሸ ። ርቃኑን የቀረ የአንዲት ልጃገረድ ሰውነት
በመከዳው ተዘቅዝቆ ተጋድሟል ።

ወ/ት ዲክቶንም የነርሶቹ ሞግዚት ወደሆኑት ወደወ
ይዘሮ ላውራ ቢሶኔ ቤት በድንጋጤ እየሮጠች ሄዳ ለፖሊስ
በስልክ ሁኔታውን አሳወቀች ። በዚያ የስልክ ጥሪም ፈጥኖ
የደረሰው የመጀመሪያው የፖሊስ መኩንን የከተማ
ሮንድ ጥበቃ ቡድን አባል ዳኒኤል አር ኬሊ ነበር ። ወ/ት
ዲክቶንና ወ/ሮ ዊንድሚለርም ስለ ሰሙትና ስለአዩት ሁ
ኔታ በጥቂቱ አስረዱት ። ኬሊም ከሞት አፋፍ የተረፈችው
ወጣት ከህንጻው ውጭ በጭንቀት በአስጊ ሁኔታ በፍርሀት
ተንጠልጥላ ተመለከተ ። በሬድዮ ርዳታ ለማግኘት ጥሪ ያደ



ረገበትን ያህል ቆየት ካለ በኋላ ከፓትሮል መኪናው ዘሎ
በመውጣት “ እዚያው ቆይ ! ወደ ውስጥ ገብቼ እረዳሻለ
ሁ ! ” በማለት ወ/ት አሙራወ ካለችበት እንድትቆይ ጮህ
ብሎ አሳወቀ ።

ኬሊ ፊት ለፊት ወደአለው በር ሲሄድ ተቆልፎ አገ
ኘው ፣ ሆኖም በሕንጻው በስተጀርባ በኩል ሲዞር በኋላ በ
ኩል ያለው በር ተከፍቶ ያገኘዋል ። የምድር ቤቱም መስ
ኮት የሸቦ ወንፊት ተዘንጥሎ መስኮቱ መከፈቱንም አረጋ
ገጠ ። ሽጉጡንም መዞ በሕንጻው ወደሚገኘው ቤት
ገባ ፣ በቅድሚያ ወደ ኩሽናው ገባ ፣ ምንም የተለዩ ነገር
አላየም ። በዕቃ ማጠቢያው ላይ የቆሸሹ ሳህኖችና ብርጭ
ቆዎች ተከምረዋል ፣ ባንኮኒው ላይም አንድ ከረጢት ቆሻሻ
ተቀምጧል ፣ በሌላ በር አድርጎም ወደ ሳሎን ገባ ። በወ
ለሉ ላይ የተለያዩ ወረቀቶች ፣ መጻሕፍትና የግል ንብረቶች
የሆኑ ዕቃዎች ተበታትነዋል ፣ ከዚህ በኋላ ትኩረቱን የሳ
በው በግራ በኩል ያለው ክፍል ሲሆን ወ/ት ዲክቶን በመ
ስኮት በኩል ያየችው የአንዲት ርቃኗን የተተወች ሴት ሰ
ውነት በሁለት ብርቱካናማ የብርኩማ ትራስ ላይ እንደ
ተጋደመ ተመለከተ ። ኬሊም የወጣቷን ሴት ሁኔታ መረ
መረ ፣ በሰውነቷ ምንም ዓይነት ምልክት የለም ፣ ሆኖም
የአንገቷ ዙሪያ በብጫቂ ነጭ ጨርቅ ጠበቅ ብሎ ታስሯል።
ፊቷንም ሲመለከት እጅግ ደነገጠ ። እንዳጋጣሚ ግሯን
ከማግባቱ በፊት በወዳጅነት ያውቃት ስለነበር ከነቤተ
ሰቧ መኖሪያዋን ሁሉ የሚያውቀው ሆኖ ተገኘ ።

የሆኖ ሆኖ ወ/ት ዶቪ — ታንቃ ሞታለች ። በሁኔታው
ኬሊ ተረብሾና ተደናግጦ እያለ ፣ ወ/ት አሙራው እንዳት
ዘል የሚወተውት ለርሱ እንግዳ ያልሆነ ድምጽ ሰማ ። ር
ሱም ከኬሊ በኋላ የደረሰው የተዘዋዋሪ ጥበቃ ፖሊስ ሊወ
ናርድ ጂ. ፖጊ ነበር ። ኬሊም ሽጉጡን ደግ ኖ እንደያዘ የፊት




“ የክፍለ ዘመኑ ወንጀል ” በመባል የታወቀውን የግድያ ወንጀል እንዲመረምር ኃላፊነት የተሰጠው መርማሪ የ፶/አለቃ ጆን — ሙርታህ ፡ /ዴቪድ ዳክሰን /።



ለፊቱን በር ከከፈተ በኋላ “ ሄይ —ፖኒ ! ልጃገረድዋን እንቆ ገድሏታል ፣ ምናልባት ገዳይ በሕንፃው ውስጥ ሊኖር ስለሚችል ሕንፃውን እንድንፈትሽ ወደ ውስጥ ግባ ” ብሎ ጮኸ ።

ፖኒም ሽጉጡን አውጥቶ የምድር ቤቱን ሲያስስ ኬሊ ወደ ሁለተኛው ፎቅ የሚያስወጡትን ደረጃዎች በመውጣት ያስስ ጀመረ ። ፖኒ ምንም ነገር አላገኘም ፣ ኬሊ ግን ሌላ ተጨማሪ ሁኔታ ገጠመው ፣ ደረጃውን እንደጨረሰ ከመታጠቢያ ቤት ወደ አዳራሽ ብቅ ያሉ እግሮች አየ ። እኒህም የአንዲት ሙታንታ ብቻ የለበሰች ወጣት ሴት ነበሩ ። ጡቷና አንገቷ በአሰቃቂ ሁኔታ ተተልትሎ ሞታለች ።

ኬሊ ከነበረበት በስተቀኝ የተከፈተውም በር ፊትለፊት ወዳለው መኝታ ቤት እንዲያመራ አደረገው ፣ በሚያስፈራና በሚያስቅቅ ሁኔታ ወደ ውስጥ እንደገባም ሁለት በወለሉ ላይ አንድ በአልጋው ላይ በጠቅላላው የሦስት ልጃገረዶች አስከሬን በሚዘገንን ሁኔታ ተጋድሟል ። በወለሉ ላይ ከተዘረሩት ወጣት ሚች ልጃገረዶች መካከል አንዷ ታፍና የሞተችና የእጅ አንጓዋም ጥፍር ብሎ ታስሮ ነበር ። በአንገቷም ላይ የተጠመጠመው ብጫቂ ጨርቅ የተገኘ ሲሆን ይህም ምናልባት ከአንሶላው ላይ የተቀደደ ጨርቅ ሳይሆን እንደማይቀር ገመተ ። በአንገቷም ላይ በውግ የሚፈጠር ቁስል ታይቷል ። ሬሣውም ከሌላዋ ተጐጂ ሬሣ ላይ በከፊል ተጋድሟል ። በወለሉ ላይ የወደቀው የሌላይቱ ሬሣ የእጅ አንጓ ወደኋሊት ተጠምዝዞ ታስሯል ፤ ተመሳሳይ በሆነ ዓይነት ጨርቅም ጉሮሮዋ ላይ ታስራለች። ኬሊ በአንገቷ ላይ በደረሰው የስንጢ ውጊያ ሳቢያ የተፈነጣጠቀ ደም በአንገቷ አካባቢ ለማዩት የቻለ ሲሆን የሕይወት ምልክት ግን ሊያገኝባት አልቻለም ። በአልጋው ላይ የተጋደመው ሶስተኛው ሬሳ እጅና እግሩ ተጣምሮ የታሰረ ሲሆን

ጉሮሮዋ ደግሞ ተቆርጧል ። በአሰቃቂ ሁኔታ የተገደሉት ሦስቱ ወጣት ሴቶች ሳይሞቱ ለብዙ ጊዜ ቆይተዋል ። የዚህም ማረጋገጫው ቀለማቸው ያልተቀየረ በመሆኑ ሲሆን እንዲያውም የአንደኛዋ ሟች ደም በመፍሰስ ላይም ነበር ።

ኬሊ ከዚህ አሰቃቂ እይታ በኋላ ከሕንጻው አስጊ ግድግዳ ላይ ተንጠልጥላ የነበረችውን ለማዳን ቢፈልግም ፊት ለፊት በሚገኘው መኝታ ቤት መስኮት በኩል ሊደረስባት እንደማይችል አረጋገጠ ። ሽጉጡን እንዳቀባበለና ጣቱንም ከምላጩ ላይ እንዳደረገ እንደገና ወደ አዳራሹ በመመለስ ወደ ሁለተኛው መኝታ ቤት ገባ ። እንደገና እጅግ በሚያስደነግጥ ሽብር ቀጥ አለ ፤ የሌሎች ሦስት ወጣት ሴቶች በሰንጢ የተዘለዘለና የተወጋ ሰውነት እንዳይሆን ሆኖ ተዘርሮ አገኘ ። የአንደኛዋ የእጅ አንጓ ታስሯል በአንገቷም ላይ ተተብትቧል ። የአንደኛዋ የግራ ጡት ምናልባት በሰንጢ ሳይሆን አይቀርም ተተልትሏል ። ከዚህ ሌላ ታንቃለች ፤ ሦስተኛ ተጉጂ ጀርባዋን ማጅራቷንና የግራ ዓይኗን ተወግታለች ።

ኬሊ ይህን ሁኔታ ቆሞ በሚመለከትበት ጊዜ ወ/ት አሙራወ በመኝታ ቤቱ መስኮት በኩል ባለው የሕንጸ ግድግዳ በፍርሃት ተረብሻ በአስጊ ሁኔታ እንደተነጠፈች ተመለከተ ።

ከዚህም በኋላ የ3ቱን ሬሣዎች ዳር ዳር በማስያዝ ወደ መስኮቱ ከተጠጋ በኋላ ከሕንፃው ግድግዳ ተንጠልጥላ በስቃይ ላይ የነበረችውን ወጣት ልጃገረድ ጐትቶ ወደ ክፍሉ ካስገባ በኋላ ወደ አዳራሹ እንድትሄድ አደረገ ።

“ ይህን ማን እንደፈጸመው ታውቂያለሽ?” አለ ኬሊ በስቃይና በጭንቅ ላይ የነበረችውን የፊሊፒኖ ልጃገረዷን “አንድ ሰው በርግጥም ማንነቱን አላውቀውም ጓደኞቼን






ይህ ፎቶግራፍ በነሐሴ 14 ስምንቱ የነርስ ተማሪዎች በቺካጐ ደቡብ አቅጣጫ በሚገኘው መኝታ ክፍላቸው በተገደሉበት ሰዓት የነበረውን ሁኔታ የሚያሳይ ነው ። /ዋይድ ወርልድ ፎቶ/

በሙሉ ፊጃቸው ” አለች ። ኬሊም “ ለመሆኑ ምን ይመ
ስል እንደሆነ ልትገልጭልኝ ትችያለሽ እስኪ ንገሪኝ?”
አለ። ፖሊሱ ያቺን በጭንቅ ላይ የነበረችና ከሞት አፋፍ
የተረፈች ልጃገረድ በተቻለ መጠን ቢታላቅ ትህትናና አቀ
ራረብ ለማነጋገር ጣረ ፤ በሁኔታዋም በማንኛውም ጊዜ ብ
ርክ ይዟት ልትወድቅ እንደምትችልና በትክክልም ልት
መልስ ለት እንደማትችል ገመተ ።

ወ/ት አሙራወ ትንፋሿ እየተቆራረጠ ነፍስ ገዳዩን
ለመግለጽ ሞከረች ፤ “ወጣት ሰው ነው ፡ ምናልባት 25 ዓመ
ት ይሆነዋል ፡ ክብደቱም 125 ፓውንድ ይሆናል ፀጉሩ በ
ጣም አጭር ነው ” አለች ፤ ቀለሙ ጠይም ወይም ነጣ ያለ
ጥቁር መሆኑን ለማስታወስ አልቻለችም ። ጠቆር ያለ ወገበ
ሰፊ ጃኬት የ“ ቲ ” ቅርጽ ከለበሰው ሸሚዝ ላይ ደርቧል፤
ሱሪውም ጠቆር ያለ ነው ። እባክህ ከዚህ አካባቢ ውሰ
ደኝ ስለርሱ የማስታውሰው ምንም ነገር የለኝ . . . ” በማ
ለት ወተወተች ።

ፖኒ ወ/ት አሙራወን እስከምድር ቤቱ አጅቦ ሲወስድ
የሮንድ ጥበቃው ፖሊስ ደግሞ በሁለተኛው ፎቅ ያሉትን
የተቀሩትን ክፍሎች መፈተሽ ጀመረ ። በዚሁ አከባቢ ካያ
ቸው ሰባት ሬሳዎችና በምድር ቤቱ ወለል ላይ ካየው ሌላ
ተጨማሪ ሬሳ ሊያገኝ አልቻለም ። በቺካጐ ታሪክ ተሰም
ቶም ታይቶም የማይታወቅ ፍጅት ይኸው ነበር ።

በርግጥ በዚህ የተናወጠ ከተማ ይህን መሰሉን ወን
ጀል ባይስተካከልም ተመሳሳይ ዓይነት ወንጀል ተፈጽሟ
ል ። በነርሶቹ መኖሪያ አከባቢ የደረሰው እልቂትና ፍጅት
ግን የተለየ ዓይነት ባህሪይ ያለው ወንጀል ሲሆን ይህም
ጥንታዊና የማይረባ የአውሬነት ጠባይ ዓይነት ሆኖ ተገ
ምቷል ።



ለዚህ ምርመራ ጉዳይ ኃላፊነት የተሰጠው መርማሪ
የፃ/አለቃ ጆን ሙርታህ በቺካጐ የፖሊስ ሠራዊት የ21 ዓ
መታት አገልግሎት ዘመኑ ከ1,000 የሚበልጥ የግድያ ወን
ጀሎችን መርምሯል ። የሆነ ሆኖ አንዳችም የዚህ መሰል
አሰቃቂ የግድያ ወንጀል ሁናቴ አልገጠመውም ።

“ ከማስታውሰው ድርብርብ በላይ የሚሆኑ የግድያ
ወንጀሎችን መርምሬአለሁ ፤ ነገር ግን አንድም የግድያ ወን
ጀል ይህን የሚስተካከል ወይም የሚቀርብ አልገጠመኝም፤
እስከ አራት ሰው የሞተበት ጉዳይ ገጥሞኛል ። ይኸውም
ሦስት ሰዎች ሲገድሉ አንደኛው ገዳይ ማለት ነው ። ይህም
ራሱን በራሱ አጥፍቷል ፡ ስምንት ነፍስ በአንድ ጊዜ
የጠፋበት የግድያ ወንጀል ግን አልገጠመኝም . . .”በማ
ለት የምርመራው ኃላፊ የሁኔታውን አሰቃቂነት ገልጧል።
ሙርታህ በዚህ ረገድ ስላለው ሁኔታም በበለጠ ሲያስ
ረዳ “ ያልተለመደ ፀጥ ያለና ሞቅ ያለ ምሽት ነበረ ። በሁ
ሉም አካባቢ በዚያ ምሽት ይህን ያህል እንቅስቃሴም ባለ
መኖሩ እኛም ብንሆን ቀልጣፎች አልነበርንም ። በርግጥ
ጥሪ ተደርጐልን ወንጀሉ በተፈፀመበት ቦታ የነበረው ፖ
ሊስ አምስት ሬሳ አለ አለን ። ቆይቶ ስድስት በመጨረሻም
ወደ አከባቢው በመጓዝ ላይ እንዳለሁ ስምንት አለን “ሙር
ታህ ምርመራውን በሚመለከት ጉዳይም ሲናገር “ በማን
ኛውም ዓይነት ምርመራ አንድ ሰው የሚረካበት ጉዳይ ሊገ
ጥመው ይችላል ። በዚህም የምርመራውን ውጤት ለማግ
ኘት በንቃትና በስሜት መጓዝ ይችላል ። በነዚህ ወጣቶች
ጉዳይ ያለው ምርመራ ጉዳይ ግን በጣም የተለየ ነው ። ምክ
ንያቱም በግል ሁላችንም የምናውቃቸውና ጥራት ያላቸው
ልጃገረዶች በመሆናቸው ነው ” ብሏል ።

መርታህ ከሁሉም ጋር በስልትና በጥበብ ለመቀራረብና ለመግባባት የሚችል ተግባቢ ሰው ቢሆንም በዚህ የአውሬነት ጠባይ በተላበሰ ወንጀል ጉዳይ ግን የተለየ ሆነ ። እንዲያውም ለዚህ ዓይነቱ እልቂት በር የከፈተው በፖሊስ በኩል በቅርቡ የታየው የልልነት ሁኔታ እንደሆነም ያምናል ።

በተጨማሪም በነፍስ ገዳይዎች ላይ በፍርድ የሚሰጠው ውሳኔ ተመጣጣኝ ያለመሆኑ ሕጉ ሕብረተሰቡን ሳይሆን ወንጀለኞችን የሚከላከልና የሚጠበቅ ይመስላል በሚል እማሯል ።

ይህ ከባድ የወንጀል ድርጊት በብሔራዊ ደረጃ አጠያያቂና አነጋጋሪ ጉዳይ ሆነ ። የፍጅቱም ሁኔታ በቴሌቪዥን ፣ በሬዲዮና በጋዜጦች በተለያዩ ርዕስ በመሰራጨቱ የሕዝቡ ትኩረት ከፍተኛ ብቻ ሳይሆን ወንጀለኛውን ለማወቅ ከፍተኛ ጉጉት አሳደረ ።

የአሁኑ ጥያቄ ግድያውን የፈጸመው ማነው ? የሚልም ከዚህ ሁሉ በላይ ነፍሰ ገዳዩ ለዘላለም ተደብቆ እንዳይቀር በምንም ዓይነት ከከተማው መውጣት የለበትም ነው ።

በምርመራው ክፍል በኩል የዚህ አስቃቂ ወንጀል ውጤት እስከሚታወቅበት ጊዜ ድረስ ማናቸውም ዓይነት ፈቃድ ተሰረዘ ።

በሁለተኛ የምርመራ ጣቢያ ዋና መምሪያ 60 የፖሊስ መርማሪዎች በዚያው ቀን ጧት በ2 ሰዓት ላይ በሥራ ላይ መሆናቸውን ሪፖርት እንዲያደርጉ ታዘዙ ። ሌሎች ስም



ንት የወንጀል ምርመራ ሠራተኞች ከሌላ እስኳድ (ተነጣይ ጓድ) ተመልምለው በመረጃ ሰጪነት ተሰማሩ ።

የሁለተኛው የምርመራ ጣቢያ ዋና መምሪያ ሁለተኛው ፎቅ ህንጻ ወለልና ሰፊው የስብሰባ አዳራሽ በአጭር ጊዜ ውስጥ የምርመራው የትዕዛዝ መስጫ ጣቢያ ሆኖ ተሰየመ ፤ ከሕዝቡና ከሌሎች አከባቢም ስለ ነፍሰ ገዳዩ የሚነገሩና የሚደርሱ ጠቃሚ ወሬዎችን ለማስተናገድ የሚችሉ ተጨማሪ ስልኮችም ገቡ ። በጠቅላላው ምርመራው በሰፊውና በጥልቀት ተያዘ ።

ልክ ከጧቱ 2 ሰዓት ማለትም የግድያው ወንጀል ሪፖርት ከደረሰ ሁለት ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ 140 የምርመራ ሠራዊት በስብሰባው አዳራሽ ተገኘ።ይህም ሠራዊት በ20 ቡድን ተከፍሎ ገሚሱ የደቡብ አቅጣጫን አሰሳ እንዲያካሂድ ተደረገ ፤ ሌሎች በርካታ ቡድኖችም ከከተማው ወሰን በመነሳት ወደ ሰሜን አቅጣጫ እንዲያስሱ ተደለደሉ ፤ ሌሎችም እንዲሁ በከተማው ምሥራቅ ምዕራብና ሰሜናዊ ምሥራቅ በስፋት አሰሳውን እንዲያካሄዱ ተደረገ ። አሰሳ የሚያካሂዱት የምርመራ ሠራተኞች መጠጥ ቤቶችን ፣ ምግብ ቤቶችን ፣ ሱቆችን ፣ የቲያትርና የሲኒማ ቤቶችን ፣ መኖሪያ ቤቶችን ፣ ሆቴሎችን ፣ የቤንዚን ማደያዎችንና ሌሎች ከነፍስ ገዳዩ ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል የተባሉትን ሁሉ እንዲያስሱ ታዘዙ ።

ከወ/ት አሙራው የተሰጠው የወንጀለኛው መግለጫም በአዳራሹ ለተሰበሰበው የምርመራ ሠራዊት ተበተነ ። በፖሊሱ የቴሌ ታይፕ መሳሪያም አማካይነት በመላው ዩናይትድ እስቴትስ ኦፍ አሜሪካ፣በካናዳና በሜክሲኮ ለሚገኙት የሕግ አስከባሪዎች ሁሉ የወንጀለኛው መረጃ ተላለፈ ። የተላለፈውም መረጃ የሚከተለው ነበር ።

" ተፈላጊ ወንድ ነጭ ፡ 6 ጫማ ፡ 170 ፓውንድ ፡ እጭር ጸጉር ፡ ወገቡ ሰፊ ፡ ጥቁር ኮት ጠቆር ያለ ሱሪ ወደ ኒው ኦርሊየንስ ለመሄድ ገንዘብ ይፈልጋል ። ምናልባት ሽጉጥ ወይም ጩቤ የታጠቀ ።"

የፃ/አለቃ ሙርታህም የምርመራውን ኃላፊነት በበላይነት ያዘ ። በዚህ ሁኔታም ላይ እንዳለ ቀደም ባሉ ደቂቃዎችና ሰዓት በርካታ መርማሪዎች በሥራ ላይ ነበሩ ። በሌላ በኩል ደግሞ የግድያውን ምክንያት ዶክተር እንድሪው ጂቶማንስ ከ6 ልዩ የሬሳ መርማሪዎች ጋር ወንጀሉ ከተፈጸመበት ቦታ ደረሱ ፡ ቶማን በተጨማሪም ግዙፍ የሆነውን የፖሊስ ተንቀሳቃሽ የወንጀል መመርመሪያ ላቦራቶር መሣሪያ ከፖሊስ ቴክኒሺያኖች ጋር ይዘዋል ። "

የቺካጐ ፖሊስ የወንጀል ላቮራቶሪ መምሪያ ሥራ አስኪያጅ ዳንኤል ቲ ድራግልና አሥር ቴክኒሺያኖቻቸውም ወንጀል በተፈጸመበት ቦታ ደርሰው ሥራቸውን ጀምረዋል ። በዚህም መሰረት ወንጀለኛው ወንጀሉን በሚፈጸምበት ወቅት ሊተወው ከሚችለው ሌሎች ማስረጃዎች ሌላ በደርዘን የሚቆጠሩ በአቧራ የተደፈኑ የጣት አሻራዎችን ፈልገው አግኝተዋል ።

የሟች ወጣት ነርስ ተማሪዎችን ማንነት ለመለየት የሚችለው የሆስፒታሉ ሠራተኛ የወጣቶቹን ማንነት አጠቃላይ ሁኔታና ጠባይ የቤተሰባቸውን አቋም ሳይቀር አንድ በአንድ እየተመለከተ አረጋገጠ ። የፃ/አለቃ ሙርታህና ሁለቱ ረዳት መርማሪዎችም በዚሁ መሰረት የሟች ነርስ ተማሪዎችን ስምና አጠቃላይ ሁኔታ ከሆስፒታሉ ቅጥጥ ሠራተኛ ጋር ሬሳው በወደቀበት አካባቢ እየተዘዋወሩ መዘገቡ ።

የሆስፒታሉ ሠራተኛ በመጨረሻ እይታው እራሱን እየነቀነቀ " ታመምኩ ከዚህ በላይ ማየት አልችልም "



አለ ። ሆኖም የሠራተኞቹን ማንነት የማረጋገጥ ኃላፊነት ስላለበት ጭንቁንና አሰቃቂ ሁኔታውን እምቆ " ሜሪ አን ጆርዳን ናት " አለ ። ይችኛዋ የ20 ዓመቷ ኮረዳ የነርስ ትምህርት ቤት ትምህርቷን የምትከታተለው እንደሌሎች በትምህርት ቤቱ በማደር ሳይሆን ከቤተሰቦቿ ጋር በመኖር ነበር ፡ ሆኖም በዚያን ወቅት በአዳሪው ት/ቤት የመታጠቢያ ክፍል ወለል ላይ ሬሳዋ ተዘርሮ ከተገኘው ከጓደኛዋ ከሱዛኔ ፋሪስ ጋር ለማሳለፍ ፈቃድ ከቤተሰቦቿ ወስዳ ነበር ። በሁለቱ ልጃገረዶች መካከል ያለው ወዳጅነት ከጓደኝነት ደረጃ የበለጠ ከፍተኛ ሲሆን የሜሪ ጆርዳን ወንድምም ሲዛን ፋሪስን ለማግባት እጭቷት ነበር ።

አንድ ጋዜጠኛ የዚያን አሰቃቂ ሁኔታ ሲገልጽ " በጫማዎችህ ደም ሳትረግጥ እንዳችም ቦታ መራመድ አይቻልም ነበር " ብሏል ።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ የሟቾች ማንነት አንድ በአንድ ከተረጋገጠና ከተመዘገበ በኋላ የሚቀጥለው ማስረጃ የመሰብሰቡ ርምጃ ቀጠለ ። የግድያውን ምክንያት የሚለየው የባለሙያተኞች ፤ ቡድን እያንዳንዱን ሬሳ መመርመር ጀመረ ። ይህ ቡድን ምን ዓይነት ጠበንጃ እኒያን ሸጋ ልጃገረዶች እንደፈጀ ለማወቅ ይቻል ዘንድ በአደጋው ምክንያት የተፈጠረውን ቁስል ሁሉ መረመረ ። በሥራ አስኪያጅ ድራግል የተመራው የወንጀል ላቮራቶሪ ቴክኒሺያን ቡድን ኤክስፐርትም ምናልባት ሟቾቹ ልጃገረዶች ከነፍሰ ገዳዩ ትንቅንቅ ገጥመው እንደሆነ የሰውነት ቆዳ ቅራፊ ወይም የሰውነት ጸጉር በሟቾቹ የጥፍር ጣት ላይ ወይም በአካባቢው እንዳለ መፈለግ ጀመረ ።

የሆነ ሆኖ ከላይ የተጠቀሰውን ዓይነት የፖሊስ ኤክስፐርቶች ምርመራ በስፋት ቢካሄድም ኮራዞን አሙራወ

ከሰጠችው የዓይን ምስክርነት የተሻለ ምንም ዓይነት የምርመራ ማስረጃ ሊገኝ አልተቻለም ። የ፶ አለቃ ሙርታህም ከኮማንደር ፍላናጋን ጋር በመሆን ወደ ወይዘሮ ቢሶን ቤት ከተወሰደችው ከዓይን ምስክር ሰጪዋ ከወ/ት አሙራወ ጋር ተጨማሪ ጥያቄዎችን ለማቅረብ ሄዱ ። ወይዘሪትዋም በደቡብ ቺካጎ የሕዝብ ሆስፒታል ሀኪሞች ትዕዛዝ የእንቅልፍ መድሃኒት ወስዳ ነበር ፤ ሐኪሞቹ እንደገመቱት ምንም እንኳን አሙራወ በነፍስ ገዳዩ ባትጎዳም በእንሶላ ቅዳጅ ራሷን ለመከላከል ትታገል ስለነበር በእጅ አንጓዋ አካባቢ የቡጭሪያ ምልክት ነበረባት ፤ ወጣቷም “ የማውቀውን ነገር ሁሉ እነግራችኋለሁ . . . እርግጥ አብዛኛውን ጊዜ ያሳለፍኩት ራሴን በመደበቅ በመሆኑ ሁሉንም ነገር አላየሁም ፤ ያየሁትን ግን እናገራለሁ . . . ” አለች ።

ከዚህ በኋላም ለሙርታህና ለሌላው መርማሪ ሁኔታውን በዝርዝር ተናገረች ። ከርሷም ለመረዳት እንደተቻለው ሮቡዕ ማታ ከምሽቱ አምስት ሰዓት ላይ ለመተኛት አሙራወ አልጋዋን ስታነጣጥፍ ፤ ስድስት ልጃገረዶች ከላይኛው ፎቅ ላይ ነበሩ ። ፊት ለፊት በቀኝ በኩል ባለው የመኝታ ክፍል ፓትሪሺያ ማቱሲክ ፣ ፓሜላ ዊልኬንግ ፤ ኒና ሽሜልና ቫሌንቲና ፓስዮን እየሳቁ ያወሩ ነበር ። አሙራወ ደግሞ በቤቱ በስተጀርባ ባለችው አነስተኛ ክፍል ነበረች ። ልብሷንም እየለወጠች ከጓደኛዋና ከመኝታ ክፍል ባልደረባዋ ጋር በመጫወት ላይ እንዳለች መርሊታ ጋርጉሎ ከሆስፒታል የተረኛነት ሥራዋ በመምጣት ደረሰች ።

በድንገትም በስተጀርባ ያለው በር ተንኳኳ ፤ ወ/ት አሙራወ “ ማነህ ! ” በማለት ወደ ምድር ቤት ሄደች ።



አሙራወ ምናልባት ከጓደኞቿ መካከል አንደኛዋ ቁልፏን የረሳች ልጃገረድ ተመልሳ የመጣች መስሏት ነበር ። ሆኖም በሩን ስትከፍት አንድ ረጅም ወጣት ሰው በግራ እጁ ጩቤ በቀኝ እጁ ሽጉጥ ይዞ እንደ ቆሞ አየች ።

ወዲያውኑም “ እኔ አልጐዳሽም ወደኒውኦርሌየንስ መሄጃ ገንዘብ ብቻ ነው የምፈልገው! ” አላት ። ወ/ት አሙራወም በፍርሃት ወደኋላ ዞራ ስትሮጥ በመጋቢያው በኩል ዘሎ አቋርጦ በሩን እየዘጋ “ እኔ አልጐዳሽም ገንዘብሽን ብቻ ነው የምፈልገው! ” በማለት በድጋሚ ተናገረ ።

ከዚህ በመቀጠል ወ/ት አሙራወን ተከትሎ በኩሽና ቤትና በሳሎን አድርጎ ወደ መኝታ ክፍሎች የሚያመራውን ደረጃ ይዞ ወጣ ።

አሙራወ ልብ ያለችውን ነገር እንዳስታወሰችው “ ስለርሱ የማስታውሰው የመጀመሪያ ነገር ቢኖር ኃይለኛ የአልኮል ሽታውን ነው ” ብላለች ።

ደረጃው ጫፍ እንደደረሰም ነፍሰ ገዳዩ ወ/ት አሙራወን በሽጉጡ እያስፈራራ ጋርጉሎ ከተኛችበት ትንሽ መኝታ ቤት እንገቱን ገባ አድርጎ “ ከዚህ ውጭ! ” ብሎ አዘዘ ፤ እሷም በፍርሃት ወጣች ።

ሁለቱን የፊሊፒኖ ልጃገረዶችም “ወደታች ! ” ብሎ እየመራ የአራት ልጃገረዶችን ጨዋታ ወደሰማበት ፊት ለፊት ወደሚገኘው መኝታ ቤት በመውሰድ ቀላቀላቸው ። በዚያ ክፍል የነበሩት ልጃገረዶችም በፍርሃት ተውጠው በመንቀጥቀጥ ላይ እንዳሉ በቁጣ ድምጽ “ ሁልሽም ፊትሽን ወደወለሉ ደፍተሽ ተኚ ! ” ብሎ አዘዘ ።

በሽጉጡና በሰንጢው የተደናገጡት ልጃገረዶችም በፍርሃት ትዕዛዙን ፈጸሙ ። ከተደራራቢው አልጋ ከታችኛው ላይ አንዱን እንሶላ ጉትቶ ካወጣ በኋላም በጩቤው፡ እስተካክሎ በእዋቂ የእተላተል ዓይነት ተለተለው። ከዚህ ቀጥሎም በዚሁ በተተለተለ እንሶላ እጃቸውን በማሰር የተጨቀለለ ጨርቅ አፋቸው ላይ ጠቀጠቀ ።

ከስድስቱቹ ልጃገረዶች በመጨረሻ ፓሲዮንን ሊያስር ምድር ቤት የግሎሪያጂን ደ ቪ ድምጽ ተሰማ ። ዴቪ ከነበራት ቀጠሮ በሰላም መመለሷን ለሞግዚታቸው ለወ/ሮ ቡሶን እያሳወቀች ነበር ። በትምህርት ቤቱ ሕግ መሰረት እያንዳንዷ ልጃገረድ ለዕረፍት ወጥታ ከተመለሰች በኋላ ለሞግዚቷ ማሳወቅ አለባት ። በዚህ መሰረት የሞግዚቷ ሪኮርድ እንደሚያመለክተው ዴቪ ለሞግዚቷ የደወለችው ከምሽቱ 5 ሰዓት ከ20 ደቂቃ ላይ ነበር ።

ዴቪ በሰላም የነበራትን ቀጠሮ አጠናቃ መመለሷን በስልክ ለሞግዚቷ ከነገረች በኋላ ወደመኝታ ክፍሏ ለመሄድ የሁለተኛውን ፎቅ ደረጃ እንደጨረሰች ሽጉጥና ሰንጢ የደገነው ሰው ገጠማት ፣ እርሱም እንደተለመደው በቁጣ ወደ ክፍሉ ውስጥ እንድትገባና ከሌሎች ጐን ከወለሉ ላይ እንድትተኛ ካደረገ በኋላ እጅዋን ጥፍር አርጐ አሰረ ።

ከዚህ በኋላ ልጃገረዶቹን ማነጋገር ጀመረ ፣ ድምፁ የሚማርክና ዝግ ያለ ነበር " እኔ እናንተን ለመጉዳት አልመጣሁም " እያለ በመናገር ላይ እንዳለ የፊት



ለፊቱ በር ተከፈተ ፣ የመጡትም ሱዛኒ ፋሪስና የወደፊት ምራቷ ሜሪ አንጆርዳን ነበሩ ።

እነዚያው ሁለት ልጃገረዶች በሁለተኛው ፎቅ የነበረውን የተለዩ ሁኔታ ባለማወቃቸው ወደኩሽና ቤቱ በማምራት ለሞግዚቷ ደወሉ ። ከዚያም በኋላ ተመልሰው በግራ በኩል ወዳለው መኝታ ቤት ገቡ ፣ በዚያን ጊዜ ሁሉ ጓደኞቻቸው በሚቀጥለው ክፍል ሰንጢ ተደግኖባቸው በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን አያውቁም ነበር ።

ወ/ት አሙራወ እንደምትለው " ሁላችንም ለመንቀሳቀስም ሆነ ድምጽ ለማሰማት ከመጠን በላይ ፈርተን ነበር ፤ ከዚያ በኋላ ሁለቱን ልጃገረዶች አስገድዶ አምጥቶ ሌሎቹን እንዳደረገው አስሮ እንዲተኙ አደረገ ፣ ሊመጨረሻዎቹም ሁለት ልጃገረዶች ይኸው ወጣት ሰው ምርኮኞቹን እንደማይጐዳ አረጋገጠ ። ምንም እንኳን ያ ቃል ኪዳን የልጃገረዶቹን ጭንቀት ባያቃልም ትንሽ እፎይታ ሰጥቷቸው ነበር ። " ካለች በኋላ " የምፈልገው ነገር ቢኖር ገንዘብ ብቻ ነው ። ወደ ኒው እርሊየንስ ለመሄድ የግድ ገንዘብ ያስፈልገኛል " በማለት መወትወቱን አስረድታለች ።

ሌሎቹ ልጃገረዶች የገዳዩን ዓላማና አቅጣጫ ይወቁ አይወቁ ባይታወቅም ወ/ት አሙራወ ግን የምታውቀው አልነበረም ። በሁኔታው በድን ሆና ነበር ፣ የርሷም ሃሳብና ትኩረት ለማምለጥ መሞከር ብቻ የነበረ ቢሆንም እንዴት አድርጋ ታምልጠው ? ገዳዩ ሁሉንም አስሮ ከጨረሰ ከግማሽ ሰዓት በኋላ የቤቱን ዕቃ ምስቅልቅሉን ማውጣት ጀመረ ። ወ/ት አሙራወም ካንዱ ክፍል ወደ

ሌላው ክፍል እየተዘዋወረ ሲያተራምስ ሰማችው ፣ ከዚያም በኋላ ተመልሶ መጥቶ "በጄ! ሁላችሁንም ከዚህ እወስዳችኋለሁ" አለ ።

ባዶ እግራቸውን እንዲቀመጡም ካደረገ በኋላ ልጃገረዶቹን በስተጀርባ በምትገኘው አነስተኛ መኝታ ክፍል አጅቦ አስገባ ፣ ከዚያም እንደተለመደው በወለሉ ላይ ተኝተው በፊታቸው እንዲደፉ አደረገ ። ከዚያ በኋላ ወ/ት ዱቪን ከክፍሉ አስወጣ ፣ ወ/ት አሙራወ ከእንቅስቃሴው ለመገመት እንደቻላቸው ይዟት የሄደው ወደ ምድር ቤት ነበር ።

ከ25 ደቂቃ በኋላ እንደገ' መጥቶ ወ/ት ፓስዮንን ይዞ ወጣ ፣ በዚያ ሁኔታ አሙራወ የእያንዳንዱ ሴት ሕይወት በአስጊ ሁኔታ ላይ እንዳለ አመነች ፣ ሌሎችን የምትረዳበት ምንም ዓይነት አማራጭ ባይኖርም ራሷን ለማዳን አንድ ነገር ማድረግ እንደምትችል ገመተች ። የሁለት እጆቿ አንጓ ግጥም ብለው ቢታሰሩም በወለሉ ላይ በመንከባለልና በድርብርቡ አልጋ ጠርዝ ላይ በማፋተግ ለመፍታት ቻለች ። ከዚያ በኋላ በተቻላት መጠን በአልጋው ሥር አድርጋ ከግድግዳው ጋር ተጠግታ ከእይታ ተሰወረች ።

ገዳዩም ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሌላ ልጃገረድ ከክፍሉ ለማስወጣት መጣ፤ አሙራወ በዚያን ጊዜ ከእይታ ተደብቃ ስለነበር የትኛዋን ልጃገረድ እንደወሰደ አላወቀችም ፣ እስኪወጣም ድረስ ትንፋሿን ውጣ ተደበቀች ። ምንም እንኳን እስከዚያ የተወሰዱት ልጃገረዶች ምንም ዓይነት ድምጽ ባያሰሙም አንድ አሰቃቂ ነገር በመፈጸም ላይ እንዳለ ግን አሙራወ ገምታ ነበር ።



በዚያ ዓይነት መመላለስ ብዙ ጊዜ ቢያሳልፍም አንዳችም ድምጽ እንዲያውም ትንፋሽ እንኳ አሙራወ አላሰማችም ነበር ። ከዚያ በኋላ ሰውየው ወደዚያ ልጃገረዶቹን እየለቀመ ወደሚወስድበት ክፍል መምጣቱን አቆመ ። ሆኖም በሚቀጥለው ክፍል በሚገኘው የማንቂያ ሰዓት ደወል እስከሚሰማበት ጊዜ ድረስ ካለችበት ቦታ ለመንቀሳቀስ አልደፈረችም ። የሰዓቱ ደወል ከንጋቱ 11 ሰዓት መሆኑን አረጋገጠላት ። ደወሉ ዘወትር ከንጋቱ 11 ሰዓት ላይ የሚሰማ ሲሆን ይህም በ12 ሰዓት ወደ ሆስፒታል ሪፖርት ማድረግ የሚገባቸውን የተማሪ ነርሶች ለመቀስቀስ ነበር ። ደወሉ በሚደውልበት ጊዜ አሙራወ የደወሉን ድምጽ ሽፋን በማድረግ በእጅ አንጓዋ ላይ የተተበተበውን የአንሶላ ቁራጭ ጨርቅ በፍጥነት ለማላቀቅ ተጠቀመችበት ፣ ከዚያ በኋላ ለሌላ ግማሽ ሰዓት በተደበቀችበት ቦታ ሆና ያለአንዳች እንቅስቃሴ አሳለፈች ፣ ከዚያም እየተሳበች ለመውጣት የምትችል መሆኑን አረጋገጠች ።

ፖሊስ እንደገመተው ነፍሰ ገዳዩ ሕይወቷን ያተረፈችውን ልጃገረድ ሳይገድላት የቀረው በቤቱ ውስጥ ስንት ልጃገረዶች እንዳሉ ባለማወቁ ወይም ሊገድላቸው ያመቻቸውን ልጃገረዶች ፈጽሞውኑ ባለመቁጠሩ ነበር ።

አሙራወ በእግር ጥፍሮቿ በመጠቀም በዝግታና በጥንቃቄ ወደ አዳራሹ ስትገባ የወ/ት ፋሪስ እግሮች ከመታጠቢያ ክፍሉ ተዘርረው በማዩቷ በማምለጥ ላይ እንዳለች ብርክ ያዛት ፣ አሙራወ ሁኔታውን ለምትነግራቸው መርማሪዎች ማለትም ለሙርታህና ለኮማንደር ፍላናጋን "ሱዛኒ መሞቷን ካየሁ በኋላ ሌሎቹም እንዳልተረፉ ለማረጋገጥ ችያለሁ" ብላለች ።

አሙራወ የባሰ ድንጋጤና ሽብር የደረሰባት ፊት ለፊት ባለው የመኝታ ክፍል 3 በስተቀኝ፣ ሦስት በስተግራ በጠቅላላው 6 የልጃገረዶችን ሬሳ ባዬች ጊዜ ነበር ። በዚያም ሁኔታ ከመጠን በላይ ተረበሸች፣ በመጨረሻ ባሉት ሦስት ሬሳዎች ላይ ዘላ የፊት ለፊቱን የመስተዋት ሽቦ ወደፊት በመንደል ሁለት ሜማ ስፋት ባለው የሕንጻ ግድግዳ ታዛ ላይ ተለጠፈች ። ከዚያ ታዛ ላይ በሽብር ላይ ሁናና ተንጠልጥላ ባሰማችው ጩኸት የቺካጐ የክፍለ ዘመኑ ወንጀል በመባል የታወቀው የወንጀል ድርጊት ለዓለም ሕዝብ ተዳረሰ ።

ወንጀለኛውን በቁጥጥር ሥር ለማዋል በስፋት የተያዘው አሰሳ በመካሄድ ላይ እንዳለ፣ በሟቾቹ ነርሶች መኖሪያ ቤት መሠረታዊ የሆኑ የቴክኒክ ማስረጃዎች እንዲሰባሰቡ ኃላፊነት የተሰጣቸው መርማሪዎች ያገኙትን ፍንጭ ሪፖርት ማድረግ ጀመሩ ። በዚያ መሠረት በየመኝታ ክፍሎችወንጀለኛው ያተራመሰውና በተለያዩ ልብሶችና ቁሳቁሶች ወለሉን ያዝረከረከው ምናልባት ገንዘብ ለመፈለግ ሲል ያደረገው እንጂ ከተጐጂዎቹ ጋር በተደረገ ትንቅንቅ ምክንያት ያለመሆኑ ተረጋገጠ ። የአንዳቸውም ልጃገረዶች የልብስ ኪስም ሆነ ቦርሳ ምንም ፍራንክ አልተገኘበትም፣ ምን ያህል ገንዘብ ከእያንዳንዳቸው ላይ እንደተወሰደ ባይረጋገጥም የአሙራወ ቦርሳ 31 ዶላር ይዞ እንደነበርና በኋላ ግን ምንም እንደሌለው አረጋግጣለች ።

የመጀመሪያውን የበድን አካል ምርመራ ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ ላይ ሆኖ እንዲመረምር ኃላፊነት የተሰጠው በዶክተር ቶማን የተመራው የሬሳ ምርመራ ቡድን እያንዳንዷ ልጃገረድ እንዴት እንደተገደለች አረጋገጠ ። በዚያም መሠረት በአብዛኛው የሞቱ ምክንያት በሰንጢ ውጊያ ሳቢያ ሲሆን የሌሎች ደግሞ በውጊያና በመታነቅ ሆኖ



ተገኝቷል ። ከሟቾች ነርሶች መካከል በመታነቅ ብቻ ያለ ውጊያ የሞተችው ዶቪ ብቻ ነበረች ። ኃኪሞች በተጨማሪ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሙከራ ተደርጐ እንደሆነ በእያንዳንዷ ልጃገረድ ብልት ላይ ያለውን ፈሳሽ መረመሩ፣ ሆኖም በዚያ በኩል ማስረጃ አልተገኘም ።

በሬሣው ምርመራ ላይ ልዩ ጠቃሚ ፍንጭ የተገኘው ነፍስ ገዳዩ የገደላቸውን ሴቶች በአንሶላ ቅዳጅ ሲያስራቸው የተጠቀመበት የአስተሳሰሰር አይነትና ቋጠሮ ነበር ።

ሁሉም ቋጠሮች(እስሮች) ጥሩ ዓይነት አራት ማዕዘን ሲሆኑ ማንም በቀላሉ ሊፈታቸው የማይችል ነበሩ ። ይህም እጃቸውን ወደኋላ በቀኝ በመጠምዘዝ የእጅ መዳፋቸውን አንድ አቅጣጫ እንዲይዝ በማድረግ ሲሆን ልክ ፖሊስ እስረኞችን እንደሚያስረው ዓይነት እስተሳሰር ነበር ። ምናልባት በዚያ ዓይነት አስተሳሰር ቀደም ሲል ታስሮ የነበረ ወይም የገመድ ማሰር ልምድ ሳይኖረው እንደማይቀር ተገምቷል ። የዚያ ልዩና አንድ ዓይነት የገመድ አስተሳሰር ቋጠሮ ሁኔታ ምናልባት ነፍሰ ገዳዩ መርከበኛ ሊሆን እንደሚችልም አስገምቶታል ። በዚያም ሳቢያ ምርመራውን በተወሰነ አቅጣጫ እንዲያተኩሩበት ሆነ ። ወንጀሉም ከተፈጸመበት ብዙ በማይርቅ ቦታ አንድ የብሔራዊ መርከብ መቅጠሪያ ተቋም ስለሚገኝ በዚያው ክትትልና ትኩረት ተደረገ ።

ያ ሁኔታ ታውቆ ብዙ ሳይቆይ በሙርታህ መሪነት አንድ ቡድን ተቋቁሞ ወደዚያው የባህርተኛ መቅጠሪያ ተቋም ጉዞውን ጀመረ ። በጉዞአቸውም ላይ ከአንድ በኢንዲያና ስቴት መስመር በሚገኝ የቤንዚን ማደያ ጣቢያ በማቆም፣ ለቤንዚን ማደያው ባለቤት ስለ ወንጀለኛው ገለጻ በማድረግ ምናልባት በአካባቢው ሲተላለፍ አይቶት

እንደሆን ጠየቁት ። ርሱም ማክሰኞ ከሰዓት በኋላ የተባለውን ሰው የሚመስል ያየ መሆኑን፣ ሰውየውም ቡናማ የበረራ ሻንጣና አነስተኛ ቡናማ ሌላ ማህደር መያዙን ፣ ለርሱም ሥራ ፍለጋ ወደ ኢንዲያና እንደሚሄድ ቢነግረውም ወደዚያ አለመሄዱንና ፣ እንደገናም መጥቶ ማረፊያ ቦታ ይፈልግ እንደነበር ገለጸላቸው ።

የቤንዚን ማደያው ባለቤት የሰውየውን ሁኔታ በተጨማሪ ሲገልፁ ያው ወጣት ሰው በጣም ለፍላፊ፣ ለስላሳ ድምፅ የነበረውና በደቡብ የአነጋገር ስልት የሚናገር መሆኑን ገልጾ ያው ሰው እሁድ ምሽቱን በሚችጋን ሐይቅ ዳርቻ ማንጋቱን ፣ ሰኞ ምሽት ደግሞ በዚሁ አካባቢ የማረፊያ ቤት ይዞ ማሳለፉን ፣ ሆኖም ማክሰኞ ዕለት ከኢንዲያና ሲመለስ መኝታ ክፍሉ ለሌላ ተከራይቶ ተይዞበት ስለነበር ሻንጣዎቹን እንዲያቆዩለት ጠይቆ በዚያው መሰረት ያቆየለት መሆኑንና በማግሥቱ እንደገና ተመልሶ መጥቶ በመርከበኞች ቅጥር ግቢ አንድ የሚከራይ ክፍል በማግኘቱ ዕቃዎቹን እንደወሰደ ተናገረ ።

መርማሪዎቹም ወደ ተባለው እንግዶችና መርከበኞች የሚያርፉበት ቅጥር ግቢ ሄደው የተፈላጊውን መግለጫ ለጸሐፊው በመንገር ጠየቁ ። ፀሐፊውም የተባለውን ዓይነት መግለጫ የሚያሟላ ግለሰብ በርግጥ አንድ ክፍል ለአንድ ሳምንት በ9 ዶላር ተከራይቶ ካረፈ በኋላ ሐሙስ ዕለት ጧት በድንገት መሄዱን ፣ በቺካጐም ከአንድ እህቱ ጋር የስልክ ግንኙነት ያደርግ እንደነበረ በተጨማሪ ተናገረ ።

ከዚህ በኋላ መርማሪዎቹ ወደብሔራዊ መርከብ መቅጠሪያ ተቋም ሄደው የተፈላጊውን መግለጫ በመንገር ጠየቁ ። የተባለው ዓይነት ሰው ሰኞ ዕለት ሥራ



ፍለጋ መምጣቱንና ወደ ኒውኦርሊየንስ በሚመላለሰው መርከብ ላይ ለመሥራት ጉጉት እንዳደረበት ሆኖም የሠራተኛ ቅጥር ኃላፊው ወደዚያ መስመር ምንም ሥራ እንደሌለና በሌላ መስመር በሚመላለስ ጀልባ ግን ሊሞክርለት እንደሚችል መንገሩን፣ ማክሰኞለትም ትንሽ ዘግይቶ ስለመጣ ሌላ ሰው መቀጠሩን ፣ ረቡዕም እንዲመጣ ተገልጾለት እንደገና መምጣቱንና በዚያም ዕለት የሠራተኛ ቅጥር ኃላፊው ሊመድበው ያለመቻሉን ተረዱ ።

በተጨማሪም እንደምንም ሥራ ሊገኝለት ስለሚችል እየተመላለሰ እንዲጠይቅና ችሎታውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲያቀርብ የተገለጸለት መሆኑ ተነገራቸው ። መርማሪዎቹም ማመልከቻው እንዲቀርብላቸው ጠይቀው ቀረበላቸው ። የተገኘውም መረጃ የሚከተለው ነበር ።

ሥራ ፈላጊ ሪቻርድ ኤፍ እስፔክ፣ ዕድሜ 25 ፣ ቁመት 6 ጫማ ፣ ክብደት 170 ፓውንድ ፣ የፀጉር ቀለም ቡናማ ከዚህም ሁሉ ሌላ አነስተኛ የፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶግራፍ ቀርቧል ።

ሙርታህና ረዳቱ በዚህ በቂ መረጃ በመርካት ወደ ሁለተኛ የምርመራ ጣቢያ ፈጥነው በመሄድ ያገኙትን አርኪ ውጤት በሪፖርት አቀረቡ ። የፖሊስ የፎቶግራፍ ላቦራቶርም አንድ ሰዓት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ የተጠርጣሪውን ፎቶግራፍ አባዙ ፣ ከቀኑ 8 ሰዓት ላይም በደቡብ አቅጣጫ በአሰሳና በክትትል ላይ የሚገኘው የያንዳንዱ ቡድን የተጠርጣሪው ፎቶግራፍ ታድሎት በዚያው መሠረት ፍለጋውን እንዲያጧጡፍ ተደረገ ።

ወዲያውኑም ሥራ ወደጠየቀበት የመርከበኞች ተቋም ሲመለስ ለማጥመድ እንዲቻል ጥንቃቄን የሚጠይቅ እቅድ ወጣ። በሌላ በኩል ደግሞ በማዕከላዊው የፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ በሚገኘው ዘመናዊ የኤሌክትሮኒክስ የወንጀለኞች ሪኮርድ መመዝገቢያ መዝገብ ቤት የሪቻርድ እስፔክስ ስምና ፎቶግራፍ ተላለፈ ፡ ሆኖም መሣሪያው ምንም ዓይነት ምልክት አላሳዩም ፡ ይህም እስፔክ በቺካጎ የፖሊስ ሪኮርድ የሌለው መሆኑን የሚያመለክት ነበር ።

የመርከበኞች ቅጥር ግቢና የተጠርጣሪው እህት ቤትምበዓይነ ቁራኛ ይጠበቁ ጀመር ። በርግጥ ከዚያ እከባቢ ሌላ ፖሊሶች ተጠርጣሪው ሊገኝ የሚችልበትን አካባቢ የማወቂያ መንገድ አልነበራቸውም ፡ ምክንያቱም ካለምንም ሪኮርድና ፋይል ተፈላጊው ለፖሊስ እንግዳ ስለነበረ ነው ። ሙርታህ በበኩሉ እስፔክስ በርግጥ የስምንት ልጃገረዶች ነፍስ ገዳይ ከሆነ በአስቸኳይ መያዝ እንዳለበትና ያን ያህል ነፍስ ያጠፋ ሰው ደግሞ ያለጥርጥር ሌላ ሕይወት ከማጥፋት እንደማይቆጠብ አረጋገጠ ።

በሙርታህ የሚመራውም የምርመራ ቡድን እንደገና ወደ ብሔራዊው የመርከብ መቅጠሪያ ተቋም ሄደ።መርማሪዎቹም ጃኬታቸውንና ከረባታቸውን አውልቀው ሸሚዛቸውን ሰቀሰቁ፣ በዚያ ዓይነት ሁኔታም ራሳቸውን በመለወጥ የዚያው የብሔራዊ መርከብ መቅጠሪያ ተቋም የቅጥር ተወካይ መስለው እስፔክስ እንደገና ሥራ ፍለጋ ሲመለስ ለመያዝ ወሰኑ ።

ከቀኑ 8 ሰዓት ተኩል ላይም መርማሪ ዊሎንስኪ ለወ/ሮ ማርታ ቶሮንቶን ደወለ ። ወ/ሮ ማርታ 38 ዓመታቸው ሲሆን በቺካጎ በአንድ የምድር ባቡር ላይ የሚሰሩ ግለሰብ ባለቤት ነበሩ። መርማሪውም የመ/ቤቱ ቀጣሪ በመምሰል ወንድማቸው የት እንደሚገኝ ጠየቀ ፡ እሳቸውም የት እንደሚገኝ ለማወቅ ያለመቻላቸውን በማስረዳታቸው መርማሪው ከገኙት ሥራ የተገኘለት በመሆኑ ወደ መቅጠሪያው ተቋም ስልክ እንዲደውል መልእክት አስተላለፈ ።



በ9 ሰዓት ከ10 ደቂቃ ላይ ወደ መቅጠሪያው ተቋም ስልክ ተደወለ ፡ ስልኩንም የመቅጠሪያ ተቋም ሠራተኛ የሆነ አንድ ግለሰብ አነሳ ።

“ ሥራ አገኛችሁልኝ ? ”

“ ማን ልበል ? ” አለ ስልኩን ያነሳው

“ ሪቻርድ . . . ሪቻርድ እስፔክ ” ስልኩን ያነሳውም ወደ ዊሎንስኪንና ወደ ሌሎች መርማሪዎች እያመለከተ “እዎ ወደ ሲንክሌር ታላቅ ኃይቆች ሥራ አገኝቼልሀለሁ፣ ለመሆኑ አሁን የት ነህ ? ” አለ ።

“ ወደታችኛው ከተማ ሩቴስ ላይ ነኝ ”

“ እዚህ ለመድረስ ምን ያህል ጊዜ ይፈጅብሃል ? ”

“ አንድ ሰዓት ያህል ይፈጅብኛል ”

ሙርታህ የተደረሰበትን መረጃ ለኮማንደር ፍላናጋን አሳወቀ ፡ 20 ተጨማሪ መርማሪዎችም ወደዚሁ ተቋም በመገስገስ ዙሪያውን ቁልፍ በሆኑ ቦታዎች ደፈጣ ይዘው ሁኔታውን ይከታተሉ ጀመር ።

የተደረገው ደፈጣና ጥበቃ ግን ፍሬ አልባ ሆኖ ቀረ። እስፔክ ተመልሶ አልመጣም ፡ ስልክ ካነሳው ግለሰብ ጋር ሲነጋገር ጥርጣሬ (ሥጋት ) አድሮበት ወይም በጀልባ ላይ መኝታ ክፍል ለማግኘት የማይቻል በመሆኑ ይሁን በሌላ በማይታወቅ ሁኔታ ሳይመጣ ቀረ ።

ያም ሆነ ይህ ሙርታህና የቡድኑ አባላት ከጥቂት
መርከበኞች ጋር ሌላ ጠቃሚ መረጃዎችን አሰባሰቡ ።
ከመርከበኞቹ መካከል ጥቂቶቹ እስቴክን አስታወሱ ፤ አን
ደኛው ሰኞ ጧት በአንዷት ሴት አሽከርካሪነት በመኪና
ከዚያው ከመርከበኞች ግቢ እንደደረሰ ያየው መሆኑን
አረጋገጠ ፤ ሌላው ደግሞ ከአዳራሹ ሲመለስ ማዬቱን ተና
ገረ ፤ መረጃ አቀባዩ ደግሞ ተጠርጣሪው ከዚሁ ቅጥር ግቢ
ከተነሳ በኋላ በክራንዶን አውራ ጐዳና አድርጐ ወደ ሎይላ
መናፈሻ ከሄደ በኋላ ከአንድ አግዳሚ መቀመጫ ላይ
ተቀምጦ ፀሐይ እየሞቀ ሕጻናት በኾርዋኾርዌና በሚዛን ሲጫ
ወቱ ሲመለከት ማዬቱን ተናገረ ።

በዚያ ተጠርጣሪው በተቀመጠበት አግዳሚ ወንበር
ላይ በመሆን ስምንቱ ልጃገረዶች ሕይወታቸውን ያጡ
በት ቤትም ያለአንዳች ችግር ይታያል ።

ሌሎች ምስክሮችም እንዲሁ የእስቴክን እንቅስቃሴ
የሚገልጹ መረጃዎችን ሰጥተዋል ። በዚህ መሰረት ከነበ
ረበት የመናፈሻ ቦታ በቀጥታ ወደ መቅጠሪያው ተቋም
ሄዷል ። እዚያም ለርሱ የሚሆን መርከብ ያልተገኘለት
መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ቦርሳዎቹን እንዲያስቀምጥ ወደፈ
ቀደለት ወደ ቤንዚን ማደያው ባለቤት በመሄድ ፓው
ላይንስ ወደተባለ መናኛ ሠፈር መኝታ ፍለጋ ሄዶ በማ
ጣቱ በረንዳ ላይ ተኝቶ አሳልፏል ።

ረቡዕ ጧት ፓውላይንስ ከተባለው ሰፈር ወደ
መርከበኞች ግቢ ተመለሰ ። እዚያም መኝታ ክፍል
በማገኘቱ ወደ ቤንዚን ማደያው ሄዶ ዕቃዎቹን ከሰበ
ሰበ በኋላ መኝታ ወደ አገኘበት ክፍል በመግባት ዕቃዎ
ቹን ካስቀመጠ በኋላ ከሆቴል ቤቱ ምድር ቤት ቀኑን
በሙሉ በመጠጣት አሳልፏል ።



የተቆራረጡ መረጃዎች በማሰባሰብ ከእሁድ ማታ
እስከ ሮብ ከሰዓት በኋላ ድረስ የነበረውን የእስቴክን ተከ
ታታይ እንቅስቃሴ ያገጣጠመው ፖሊስ ወደ በኋላ የነ
በረውን ፈለግ ለማገጣጠም ችግር ገጠመው ። ያም ቁራ
ጭ የእንቅስቃሴ ጊዜ ጠቃሚው ጊዜ ሲሆን ይኸውም በል
ጃገረዶቹ ላይ የደረሰው ፍጅት ከመድረሱ ጥቂት ሰዓታት
በፊትና የግድያው ጊዜ ነበር ።

የሆነ ሆኖ ሙርታህና ረዳቶቹ ተጠርጣሪውን ነፍሰ
ገዳይ ማለትም እስቴክን ሐሙስ ልክ ከንጋቱ አንድ ሰዓት
ማለትም ግድያው ከታወቀበት ልክ ከአንድ ሰዓት በኋላ
ያዩትን ሰዎች አገኙ ። በዚያን ጊዜ ነርሶቹ በተገደሉበት
ሕንጻ አካባቢ ከሚገኝ አንድ መጠጥ ቤት ታይቷል ፤ ይህ
ንኑ ሁኔታ ያየው ምስክር ከአራት ወር በፊት እስቴክን
ተገናኝቶት የነበረ አንድ የ22 ዓመት የቀን ሠራተኛ ኪርክ
ላንድ የተባለ ወጣት ሲሆን ርሱም እንደተናገረው “ እየ
ጠጣን እናወጋ ነበር ፤ ርሱም ዊስኪና ቢራ ይጠጣ ነበር ፤
አንድ ሰንጢም አወጣ ፤ ስለጩቤውም እንደነገረኝ በመ
ርከበኝነት ይሰራ ስለነበረ በመርከብ ጉዞ ላይ እንዳለ ከፊ
ትናም እንደገዛው ነግሮኛል ፤ ጩቤው ቢያንስ 12 ኢንች
ርዝማኔ ስለት አለው ። ይሸጠው እንደነበረም ጠይ
ቄው ፈቃደኛ በመሆኑ በአንድ ዶላር ገዝቸዋለሁ ”
ብሏል ።

መርማሪዎቹም ጩቤውን ኪርክላንድ እንዲያመ
ጣው ጠይቀውት ወደ ክፍሉ ሄዶ ይዞት መጣ፤ ጩቤውም
ወደ ፖሊስ ላቦራቶር ተላከ ።

ከዚያ ሁሉ ሌላ የዚያው መጠጥ ቤት ባለቤት እስቴ
ክ በመጠጥ ቤቱ ሐሙስ ከሰዓት በፊት ሲያደርግ የነ
በረውን እንቅስቃሴና ሁኔታ ያስታውስ እንደሆን ተጠይቆ

በሚከተለው ሁኔታ በዝርዝር አስረዳ ። “ ይኸው ሰው ንግግሩን የጀመረው ጩቤውን በማስመልከት ነበር ። ከዚያም በመጠጥ ቤቱ እየተዘዋወረና እየቀለደ ለሌሎች የመጠጥ ቤቱ ደንበኞች መጠጥ ይጋብዝ ነበር ። በዚያ ሁኔታም ወደስምንት ዶላር አጥፍቷል ። በመሃሉም በድንገት መጠጥ ቤቱ ውስጥ ጩቤውን መዞ አውጥቶ በኔ ፊት ለፊት ከተራመደ በኋላ በአንድ እጁ አንገቴን አፈፍ ካደረገ በኋላ የጩቤውን ስለት በጉሮሮዬ አቅጣጫ አደረገ ፣ እንደሁኔታው እንዴት ሰውን መግደል እንደሚቻል ለማሳየት ነበር ። እንዲያውም እንደማስታውሰው “ይህ ጩቤ ብዙ ሰው ገድሏል . . . . ለዚህ ነው አንተን መግደል የፈለግሁት ” በማለት መናገሩን ገልጿል ።

በዚያን ምዕራፍ ላይ ቀደም ሲል እስቴክን የሚያውቀውና ከአንድ ጀልባም ላይ አብሮት ሲሰራ የነበረ ሰው መጣ ፤ ከዚያም በኋላ ሁለት ዶላር ከሰውየው ተበድሮ ከመጠጥ ቤቱ ተያይዘው ወጡ ። መርማሪዎቹም እስቴክ የሚያውቀውንና ከመጠጥ ቤቱ አብሮት የወጣውን ሰው ፈልገው ካገኙ በኋላ ከመጠጥ ቤቱ ድርጊት በኋላ የተፈጸመውን ሁኔታ ተረድተዋል ። ይኸው ሰው እንደተናገረውም “ ከዚህ በኋላ ሶስት ወይም አራት መጠጥ ቤቶች አዳርሰናል፤ በአንደኛው መጠጥ ቤት እንዳለን ስለግድያው ዜና ሰማን እስቴክም ይህን የፈጸመው በሽተኛ መሆን አለበት ” አለኝ ብሏል ።

የመጨረሻውን መጠጥ ቤት ከለቀቁ በኋላም እስቴክ በመርከበኞች ግቢ ያለውን ሁኔታ አጣርቶ በታክሲ አከባቢውን ለቋል ። ይህም ሐሙስ ከጧቱ አንድ ሰዓት ከአርባ አምስት ደቂቃ ላይ ነበር ።

ከዚያ ነጥብ በኋላ የእስቴክ ዱካ እንደገና ጠፋባቸው ። ፖሊስም የነበረው አማራጭ ተጠርጣሪውን ባለታክሲ ለማ



ግኘት ሙከራ ማድረግ ነበር ። ዓርብ ጧት ያ ጠንካራ መንፈስና ጥረት ውጤት አስገኘ ። ሙርታህ ባደረገው ክትትል ታክሲ ነጂውን አግኝቶ ጠቃሚ መረጃ ሰበሰበ ። ታክሲ ነጂውም ተሳፋሪውን በሰሜን ሴጂ ዊክ አውራ ጐዳና 1300 ብሎክ ድረስ አድርሶት ተሳፋሪውም 5 ዶላር ከ90 ሳንቲም ከፍሎት የተለየው መሆኑን አስረዳ ።

ፖሊስም የተፈላጊውን መግለጫ በመንገር ከታክሲው የወረደበትን ሠፈር ማሰስና ማፈላለግ ተያያዘው ። ወዲያውኑ በዚሁ አካባቢ የሚኖሩትን ወ/ሮ ጆ-ሆላንድን አገኘ ። ርሳቸውም የሚከተለውን ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው መረጃ ሰጡ ።

ወ/ሮ ጆ-ሆላንድ ሐሙስ ጧት ከሁለት ሰዓት በፊት በመስኮታቸው ላይ ተቀምጠው ስለነፍስ ገዳዩ የራድዮ መጽሔት እያደመጡ በመመልከቻ መነጽር መንገዱን ያስሱ ነበር ፣ በዚሁ የርቀት መሳሪያ መነጽራቸው በመመልከት ላይ እንዳሉ በስሜን ሴጂዊክ አውራ ጐዳና 1300 ብሎክ ላይ አንድ ታክሲ ቆመ፤ ረጅም ነጣ ያለ ወጣትም ከሁለት ሻንጣዎቹ ጋር ወርዶ ለባለታክሲው ከከፈለ በኋላ ወደ ስሜን ሴጂዊክ አውራ ጐዳና 1200 ብሎክ ተመለሰ ፣ ከዚያም ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ በመራመድ ላይ እንዳለ በርቀት ማሳያ መነጽር በደቡብ በኩል አድርጐ ወደ ዲርቦርን አውራ ጐዳና እስኪደርስ ድረስና ለእይታ እስኪሰወር ድረስ ማየታቸውን ገለጹ ።

ወ/ሮ ሆላንድ ከዚህም ሌላ በርቀት ከዚሁ ሰው ሰውነት ያዩትን ነገር አስረድተዋል። ይኸውም ክንዱ ላይ የተነቀሰውን ንቅሳት ሲሆን በርቀት ማሳያ መነጽራቸውም በቀላሉና በግልጽ ሊያነቡት እንደቻሉ አስታወሱ ። ንቅሳ

ቱም “ BORN TO RAISE HELL ” የሚል ነበር ።

ፖሊሶቹ ባለንቅሳቱ ሪቻርድ እስፔክ ነው የሚለው
ትንሽ አጠራጥሯቸው ነበር ። የሆነ ሆኖ የዚያ ንቅሳትና
ልዩ ምልክት ሁኔታ ከእስፔክ የግል ማህደር ላይ መስፈሩ
ተረጋገጠ ።

ምንም እንኳን ወ/ሮ ሆላንድ በርቀት ማሳያ መነጽራ
ቸው እስፔክን ካዩት 24 ሰዓት ቢያልፍም ሙርታህና የቅ
ርብ አለቃው መ/አለቃ ማካርቴ በዚሁ በዲርቦርን አውራ
ጐዳና ወይም በክላርክ ጐዳና ከሚገኙት ሆቴሎች ባንደ
ኛው የመኝታ ክፍል ሊገኝ እንደሚችል ገመቱ ። በዚ
ህም መሠረት በአካባቢው በሚገኙ ሆቴሎች በመዘዋወር
በየክፍሉ እስፔክን የሚያድን የምርመራ ቡድን አሰማሩ ።

በሥምሪቱም እስፔክን ለማግኘት በአንድ በኩል
የተቃረበ መረጃ ሲደርስ በሌላ በኩል ደግሞ እስፔክን ለማ
ግኘት የሚደረገው ርምጃ እየተፋጠነ መሄዱ ተጠቆመ ።
በሌላ በኩል ደግሞ በደቡብ ቺካጐ የሕዝብ ሆስፒ
ታል እንድታርፍ የተደረገችውና ከሞት አፋፍ የተረፈ
ችው ኮራዞን አሙራወ አገግማ ስለነበር የሪቻርድ እስፔ
ክን ፎቶግራፍ ከሌሎች ፎቶግራፎች ጋር እንድትመለከትና
ስምንቱን ነርሶች የፈጀው ሰው መሆኑና አለመሆኑን እን
ድታረጋግጥ ተጠየቀች ። አሙራወ የመጨረሻውን ፎቶግ
ራፍ እንደተመለከተች፣ “ ይህ!” ብላ ከጮኸች በኋላ” ይህ
ሰው ነው ! ” በማለት አረጋገጠች ፤ ቀጥሎም “ እርግጠኛ
ነሽ?” ተባለች እርስዋም “እዎ ይህ ርሱ ነው !” በማለት
ርግጠኛ መሆኗን ደጋግማ መሰከረች ።

በዚያ ሁኔታ ዓርብ ከቀኑ ሰባት ሰዓት ደረሰ ። በዲር
ቦርንና በክላርክ ጐዳናዎች አካባቢ የተሰማራው የምርመራ
ቡድንም የደረሰበትን ደረጃ ሁሉ ማጉረፍ ጀመረ ።



ከዚያና ከመሳሰሉት መረጃዎች ሊደረስበት እንደቻ
ለው ተጠርጣሪው በቺካጐ ከተማ መናኛ የሴተኛ አዳ
ሪና መሸታ ቤት ማለትም ሰዎች በየሸንት ቤቱና በቡና
ቤት ወለሎች በጩቤ እየተዋጉ በደም በሚዋዥቡበት ፤
ሴተኛ አዳሪዎች ወንዶችን በሚያስገድዱበት ፤ የሐሺሽ
ሱሰኞች በክንዳቸው በመርፌ በይፋ ሐሺሽ በሚወስዱበት፣
ጆሮ በጥስ ሙዚቃ በሚንጣጣበትና ምድረ ጠጪ በሚያው
ካካበት መናኛ ሠፈር እንዳለ ተረጋገጠ ።

ነገር ግን የት ? የሚለው የመጨረሻው የፖሊስ ጥያቄ
አልተመለሰም ነበር ። በዚያው መናኛ ሠፈር ቀደም ሲል
የታወቀ የመደነሻ ቤት የነበረ ተራ ሰከራሞችና የትም
አዳሪዎች የሚፏልሉበት ጠመዝማዛ መዝናኛ ክፍል ያለው
መጠጥ ቤት ውስጥ ሊኖር እንደሚችል በተገመተው መሠ
ረት አንዱ የሙርታህ መርማሪ የመጠጥ ቤቱን ባለቤት
ጠየቀ ። ርሱም “ በርግጥ የተባለው ሰው እዚህ ነበር ፤ በእ
ውነት ሰውየው ፍጹም ተግባቢ ነው ፤ አብዛኛውን ምሽት
ከቁማር መጫዎቻዎቹ ሳጥን አጠገብ ቁሞ ካርታ እየተጫ
ወተ ይጠጣ ነበር ። አንድም ሰው ሲያስቸግር አላየሁም ፤
ላስታውሰው የቻልኩት በነጭ ሹራቡ ነው ፤ ነጩን
ሹራብ ከላይ ለብሷል ፣ ሹራቡም ቀይና ሰማያዊ መስ
መሮች አሉት ” በማለት አረጋገጠ ።

ከዚያ በኋላ የመጠጥ ቤቱ ባለቤት ወደየት እንደሄደ
እንዲናገር በመርማሪው ፖሊስ ተጠየቀ ፤ ምሽቱ ግርግርና
ሥራ የበዛበት ስለነበር ፤ ጥቂት እንደማሰብ ብሎ ጥቂት
ደንበኞቹ በብርማው የመጠጡ በርሜል በጀርባ በኩል
ባለው ግድግዳ ጥግ ተቀምጠው እንደነበር ፊት ለፊት የነበ
ሩት ጠረጴዛዎች ደግሞ ጢቅ ብለው በጠቅላላው ሁሉም
እንዳሻው ያወራና ያስካካ ስለነበር ምንም ነገር ለማስታ

ወስ የማይችልበት ምሽት እንደነበር እየተናገረ በድንገት እንድ ነገር ትውስ አለው “ እህ ! ይህ ፎቶግራፉን የምታሳየኝ ሰው ዛሬ ጧት ልክ 2 ሰዓት ላይ ከነጋባቸው ሴቶች እንድዋ ጋር ይጫወት ነበር ፣ ስሟም ሜሪ ይባላል ፡ አንዳንድ ጊዜ ራሷን ሲልቪያ ወይም ቶሚ ብላ ትሰይማለች ። በማንኛውም ስም ትጠራ በየትኛውም ጊዜ ትገኛለች ። በግምት ከቀኑ 9 ሰዓት ላይ እስፔክና ይህቺው ልጃገረድ ከዚህ አካባቢ ሄደዋል ” በማለት አረጋገጠ ።

ይህን መረጃ ሙርታህና የምርመራ ሠራተኞቹ ከመጠጥ ቤቱ ባለንብረት የሰሙት ዓርብ ከሰዓት በኋላ ነበር ። ሜሪ ወይም ሲልቪያ ወይም በማንኛውም ከምትጠራ ከእስፔክ ጋር የወጣችውን ልጃገረድ ለማግኘት በመቻሉ ረገድ ምንም ችግር አልነበረም ። መርማሪው ወደምትገኝበት ክፍል በመሄድ በቀላሉ ካገኛት በኋላ የምታውቀውን እንድታስረዳ ጠየቃት ። ርሷም “አንድ ሰዓት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ከኔ ጋር ነበር ፣ በጣም ርካሽና ተራ ሰው ነው ፡ የከፈለኝ ሶስት ዶላር ብቻ ነው ” በማለት አስረዳች ። ከዚያ በኋላ ግን ያው ሰው የት እንደቆየ ምንም የምታውቀው ነገር የሌለ ሲሆን ርሱ ግን እዚሁ አካባቢ ቢራ ፍለጋ የሚመጣ መሆኑንና እንደገና እንደሚያገኛትም እንደነገራት አስታውሳለች ።

የሆነ ሆኖ መርማሪው በዚያው አካባቢ ክትትሉን በመቀጠል ላይ እንዳለ የተፈላጊውን ፎቶግራፍ የተመለከተ እንደኛው የቡና ቤት ሠራተኛ ተፈላጊው ካንዲት መካከለኛ ዕድሜ ካላት ጥቁር ሴተኛ አዳሪ ጋር ተያይዞ ከቡና ቤቱ መውጣቱን የተከታተለ መሆኑን ገለጸ ።

የቡና ቤቱ ሠራተኛም የተባለችውን ሴተኛ አዳሪ የሚያውቃት ቢሆንም መርማሪው ግን በቀላሉ ሊያገኛት



አልቻለም ። ሆኖም በመጨረሻ ተገኝታ በሰጠችው ቃል ተፈላጊው ጋር በርግጥ ከቡና ቤቱ ተገናኝተው እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት አብረው ከተዝናኑ በኋላ አምስት ዶላር ከፍሏት የተለያዩ መሆኑን አረጋገጠች ።

በዚህ ረገድ በተደረገው ምርመራ በአካባቢው በሚገኝና ራሌ ሆቴል በመባል በታወቀው ሆቴል ውስጥ መዝናናታቸውንና ለሆቴሉም አስተናጋጅ (መዝጋቢ) ተጠርጣሪው በክፍሉ ውስጥ ሽጉጥ እንዳስቀመጠ ሴተኛ አዳሪዋ ማመልከቷን ተገነዘበ ።

መርማሪውም በአካባቢው በመሆን ለተሰማራውና ለሚጠባበቀው የተሽከርካሪ ትዕዛዝ መስጫ ጣቢያ ኀድ አመለከተ ፣ በሌሎችም አካባቢዎች የተሰማሩት መርማሪዎች በአካባቢው በመሆን ርምጃውን በንቃት እንዲጠባበቁ ጥሪ ተደረገላቸው ።

ሙርታህም ባለ 6 ፎቅና የሶስተኛ ደረጃነት ባለው ራሌ ሆቴል አመራ ። የሆቴሉ አስተናጋጅም በሆቴሉ ያረፉትን እንግዶች ሊስት አንድ በአንድ በማገላበጥ መረመረ ፣ ጮህ ብሎም “ ይኸውላችሁ ” ብሎ የእስፔክን ስም አመለከተ ፡ እስፔክም ሐሙስ ጧት በ3 ሰዓት ተመዝግቦ የሳምንት የአልጋ ኪራዩን የከፈለበት ሊስት ተገኘ ።

“ ከሰላሳ ደቂቃ በፊት ጀምሮ እዚሁ ነበር ፣ ከዚህ በኋላ አንድ የተጠቀለለ ነገር ይዞ ወደ ልብስ ማጠቢያ ቤት ሄድዋል ፣” ተብሎም ለመርማሪዎቹ ተነገረ ።

ሙርታህም በራሌ ሆቴል ፊት ለፊት በሚገኙት አውራ ጐዳናዎችና በሌሎችም በርካታ የሆቴሉ አካባቢዎች የምርመራ ሠራተኞች ቡድን አሰማራ ። በዚያ መሥረት እንደኛው የምርመራ ቡድን እስፔክ ወደተከራየበት

ክፍል አምርቶ በሁለት ተራ ሻንጣዎች የታጨቁትን የእስ ቴክ የግል ንብረቶች ሲፈትሽ ከሌሎች ንብረቶች ሌላ ወ/ት አሙራወ ነፍስ ገዳዩ ለብሶት ነበር ብላ ያመለከተቻቸው ጨርቆች ማለትም ጥቁር ጃኬት ፣ ጥቁር መታንቲ የ"ቪ" ቅርጽ ያለው ሸሚዝና ሌሎችም የተገኙ ሲሆን ሁሉም በቅርቡ በላውንደሪ የታጠቡ ነበሩ ።

በሌላ በኩል ደግሞ ሙርታህና ሌሎች ረዳት መርማሪዎች የእስቴክን ተመልሶ መምጣት ይጠባበቁ ጀመር ።

ይህ ሁሉ በመሆን ላይ እንዳለ እስቴክ በባህርተኛነት ሥራ ለማገልገል ያመለከተበት ደብዳቤ በዋሽንግተን ለሚገኘው የፌዴራል ምርመራ ቢሮ ተላልፎ ኖሮ ስለእስቴክ በቂና የሚያስገርሙ መረጃዎች መጉረፍ ጀመሩ።

በፌደራሉ ቢሮ ምርመራ የእስቴክ ፋይል እንደሚያመለክተው ፤ እስቴክ በዳላስቴክሳስ ይኖር ከነበረበት ከ16 ዓመቱ ጊዜ አንስቶ በፖሊሶች ዘንድ የታወቀና ረዥም የስቃይ ዘመን ያሳለፈ፣ለብዙ ጊዜ የተፈረደበትና የተለቀቀ ወንጀለኛ መሆኑን አስረድቷል ። ሪኮርዱ እንዳመለከተው በቅርብ ጊዜ ይኸው ሰው የፈጸመው በ1963 በዳላስ በሰነድ የማጭበርበር ወንጀል ሲሆን በዚያም ወንጀል በአገሩ የመጨረሻ የደህንነት እስር ቤት ለ3 ዓመታት ታስሯል ።

ጥር 1965 ከእሥር ቤት ከተለቀቀ በኋላ በአንዲት ሴት ላይ በፈጸመው ከባድ የድብደባና በጩቤ የማስፈራራት ወንጀል እንደገና ተከሷል ።

አባትየው ገና እስቴክ ታዳጊ ወጣት በነበረበት ጊዜ የሞቱ በመሆኑ እናቱ ከተወለደበት ከሞንማውዝ ኤልኖይስ ወደዳላስ እንዲኖር ወሰዱት ፣የእስቴክ ፋይል በትላልቅ



ባህር መርከቦች ላይ በመርከበኛነት የተቀጠረ መሆኑን የሚያንጸባርቅ ሲሆን በዚህ ረገድ የተመዘገቡት ሁሉ በአጭሩ የተቀነባበሩ ነበሩ ።

የቺካጎ ፖሊስ ያለ የሌለ ኃይሉን አስማርቶ እንዳለና የሪቻርድ እስቴክን ዱካ የመከታተሉ ኃላፊነት የተሰጣቸው መርማሪዎች እንቅልፋቸውን አጥተው በመናወጥ ከፍተኛ ጥረት በሚያደርጉበት ጊዜ ወንጀለኛውን ለማግኘት ሲባል በተፈጠረው ግርግር መሃል አንድ ከባድ ስህተት ተፈጸመ ።

በመሠረቱ በየትኛውም አካባቢና ቦታ የሚገኝ ፖሊስ ሰብዓዊነትን የሚከተል መሆን አለበት ። ፖሊሶች በቺካጎ " የክፍለ ዘመኑን ወንጀል " ዓይነት እጅግ የሚያሳዝን የወንጀል ድርጊት ከተፈጸመ በኋላ ጽኑ ቁጣንና ግንፍልታን ከማሳየት ይልቅ በአጠያያቂ ጉዳይዎች ላይ የኀሊና ፍርድ ለመስጠት የሚያስችሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ በትዕግሥትና በንቁ ስሜት ጉዳዩን መከታተል ይኖርባቸዋል።

ነገር ግን ዓርብ ማለዳው ላይ ሪቻርድ እስቴክ ከራሌ ሆቴል ሲወጣ በአንድ ፖሊስ ጥያቄ ቀርቦለት እንደ ነበር የሚገልጽ አስፈሪና አስደ ንጋጭ ሪፖርት ተሰማ ። ሁኔታውም እንዲህ ነበር ፤ በዚያን ዓርብ ዕለት ከጧቱ 12 ሰዓት ላይ እስቴክ ወደ ሆቴሉ አልተመለሰም ነበር ። አንድ የፖሊስ መ/አለቃ የሆቴል ቤቱን እንግዳ ተቀባይ እስቴክ የት ሊገኝ እንደሚችል የሚያውቅ ሰው እንዳለ ይጠይቃል ። የሆቴል ቤቱ እንግዳ ተቀባይም ፖሊሶች ለምን እስቴክን ለማግኘት ከፍተኛ ጉጉት እንዳደረባቸው በመገረም " ፖሊሱ የሚፈለግበትን የሆቴል ቤት ወጭ በሙሉ ዘግቷል " በማለት ለመ/አለቃው ይነግረዋል ፤ መ/አለቃው በመገረምና በመደናገጥ

"የምን ፖሊስ ስለ ምንድ ነው ለመሆኑ የምታወራው?" በማለት ይጠይቃል ።

እንግዳ ተቀባዩም ሁኔታውን በዝግታ እንደሚከተለው ያብራራል " በጂ ሁኔታው እንዴት እንደሆነ እነግርሃለሁ ፤ ስለዚህ ቦታ ምናልባት የማታውቀው ሁኔታ ሊኖር ይችላል ። እኛ ይህን ሆቴል የምናካሂደው በጥንቃቄና በሕጋዊ መንገድ ነው ፣ ዛሬ ማለዳ ላይ ሴትየዋ ከእስፔክ መኝታ ቤት ስትወጣ ሰውዬው ሽጉጥ በክፍሉ ውስጥ እንዳለው ስትነግረኝ ምን እንዳደረግኩ ታውቃለህ ? ወዲያውኑ ፖሊስ ጠራሁ "

" የምን ፖሊስ ?"

" የቺካጐ አውራ ጐዳና ፖሊስ ጣቢያ "

" ከዚያ በኋላስ ምን ሆነ ? "

" ከዚያ በኋላማ በመኪና መጥተው ጥቂት ፖሊሶች ከዚሁ ሰው ጋር ተነጋገሩ "

የቺካጐ አውራ ጐዳና ፖሊስ ጣቢያም ሁኔታውን ያውቅ እንደነበረ ተጠየቀ ። ወዲያውም እንዲ ይህን በሚመለከት ሪፖርት መድረሱን አረጋገጠ ። በጥሪውም መሠረት አንድ የፖሊስ ቃኝ ጓድ ሁኔታውን እንዲያጣራ ተደረገ ። በዚያም መሠረት በደረሰው ሪፖርት ሰውየው በርግጥ የተባለው ሽጉጥ በክፍሉ ውስጥ እንዳለ አረጋገጠ ፣ ሽጉጡ ነጥብ 22 ካሊቨር የሆነና ከአንድ መረጃም እንደተነገረው ለባለሥልጣኖች የሚሰጥ ዓይነት መሆኑን ስድስት ጥይቶችም እንደጉረሰ ለቃኝ ጓድ ማስረከቡ ተረጋገጠ ።

እስፔክ ግን ሽጉጡም ሆነ ጥይቶቹ አብራው የነበረችው ሴት መሆናቸውን ተናግሯል ። መኰንኖቹ



ደግሞ ሽጉጡና ጥይቶቹ እንዲወረሱ አድርገው ዓርብ በ3 ሰዓት ላይ በፖሊስ ጣቢያው የንብረት መዝገብ እንዲመዘገብ አድርገዋል ።

" ለመሆኑ በሪፖርቱ ላይ የተመዘገበው ማን ይላል?" ተባሉ ። የፖሊስ ጣቢያ መዝጋቢዎችም " ሪቻርድ እስፔክ " ብለው መለሱ ።

ሙርታህም በ2ኛው ክልል ዕዝ ያሉትን የምርመራ ሠራተኞች በጥንቃቄና በንቃት እንዲጠባበቁ አደረገ ። በዚሁ ዕለት ከረፋዱ ጀምሮ የእስፔክ ስም ብቻ ሳይሆን ፎቶግራፉም ጭምር በከተማው በሚገኙ ቀበሌዎች ሁሉ መዳረስ ነበረበት ፣ የሆነ ሆኖ ምናልባት እስፔክ ተጠርጣሪው ሳይሆን ቢቀር በስም ማጥፋት ወንጀል ያስጠይቃል በሚል ስጋት የተፈላጊው ፎቶግራፍ እንዳይደርስ የተደረገው ለጥቂት መርማሪዎች ብቻ ነበር ።

የፖሊስ ቃኝ ጓዶች ለሥራ ከመሠማራታቸው በፊት የተፈላጊው ስም ቢነገራቸውና ፣ ፎቶግራፉም በየፖሊስ ጣቢያው የመረጃ ሰሌዳ ላይ ቢለጠፍ ኖሮ እያንዳንዱ የቺካጐ ፖሊስ ዓይን በሪቻርድ እስፔክ ላይ ባነጣጠረ ነበር ። በዚህ ፈንታ የሆነው ነገር ቢኖር ከአስራ ስምንት ሰአታት በኋላ ሁለት የፖሊስ ቃኚ ጓዶች ጠብመንጃቸውን ወድረው እየጮሁ በሩጫ ወደ እስፔክ ከሄዱ በኋላ ሽጉጡ የሴተኛ አዳሪዋ ነው የሚል ታሪክ ይዘው መምጣትና እስፔክንም መለማመጥ ነበር ። በርግጥ እኒህ ፖሊሶች ስለእስፔክ የተነገራቸው ምንም ነገር ባለመኖሩ በአድራጐታቸው ሊወገዙ አይገባም ።

ሙርታህ በዚህ ደረጃ የእስፔክን አደገኛ ነፍሰገዳይነትና ሕጉም በጥብቅ የሚፈልገው መሆኑን ከምን ጊዜ

ውም የበለጠ በመገንዘቡ እስቴክን በራሴ ሆቴል አካባቢ መጠበቁን ከመቀጠል ይልቅ አንድ ነገር ማድረግ እንደሚገባው አመነ ።

በሌላ በኩል ደግሞ ከዋሽንግተን ዲ.ሲ. በኮምፒዩተር በዚያው ዕለት ምሽት የተላለፈው የጣት አሻራ ግድያውን ከፈጸመበት አካባቢ ከተነሳው አሻራ ጋር በ12 ነጥቦች በመመሳሰሉ ሐሳቡ ይበልጥ ተጠናከረ ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ፤ እስቴክ በራሴ ሆቴል ወደሚገኘው ክፍሉ ገና ሳይመለስና ሌሊቱን ሙሉ ቢቃኝ ፖሊሶች ሲታሰሱ ባደሩት በአንዳቸውም መጠጥ ቤቶች እንኳ ባልታየበት ሁኔታ በፖሊስ ተቆጣጣሪ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጠ ። ከዚህ በኋላ ሙርታህ ተፈላጊው ተመልሶ ሊመጣ እንደማይችልና ረዳቶቹም የሕዝቡን ድጋፍ እንደሚሹ አመነ ።

በዚህም መሰረት ፖሊስ ግድያውን የፈጸመው እስቴክ መሆኑን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ያለው ከመሆኑም በላይ ኮራዞን አሙራወ ፎቶግራፉን በሚገባ የለየችው መሆኑን አስታወቀ ። የፖሊስ ተቆጣጣሪውም “ ተፈላጊው ሰው ይህ መሆኑን አረጋግጣለሁ ” በማለት ተናገረ ።

የእስቴክ ፎቶግራፍ በቺካጎ ጋዜጦችና በሌሎች በዩ. ኤስ. አሜሪካ በመቶ የሚቆጠሩ የጋዜጣ ዓይነቶች ታትሞ ተሰራጨ ። እስቴክም ከከተማው እንዳይወጣ በየኬላው የተከታታይና የፖሊስ የጥበቃ ጓዶች ብርቱ ቁጥጥርና ፍተሻ እንዲያደርጉ ተደረገ ። ስለሆነም የፌዴራል ቢሮ ምርመራ አስሳውን በግልጽ እንዲያካሂድ የሚያስችል ሁኔታ ተፈጠረ ።

በቺካጎ ሪቻርድ እስቴክን ለማደን የሚደረገውን ጥረት ሙርታህ ያለማቋረጥ መከታተልም ጀመረ።የምርመራ ሠራ



ተኞቹ ጓድና ዩኒፎርም የለበሱ ፖሊሶች የባቡር ጣቢያዎች ፤ የአውቶቡስ መናኸሪያና የአውሮፕላን ማረፊያዎችንና የውሃ መገናኛዎችን ሁሉ ወጠረ ። እስቴክ በመጨረሻ ከታየበት ጊዜ አንስቶ በትልቅ ኃይቆች የተጓዙት መርከቦች እስቴክን ጭነው እንዳይሆን መልእክት ጉረፈ ። እስቴክን ፍለጋ የተጠመዱት መርማሪዎችም በአውራ ጎዳናዎች ፣ በየደሳሳው ጎጆ ፣ ቡና ቤቶች ፣ ተራ ሲኒማ ቤቶችና በመሳሰሉት አጣቃ ቦታዎች ሁሉ የአንድ በአንድ ፍተሻቸውን ተያያዙት ። የሆነ ሆኖ የእስቴክ ደብዛው እንኳ ሊገኝ አልቻለም ።

ቅዳሜ ምሽት ላይ በሰሜን ቺካጎ አቅጣጫ የተለመደ የአደጋ ጥሪ ድምጽ ተሰማ፤ያ የተለመደ የአደጋ ጥሪ ድምጽ ሲሰማ ይህን ያህል ግምት የሰጠው ሰው አልነበረም። በሌላ በኩል ደግሞ በቺካጎ ምዕራብ ማድሰን ጎዳና 617 ቁጥር ላይ በሚገኘው በስታር ሆቴል አንድ የተለየ ሁኔታ ተፈጠረ ፡ የስታር ሆቴል ተረኛው የምሽት የእንግዳ ተቀባይ በሆቴሉ ካረፉት እንግዶች መካከል በዚያን ዕለት ምሽት ቀደም ሲል በቢ. ብራይን ስም የተመዘገበ አንድ ወጣት እንግዳ አደጋ ስለደረሰበት ፖሊስ ጠራ ፣ ይኸው ሰው በአረፈበት በአምስተኛው ፎቅ በምትገኝ አነስተኛ ክፍል በመሆን በግራ እጁና በቀኙ የእጁ አንጓ ላይ ያለውን የደም ስር በመበጠስ ራሱን በራሱ ለማጥፋት ባደረገው ሙከራ በደም ተበክሏል ። የዚህ መሰሉ አደጋ በከተማው በሚገኙ ሆቴሎች አካባቢ በማንዳለጥና በመንሸራተት ሳቢያ ሁሉ ስለሚደርስ በቦታው ለደረሱት ሁለት የፖሊስ ቃኚ ጓዶች ተራ የአንቡላንስ አገልግሎት ሥራ ሆኖ አምሽቶም ነበር ።

የፖሊስ ቃኚ ጓዶቹም የእስታር ሆቴልን ውስጣዊ ይዞታ በሚገባ ስለሚያውቁት ተግባራቸውን ለማከናወን አ

ሲቀሩ የመነሻ ቦታ አድርገው ቆጥረውት ነበር ። በሆቴሉም ከነበሩት ዕቃዎች እንስቶ በየግድግዳው የተጻፉትን ጽሁፎች ጭምር አብጠርጥረው ያውቋታል። በአረንጓዴው ጡብ ግድግዳ ላይ “ በዚህ ግቢ መጠጣት የተከለከለ ነው ” ተብሎ የተጻፈውን ፣ በፊት ለፊት መቀመጫ ላይ ለምሽት 90 ሳንቲም የቁልፍ እንደሚከፈል ፣ በመተላለፊያው ላይ የተለጠፈውን የሊንኮሊንና የኬኔዲን ፎቶግራፎች ፣ በአንድ እዛውንት የሚንቀሳቀስውን አሳንሰርና “ በራስህ ዋስትና ግባ ” በሚል ጽሁፍ የሚያስጠነቅቀውን ሁሉ በሚገባ ያውቋታል ።

እኒሁ ሁለት የፖሊስ ቃኚ ጓዶች በአምቡላንስ እንደደረሱ በደም የተነከረው እንግዳ በአምስተኛው ፎቅ ላይ እንደሚገኝ ፣ እነስተኛ ክፍሏም የአየር መቆጣጠሪያና የመጠጫ ብርሌዎች ትንፋገን መከላከያ እንደሌላት ተነገራቸው ፣ ክፍሏም በጣም ጠባብና ተራ የሆን መገልገያ ዕቃዎች ያሉባት እነስተኛ ክፍል ነበረች ።

ወጣቱ ሰው በዚያች ቁጥር 584 ክፍል በምትገኝ ሸራ አልጋ ላይ በጀርባው ተንጋሏል ፣ እጆቹም በአልጋው ግራ ቀኝ ተንጠልጥለው ይወዛወዛሉ ፤ ደሙ ወደወለሉ ይንቆረቆራል ፣ የፖሊሱ ቃኚ ጓድ አባል በርንስ በአደጋ ላይ በሚገኘው ሰው ግራ እጅ ላይ ፋሻ በፍጥነት ጠመጠመ ። ከራውስ ደግሞ ወደ ተረኛው የእንግዳ ተቀባዩ በመሄድ ይህ እንዴት ሊሆን እንደቻለ የሚያውቀው ነገር እንዳለ መጠየቅ ያዘ ። እንግዳ ተቀባዩም በ582 ክፍል የተከራየውና ጆርጅ በመባል የሚታወቀው በዚሁ ጉዳይ ተጠርቶ እንደነበር አስረዳ ። የተጐጂው ጐረቤት ጆርጅም ሁኔታውን በሚከተለው መሰረት ገለጸ ።



“ በመጀመሪያ ከዚህ ሰውዬ ጋር መነጋገር አልፈቀድኩም ነበር ። ባለፈው ምሽት ሁለት ጠርሙስ ቪኖ ይዞ ወደ ክፍሉ ገባ ፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እኔን መጥራት ጀመረ ፣ እኔም መረበሽ ስላልፈለኩ ዝም አልኩት ፣ ወደበኋላ ግን ተኛ፣በመጨረሻ ዛሬ ጧት ወደ አራት ሰዓት ገደማ ወደ ታችኛው ፎቅ ሄዶ ሌሎች ተጨማሪ ጠርሙስ ቪኖዎችና ጋዜጦች ይዞ ወደ ክፍሉ ገባ ፣ ከሰዓት በኋላ ወደ ምሽቱ ላይ ውሃ ውሃ ሲል ሰማሁት እኔም አፉን እንዲዘጋ ነገርኩት ርሱ ግን “ውሃ እፈልጋለሁ” በማለት ይጮህ ጀመር፣ ከዚያም ወደ አዳራሹ በመሄድ “ እባካችሁ ቢራ ስጡኝ ፣ ለቢራ የተፈለገውን ሁሉ እከፍላለሁ ” እያለ ሲጮህ ሰማሁት ፣ እኔም ከሚጮህበት አዳራሽ ወጥቶ ሰላም እንዲሰጠኝ ነገርኩት ፣ ከዚያ በኋላም በሌሎች ክፍሎች ያሉትን ሰዎች ሲያስቸግር ሰማሁት ፣ ጥቂት ደቂቃዎች ቆይቶ አንድ የእውነተኛ የስለላ መጽሐፍ በማንበብ እንዳለሁ ከመኝታ ቤቴ በራፍ ላይ ወድቆ በሩን ሰበረው ፣ ቀና ብዬ ሳይ ሰውዬው እንደ ተወጋ አሳማ ደሙ ይፈስ ጀመር፤እኔም ወደ ክፍሉ ወስጄ ካስተኛሁት በኋላ ለእርዳታ ሮጥኩኝ ፣ እርዳታ ጠይቄ እንደተመለስኩም ጥቂት አልኮል ሰጥቼው ዝም እንዲል ነገርኩት ።”

ቃኚው ጓድ ይህንኑ በደም የተነከረ ሰው “ ስምህ ማነው ? ” አለ ፣

“ ብራይን . . . . ቢ ብራይን ” በማለት መለሰ

“ እንዴት ራስህን በራስህ ትቆርጣለህ ?”

“ ይህን ማን ያውቃል . . . . እኔ የማውቀው ነገር ቢኖር መቁረጤን ብቻ ነው” አለ ።

አንድ ሌላ በሆቴል ቤቱ ያረፈ ሰው ደግሞ ለበርንስ በሰውየው ክፍል የተሰባበረ ጠርሙስ መኖሩንና ምናል

ባት ይኸው ሰው ራሱን የቆረጠው በዚሁ ጠርሙስ ሊሆን እን ደሚችል ነገረ። ሁለቱም የፖሊስ ቃኚ ጓዶች ደግፈው ካነሱት በኋላ በርንስ ከክፍሉ ወደ እሳንሱር ሲወስደው፣ ክራውስ ደግ ሞ መኝታ ክፍሉን መፈተሽና ንብረቶች መሰብሰብ ጀመረ፣ ያገኛቸው ንብረቶችም የሚከተሉት ናቸው ። የጥርስ ቡርሽ መያዣ፣ የቤሳ ምላጭ መያዣ ፣ ለተላጨ ጺም ቅባት ፣ የወ ንዶች ኮሎኝ ጠርሙስ ነበሩ ። አረንጓዴ ከተቀባው የአንደ ኛው የብረት ግድግዳ ላይም "የእስታር ክፍሉን ያጌጠ" የሚል አንድ ጥልቅ ጽሁፍ ተጽፏል ። የተሞጫጨረውም በርሳስ ሲሆን " 25 ዓመት ለሚሆነው ወጣት 5 ዶላር እከፍላለሁ ። ርሱም የሚሸት እግር ካለው ነው. . ." የሚልም ነበር ።

ያም ሆነ ይህ በአስጊ ሁኔታ በመድማት ላይ ይገኝ የነበረው ሰው ወደ ኩክ ካውንቲ ሆስፒታል ተወስዶ በድንገተኛ ክፍል አስፈላጊው ሕክምናና ርዳታ ተደረገ ለት ። ሐኪሙም በደም የተነከረውን እጅ ካጸዳዳና ቁስሉን ካጠበ በኋላ በግራ እጁ ክርን ሥር በአንድ የተጐዳ የደም ሥር ደም እንደሚፈስና በቀኝ የእጁ አንጓ የአጥንት ክፍል በጥቂቱ ላይ የተቆረጠ መሆኑን አረጋገጠ ።

ሐኪሙ ልዩ ትኩረት በበሽተኛው ቁስል ላይ ብቻ ሳይሆን በገጽታውም ላይ ተነጣጠረ ፤ ሐኪሙ ነርሶቹን ስለገደለው ወንጀለኛ በጋዜጣ አንብቦና ፎቶግራፉንም በሚገባ አጥንቶት ስለነበረ የበሽተኛውን ፊት ለበለጠ እይታ እያገላበጠ ያይ ጀመረ ፤ ወዲያውም ነርሷን ጠርቶ እስቲ ጋዜጣውን አምጪልኝ ብሎ ጠየቀ ።

ነርሷ ጋዜጣውን ፍለጋ ስትሄድ ሐኪሙ ከበሽተኛው ክንድ ላይ ያለውን ደም ይጠርግ ስለነበረ የበሽተኛው





ሪቻርድ እስፔክ በስምንት ነርስ ተማሪዎች ነፍስ ግዳይ ወንጀል ከተ ከሰሰ በኋላ በኩክ ካውንቲ ወህኒ ቤት ሆስፒታል ። (ዋይድ ወርልድ ፎቶ)

ጥቂት ንቅሳትም መታዬት ጀመረ ፡ ሐኪሙ “ ቢ ” የሚለውን ፊደል ለየ ከዚያም ደሙን ሲጠርግ “ B.O.R.N. ” የሚለውንና በመጨረሻም በእጁ ላይ የተነቀሰውንና ቢጋዜጣ የተገለጸውን ጽሁፍ በሙሉ አነበበ ።

ነርሷ ጋዜጣውን ይዛ ከመመለሷ በፊት ዶክተሩ በሚገባ የበሽተኛውን ማንነት በመለየቱ ጋዜጣውን ይዛ እንደተመለሰች በዝግታ “ፖሊስ ጥሪ” ብሎ እንደገና ላካት ፣ ነርሷም ፈጥና ወጥታ በሆስፒታሉ ተረኛ የነበረውን የፖሊስ ቃኚ ጓድ ጠራች ።

ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ዶክተሩ ጥቂት የራሱን የመጀመሪያ ደረጃ የምርመራ ጥያቄዎች እንዲህ በማለት ጠይቆ ነበር ።

“ ስምህ ማነው ? ”

ሲለው በሽተኛው በድንጋጤ ፈዞ ዶክተሩን ይመለከት ጀመር፣ “ፖሊስ የሚፈልግህ ሰው አይደለህም?” በማለት ዶክተር እስሚዝ ጥያቄውን ደገመ ። በሽተኛውም ግድ ሆኖበት ራሱን ነቀነቀ ።

“ስምህ ማነው?” አለ ዶክተር እስሚዝ በድጋሚ ። በሽተኛውም “ሪቻርድ” አለ ፣ ዶክተር እስሚዝም ጥቂት ቆየት ብሎ የሚቀጥለውን በመጠባበቅ ላይ እንዳለ ሪቻርድ እስፔክ በማለት ትክክለኛ ስሙን በድንገት አፈረጠው ።

በነርሷ የተጠራው የፖሊስ ቃኚ ጓድም ወደ ድንገተኛ ክፍሉ በመግባት በሽተኛውን በቁጥጥር ሥር አደረገ። ዶክተር እስሚዝም አፋጣኝ የድንገተኛ ርዳታውን ካደረገ በኋላ ከክፍሉ ወጣ ።



የእስፔክ እሰሳ በዚህ ተፈጸመ ። ስዓቱም እሁድ ሰኔ ,7 ከሌሊቱ 6 ሰዓት ከ45 ደቂቃ ማለትም ኩራዞን አሙራ,ባ ሕይወቷን ከዚያ አሰቃቂ ሞት አትርፋ ነርሶቹ በተፈጁበት ፎቅ ታዛ ላይ ተንጠልጥላ “ ርዱኝ ፡ ርዱኝ ሁሉም አልቀዋል ” ብላ ከጮኸችበት ከ67 ሰዓታት በኋላ መሆኑ ነው ።

ከ9ኝ ወራት በኋላ ዓለምን ያተራመሰውና የሰውን ሁሉ ሕሊና ያቆሰለው የወንጀለኛው ፍርድ በከፍተኛ ፍ/ቤት ታዬ ፣ በኤሌትሪክ ወንበር ላይ ተቀምጦ የሞት ፍርድ ይገባዋል የሚለው የፍርድ አስተያየትም ተሰረዘ ።

በ1972 በወጣው የአሜሪካን ሕግ ስምንት ነርሶችም ቢፈጅ ነፍስ ያጠፋ ነፍሱ ይጠፋል የሚለውን ቅጣት ስለማይደግፍ የእድሜ ልክ እሥራት ተፈረደበት ።

# ባለቤቱ እንኳ የማታውቀው ጉድ!

የሚያሚ ጠበቃ የሆነው ሲድኒ አሮኖቪትዝ ሰዓ
ቱን ከተመለከተ በኋላ በተጨነቀ መንፈስ ፊቱን አኮ
ሳትሮ ወደ ፀሐፊው በመዞር ለኤትል ቤት አከራይ
ደውላ እስካሁን ስለሁኔታዋ ያስተላለፈችው መል
ዕክት ባለመኖሩ መቸገሩን በመንገር ስለርሷ ያውቁ
እንደሆን ጠይቃ እንድታረጋግጥለት ያዛታል ።

ያ! ጭንቀት እንዲሁ የመጣ አልነበረም ፣ ራሱን
የቻለ ዕውነት ነበረው ። ያን ዕለት ማለትም በዕለተ ማክ
ሰኞ ነሐሴ 15/1959 ከእኩለ ቀን በፊት በነበረው የሥራ
ሰዓት ኤትል አይወን ሊትል ያለአመልዋ ፈጽሞ ባልተለ
መደ ሁኔታ ከ3 ሰዓታት በላይ ከሥራ አርፍዳለች። ከዚህም
ሁሉ ሌላ ያቺው የ55 ዓመት ዕድሜ ባለፀጋዋና 115 ፓው
ንድ ክብደት የነበራት ሴተላጤዋ ጸሐፊ ፣ እንኳን ከሥራ
ልትቀር ትንሽ እንኳ ስታረፍድ የማሳወቅ ልምድ ነበራት፣
በዕለቱ ግን ከእኩለ ቀን በኋላ ደብዛዋም አልነበረ ። በመ
ሆኑም ሴላይቱ የአሮኖቪትዝ የጥብቅና ድርጅት ጸሐ
ፊው ለወ/ት ሊትል አከራይ ደወለች ።

ወ/ሪት ሊትልም ከአከራይዋ ትልቅ አፓርታማ በስ
ተጀርባ በምትገኝ በአንዲት አነስተኛ ፎቅ ውስጥ ትኖር
ነበር ፣ ለብዙ ዓመታትም በዚያቹ ቤት ተከራይና ያንበኛ
ስለነበረች የታወቁ ጉብኝዎች በጓዳ በር ዘው ብለው መግባት
እንኳ በተለይም ለአከራይዋ ለባንክስ ፈጽሞ እንግዳ ነገር
አልነበረም። የአሁነኛው የባንክስ አገባብ ሁኔታ ግን ክጭ
ንቀትና ከሐሳብ ጋር ስለነበረ የተለየ ሆኗል ። ልክ ከቤቷ



እንደደረሰ በጧት የመነሳት ልምድ በነበራትና የጧት
ዜናን በጧቱ በምታገባድደው ወይዘሪት ቤት የሚያሚ ሄራ
ልድና (የጠዋት ጋዜጣ) የወተት ዕቃ ከቦታቸው ሳይነሱ
በማዬቱ በቅድሚያ ተደናገጠ ። በመቀጠልም እንደተለመ
ደው በሩን ደመቅ አድርጎ አንኳኳ፣ ከውስጥ ምንም
መልስ አልነበረም ፤ ሌላም ትርፍ ቁልፍ ስለነበረው
በሩን ከፍቶ ገባ ። ከፊት ለፊትከነበረው የማስገቢያ በር
አንስቶ እስከ ሳሎኑ ድረስ ከተለመደው የቤቱ አቀማ
መጥና ሁኔታ ምንም የተለዩና አዲስ ነገር አልገጠመውም፣
ወንበሮቹ በተለመደው የአቀማመጥ ሥርዓት በሚገባ ተሰ
ትረዋል ፣ የቤቱ ንጽህናም በሚገባ ተጠብቋል ። ወደ ወጥ
ቤቱ በር በሚያመራው ማከፋፈያ ክፍል ሲደርስ ግን
ከአንድ ጥንቁቅ ባለሙያ ሴት በተለይም ከወይዘሪቷ የማ
ይጠበቅ የተመሰቃቀለና ቀደም ሲል ያልተለመደ ጉድ
ያያል ። በወለሉ ላይ ቡና ፋሷል ፣ በጠረጴዛውም ላይ
አንድ በከፊል የተከፈተ የገና ስጦታና አይስክሪም የተ
በላበት ባዶ የወረቀት ብርጭቆ ይታያል ።

በዚህን ጊዜ የባንክስ ሃሳብ ወደማታው ሁኔታ ተመ
ለሰ ። ከምሽቱ 2 ሰዓት ተኩል ቴሌቪዥን በመመልከት
ላይ ሳለ የኤትል የብረት የፖስታ ሳጥን በር ሲከፈት ይሰማ
ዋል ። ከዚያም በጠጠሩ ላይ የሚራመደውን የወይዘሪቷን
የእግር ኮቴ ካዳመጠ በኋላ ከሥራ መግባቷን በማወቅ
ቴሌቪዥኑን መመልከት ይቀጥላል ። ይህን እያሰላሰለ
ከአንድ ክፍል ወደ ሌላው በመዟዟር ወይዘሪቷን ቢጣራም
መልስ ሊያገኝ አልቻለም ። በመጨረሻም ወደ መኝታ
ክፍሏ ሲያመራ በሩ ፈጽሞ ባልተለመደ ሁኔታ ተበርግዶ
አገኘው ፣ በድንጋጤና በስጋት ወደ ውስጥ ሲገባም ዓይኑ
ሊያምነው ያልቻለ ጉድ ተደነቀረበት ።

ባለአራት ጌጣማ ጉጥ በነበረው አልጋዋ ላይ የደጊ

ቷ ወይዘሪት ሬሳ ዕርቃኑን ተዘርሯል ፣ እጆችዋና እግሮቿ
በአራቱ የአልጋዋ ጉጦች ላይ ተወጥረው ታስረዋል ።
ደረቷና የተለያዩ አካላቷ በጩቤ ተሸቅሽቀዋል ። በተለ
ይም ከሟችዋ ደረት ላይ አንድ ጡት ተቆርጦ ሲያይ ወት
ሮውንም በብርክ የተያዘው አካሉ ደነዘዘ ፤ መላው አካሉ
በድንጋጤ ድንጋይ ሆነበት ፤ ከዚያም ወዲያ ምንም የሚያ
ደርገው ነገር ባለመኖሩ ምንም ነገር መንካት የሌለበት
መሆኑን በመገንዘብ ቤቱን ዘጋግቶ በፍጥነት ወደ ፖሊ
ሶች በመደወል የደረሰውን ሁኔታ በዝርዝር አሳወቀ ።

በወቅቱም በፈጠነ ሁኔታ ወንጀሉ ወደ ተፈጸመበት
ቦታ ለመድረስ የቻለው ከሚያሚ የነፍስ ግድያ ወንጀል
ምርመራ ንዑስ ክፍል ከነበሩት መርማሪዎች መካከል በዕ
ድሜው ወጣት የነበረው ማይክ ጉንዛሌዝ ነበር ። በአባቱ
አርጀንቲናዊ በእናቱ ኢጣሊያዊና አሜሪካዊ የተገኘው
የኒውዮርክ ተወላጅ ጉንዛሌዝ ለዚያ ታላቅና አሰቃቂ ወን
ጀል ምርመራ ኃላፊነት እንደተሰጠው ዝናውን የሚያ
ጉላለት መሆኑን በሕልሙም በውኑም በወቅቱ ያልተገነዘ
በው ቢሆንም ፣ የወንጀሉን ውስብስብነትና አስቸጋሪነት
ያጤነው ግን ከጧቱ ነበር ።

በዕለቱ በሰዓት መገባደጃው ላይ የተፈፀመው የአ
ሰቃቂው ወንጀል ሁኔታ የሌሎችንም ዕውቅ መርማሪዎ
ችን ስሜት ስለቀሰቀሰና ስለነካ በማንኛውም የትርፍ
ጊዜያቸው ከወጣቱ መርማሪ ጉን ለመሰለፍ ወሰኑ ።
ርምጃው የተፋጠነ ሊሆን ይችል ዘንድም ተገቢው ፖሊ
ሳዊ የምርመራ ድጋፍ ሁሉ በተፈለገው ጊዜ በአስቸኳይ
ሊደርስ የሚችልበት ሁኔታም ተመቻቸ ።

በወይዘሪትዋ ፊትና በመላው ሰውነቷ ላይ የተ
ደረገው ግፍ ሰብአዊነት ከጐደለው አረመኔ ወንጀለኛ
እንጂ በድንገተኛ ሁኔታ የተፈጠረ አላስመሰለውም ። ሰው



ነቷ ከመሞጫጨሩና ከመጐሳቆሉ ሌላ በቡጢና በክርን
የተደቀሰች ይመስላል ፤ አንገቷ በአሰቃቂ ሁኔታ መታነ
ቁን የሚመሰክረው ማነቂያው ከዚያው ከአንገቷ ላይ
ተተብትቧል ፤ በደረቷ ላይ በተደጋጋሚ የተወጋውን ቁስል
የሚያረጋግጠው ጩቤ በልብስ ኮሞዲኖ መሳቢያው ውስጥ
ተገኘ ። የተገሸለጠው ጡትዋም በቁምሳጥኗ መስተዋት
ላይ ተጣብቋል ። መርማሪዎቹ ቁም ሳጥኑን ሲያስሱ አንድ
በደም የተበከለ የእጅ ባትሪ አገኙ፤ ያ የእጅ ባትሪም የኬሚ
ካል ምርመራ ሲደረግበት በወይዘሪትዋ ብልት ውስጥ ገብቶ
እንደነበር ተረጋገጠ ። መርማሪዎቹ የሚፈለገውን ማስረጃ
ሁሉ በመሰብሰብ ላይ እንዳሉም ያን መሰሉን አሰቃቂ ግፍ
ፈጻሚ የማጋለጡ እልህም ይተናነቃቸው ነበር ። ምን የሚያ
ስመርር ነገር ቢፈጠር ነው ያን የመሰለ የሚዘገንን ወንጀል
በኤትል ላይ የተፈጠረው? የሚልም ጥያቄ ይወረወር ጀመር።

በወቅቱ በተፈጸመው በዚያው አሰቃቂ ወንጀል የሚ
ያሚው የነፍስ ግድያ ምርመራ ንዑስ ክፍል በዚያ መሰል
ወንጀል ምርመራና የጾታ ሥነ- ልቡና ጠቢብት የነበሩ
ትን ሁለት አዋቂዎች በሙያቸው የምርመራ ሥራና በአ
ማካሪነት ተጠቅሟል ። ጉንዛሌዝና የሥራ ባልደረቦቹም
የወይዘሪቷን ገዳይ በአእምሮ መታወክ ብስለት ሰውን ቆራ
ርጦ የመግደል ልምድ ካዳበረውና ከዓመታት በፊት
በለንደን አውራ ጐዳና በመዘዋወር በተለይ ሴቶችን በሆነ
ባልሆነው ምክንያት ይገድል ከነበረው ጋር ተመሳሳይነት
እደነበረው እገናዝበውታል ።

ዶክተር ዴሪቨርም “ ሪፐር ” ተብሎ በሚታወቀው
ጽሑፋቸው የዚያን መሰል አሰቃቂ ግድያ መሠረታዊ የአ
እምሮ ሁከት ያለባቸው ሰዎች ናሙና አድርገው በመው
ሰድ ጠቢባዊ ትንተና አድርገውቢታል ። በትንተናቸው
መሠረት በዚያ መሰሉ የአእምሮ ሁከት የተጠቃ ሰው

ሕግን ከምንም ባለመቁጠርና ወደጉን በሙተው የፈለገ ውን ለመፈጸም ወዲያው የሚመኝና የማሰቃየት ተግባሩን በሚያከናውንበት ወቅትም ጭራሽ ራሱን እየሳተ የሚያ ደርገውን ሁሉ የሚያሳጣው መሆኑን አትተዋል ።

መርማሪዎቹ የዶክተሩን ጥናታዊ ጽሑፍ ለምርመራ ቸው መመሪያ ይሆን ዘንድ ደጋግመው አንብበውታል፣ቃል በቃልም አጥንተውታል።ከዚያው ጽሑፍ ከአንደኛው ምዕ ራፍ ላይ እንደተከታተሉት አንዳንድ በአእምሮ ሁከት የተ ለከፉ ገዳይዎች ከግድያው በኋላ ፍትወተ ሥጋ ይፈጽማሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ በግድያው ወንጀል የተለከፉ በሽ ተኞች በጣም ንቁዎችና ብልሆች ፣ ሲሆኑ አሰቃቂ ግድ ያቸውን ከፈጸሙ በኋላ ዱካቸው እንዳይታወቅና እን ዳይነቃባቸው ከፍተኛ ጥንቃቄ እንደሚያደርጉ ጥናታዊ ጽሑፉ ያስረዳል።በመሆኑም የኤትል ገዳይ በዚያ ጥናታዊ ሥራ በቀረበው ባሕሪይ በተጠመደ በሽተኛ ሊፈጸም የሚ ችል መሆኑን መርማሪዎቹ ቅንጣትም አልተጠራጠሩም ።

ኤትል አይወን ሊትል ንቁና ቀልጣፋ በአብዛኛው በስህተት ላይ የማትወድቅና አመለሸጋ ወይዘሪት ነበ ረች ። ከዚህም ሌላ በማህበራዊና ኃይማኖታዊ እንቅስቃ ሴዋ በጣም የተከበረችና የእሁድ የሚያሚ ማዕከላዊ ባብቲስት ቤተክርስቲያን ተከታይም ነበረች ።

ሰኞ ታህሣሥ 14 ከሰዓት በኋላ ከረፋዱ ከአለቃዋ ከጠበቃው ሲድኒ አርኖቪትዝ ዘንድ በመሸማቀቅና በፍርሃት ቀረባ በጉርብትና ከምትኖረው እማችዋ ወይዘሮ ጄፈርሰን ሊትል ጋር ሆና የገና ስጦታዎች ለመግዛት ፈቃድ ጠይቃ ነበር ። ከተፈቀደላት በኋላም ሊወዘፍ የሚችለውን ሥራ በማግሥቱ ማለዳው ላይ ገቢታ ለማጠናቀቅ የምት ችል መሆኗንም አረጋግጣለች ። በፕሮግራሟም መሠ ረት ሚያሚ ከተማ በመውረድ ስጦታዎቹን ገዛዝታ



ወደቤትዋ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ለመግባቷ በአከራይዋ ተመዝግቧል ።

ከዚህ ወዲያ የነበሩት የ7 ሰዓታት ጉዳይ ግን ማንም ሊያውቃቸው ያልቻለ ድፍን ያሉ ነበሩ ። ከሁኔታው ለመ ረዳት እንደተቻለው ወይዘሪትዋ የገዛቻቸውን ስጦታ ዎች ሽፋኖች መከፋፈት ጀምራ ነበር ፣ ግን ለምን ጨርሳ አልከፈተቻቸውም ነበር ? ምናልባት ከአድካሚው የገበያ ውሎ በኋላ ደክሟት ይሆን?የሚልም ግምት ነበር ። በሌላም አቅጣጫ ከተገኙት መረጃዎች ለመገመት እንደ ተቻለው አሰቃቂው ግድያ የተፈጸመባት አከራይዋ ስት ገባ ከሰማት ከ7 ሰዓታት በኋላም ነበር ። ለዚህ ግምት ዋንኛ መሰረት የሆነው በጉርብትና የሚኖረው ወተት አዳዩ አሌክሳንደር ስኔሊንግ የሰጠው የምስክርነት ቃል ነው ። ስኔሊንግ የወተት ዕደላውን ለማካሄድ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ተነስቶ በሚሄድበት ወቅት በአካባቢው ለየት ያለ የሴ ት የጭንቀትና የስቃይ ድምጽ ሰምቶ ነበር ፣ ሆኖም ጉረ ቤቱ ከሰው ጋር የተለመደ አይነት ጠብ የፈጠረች መስሎት በቸልታ በማለፉ የኤትልን መሞት እስከ ሰማ ድረስ ለማንም እንዳልተናገረ ገልጾ የአሰቃቂውን ግድያ ጉድና ሁኔታ እንደሰማ ግን ለመርማሪዎቹ የሰማውን በፍላጐቱ ለመንገር መፈለጉን አረጋግጧል ።

በኤትል ላይ የተለየ ድብደባ፣የጩቤ ትርተራና ሌላም ግ ፍ የተደራረበባት ቢሆንም የመጨረሻው ሕልፈቷ የተጠና ቀቀው በአንገቷ ውስጥ በጠለቀው ማነቂያ ሳቢያ የመሆኑን ሁኔታ የሬሳውን ምርመራ ያከናወኑት ዶክተር አረጋግጠዋ ል። በአንገቷ ላይ የጠለቀው የማነቂያ ክር በእልጋው ጉጦች እጆቿና እግሮቿ ከታሰሩበት ጋር ተመሳሳ ይነት አልነበረ ውም።የሆነ ሆኖ የላቦራቶሪ ቴክኒሺያኖች በአንገቷ ላይ የተ ጠለቀው ማነቂያ ከመኝታ ቤቱ ጣሪያ ላይ የተወሰደ የመ ብራት ክር መሆኑን አረጋግጠዋል ። በሟችዋ በድን አካል

ላይ በተደረገው ምርመራ መሰረትም የተፈጸመባት የግፍ ቅጥቀጣ ፡ የፊትዋ መጠፍጠፍ ፡ የደረቷ በጩቤ መሸቅሸቅና የጡትዋ መዘንጠል ቀጥተኛ የሞቷ ምክንያት እንዳልሆኑ አመልክቷል ። በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት አሰቃቂ ድርጊቶች ሁሉ የተፈጸሙት ወይዘሪትዋ ከተገደለች በኋላ ነበር ።

ገዳዩ በቤቷ ውስጥ ገብቶ ወይዘሪቷን በማስገደድ የታገለበት ምክንያቶችም አልዳበሩም ። ሆኖም የወጥ ቤት ክፍሏ በግማሽ ተከፍቶ መቅረቱና እንደተለመደው ያለመቆለፉ ጥቂት አጠራጣሪ ጥያቄዎችን ማስከተሉ አልቀረም ። ምንም እንኳን ገዳዩ ወደቤቷ ከመግባቱ በፊት ተከፍቶ የነበረ ሊሆን ቢችልም በሌላ በኩል ግን ወይዘሪቷ ገዳዩን ቤቷ ውስጥ በፍላጐቷ አስገብታው ይሆናል የሚልና ገዳዩ የምታውቀው ሰው ሊሆን ይችል ይሆናል የሚሉም አጠራጣሪ ጥያቄዎች እንዲነሱ አድርጓል ። ገዳዩ ተገኝቶ በዚህ ረገድ የነበረውን አጠራጣሪ ሁኔታና ውዝግብ አልባት እስካላስገኘለት ድረስ አጥጋቢ መልስ ሊያገኝ የማይችል ጥያቄ ቢሆንም ወዳጅዋ ገብቶ ገድሏት ይሆናል የሚለው ጥርጣሬ ግን መሰረት ሊይዝ ችሏል ።

ወይዘሪት ኤትል ምንም እንኳን ትዳር ያልያዘች ብትሆንም በዕድሜ የገፋች ሴት ነበረች ፡ በዕድሜ መግፋት ብቻ ሳይሆን ወንድሟ ዊልያም ኤትል እንደመሰከረው ከወንድ ጋር ስትማግጥና ቀጠሮም ስትወስድ ሰምቶም አይቶም የማያውቅ መሆኑን አረጋግጧል ። የዚህ ሁኔታ ደግሞ የግድያውን ወንጀል ከመፍትሔ ቁልፍ ውጭ እያራቀው መጥቷል ።

ገዳዩ የሟቿን እግርና እጆች ከአልጋው ጉጦች ጋር ጥፍር አርጎ ለማሰር የተጠቀመበትን ክር ካለመሰላል መንጠልጠያ ካወረደበት ቦታ አኳያ ለማነጻጸር እንደተቻለው ቁመቱ ከ6 ጫማዎች በላይ ርዝማኔ እንዳለው ለመ



ገመት ተችሏል ። የዚህን ግምት ለመርማሪዎቹ ይበልጥ ሊያጠናክርላቸው የቻለው ደግሞ በእጅ ባትሪው ወንጀሉን ከፈጸመ በኋላ ለማኖር በሞከረበት ወቅት በቁም ሳጥኑ ላይ የእጅ ምልክቶች በመገኘታቸውና የእጁ መዳፍ አሻራ በመስኮቱ የላይኛው ጠርዝ ላይ በመታየቱ ነው ። መርማሪዎቹ በፖሊስ ሳይንሳዊ ምርመራ ተጨባጭነት የነበራቸውን እኒያን ማስረጃዎች በሚገባ ፎቶግራፍ በማንሳት በዓለም አቀፍ ፖሊስ ድርጅት በኩል የጣት አሻራውና የወንጀሉ መግለጫ እንዲሰራጭ አደረጉ ።

ሬሳው ከነበረበት ሲነሳም መርማሪው ከመስኮቱ የላይኛው ጠርዝ ላይ ከተገኘው አሻራ ላይ የተለየ ጥርጣሬና ግምት አሳድሮበት ነበር ፡ ይኸውም ምናልባት ሠራተኛ ወይም የቤቱ እንግዳ ሊሆን ይችላል የሚል ሲሆን ፡ የአሻራው ትልቅነት ሲታይ ግን ከወይዘሪቷ ሁለት ጊዜ እጥፍ ሆኖ ተገኝቷል ። በእጅ ባትሪው ላይ የተገኘው አሻራ በማያጠራጥር ሁኔታ የገዳዩ መሆኑን መርማሪው ወትሮውንም ተማምኖበታል ። ከዚህም ሁሉ ሌላ የሬሳ ምርመራ ያካሄደው ዶክተር ዲ ጁስቲ እና መርማሪዎቹ የእጅ ባትሪውን ሴትየዋ ብልት ውስጥ አስገብቶ ያስወጣው ሰው አሻራ ለመሆኑ በላቦራቶሪ የምርመራ ውጤቶች አማካይነት አረጋግጠዋል ። ስለሆነም በእጅ ባትሪው ላይ የተገኘው በደም የተበከለ የእጅ አሻራ ያለ ጥርጥር የገዳዩ አሻራ ለመሆኑ ተደረሰበት ።

ከወንጀሉ አፈጻጸም ለየት ያለውና አስገራሚ ሆኖ የተገኘው ደግሞ የወይዘሪትዋ እጅና እግር ከአልጋው ጋር የተተበተበበት የቬኒሺያን የመስኮት መጋረጃ ክር ጉዳይ ነበር ። በአንድ በኩል ክሮቹ ገዳዩ ሟቿን መልቀቅ ከፈለገ በኋላ የተበጠሱ ሲመስል ፡ በሌላ በኩል ደግሞ እግርና እጆቿ ተዘርረው መታሰራቸው ከሞተች በኋላ የመስኮቱን

የመጋረጃ ክር ቆርጦ ማሠሩን ያሳያል ። ይህም ሊደረስበት የቻለው ከደም ምርመራው ውጤት በኋላ ነበር ።

በሚቿ በድን ሰውነት ላይ ከተደረጉት ምርመራዎች ውጤት እንዱም በሚች ላይ ምንም ዓይነት ወዘፍ ( የወንድ ዘር ፍሳሽ) በብልቷ ላይ ባለመገኘቱ ከወይዘሪቷ ላይ የግዳጅ ፍትወተ ሥጋ አላደረገም ማለት አልነበረም ። ምክንያቱም ምንም እንኳን በፍትወተ ሥጋ የስሜት መጠናቀቂያው ደረጃ ባይደርስም ሙከራና ክንዋኔ ሊያደርግ እንደሚችል በመገመቱ ነው ። በመሆኑም ገዳዩ ምናልባት የሩካቤ ሥጋ አቅም ያጣ ወይም የመጨረሻው ደረጃ ሳይደርስ ለማቋረጥ ችሎታ ወይም ምክንያት ያለው ጉልማሳ ሊሆን እንደሚችል ተገምቷል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ገዳዩ የፍትወተ ሥጋ አቋሙ ያልተስተካከለ ሊሆን እንደሚችልም ተገምቷል ። ከዶክተር ዴሪቨር የወንጀልና ፍትወተ ሥጋ በሽታ ጥናታዊ ጽሁፍ ለማመሳከር እንደተቻለውም ገዳዩ ሴት ጠል ወይም የሴት ጥላቻ ያደረበት ሊሆን እንደሚችል ተገምቷል ።

በኤትል ላይ የተፈጸመው እጅግ የሚዘገንንና ከፍተኛ ግድያ በመላው ሚያሚ ከተማ እንደተሰማ ሕብረተሰቡ በፍርሃት ተዋጠ ። የወላጅ አንጀት ሊሸከመው ባልቻለው አሰቃቂ ወንጀል ወይዛዝርት የሚውሉበትንና የሚያድሩበትን ቀርቶ የሚሄዱበትን ጉዳና እንኳን ማመን አልቻሉም ፣ በርግጥ የዚህ መስሉ ወንጀል በዚያው በሚያሚ ከ5 ዓመት በፊት በአንዲት የ7 ዓመት ታዳጊ ሴት ልጅ ላይ ተፈጽሟል ። ሆኖም ያ ወንጀል የመጨረሻ ዓይነት መስሎ በመረሳት ላይ ነበር ።



በፖሊሶች በኩል ደግሞ የቴክኒክ ማስረጃዎች በአንድ በኩል ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በሬሳ ላይ የሚደረገው ምርመራ እየተቀላጠፈ ልዩ ልዩ ተጨባጭ መረጃዎችና ግምቶች ሲተንትኑ ሬሳው ከተገኘ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ደግሞ ክትትሉ በየቅርንጫፉ እንዲቀጥል ተደረገ ። የምርመራ ቡድኖችም በሚቿ የቅርብ ጐረቤቶች አካባቢ ሁሉ በመሄድ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት የተለያዩ ምርመራዎችን ማካሄድ ጀመሩ ።

በዚያ መስሉ መሰረታዊና የተቀላጠፈ ማስረጃ ስብሰባ በጾታ ጸባያቸው ለየት ያለ ሁኔታ በሚታይባቸው ላይ የተለየ ትኩረት በማድረግ 60 የሚሆኑ ተጠርጣሪዎች ተይዘው ምርመራቸው በጥንቃቄ ይካሄድ ጀመር ። ሆኖም በተያዙት ተጠርጣሪዎች ላይ በተደረገው ጥብቅ ምርመራ አንዳቸውንም ከወንጀሉ ድርጊት ጋር ሊያዛምዷቸው ባለመቻሉ በኤትል ሊትል ግድያ ላይ ያለመሳተፋቸው በመርማሪዎቹ ተረጋገጠ ።

በሌላ በኩል ግን በዋና መርማሪው ጐንዛሌዝና በሥራ ጓደኛው በዊሊያም ቦነር አንድ ለየት ያለ ሁኔታ ተከሰተ። ሁኔታው የምዕራብ የዘምባባ ዳርቻ ተብሎ በሚታወቀው አካባቢ በአንዲት ሴት ላይ ከደረሰው አሰቃቂ ግድያ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ ተገኘ ። በዚያም ሁኔታ ይህን መሰል የወንጀል ድርጊት በብዛት እንደተፈጸመና ሊፈጸምም እንደሚችል ደረሱበት ። ሆኖም ቀደምሲል የተፈጸሙትን አሰቃቂ ወንጀሎች ከኤትል ሊትል ግድያ ጋር መርማሪዎቹ የሚያገናኙበት ሁኔታ ሊገለጽላቸው አልቻለም ። በተለይም በጣት እሻራ ረገድ ያለውን ጉዳይ ለማጣራት 14 የሚያሚ የነፍስ ግድያ መርማሪ ቡድን በመያዝ የተሰየመው ቡድን የአሻራ

ምርመራ ዘመቻው ያለመሳካቱ በመርማሪዎቹ ዘንድ አሳዛኝ ሁኔታን ፈጥሯል ፣ የአሻራ ምርመራው ሚቿ በምትኖርበት አካባቢ በሚያውቋት ሰዎችና በዘመዶቿ ላይ ሳይቀር ተካሄዶ ውጤት አልባ የመሆኑ ጉዳይ አሳሳቢ ሁኔታን በመፍጠሩ ከሚያሚና ከፍሎሪዳ አቅም በላይ ሆኖ ተገኘ። በመሆኑም ጉዳዩ የተመለከተለትና በዓለም ዓቀፋዊ ችግሩ እንጻር የሚመለከተው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሳይቀር ሊፈታው ያልቻለ አስቸጋሪ ምስጢር ሆኖተገኘ ።

አንድ በ1300 ስሜናዊ ምዕራብ 12ኛ አውራ ጐዳና ላይ የሚገኝ አማካይ ግሮሰሪም ለዚሁ ዘመቻ ሲባል ወደ ፖሊስ ጣቢያነት ተለወጠ ። በዚያው ዘመቻ ከ2500 ሰዎች በላይ በፍላጐት ጭምር እየመጡ አሻራቸውን ከማስመርመር ደረጃ ደረሱ ። የዚያ ሁሉ ውጤት ግን ምንም ዋጋ አላስገኘም ። እንዲያውም የተገላቢጦሽ ባለሥልጣናቹን " የጌስታፖ " ታክቲክ ተጠቀሙ በሚል ይተችዋቸው ጀመር ። በዚያ መስሉ ዘመቻ ከተከማቹት አሻራዎች መካከል አንዳቸውም ከባትሪው ላይ ከተገኘው አሻራ ጋር ሊመሳሰሉ ባለመቻላቸው የምርመራ ካርዶቹን ለማስወገድ ተገደዱ ። በዚያ መልክ ሳምንታት እያለፉ ወራት እየተተኩ ወራትም በዓመታት ተተኩ ። የገዳዩ ምርመራ ጉዳይ ግን የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ ። በሚያሚ የፖሊስ መምሪያ በጉዳይ ላይ ቸልተኝነት ያላሳየና ያልተኛ ሰው አለ ቢባል ጐንዛሌዝ ብቻ ነበር ፣ በዚህም መሰረት አንድ ወንጀለኛ በተያዘ ቁጥር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከኤትል ሊትል ጋር ያለውን ግንኙነት ለማግኘት ሲል የሚያልፈው አንዳችም ምርመራ አልነበረም ። ይህም



ስልት (ሁኔታ) ለወንጀሎች ዝርዝር ጥናት በቂ መረጃዎችን በማሰባሰብ ረገድ ጠቅሞታል ።

በተለይም ጐንዛሌዝና ተከታይዎቹ በፍትወተ ሥጋ ሳንካ በተወነጀሉ ሰዎች ላይ ልዩ ትኩረት ይሰጡ ስለነበር በዚህ ረገድ ያመለጣቸው አንድም ወንጀለኛ አልነበረም ። በሌላ በኩል ደግሞ የኤትልን ግድያ በሚመለከት 60 የሚሆኑ ኑዛዜዎች ቢመዘገቡም ጐንዛሌዝ ከነበረው ልምድና ከፍተኛ ግንዛቤ ከዕውነት የራቁ ሆኖ አግኝቶዋቸዋል ። ያን መሰል የሚያሳስቱና የተወሳሰቡ ጉዳይዎችን አጣርቶ ማቅረብም የዕለት ተግባሩ ስለነበር የኑዛዜዎቹን ሐሰትነት በመመርመር ረገድ ልዩ ንቃት አሳይቷል። በመሆኑም እያንዳንዱ ተናዛዥ ለምን የወይዘሪቷ ገዳይ ለመሆን እንደሚፈልግ በመቆጣጠሪያ ጥያቄዎቹና የምርመራ ስልቱ በመረዳት ተጨባጭነት ያለው ማስረጃ እየተነተነ አቅርቧል ። በዚያው መሰረት የወንጀሉን ድርጊት ፈጽመናል ብለው ለሚቀርቡት ተናዛዥዎች ያቀርብላቸው የነበሩት ጥያቄዎች ሚችን በምን ዓይነት መሳሪያና እንዴት እንደቀጠቀጧት ፣ ለማነቂያውና እግርና እጇቿን ለማሰር የተጠቀሙባቸው ክሮች ወይም ገመዶች ምን ዓይነት እንደነበሩና የመሳሰሉት ናቸው። የተጠቀሱት መረጃዎች ወይም የገመድ ዓይነቶች በጋዜጣና በሬድዮ የተገለጹት በተለያዩ ዓይነትና መረጃ በመሆኑ ትክክለኛውን ሊያውቅ የሚችለው ገዳይ ብቻ ነበር ። በመሆኑም ወሳኝ ጥያቄዎች ነበሩ ። ያም አለ ይህ የገዳዩ ምርመራ ጉዳይ በርካታ ዓመታትን ያለ አንዳች ተጨባጭ ውጤት አሳለፈ። እንዲያውም ምርመራው ገና በእንጭጩ በነበረበት ጊዜ የነበሩት መርማሪዎች ጉዳዩ እልባት ሳያገኝ የጡረታቸውን መብት አስከበሩ ። በምርመራው ከፍተኛ ሚና የነበራቸው ማይክ ፣ ጐንዛሊዝና ዊሊያም

ማክሉር ግን ዕድሚያቸው ለጡረታ ባለመድረሱ በፖሊስ የወንጀል ምርመራ መምሪያ ውስጥ በጉዳዩ የረጅም ጊዜ ልምድ የነበራቸውና ከፍተኛ ተዋናያን ለመሆን በቁ ። ማክሉርም ከመቶ ዕልቅና ወደ ሻምበልነት ማዕረግ በማደጉና በአስተዳደር ሥራ በመጠመድ የኤትል ሊትልን ገዳይ ማሳደድ በጉንዛሌዝ ላይ ተጥሎ ሙሉ ኃላፊነት ተሰጠው ።

ጉንዛሌዝ ሰውነት ቀላል ፡ ቀጠን ያለና ቀልጣፋ እንዲሁም ዘወትር ፈገግታ የማይለየው ስለነበር “ የነፍሰ ግድያ ሮኪ ” በመባልም ይታወቅ ነበር ። በርግጥ በኤትል ሊትል አሳሽ ቡድን ውስጥ ሲመደብ ለሥራው አዲስ ነበር ፡ ሆኖም የወይዘሪቷ ግድያ ጉዳይ ውሎ እያደረና ደብዛው እየጠፋ በሄደ ቁጥር ዓመታትም በዚሁ አኳያ መቆጠር በመያዛቸው ጉዳዩ የግሉ ዓይነት ሆነ። በመጨረሻም ከምርመራው ቡድን አባላት የቀረው ርሱ ብቻ ስለነበር ለጉዳዩ እልባት የመስጠት ሙሉ ኃላፊነቱ በራሱ ላይ ብቻ ተጫነ ። በተለይም የወይዘሪቷ ግድያ እጅግ የተወሳሰበና እልክ አስጨራሽ የመሆኑ ሁኔታ ልዩ ስሜት አሳደረበት እንጂ ተስፋ አላስቆረጠውም ። በዚህም ሁኔታው ቆራጥነቱን በተግባር አስመስክሯል ። በሌላ በኩል ደግሞ በተመሳሳይ ሁኔታ ሌላ የያዘው የወንጀል ጉዳይ በጁአና ብሎክ ላይ የተፈጸመውን ግድያ ነበር የዚያም ግድያ ውስብስብነት ከወይዘሪቷ ጋር ተመሳሳይ የመሆኑ ጉዳይ የወይዘሪቷን የግድያ ምስጢር ለማጋለጥ በር ከፋች ሳይሆነለት አልቀረም ።

ጁአና ብሎክ የ33 ዓመት ዕድሜ የነበራት ቆንጆ ሴት ነበረች ፡ ያቺው ሴት ትዳሯን ፈታ በሚያሚ በ1721 ሰሜን ምዕራብ 41ኛ መንገድ ላይ በሴተ ላጤነት





የሚያሚ የነፍስ ግድያ መርማሪ ማይክ ጉንዛሌዝ የሴተላጤዋን የኤትል ሊትል ግድያ ከ13 ዓመታት ያላቋረጠ ክትትል በኋላ መፍትሔ ሊያስገኝ ችሏል ።

ሕይወቷን በመምራት ላይ እንዳለች በድንገት የሞት
ጽዋዋን የተጐነጨችው በጩቤ ተተርትራ ነበር ። አሰቃ
ቂው ወንጀል የተፈጸመው ከኤትል ሊትል ግድያ ከ17
ወራት በኋላ ቢሆንም የወንጀሉ አፈጻጸም ሁኔታ ማለትም
የድብደባው ፣ የማነቁ ፣ በጩቤ የመሸቅሸቁ ከወይዘሪቷ
አገዳደል ጋር ተመሳሳይነት ነበረው ። በሁለቱ ሴቶች ግድያ
መካከል ጥቂትም ቢሆን ልዩነት አለው የሚያሰኝ ሁኔታ
ቢኖር በጄእና ሰውነት ላይ መጉሳቆልና መቀጥቀጥ ያለመ
ድረሱ ብቻ ነበር ።

የ33 ዓመቷ ሴት ወይዘሮ የተገኘችው ዕርቃን ሥጋ
ዋን ሆና ነበር ። ሃያ ጊዜ በመቀስ ደርቷ ላይ ተወግታለች።
የተወጋችበት መቀስም ባቅራቢያው በሚገኝ የኮሞዲኖ
መሳቢያ ውስጥ ተጥሎ ተገኝቷል ። መታነቁ የደረሰባትም
በእጅ ሲሆን በጥፊ በተደጋጋሚ መጠፍጠፏም ከፊቷ
ይነበብ ነበር ።

ጉንዛሌዝ በሁለቱም ሴቶች ግድያ ረገድ የነበረው
የወንጀል አፈጻጸም ሁኔታ ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ ቢያ
ገኘውም የኤትል ሊትል አገዳደል በጣም ድብቅና ምስ
ጢራዊ ሲሆን የጄእና ግን ለፖሊስ ምርመራ ሻል ያለ
አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ሆኖ አግኝቶታል ።

ጄእና በአሰቃቂ ሁኔታ ተዘርራ የተገኘችው በምትኖ
ርበት አፓርታማ መኝታ ቤት ወለል ላይ ነበር ፣ ሚች የሁለ
ተኛው የዓለም ጦርነት እንደተናጠቀቀ በጀርመን ሀገር በ18
ዓመቷ ከአንድ ሰው ጋር ትዳሯን መሠረተች፣ ቀጥሎም ወደ
ተባበሩት መንግሥታት መጣች ፣ ከጥቂት ዓመታት በኋ
ላም ከባሏ ተፋትታ ሌላ ሰው አግብታ ፈታለች ፣ በዚያ
ዓይነት ሁኔታና መልክ እስከ 1950 ባሉት ዓመታት በር



ከት ያሉ የጋብቻና ፍቺ ሁኔታዎች በሕይወቷ አሳልፋለች።
ከ1950 በኋላ ግን በቡና ቤት ተቀጥራ ትሠራ ጀመር ።

የሚች በትዳር ዓለም ያለመርጋት ሁኔታ በምርመራው
ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ አልቀረለትም ፣ ምክንያቱም ግድያ
ውን ሊፈጽመው የሚችለው ከወዳጆቿ ወይም ከተፈቱ
ባሎቿ አንዱ ይሆናል በሚል ሲሆን በርካታ ወዳጅና
የተፈቱ ባሎችን መጥራትም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቶ ነበር።

በመሠረቱ ጥርጣሬው ያዘነበለው በሁለት ወዳጆቿ
ላይ ነበር ። ሁለቱም ወዳጆዎቿ መኪና አሽከርካሪዎች
(ሹፌሮች) ነበሩ ። ሁለቱንም ካለአንዳች ችግር የምታስተ
ናግደው በተለያዩ ጊዜያት ነበር ፣ ከአንደኛው ጋር በሳም
ንቱ ውስጥ ባሉት ቀናት መካከል በአንደኛው ቀን ስትገናኝ
ከሌላው ጋር ደግሞ በቅዳሜና እሁድ ብቻ ነበር ። የሚገር
መው ጉዳይ አንደኛው ሌላውን ፍጹም የማያውቅና የማይ
ጠራጠር እንዲያውም እያንዳንዳቸው ጄእናን የግል ያደረጉ
ይመስላቸው ነበር ። ጉንዛሌዝ በዚህ ረገድ የነበረውን ሁ
ኔታ ሲገልጽ "ከሞተች በኋላ በምርመራው ሂደት ሁለቱም
በርሷ ላይ በተለያዩ መንገድ የነበራቸውን ግንኙነት ሲገ
ነዘቡ ከመጠን በላይ ተደናግጠው ነበር" ብሏል። ያም ሁሉ
ሆኖ በምርመራው ሁለቱም ከሚች ደም ነጻ ሆኑ ።

ጉንዛሌዝ በመጨረሻ የተገነዘበው ጉዳይ ቢኖር የሚቿ
አሳዛኝ የግድያ ሁኔታ አጋጣሚ ሊሆን እንደሚችል ነበር።
በመሆኑም ክትትሉን ለዬት ባለ ፖሊሳዊ ጥበብ ለመያያዝ
ወሰነ ። በውሣኔውም መሠረት ከሩቅ ሆና ጥቆማ የምትሰ
ጠው ኮረዳ መምረጡ አስፈላጊ ሆና ስላገኘው ሜሪ አላይስ
ብራት የምትባል የአንድ በጡረታ የተገለሉ የፖሊስ ሻም
በል ልጅና የሚች የቅርብ ጓደኛ የነበረች ተመረጠች ። በዚ
ያች ኮረዳ በኩል የሚች ወዳጅ የነበሩትም በተለይም ሁለቱ

ሾፌሮች ተፃኙተዋል ፣ በሟቿ ሕይወት ከፍተኛ ሚና
ይጫወቱ የነበሩ የሌሎች ግለሰቦች ስም ዝርዝርም ተገኝ
ቷል ። በአጠቃላይ ኮረዳዋ የሟቿን ሕይወት እንደመስተ
ዋት ቁልጭ አርጐ በማሳየት ረገድ ለጐንዛሌዛ ከፍተኛ
ድጋፍ ሠጥታለች ።

የግድያው ሁኔታ ማለትም በመቀስ በተደጋጋሚ
መሸቅሸቅ ፣ በባዶ እጅ መታነቅ ፣ በአንገት አካባቢ ያለው
አጥንት መንኮታኮት ፣ በቡጢ የወላለቀው የአገጭዋ አጥን
ትና የመሳሰሉት ከተጠረጠሩት ግለሰቦች ሁኔታ ጋር ሲነ
ጻጸር እንዲያውም ከትትሉን እያጨለመው ሄደ ።

ጐንዛሌዝ ከዕለታት አንድ ቀን በምርመራው ቢሮ
ሆኖ በምርመራ ጉዳይ ተመስጦ ሳለ መረጃ ታቀብለው
የነበረችው ኮረዳ በድንገት መጥታ ከወዳጅዎቿ አንደኛው
የሆነው ሾፌር ግድያው ከተፈጸመበት ጥቂት ቀናት በፊት
ከፍተኛ ግጭት ፈጥሮባት ተጨቃጭቀው እንደነበር
በችኮላ ገለጸችለት ። ጉንዛሌዝ የደረሰው መረጃ ቀላል
ባለመሆኑ ችኮላ እንደማያስፈልገው ገልጦ በርጋታ እንድ
ታዋየው ቢጠይቅም እጮኛዋ ከውጭ ስለሚጠብቃት መታ
ገስ እንደማትችል ገለጸች ፣ ጐንዛሌዝ ግን በረጋ መንፈስ
ለማግባት ስለማቀዷና ስለመታጨቷ እስከዚያ ጊዜ ድረስ
ምንም የሚያውቀው ጉዳይ አለመኖሩን አውስቶ ከእጮኛዋ
ጋር እንድታስተዋውቀውና እጮኛዋ ስለሟችዋ ጓደኛዋ
የሚያውቀው ካለ እንዲነግረው እንድታደርግ በትጋት ጠ
የቀ ። ርሷ ግን እጮኛዋ ጓደኛዋን የሚያውቃት ቢሆንም
ስለ ግል ኑሮዋና ሕይወቷ ከርሷ የበለጠ ምንም ነገር የሚያ
ውቀው እንደሌለ አስረዳች ።

በዚያ መሰል የክትትልና የምርመራ ሂደት የኤትል
ግድያ ጉዳይ አራት ዓመት ተኩል ሲያልፍ የጁአና ግድያ



ደግሞ 3 ዓመት አሳለፈ ። ዓመቱም 1964 አጋማሽ ሆነ ።
በርግጥ ባለፉት ዓመታት የበርካታ ወንጀሎችን ክትት
ልና ምርመራ አድርጓል ። የኤትል ሊትል ግድያ የተ
ዳፈነ ምስጢር ግን ከአንጐሉ ሊሰረዝ አልቻለም ።
ከዕለታት አንድ ቀን በዚያው መንፈስና ትኩረት
ከሜሪ ብራት ምናልባት ተጨማሪ መረጃ አገኝ ይሆን
በሚል እምነት ፈለጋት ። ብራት ግን በተለያዩበት 3 ዓመ
ታት ውስጥ አግብታ ከአካባቢው ወደ ሌላ ቦታ በመዘዋ
ወሯ ሊያገኛት አልቻለም ። ትዝ ያለችውም አንድ
በጥርጣሬ የተያዘ ሰው ሲመረመር ተጠርጣሪው በአብዛ
ኛው ሲዘዋወርና ሲመላለስ ይታይ የነበረው ጁአና
ትሰራበት በነበረው ቡና ቤት አከባቢ መሆኑን እንደተገነ
ዘበ ነበር ። ሆኖም ተጠርጣሪውን በሚመለከት ሌላ የማ
ረጋገጫ ምንጭ በመገኘቱ ሰውየው ከጥርጣሬው ነጻ ወጣ።
ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ ስምንት ዓመታት ያላአንዳች ውጤት
አለፉ ፤ በዕለተ ቅዳሜ ነሐሴ 22-1972 መርማሪ ጐን
ዛሌዝ ለዳዴ ወረዳ ፍ/ቤት የዳኞች ጉባኤ የተጣራ ጉዳይ
ለማቅረብ በመዘጋጀት ላይ እንዳለ የቢሮው ስልክ አንቃ
ጨለ ። ስልኩን እንዳነሳውም በሌላ የወረዳ ፖሊስ የሚ
ገኘውን መርማሪ መ/አለቃ ዊልያም ማክኤልሮይን ሰማ ።
መ/አለቃውም አንድ ሰው በሚያሚ ሁለት ሴቶች መ
ግደሉን እንደተናዘዘለት ሪፖርት አደረገ። ጐንዛሌዝም በሁ
ኔታው በመገረም የሟችን ስም እንዲነገረው ጠይቆ፣ ሊትል
የሚል መልስ አገኘ "ኢትል—ሊትል !" በማለት ጐን
ዛሌዝ ከቁጥጥር ውጭ በሆነ ሁኔታ ጮኸ።በርግጥ ጐንዛሌዝ
ቀደም ሲል ትክክለኛ ያልሆኑ ኑዛዜዎችን በመመርመር
የተሳካላት ቢሆንም በምርመራና በክትትል ሥራው ትክ
ለኛ መስመር ለመያዝ የተስፋ ብልጭታ ሲያይ ከመጠን
በላይ የመደሠቱ ሁኔታ አዲስ ክስተት አልነበረም ። ጐን

ዛሌዝ ትክክለኛ ያልሆን ኑዛዜ በሚሰጡት ግለሰቦች ረገድ ያለውን አሰልቺ ሁኔታ በሚመለከት የዚያ መሰል ደደብ ሰዎች ኑዛዜ ለምርመራ ስራው ተጨማሪ ክብደት አሰልቺ ሁኔታን እንደፈጠሩበት አማርሮ ይናገራል ። መቶ አለቃ ማከኤልሮይ ሰውየው የገደለው ጆአናን መሆኑን አረጋገጠለት ፣ የሆነ ሆኖ ስለሚቿ ጉንዛሌዝ የሚያውቀው ዝርዝር ሁኔታ እንዳለ ጠየቀው፣ ጉንዛሌዝም በሁለቱ ግድያዎችና ሟቾች ረገድ የተሟላ ማህደር እንዳለው አረጋገጠለት ። በሌላ በኩል ደግሞ የቀየውን የምርመራ ሂደት ረጋ ባለመንፈስ እንደገና ማስታወስ ጀመረ ። በጥርጣሬ ስለተያዘውና ስለተናዘዘው ሰው ማንነትም እንዲያሳውቀው ጉንዛሌዝ ጠይቆ ቬርኖን ዴቪድ ኤድዋርድስ እንደሚባል አረጋገጠለት ፣ ስለሰውየውም የሕይወት ታሪክ ትንታኔ በመጠኑም ቢሆን አቀረበለት ። ያው ሰው የአራት ዓመት ህፃን በነበረበት ዘመን ከተወለደበት አትላንታ ወደሚያሚ በ1958 ሂዶ ነበር ፣ ከዚያም በ21ኛው ዓመቱ ወደአትላንታ በመመለስ በትዳር እንደሚኖር አስረዳው ። የሚተዳደረው በቤት ቀለም ቀቢነት ሥራ ሲሆን የሰውነት አቋሙ ግዙፍና ረጅም ከመሆኑ የተነሳ ለሥራው ማከናወኛ በአብዛኛው መሰላል እንደማያስፈልገው ተገልጾለታል ። ቁመት 6.8 ጫማ ሲሆን ክብደት ደግሞ 285 ፓውንድ መሆኑም በተጨማሪም ተነገረው ።

ከሰውየው መግለጫዎች መካከል በተለይ የቁመት ሁኔታ ሲነሳ የጉንዛሌዝን ስሜት ቀሰቀሰ ፣ ይህም የሆነበት በእትል የግድያ ምርመራ ወንጀሉን የፈጸመው ቁመቱ ረጅም ለመሆኑ የተረጋገጠ ስለነበረ ሲሆን በዚያም መሠረት ጉንዛሌዝ በረጅም ዓመታት ክትትሉና ምርመራው ካከማቻቸው ሥራዎች በማንሳት በመቆጣጠሪያነት የሚጠቀምባቸውን ጥያቄዎች ያሾርጉዳጉድልለት ጀመር ። መልሱንም ጉንዛሌዝ በጉጉት ይጠብቅ ስለነበር የተላኩት ጥያቄዎች በአብዛኛው ተመለሱለት ። ጉንዛሌዝም በሁኔታው በመርካት በማግሥቱ ጥዋት በአይሮፕላን ወደ አትላንታ ለመሄድ ወስኖ የምርመራው መዛግብትን ወደአከማቸበት ሳጥን በመሄድ ለምርመራ ሥራው የሚያግዙትንና ከጉዳይዎቹ ጋር የተያያዙ መረጃዎችንና መዛግብቶችን አሰባስቦ ለጉዞው ተዘጋጀ ።



ጉንዛሌዝ በአትላንታ እስከሚደርስ ድረስ ጀምስ ቲ ስታንሌይ የሚባለው የዴካልብ የፖሊስ ሻምበል የተጠርጣሪውን የኤድዋርድን አስተዳደግና የሕይወት ታሪክ በሚመለከት በቂ መረጃዎችን አሰባስቦለት ነበር ፣ ኤድዋርድ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን ያጠናቀቀው በትውልድ ሀገሩ በአትላንታ ሲሆን ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የተመረቀው በ1955 ነበር ። የውትድርና አገልግሎት ሥራም የተመዘገበውና የገባው በ17 ዓመቱ ሲሆን በሰጠውም የ5 ዓመት አገልግሎት የአንድ ዓመት የኮሌጅ ደረጃ አግኝቷል ። በአገልግሎት ዘመኑም ከደንብና ሥርዓት ውጭ እየተገኘ ከአንድየ ሶስት ጊዜ በጦር ፍ/ቤት ቀርቦ የተለያዩ ቅጣቶች ተበይነውበት ተቀጥቷል ። በ1959 በዚያን ጊዜ ቤተሰቦቹ ይኖሩበት ወደነበረው ሚያሚ ሂዶ በቀን 6 ዶላር በመቀበል ከአንድ አነስተኛ የማጓጓዣ መርከብ ተቀጥሮ ይሠራ ነበር ። ሆኖም መርከቧ ወደሌላ አካባቢ በመዘዋወሯ ዓሳ በማስገር ተግባርና አንዳንድ ጊዜም ከመርከቧ ተሳፋሪዎች ጋር በመሳፈር ዕርዳታ በመስጠት ይተዳደር ነበር ። ወደኋላ ጊዜም በቤት ቀለም ቀቢነት ሥራ ተሰማርቷል ። የቀለም ሥራ አሰሪው ስለዚሁ ሰው ሲናገር በጣም ታታሽና ጸባዩ ሸጋ እንደነበር አድርጎ ነበር። ሌላ በጉርብትና የሚኖር ሰው ስለዚያው ሰው ሲናገር ተራ ሰውና መጠጥም በብዛት እንደሚወስድ በዚያው ጠባዩ ካለሚስቱ

በስተቀር ማንም ሰው እንደማይጠጋው ፤ ባለቤቱን ግን ከመጠን በላይ እንደሚያከብርና በርሷም ኩራት እንደሚሰማው አረጋግጧል ። ያው ሰው በሚጠጣበት ወቅት ከፍተኛ አንባጓሮ የሚፈጥርና የሚጮህም መሆኑ በሚገባ ታውቋል ።

በአትላንታ አንድ የመጠጥ አከፋፋይ ኤድዋርድ በየሳምንቱ በደህና ዋጋ 8 ጠርሙስ ዊስኪ ስለሚገዛቸው ጥሩ ደንበኛቸው እንደሆነም ተናግረዋል ።

ጉንዛሌዝ ኤድዋርድን በሚመለከት የተቻለውን ያህል መረጃዎች ከሰበሰበና ካጠናከረ በኋላ ከባለታሪኩ በመገናኘት የበለጠ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ይቻለው ዘንድ ኤድዋርድ ወዳለበት ሂዶ በመ/አለቃ ማከኤልሮይል አማካኝነት ተዋወቀ ። ከዚህ በኋላ ዕውነቱ ፍርጥርጡ የሚወጣበትና የመረጃዎችን ዓውደ ጥበብ የሚጠቀምበት ወቅት እየተቃረበ መጣ ። ጉንዛሌዝ ንግግሩን የጀመረው የኤድዋርድን ሕጋዊ መብት የሚገልጽ ጽሑፍ በማንበብ ሲሆን ከዚህ በኋላ ወደጥያቄ ማቅረቡ ጉዳይ በቀጥታ ገባ ።

ጉንዛሌዝ ኤድዋርድን በቅድሚያ የጠየቀው "ኤትል ሊትልን መግደልህና ትላንትና ለባለቤትህ መንገርህን ርሷም ሂደህ ለፖሊስ አሳውቅ ማለቷን ታረጋግጥልኛለህ?" በማለት ሲሆን ኤድዋርድም " እዎን ልክ ነው ! እንዲያውም ራሷ ሄዳ ለፖሊሶች እንድትደውል ስለነገርኳት ፖሊሶች መጥተው የወሰዱኝ ከደወለችላቸው በኋላ ነው" ብሏል ።

ጥያቄ ፦ ለባለቤትህና ለፖሊስ ስለ ኤተል ሊትል ግድያ ለመንገር የተገደድከውና የወሰንከው ለምንድን ነው ?



መልስ ፡ በበኩሌ ጉዳዩን ሳስበውና ሳልመው የሕሊና ጸጸት ስለያዘኝ ነው ።

ጥያቄ ፦ ከዚህ በፊት በአጋጣሚ ስለ ኤትል ሊትል ግድያ ለሌላ ሰው አውስተህ ታውቃለህን ?

መልስ ፦ አላወሳሁም ።

ጥያቄ ፦ ገድለሃታል ወይ ?

መልስ ፦ አዎን

ጥያቄ ፦ ግድያ በርሷ ላይ ከመፈጸምህ በፊት ታውቃት ነበርን ? ( ይህ ጥያቄ ሆን ተብሎ የተጠየቀው ኤትል ሊትል የተወለደችው ገዳይዋ በተወለደበት ከተማ አትላንታ ውስጥ ስለነበር ነው )

መልስ ፦ አላውቃትም

ጥያቄ ፦ የተገደለችበትን ቦታ ታውቀዋለህን ?

መልስ ፦ ትክክለኛውን አድራሻ ባላውቀውም ፡ የትኛው መንገድ እንደሆነ ግን አውቃለሁ ፤

ጥያቄ ፦ በዚያን ጊዜ የት ትኖር ነበር ?

መልስ ፦ 32ተኛና 13ተኛ አውራ ጐዳና ላይ

ጥያቄ ፦ ከማን ጋር ትኖር ነበር ?

መልስ ፦ ከእናቴና ከአባቴ ጋር

ጥያቄ ፦ መልካም ፈቃድህ ከሆነ የግድያው ሁኔታ እንዴት ሊከሰት እንደቻለ በዝርዝር በራስህ ቃላቶች ልትገልጽልኝ ትችላለህን ?

መልስ ፡- የተጀመረው ያንለቱ ነው። በዚያን ዕለት የምሰ ራበት ኩባንያ በኤይቲሲክስ ሀንድረድ ክበብ የገና ድግስ አዘጋጅቶ ስለነበር የተትረፈረፈ የ መጠጥ ግብዣ ነበር ። እኔም መጠጥ ከአቅሚ በላይ መውሰድ ጀመርኩኝ ፤ ከግብዣውም በኋላ አልበቃ ብሎኝ ይባሱን ለመጠጣት ከፍተኛ ም ኞት ተቀሰቀሰብኝ ። ሆኖም ኪሴ ባዶ ስለነበረ ወደ ቤቴ በመሄድ ላይ ሳለሁ ገንዘብ ከአንዷ መንትፈህ መጠጣትን ቀጥል የሚል ሃሳብ መጣ ብኝ ፤ ወይዘሪት ሊትልም በቤቷ ገብቼ አደርግ በነበረው እንቅስቃሴና ማንጓጓት ነቃችብኝ ፤ እኔም መኝታዋን እንደተመለከትኩና እንደደረ ስኩበት አልጋዋ ላይ እንዳለች አፈንኳት ።

ጥያቄ ፡- እንዴት በአፓርታማዋ ልትገባ ቻልክ ?

መልስ ፡- የኋላውን በር የመስተዋት ተካፋች በማንሳት አፓርታማዋ ውስጥ ገብቻለሁ ፤

ጥያቄ ፡- የመስተዋቱን ተካፋች የት አደረከው ?

መልስ ፡- መልሼ ከበሩ ላይ መሰካቴ ወይንም ከምድር ላይ ማስቀመጤ ትውስ አይለኝም ! (እንደሚመስ ለው የመስተዋቱንተካፋች በቦታው መልሶታል። ተከታታይዎቹም ድርጊቱ በተፈጸመበት ወቅት እንዲህ ዓይነቱ ተካፋች ለመንቀ ሳቀሰምንም መረጃ አላገኙም ነበር ።)

ጥያቄ ፡- በቦታው ላይ ከምሽቱ ስንት ሰዓት ላይ ደረስክ ?

መልስ ፡- በግምት ከሌሊቱ 8 ሰዓት ደርሻለሁ

ጥያቄ ፡- እንደገባህ በመጀመሪያ ምን አደረክ ?



መልስ ፡- እንደማስታውሰው ከሆነ ወጥ ቤቱ ውስጥ ጠቅ ላላ ልብሴን አወለኩ ፤

ጥያቄ ፡- ምን ዓይነት አፓርታማ ነበር ?

መልስ ፡- ከአንድ ትልቅ ፎቅ በስተጀርባ የሚገኝ አነስ ያለ አፓርታማ ነበር ።

ጥያቄ ፡- ከዚያ በፊት በዚህ አፓርታማ ውስጥ ነበርክወይ?

መልስ ፡- አልነበርኩም

ጥያቄ ፡- ቀጥሎም የሆነው ምን ነበር ?

መልስ ፡- ከእንቅልፏ ስትነቃብኝ ጊዜ ከፊቷ ላይ አንድ ትራስ አደረኩባት ፤ ከዚያ በአልጋዋ ላይ መታ ገል ጀመርን ፤ ከዚያም አነቅኳት፤ ልብስዋን አወ ላልቄ ከጨረስኩ በኋላ በቬኒሺያን የመጋረጃ ክር አሰርኳት ፤ በዚያን ሰዓት እንደሚመስለኝ ሳትሞት አልቀረችም ። ወደ ኩሽና እንደገና ተመልሼ አንድ ቢላዋ ከወሰድኩ በኋላ የግራ ጡቷን ቆረጥኩት ፤

ጥያቄ ፡- ለምን እንደዚያ አደረክ ?

መልስ ፡- እንጃ ! ምናልባት ክፉኛ ስለሰከርኩ ይሆናል ።

ጥያቄ ፡- ምን ዓይነት ቢላዋ ነበር ?

መልስ ፡- በትክክል የማስታውሰው ነገር ቢኖር ቢላዎው ተራና በወጥ ቤት ውስጥ የሚጠቀሙበት ዓይ ነት መሆኑን ነበር ። ምናልባት የእንጨት እጀታ ያለው የወጥ ቤት ቢላዋ ሳይሆን አይቀርም ።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ ጥያቄዎች የወንጀሉን ድርጊት በትክክል ሊገጣጥሙና ሊያመለክቱ ይችሉ ዘንድ ተቀጣጥለው ቢቀጥሉም መልሱም ያለአንዳች ማመንታት እንዲሁ ይጎርጉዱጉድ ነበር ። በተለይ የቀረቡት ዝርዝሮች ገዳዩ ብቻ ሊያውቃቸው የሚችሉ ነበሩ ።

ጥያቄ ፦ በቢላዋው ወግተሃት ነበር ?

መልስ ፦ የወጓኋት ይመስለኛል

ጥያቄ ፦ ስንት ጊዜ ?

መልስ ፦ አይታወሰኝም

ጥያቄ ፦ በሌላ አካላቷ ላይ ያደረከው ነገር ነበርን ?

መልስ ፦ አይመስለኝም

ጥያቄ ፦ ጡትዋን የቆረጥከው በሙሉ ነው ወይስ በከፊል?

መልስ ፦ ሙሉውን ጡት ነው የቆረጥኩት

ጥያቄ ፦ ሌላ በርዕ ላይ የፈጸምከው አለ ?

መልስ ፦ የእጅ ባትሪውን በመጠቀም በመቀመጫዋና በብልትዋ አስገብቻለሁ ፤

ጥያቄ ፦ ምን ዓይነት የእጅ ባትሪ ነው ?

መልስ ፦ የብር ቅብ የሆነ ባለሁለት ባትሪ ነበር

ጥያቄ ፦ በየትኛው በኩል ነው ያስገባህባት ?

መልስ ፦ በታችኛው በኩል



ጥያቄ ፦ የባትሪው የታችኛው ቅርጽ ምን እንደሚመስል ታስታውሳለህ ?

መልስ ፦ የጥይት ቅርጽ ያለው ይመስለኛል

ጥያቄ ፦ ለምንድነው ባትሪውን ያስገባህባት ?

መልስ ፦ አላውቀውም ! በጣም ስለሰከርኩ ይመስለኛል

ጥያቄ ፦ ድርጊቱን የፈጸምከው ከማሰርህ በፊት ነው ወይስ በኋላ ?

መልስ ፦ በኋላ ነው

ጥያቄ ፦ እንዴት ነበር ያሰርካት ?

መልስ ፦ አላስታውሰውም የማስታውሰው ፤ በቬኒሺያን መጋረጃ ክር ማሰሬን እንጂ በትክክል የኦስተሳሩን ዓይነት አላስታውሰውም ።

ጥያቄ ፦ ሌላ ምን አደረክ ?

መልስ ፦ ገንዘብ ፍለጋ ቤቱን በርብሬ 50 ወይም 60 ዶላር የሚያክል አግኝቻለሁ

ጥያቄ ፦ የት ቦታ ነው ብሩን ያገኘኸው ?

መልስ ፦ በኮሚዲኖው ወይንም በልብስ ማስቀመጫው መሣቢያ ውስጥ ይመስለኛል ።

ጥያቄ ፦ ከማስታወሻ ደብተርዋ ውስጥ የወሰድከው ነገር ነበርን ?

መልስ ፦ ገንዘብ ባገኘኑር ስለማልምረው ወስጄ ይሆናል።

ጥያቄ ፦ የታነቀችው በእንገቷ በተጠመጠመው ነገር ነው ? ወይስ በሌላ ነገር ?

መልስ ፦ (ብዙ ካሰበ በኋላ) እንደሚመስለኝ በቬንሽያኑ መጋረጃ ከር ቁራጭ ሳይሆን አይቀርም ፤

ጥያቄ ፦ በዚያ ሳለህ ወደ ቁም ሳጥኑ ሂደህ ነበርን ?

መልስ ፦ ምናልባት ፤

ጥያቄ ፦ ለምን ?

መልስ ፦ ዝም ብዬ ለመመልከት ፤

ጥያቄ ፦ በቁም ሳጥኑ ምን እንደነበር ታስታውሳለህ ?

መልስ ፦ የገና ስጦታዎች የነበሩ ይመስለኛል ፤

ጥያቄ ፦ በሌላ ቦታስ የገና ስጦታዎች ተቀምጠው ተመልክተሃል ?

መልስ ፦ አዎን ፤ በከፊል በወጥ ቤቱ ጠረጴዛ ተቀምጠው ያየሁ ይመስለኛል ።

ጥያቄ ፦ ፍትወት ሥጋ ለመፈጸም አስበህ ነበርን ?

መልስ ፦ ይህ ጥርጣሬ ሊኖር አይገባም ፤

ጥያቄ ፦ ፍትወት ሥጋ ከርሷ ጋር ፈጽመሃል ወይ ?

መልስ ፦ አልፈጸምኩም ፤

ጥያቄ ፦ ለምን ?

መልስ ፦ በጣም ሰክሬ ስለነበር ፤

ጥያቄ ፦ ትራሱ በሌላ ቦታ ተጥሎ የተቀመጠበትን ቦታ ታስታውሰዋለህን ?



መልስ ፦ ምናልባት በስተግርጌዋ ሊሆን ይችላል ፤

ጥያቄ ፦ ስታስቀምጠው ታስታውሰዋለህን ?

መልስ ፦ አላስታውሰውም ፤

ጥያቄ ፦ ታዲያ ለምን በስተግርጌዋ ነበር አልክ ?

መልስ ፦ ምክንያቱም አስቀምጥበታለሁ ብዬ የማስበው ከዚያ ቦታ ስለነበር ነው ፤

ጥያቄ ፦ ለምን ገደልካት ?

መልስ ፦ ሰላየችኝ ነው ፤ በአንድ መንገድ ስለምንኖር ሌላ ቀን ካየችኝ ስለምታውቀኝ በመፍራት ነው ፤

ጥያቄ ፦ (ኤድዋርድ ከቤተሰቦቹ ጋር ይኖርበት የነበረው ቤት ከሚችዋ ቤት ሰባት ቤቶችን አልፎ ነበር) ልትገድላት ስትሞክር ብዙ ታግለህ ነበርን ?

መልስ ፦ አዎን ?

ጥያቄ ፦ እንዴት ?

መልስ ፦ ተጠመጠመችብኝ ፤ ታገለችኝ ፤ ነከሰችኝም ፤

ጥያቄ ፦ የት ቦታ ነከሰችህ ?

መልስ ፦ አውራ ጣቴን ፤

ጥያቄ ፦ የትኛውን ?

መልስ ፦ ይኸው ! የቀኝ አውራ ጣቴን ፤

ኤድዋርድ የኤትል ሊትል ግድያ በትኩሱ በተነዛበት ጊዜና ክትትል በሚደረግበት ወቅት በጥርጣሬ ተይዞ እንዲት የሴት ፖሊስ መጠይቅ አቅርባለት እንደነበር አስታ

ውስ “ በአውራጣቴ አስሬ የነበረውን ፋሻ በፍጹም አላስታወሰችውም ፤ ስለርሱም ምንም አልጠየቀችኝም ” ቀጥሎም “ በአውራ ጣቴ ላይ ፋሻዬን አስሬ ስታዩኝ ከአሁን አሁን ትጠይቀኝኛለች በሚል ተጠባብቄያት ነበር ፤” ብሏል ። ኤድዋርድም በዚያን ጊዜ ከአካባቢው የአሻራ መሰብሰብያ ዘመቻ ሊያመልጥ ችሏል ።

ጥያቄ ፡- እንዴት አመለጥክ ?

መልስ ፡- ከውጪኛው ግሮሰሪ ውስጥ ገብቼ በዚያው ለመሹለክ ስላመቸኝ ተሰወርኩ ።

ጥያቄ ፡- የሚች ሁኔታ እንዴት ነበረ ?

መልስ ፡- አላስታውሰውም ፤

ጥያቄ ፡- በልብስ ኮሞዲኖው ላይ በነበረው መስተዋት ምን እንደነበረ ታስታውሳለህ ?

መልስ ፡- የሚታይ ነገር አልነበረም ፤

ጥያቄ ፡- ጡትዋን ስትቆርጣት በሕይወት ነበረች ወይ ? (ኤድዋርድን ለመፈታተን ጐንዛሌዝ ያቀረበው ጥያቄ ነው )

መልስ ፡- አልነበረችም

ጥያቄ ፡- እንዴት አወቅህ ?

መልስ ፡- አልደማችም

ያን ሁሉ አሰቃቂ ግፍ ሲፈጸም ራቁቱን እንደነበርና ቢላዋውን እንደ ተወው ባያስታውስም እጁን መታጠቡንና ለባብሶ ከቤቱ መውጣቱን ሁሉ አስታውሷል ። አንዳንዱንም መዘባረቁ አልቀረም ። ለምሳሌ ጐንዛሌዝ በብልትዋ የእጅ ባትሪ ስታስገባ ትወራጭ ነበር ወይ ? ተብሎ ሲጠየቀው በዚ



ያን ሰዓት የሞተች ሆና እንደተሰማው ነግሮታል ። እንደዚሁም እንዴት ብሎ እንዳነቃት በትክክል ሊመልስ አልቻለም ። ጐንዛሌዝ ከቁም ሳጥኑ የሳበውን ሽቦ እንዲያስታውስ ቢጠየቅም ማስታወስ አቅቶታል ።

የእሁድ ትምህርት ቤት አስተማሪዋን ሕይወት ለማጥፋት የፈለገበትንም ምክንያት በተደጋጋሚ ቢጠየቅ አለማስታወሱን ተናግሯል ። ሆኖም ኤድዋርድ አንዳንድ ነገር በዝርዝር እያስታወሰ አንዳንዱን መርሳቱ ሰክሮ የነበረ መሆኑን ያረጋግጣል ። እንዲያውም በጥያቄዎቹ መሀል ኤድዋርድ ጐንዛሌዝን ፍጥጥ ብሎ እየተመለከተ “ አንተ ሰውዬ ለብዙ ዓመታት ጉዳዩን ትከታተለው ስለነበረ በዝርዝር ለማስታወስ ትጥራለህ ፤ እኔ ደግሞ በዚሁ ሁሉ ዓመታት ጉዳዩን ለመርሳት በመጣሬ ብዙ ነገሮች ሊረሱኝ ይችላሉ ። ” ብሎ ጮሆበታል ።.

ያም አለ ይህ ግዙፉ የቤት ቀለም ቀቢ ሊያሳምነው በመቻሉ በትክክል ይፈልገው የነበረው ሰው ለመሆኑ አልተጠራጠረም ። ለአንድ ግትር ተከታታይ ይህ ውሳኔ ቆራጥነትን ይጠይቃል ። ከመቶ ያለነሱ የኤትል ሊትል ተናዛዦችን ሳይቀበል የቀረው ጐንዛሌዝ ኤድዋርድ በሰጠው መልሶች በመተማመን ቴሌፎኑን አንስቶ ወደሚያሚ ማዕከላዊ የአሻራ መዝገብ ቤት በመደወል የእጅና የመዳፍ አሻራ እንዲላክለት ጠየቀ። ጐንዛሌዝ የአሻራውን ቅርጽና መለያዎች በሚገባ ማንበብ ስለሚችል በዝርዝር በቴሌፎን መልዕክቱን አስተላለፈላቸው ። በዚያም መሠረት ከወንጀሉ ቦታ ለማመሳከሪያ ከተያዘው የጣት አሻራ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ተገኘ ። ከዚያ በኋላ ጐንዛሌዝ ኤድዋርድን ለፈጸመው የግድያ ወንጀል በቁጥጥር ስር ማዋሉን ገለጸለት ። ኤድዋርድም አዎን አውቀዋለሁ በማለት ሳይረበሽ ጉዳዩን ተቀበለው ።



ቹርኖን ዴቪድ ኤድዋርድ ጂ፣ አር የሊትል እና የባሪስትዋ ጂእና ብሎክ ገዳይ ነኝ ብሎ ተናዘዘ ። በጐንዛሌዝ እነጋገር ገዳዩ ከጃክ ሪፐሩ ተመሳሳይ የሆነ የእንጐል መታወክ ያለበት ነው ። /ሚያሚ ሔራልድ/



ጐንዛሌዝም ወደ ፍሎሪዳ ተጓዘ ፤ የሄደውም ከበላዮቹና ከዓቃቤ ሕግ ቢሮ ጋር ለመመካከር ነበር ። የኤድዋርድ ት ግ\ ከሚገባው ውጭ ይሆን ወይ የሚል ጥያቄም ተመላልሶ በአንጐሉ ተጉላላ ። መልሱ ግን አይደለም ነበር ። ኤድዋርድ ወደሚያሚ በራሱ ፈቃደኝነት ሂዶ ቅጣቱን በመቀበል ፊት ለፊት እንደሚጋተር ተማመነ ።

ኤድዋርድ በዚያው መሠረት በጐንዛሌዝ አጃቢነት ወደፍሎሪዳ ከተመለሰ በኋላ በወንጀለኞች መመዝገቢያ መዝገብ ውስጥ የሁለት ሴቶች የግድያ ወንጀል ፈጻሚ በመ ሆን ተመዘገበ ።

ጐንዛሌዝ የረጅም ጊዜ የክትትልና የምርመራ ሁኔታውን ካስታወሰ በኋላ “ ኤድዋርድን የለየለት አፋኝ ወይንም ነፍሰ ገዳይ ይሆናል ብሎ የሚገምትም ሆነ የሚያምን ሰው ሊኖር አይችልም ፤ በመሆኑም የርሱ ጉዳይ ለፖሊስ ምርመራ ጥሩ ናሙና ነው ። በአንድ አካባቢ አን ድ ሰው ለብዙ ጊዜ ከቆዩ የዕውነተኛ ወንጀለኛ ገጽታ ወይም ጥርጣሬ አይኖረውም ። እንዲሁም ገዳይዎች በሰውልቡና የሚያሳድረውን ዓይነት ጠባይዎችና ገጽታ አይዙም ፤ በተለይ በፍትወተ ሥጋ ግንኙነት ምክንያት ሰው በሚገድሉት ላይ ይህ ሁኔታ አያስታውቅም ፤ በሲኒማና በቴሌቪዥን የሚቀርበውን የነፍስ ገዳይዎች ገጽታ በመመልከት ገዳይዎች የተለዩ አስፈሪና አስደንጋጭ ገጽታ ያላቸው መስሎ ይቀርባል ፤ በአብዛኛው ግን አይደሉም ። ጐረቤት የሚገኘውን ማንኛውንም ዐይነት ሰው ነው የሚመስሉት፣ በርግጠኛ የእነርሱን ልብ የሚያነሳሳ ወይም የሚነካ ለየት ያለ ችግር በሕይወታቸው ሊያጋጥማቸው ይችላል ” ። ብሏል ።

ጉንዛሌዝ እንደኤድዋርድ ዓይነቱ ለምን ወ/ት ኤትል
ሊትልና ወ/ሮ ጁአናን ለመግደል ተነሳሳ የሚለውን ጥያቄ
እያነሳ ማብሰልሰሉ አልቀረም ። በዚህም ረገድ ያለውን
ሁኔታ ሲያስረዳ “ አንዱ ሊገባኝ ያልቻለ ጉዳይ ቢኖር ይ
ኸው ብቻ ነው፤በሁለቱም ግድያዎች በኩል የፈጸማቸውን
ሁኔታዎች በዝርዝርና በአጥጋቢ ሁኔታ ቢናዘዝልንም አሁ
ንም ኤድዋርድ ድርጊቱን ለመፈጸም የገፋፋውን ምክንያት
ለማፈቅ ባለመቻሌ ፍላጎቴ አልረካም ። በሚያሚ ፖሊ
ስ መምሪያ ባሳለፍኩት የምርመራ ሥራ ዘመኔ ከሺ በላይ
የሚሆኑ የነፍስ ግድያ ወንጀሎችን ሳስተናግድ በግምት አም
ስት መቶዎች የልጃገረዶችን ክብረንጽህና አስገድዶ የመው
ሰድ ወንጀሎች ነበሩ ። በዚህ ሰውዬ ላይ ግን የነበረው ሐሳብ
ምን እንደነበረ ለማወቅ ብጥርም አልቻልኩም ፣ ስለሆነም
አሁንም ቢሆን ምን ያስብ እንደነበር ለማወቅ በጣም እጥ
ራለሁ “ ይል ነበር ። ጎንዛሌዝ ሐሳቡን በማያያዝ ” ኤድ
ዋርድ የአስተዳደጉን ሁኔታ እንዲነገረኝ ጠይቄው ተረድ
ቻለሁ ምናልባት ለአገዳደሉ ምክንያት ሊሆን የሚችል የጠ
ራ ሁኔታ ሊያሳዩኝ ችሎ ይሆናል ። ሆኖም ሌላው ቀርቶ
ራሱ በትክክል የገደለበትን ምክንያት አያውቀውም ነበር።
እኔ ግን በትክክል ይህ ነው ለማለት ባልችልም በህጻንነቱ
ካሳለፈው ሕይወት ጋር የተያያዘ ለመሆኑ አልጠራጠርም”
በማለት ማስረዳቱን ቀጥሏል ።

ጉንዛሌዝ ስለ ኤድዋርድ የልጅነት ሕይወት ሁኔታና
ጊዜ በዝርዝር በመጠየቁ በጣም ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎ
ችን ለማሰባሰብ ችሏል ። ኤድዋርድ ያደገው ከቤተሰቦቹ
ጋር ነበር ፤ አሥራ ሁለት ዓመት እስኪሞላው ድረስ በጣም
በሚያስደስት የልጅነት ጊዜ አሳልፎ ነበር ። ኋላ ግን ወላጅ
አባቱ በሂሳብ ሥራ በተሰማሩበት አንድ ትልቅ ኩባንያ



ውስጥ በከባድ የገንዘብ ቅጥፈት ወንጀል ተወንጅለው ፍ
ርድ ቤት ቀርበው ከተፈረደባቸው በኋላ ታስረዋል ። ኤድዋ
ርድ በዚያን ጊዜ በጣም ወጣት የነበረ ቢሆንም በናትና በአ
ባቱ መካከል የነበረው ፍቅር ከልቡናው ሊፋቅ አልቻለም ።
ነገር ግን ወላጅ እናቱ ባለቤታቸው በዚያን መሰል ወንጀል
ተከሰው መታሰራቸውን ሲያውቁ በሁኔታው በመቆጣት
ፈተዋቸዋል ። ያ ሁኔታ የኤድዋርድን ስሜት ስለነካው በ
ናቱ ላይ ቂም ይዞ ነበር ። ጉንዛሌዝ እንዳስረዳው ከሆነ በመ
ሠረቱ ኤድዋርድ ክፉና ጨካኝ ሰው አልነበረም ። የሆኖ
ሆኖ የልጅነቱ ዘመን እንዲታወስበት አይፈልግም።የአባቱና
የእናቱ መፈታት ክፉኛ መንፈሱን እንደረበሸውና እንደነ
ካውም ለጉንዛሌዝ ተናግሯል ። ብዙ ሌሎች የልጅነት
ጊዜ ሁኔታዎችን እያስታወሰና እያነሳም ተንሰቅስቆ ያለ
ቅስ እንደነበር በተጨማሪ ገልጾለታል ። በዚያ ታሪኩ
ያባቱን ወንጀል ፈጽሞ ካለማመኑና ካለመቀበሉም በ
ላይ እናቱ ለመፈታት ያአደረጉት ድርጊት በጣም አስቆ
ጥቶት እንደነበር ያወሳል ።

በመሆኑም በጉንዛሌዝ አባባል የኤድዋርድ ቂም በእ
ናቱ ምክንያት የተጸነሰ እንደነበርና ለሰው ልጅ የእናት
ጉዳይ እንጉል እንደሚበጠብጥ ነገር አድርጎ ለመገመት መ
ቻሉ ተገምቷል ። በዚሁ አኳያ ኤድዋርድ ለጉንዛሌዝ እን
ዳስረዳው እናቱን በጣም ይወዳቸዋል ፤ እንዲሁም በጣም
ይጠላቸዋል ። ሆኖም ወደነበረበት ሁኔታ ለመመለስ በጣም
ምኞት ነበረው ።

በሌላ በኩል ደግሞ አባቱ እስር ቤት በነበሩበት ጊዜ
ለመጠየቅ ፈልጎ እናቱ እንዳይጠይቅ ስለከለከሉት አንድ
መኪና ሰርቆ አባቱ ያሉበት እሥር ቤት ድረስ በመሄድ ጠ
ይቋቸዋል ። መኪና መስረቅ የመጀመሪያ ጊዜ ወንጀሉ ቢ
ሆንም ምን ያህል አባቱን ያፈቅር እንደነበር ግን ከዚህ መገ

መት ይቻላል ። በዚያው የመኪና ስርቆት ወንጀል ተከለ
በጠባይ ማረሚያ ለ7 ወራት እንዲቆይም ተደርጓል ።

ኤድዋርድ ኤትልን በገደለበት ምሽት እንጉሉ በነ
ባር የነገር ቁስሎች ተወጣጥሮ እንደነበር ጉንዛሌዝ ገም
ቷል ። ከኑዛዜውም ለመረዳት እንደተቻለው ባለፉት ዓመ
ታት በወይዘሪቷ መስኮት እየተሾለከ አልጋዋ ላይ እንዳለች
ይመለከታት ነበር ፣ ከታሪኩ ለመረዳት እንደተቻለው ወደ
ተዘጋጀው የኩባንያው የገና ድግስ እንደሄደ በጣም ከመ
ጠጣቱ በተጨማሪ ሪንስ ዴክስሪንስ (የሚያዝናኑ እ
ንክብሎች) ይወስድ ነበር ። በግብዣው ሥነ ሥርዓት
ወቅት በዝርዝር እንኳ ባያስታውሰውም በአንድ በሥራ
ባልደረባውና በዕድሜ ገፋ ካለች ሴት ጋር ጨዋታ ይዞ
እንደነበርና ከሚያስፈልገው በላይ ይንከባከባትና በጨዋ
ታም ጠምዷት እንደ ነበር ትዝ ብሎታል ። ከዚያም አንድ
ያልታሰበ ድርጊት ፈጽሞ ተወቅሶበት ፣ በጉዳዩም በጣም
ተርበተበተ ፣ ተጨነቀም ፣ ቀጥሎም የሚያስታውሰው
ነገር ቢኖር በኤትል ሊትል አፓርታማ ውስጥ መኖ
ሩን ነበር ።

ጉንዛሌዝ ኤድዋርድን ያን የመሰለውን የሚዘገንን
ወንጀል በሴት ላይ ለመፈጸም የተገፋፋው በእናትና በአ
ባቱ በደረሱት ሁኔታዎች ሳቢያ በሴቶች ላይ ልዩ ጥላቻ
በማካበቱ መሆኑን ገምቷል ። ይህን እምነቱን ግን ፍጹም
ለማድረግ ሌላው ቀርቶ ኤድዋርድ ከወህኒ ቤት እንዳለ
ለምን ያን የመሰለ አሰቃቂ ወንጀል እንደፈጸመ ደግሞ
ይጽፍለት ነበር ፣ ሆኖም በትክክል የጠበቀውን ያህል ሊደ
ርስበት አልቻለም ።

ኤድዋርድ በሌላም በኩል የጄአናን ግድያ ከኤ
ትል ሊትል ግድያ በተሻለ ሁኔታ ሊያስታውስ አልቻ



ለም ፣ የፈጸመው ወንጀል የመንፈስ ጸጥታ ስለነሳውና የጎ
ሊና ወቀሳው ጤና ሰላሳጣው ከባለቤቱ ጋር አትላንታ በነ
በሩበት ጊዜ ስለ ግድያዎቹ ገልጾ በተያዘበት ቀን ማለትም
ነሐሴ 22/1972 ስለጄአና ተናግሯል ። ሆኖም ስለጄአና
ሲናገር “ የጓደኛዋን ገዳይ ሳታውቅ ካልሆነ በስተቀር አቅ
ፋየምትኖር ሴት የመኖሯ ሁኔታ አጠራጣሪ ነው ።” ብሏል

ወይዘሮ ኤድዋርድ የተባለችው ከማግባቷ በፊት ሜሪ
አለይስ ብራት በመባል የምትታወቀው ባለቤቱደግሞ በከ
ትትሉ ሂደት ከፍተኛ ሚና የነበራት መሆኑ ሲታወቅ ነገ
ሩን ይብስ ጉድና አስገራሚ አድርጎታል ። ባለቤቱ ለቀድ
ሞው የሚያሚ ፖሊስ ጣቢያ መርማሪ ለጉንዛሌዝ ስለ
ጄአና ዋና ዋና መረጃዎችን ታቀብለው የነበረችው
ነበረች ። ይህችው ሜሪ አላይስ ብራት ለጉንዛሌዝ መረጃ
ለመስጠት በአስቸኳይ ከቢሮው ድረስ ሄዳ እጮኛዋ ከፖ
ሊስ ጣቢያ ውጭ ይጠብቃት እንደነበርና እጮኛዋ ደግሞ
ምንም ያህል የሚጠቅም መረጃ ሊሰጥ የማይችል መሆኑን
የተናገረችው ባጭሩ “ እያውቃትም ርሱ የሚያውቃት እኔ
አብሬው ባለሁበት ጊዜ ስላያት ብቻ ነው ” በማለት ነበር።

ኤድዋርድ የጄአና ግድያ እንዴት እንደፈጸመ ተና
ዟል ፣ የግድያውንም አፈጻጸም ሁኔታ እንዳስረዳው በግን
ቦት26/1962 ጄአና በአስተናጋጅነት ወደምትሠራበት ቡና
ቤት ካደረሳት በኋላ የቀረበለትን መጠጥ ተጎነጨ፣ ከዚ
ያም ባለቤቱን ወደ ቤቷ አድርሶ እንደገና ወደም መጠጥ
ቤቱ ተመለሰ ፣ በመጨረሻም ጠብቆ ወደ ቤቷ ካደረሳት
በኋላ በአሰቃቂ ሁኔታ መግደሉን በዝርዝር አስረድቷል።የሆ
ነ ሆኖ ለምን ግድያውን እንደፈጸመ ለጉንዛሌዝ እንኳን በ
ውል ሊነግረው አልቻለም ። መርማሪዎቹን ያስገረመ ነገር
ቢኖር ስለግድያው ለፖሊሶች አንዳንድ ጥቃቅን ነገሮችን
ማስመዝገቡና በተለይ መርማሪዎቹ ግድያውን ኤድዋርድ

ይፈጽመዋል ብለው ይገመቱ ስላልነበረ ከግምት ውስጥ
ሳያስገቡት መቅረታቸው ነው ። ጐንዛሌዝ ከምርመራ ትዕ
ግሥቱና ቆራጥ አቋሙ የግዳያዎቹ መረጃ ግምጃ ቤት ለመ
ሆንም በመቻሉ በዚያ ግንዛቤና ዕውቀቱ ለግድያው ጉዳይ
ከፍተኛ እልባት አስገኝቷል ። እርግጥ ነው ኤድዋርድ ለመ
ናዘዝ ቀርቧል ። ሆኖም 13 ዓመታት ባሳለፈ የግድያ ታሪክ
ላይ ተመጣጣኝ ጥያቄ በማቅረብ ነገሩን የዛሬ 13 ዓመት
በተፈጸመበት ሁኔታ ባይቀነባበር ኖሮ የኤድዋርድ ኑዛዜ
ይረሳ ወይም እንዳይቀርብ ይደረግ ነበር ። ኤድዋርድ የፈ
ጸማቸው ግድያዎች ሁሉ አላስፈላጊዎች ነበሩ ። ዳኛው ቤ
ከር በሚያሚ የዳዴ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተቀምጠው ክርክሩን
ከተቀበሉ በኋላ በዓቃቤ ሕጉ የተነሳውን የወንጀለኛነት
ጥያቄ ሳያወላውሉ ተቀብለው በኤድዋርድ ላይ የዕድሚ
ልክ እሥራት ፈረዱ ።



# ወደር የለሹ አግባቢ

በኒውዮርክ ሎንግ አይላንድ በምትገኝ አንዲት ዘመ
ናዊ ጉጂ አዴል ከእናትና አባቷ ጋር ትኖር ነበር ።
አዴል በጐረቤት ከተማ ማለትም በሜልቪል በሚገኝ
አንድ አንጐላቸው እንጭጭ የሆነ ልጆችን በሚያስለጥን
ተቋም ውስጥ የምትሠራ መልከ ቀና ነርስ ነበረች ። ሰኞ
ነሐሴ 20/1970 አዴል ያለአመልዋ እስከ እኩል ሌሊት
ወደ ቤቷ ባለመመለሷ ወላጅ አባትና እናትዋ በጭንቀትና
በስጋት መጠባበቅ ያዙ ።

አዴል ምንም ቢሆን ከቤቷ ከተለመደው ሰዓት ውጭ
አምሽታ የማትገባ ከመሆኗም በላይ ትሰራበት የነበረበት
ተቋምም ከመኖሪያ ቤቷ የ18 ማይልስ ርቀት የነበረውና
በተንጣለለ አውራ ጉዳና ዳር ላይም ነበር ።

በዕለቱ የምሽት ተረኛነቷ እስከ ሌሊቱ 5 ሰዓት ስለነ
በረ ከቤቷም ትደርሳለች ተብሎ የምትጠበቀው ከዚሁ
ብዙ ባላለፉ ደቂቃዎች ውስጥ ነበር ፣ ሆኖም የነሐሴ 20
ምሽት የእኩል ሌሊት ማብሰሪያው የሰዓት ደውል ቢያን
ቃጭልም የቤተሰቦችዋን በር የሚያንኳኳ እንኳ ብቅ
አላለም ። በሁኔታው ግራ የተጋቡና ክፉኛ የተጨነ
ቁት ወላጅ አባቷም እኩለሌሊቱ ተሻግሮ ሰባት ሰዓት
እንደሞላው ልጃቸው በሥራ ላይ መኖርና አለመኖሯን ለማ
ረጋገጥ ወደ ሱፎልክ እስቴት ስልክ በመደወል ለማረጋገጥ
ሲዘጋጁ በድንገት የመኖሪያ ቤታቸው መጥሪያ ደወል እን

ቃጨለ ። የአዴል አባትም በመደናገጥ በሩን ሲከፍቱ ከሁ
ለት ፖሊሶች ጋር በግንባር ተጋጩ ። ፖሊሶቹ በዚያን ምሽ
ት የመጡት ለምንም ሳይሆን አባቷ በጉጉት ስለሚጠብ
ቋት ስለመልከ ቀናዋ ነርስ ስለ አዴል እንግዳ የሆነና ግራ
የተጋባ መረጃ ለመስጠት ነበር ።

ፖሊሶቹ የወይዘሪቷን የ1970 ሰማያዊ ፎርድ ማቬ
ሪክ ሞዴል መኪና ከቤታቸው ሩብ ማይልስ በሚርቅ በአ
ንድ ሰው እልባ መጠለያ አጠገብ ለዩት ባለ ሁኔታ ማግኘ
ታቸውን ገለጹ ። በመቀጠልም በመኪናው መሪ አጠገብ
ያለው በር ክፍት እንደነበረና የመኪናው ሞተርም
እየሠራ ፡ መብራቶቹም እንዲሁ ቦግ ብለው በርተው እን
ደነበር አብራሩላቸው ። በዚያም መረጃ ቤተሰቦቿ ከፋኛ
መረበሻቸውን ፖሊሶች ስለተገነዘቡ ለማረጋጋት ሲሉ
ምናልባት በእግርዋ ባልታወቀ ምክንያት ለመሄድ ፈልጋ
ወደ ቤቷ መጥታ እንደሆነ ለማወቅ ሲሉ የመጡ መሆና
ቸውን አስረዱ ። መኪናውን ሲያገኙ በመሪው በኩል
ያለው መስተዋት መሰባበሩን ለአቶና ለወ/ሮ ኮሀር
ከመናገርም ተቆጠቡ ፡ ያም የተደረገበት ዋናው ምክንያት
ቤተሰቦቿን ከባሰ ድንጋጤ ለማዳን ሲባል ነበር ። ከመስ
ተዋቱ የአሰባበር ሁኔታና በመኪናው የፊት መቀመጫዎ
ችና ወለል ላይ የሚበለጨለጩ የመስተዋት ስብርባሪዎች
ተበታትነው ከመገኘታቸው አኳያ ለመገንዘብ እንደተቻለው
ከነጂው በኩል የሚገኘው የመኪናው መስተዋት ሊሰበር
የቻለው መስተዋቱ ተዘግቶ በነበረበት ሁኔታ ነበር። መኪና
ው በምንም ሁኔታ ግጭት ያልደረሰበት ለመሆኑ ሌላ
ው ማረጋገጫ በመኪናው አካል ሌላ የተጣመመ ወይን
ም የተገጨ አካል ያለ ሙኖሩ ነበር ። ከዚህ ሁሉ ሌላ
ግን ፖሊሶች በአንድ ማስታወሻ ደብተር ላይ በጣም
በተንቀጠቀጠ እጅ የተሞነጫጨረ የጽሑፍ መልዕክት



ያገኙ ሲሆን መልዕክቱን ግን ለቤተሰቦቿ ከመናገር
ተቆጥበዋል ። ማስታወሻው የተገኘው በመኪናው የጐን
ኪስ ውስጥ ሲሆን በውስጡም 50 ዶላርና ጥቂት ዝር
ዝሮች ተገኝተዋል ፡ ያም የሚያመለክተው ቢኖር በወ
ጣቷ ላይ የደረሰው አደጋ ከዘረፋ ጋር ያልተያያዘ መሆ
ኑን ነው ። በመሆኑም በወይዘሪቷ ላይ የደረሰው አደጋ
ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል ገመቱ ።

ፖሊሶቹ የተገኘውን ማስታወሻ ሲያገላብጡ በመጀ
መሪያዎቹ ሰባት ገጾች ላይ የተመዘገበው በመኪናው የተሞ
ላው የቤንዚን መጠንና የተጓዘበት ርቀት ነበር ። አዴል
የመኪናዋን የቤንዚን ፍጆታ ለማወቅ ስትል በመኪናዋ የቤ
ንዚን መያዣ ሙሉ ቤንዚን ባስሞላች ቁጥር የምትመዘግብ
ሲሆን በዝርዝር ምትመዘግብበትን ማስታወሻ መያዝና በማ
ስታወሻውም ላይ መጻፍ የጀመረችው ግን ባለፈው ጥር ወር
መኪናውን ከገዛችበት ጊዜ ጀምሮ ነበር ። አዴል መኪናዋ
ቤንዚን ቆጣቢ የመሆኗ ሁኔታ ያስደስታትም ነበር ። ዕለታዊ
ምዝገባውንም ታካሄድ የነበረው በአንድ በኩል ለጓደኞቿ
በማሳየት ልትኩራራባቸው ትፈልግ ስለነበር ሲሆን ፡ በሌላ
በኩል ደግሞ ራሷን በፕሮግራምና በቁጠባ መምራት
ትወድ ስለነበር ነው ። ከቤተሰቦቿና ከቅርብ ጓደኞቿ ለማ
ወቅ እንደተቻለውም አዴል ጥሩ የመረጃ መዝጋቢ ነበረች ።
በሚቀጥሉት የማስታወሻዋ አራት ገጾች ላይ የተጻፉት
መረጃዎች ግን ቀደም ብለው ከተመዘገቡት ተከታታይ
ጉዳይዎች ጋር የማይገጥሙ በችኮላና በመንቀጥቀጥ የተ
ጻፉና በጣም የሚዘገንን ስሜትን የሚቀሰቅሱ ሆነው ተገ
ኝተዋል ። መልዕክቱ ሰማያዊ ቀለም በተሞላ ብዕር የተ
ሞጫጨረ ነበር ።

መልዕክቱም ሲነበብ እንደሚከተለው ነው “ እንድ
ሰውዬ መኪናውን ከጐኔ መንዳት ጀመረ ። በላግቲኮስ



ውብዋ አዴል ኮሀር፣ በኒውዮርክ ብቸኛ የሎንግ አይላንድ የመናፈሻ መንገድ እምሽታ ከምትሠራበት ወደ ቤትዋ ለመሄድ በምትነዳበት ሰዓት የተጠለፈችው ናት ፣ ወጣትዋ ከመኪናዋ ተገድዳ ከወጣች በኋላ ተደበደበች ፡ ያለ ፍላጐትዋ የፍትወተ ሥጋ ተካሄደባት ፤ ከታነቀች በኋላ ገዳይዋ በላይዋ ላይም በመኪና ሄደባት ። /ኒውዮርክ ዴይሊ ኒውስ ፎቶ/



እንዳቆም ይነግረኛል ከአንድ መስመር ላይ በመሆን እየተከታተለኝ ነው ። . . . ልቀድመው ፈጽሞ አልቻልኩም እስከ 65 ደርሻለሁ ። አሁን ከጐኔ መሆኑን ቀጠለ ፤ ጢም ሙነጽር . . . ረጅም ፀጉር . . የሂፒ ዓይነት . . ሰማያዊ ሸሚዝ… የመኪናዋ ሞዴል ቴምፐስት… ቀለምዋ ስስ አረንጓዴ . . ቲ. 37 . . ”

ከመልክቱ አፃፃፍ ሁኔታ ለመገንዘብ እንደተቻለው ወይዘሪቷ መኪናዋን በማሽከርከር ላይ እያለች በችኮላ የሞናጫጨረችው መሆኑ ያስታውቃል ። የመልዕክቱ መጨረሻ ግን ራሳቸውን የቻሉ ሁለት ቃላቶችን የያዘ ነበር ። በጣም በተንቀጠቀጠ እጅም የተጻፈ ይመስላል ። “ ጥቁር . . ሱሪ . . . ” የመጨረሻው ቃልም በገጹ ላይ የተሳበ ቅርጽ ነበረው ።

ወይዘሪቷም በሌላ መኪና ላይ የተቀመጠውን ሰው ሱሪ ለማዬት አስቸግሯታል ፡ ፖሊሶቹ እንደገመቱት ግን ያንን ቃል ልትጽፍ የቻለችው በአንድ ወና የመኪና ማቆሚያ አጠገብ መኪናዋን ካቆመች በኋላ ሰውየው ከመኪናው ወጥቶ ወደርሷ እስከ በመጣበት ጊዜ ድረስ እንደሆነ ገምተዋል ።

አዴል 5 ጫማ ከ2 ኢንች ቁመት ያላት ፡ 120 ፓውንድ የምትመዝን፡ዞማ ጥቁር ፀጉር ፡ ብሩህ ዓይን ፡ ለስላሳ የፊት ቆዳ ፡ ቀጠን ያለች ፡ የተዋጣ ቅርጽ የነበራትና በአጠቃላይ ያያትን ሁሉ የምታስደነግጥና ልብ የምትሰልብ ለግላጋ ወጣት ነበረች ። በተለይ ቤተሰቦቿ ያቀረቡት ፎቶግራፍ ውበቷን ያፈካና ብሩህና ሙሉ ገጽታ ያለው ነው ። በዚያ የደስ ደስ ያለው ገጽታዋና ውበቷ ፎቶግራፍ ጀርባ እውነተኛ የአሜሪካ ልጅ የሚል ታትሞበት ነበር ። ፀጉሯን ያበጠረችው ወደኋላ ጣል በማድረግ ሲሆን በጀርባዋ ተነስንሷል ። በዚያም ውበቷ ብዙ ጐረምሶችን ታተ

ራምስ ስለነበር ሊጋብቻ የነበራት ሐሳብ እጅግ የመ
ነመን ነበር ።

በጣም ያስደንቅ የነበረው የአዴል ጠባይ ደግሞ ወደ
ምትሠራበት ማሠልጠኛ ተቋም ስትሄድ የነበራት የአለ
ባበስ ሁኔታ ሲሆን በዚያ አለባበሷም የመዋኛ ልብሷን ከሰ
ማያዊየነርስ ዩኒፎርሟ በታች ታጠልቀው ነበር ፡ በተለይ
አንጐላቸው ያልጐለመሰውን ወይም አንጐለ እንጭጭ
የሆኑትን ልጆች ዋናማስተማር አንዱ የሕክምና ዘዴ ስለነ
በርና ርሷም ስለምታስተምር የዋና የትምህርት ፕሮግራሙ
የርሷ ተራ በሚሆንበት ጊዜ ትጥቁ አይለያትም ነበር ።

በሱፎልክ ወረዳ የነፍስ ግድያ ወንጀል ምርመራ
ቡድን ይሠራ የነበረው መርማሪ የአምሳ አለቃ ቶም
ሪክሞንድ ወደ ወንጀሉ ቦታ በመሄድ ምርመራውን እንደ
ጀመረ በልጅቷ ላይ ግድያ እንደተፈጸመ ወዲያውኑ ተጠ
ራጥሯል ። በዚያም ጥርጣሬ መሠረት ከጥቂት ሰዓት በኋላ
ጉዳዩ እውን ሆነ ፤ ወጣቷ በጠፋች ማግሥት ከሰዓት በፊት
5 ሰዓት ላይ ቢፓታጐ መንደር በሚገኝ የዌብ አውራ ጐዳና
መጨረሻ ላይ 8 ማይልስ ራቅ ብሎ ሁለት ሕጻናት በመጫ
ወት ላይ እንዳሉ ከሂክሸር መናፈሻ አጠገብ በሚገኘው ጫካ
ራቁቱን የተጣለ የሴት በድን ሰውነት አግኝተዋል ።

የትም ተጥሎ በአሳዛኝ ሁኔታ የተገኘው ሬሳ
የማንም ሳይሆን የመልከ ቀናዋና ማራኪዋ ወይዘሪት
ነበር ። በዌብ አውራ ጐዳና መጨረሻ ላይ የወይዘሪቷ
ሬሳ በጀርባው በአሸዋ ላይ ተዘርሮ ተገኘ ። በርግጥ ፊቷ
ሊታወቅ በማይችልበት ደረጃ ተቀጥቅጦ ነበር ። ዓይኖቿም
ተጠፍጥፈው ጠቋቁረዋል ፡ ከንፈሮቿ ተሰነጣጥቀው አብ
ጠዋል ፡ ያ ! ስልካካ አፍንጫ እንዳይሆን ሆኖ በደረሰበት
ድብደባ ተደፍጥጧል ።



በምርመራ የሟቿ አሟሟት ሁኔታ እንደተጣራው
የሞቷ ቀጥተኛ ምክንያት መታነቅ ነበር ። በሰውነቷም
ላይ ጥቁር የመኪና ጐማ አሻራ የሠራ ምልክት በግልጽ
ይታይ ነበር፤ ያም የሚያሳየው ሁኔታ ገዳዩ በድብድባና
በማነቅ የግፍ ድርጊት ላይ ብቻ ያለማቆሙንና በመኪና
ውም በላይዋ ላይ ወጥቶ የነዳባት መሆኑን ነበር ።ከሬሳው
ምርመራ እንደ ተረጋገጠው በሬሳው ብልት የተባዕታይ
ዘር ተገኝቷል ፡ ይህም የሚያመለክተው የግዳጅ ፍትወተ
ሥጋ መፈጸሙን ነው ።

ሪክሞንድ ከቤተሰቧ የተሰጠውን የደመ ሙሉና
የውብ ልጃገረዲቷን ፎቶግራፍ ያለርህራሄ ከተጨፈጨ
ፈውና ከተበላሸው የወይዘሪቷ በድን ጋር የሚያወዳድ
ርበት ምንም መለያ ለጊዜው አላገኘም ። ሆኖም ሌሎች
እሷነቷን የሚያረጋግጡለት ምልክቶችን በአማራጭነት
ወሰደ ። አንዱ ቁልፍ ዘዴ በገዳዩ ያልተወሰዱት የልጃገረ
ዲቷ ጌጣጌጦች ነበሩ ። በዚያም መሠረት ሪክሞንድ ወጣቷ
ከቤቷ ከመውጣቷ በፊት አድርጋቸው የነበረውን ጌጣጌጦች
ቤተሰቦቿ እንዲያስመዘግቡ አድርጐ ገዳዩ ሳይወስዳቸው
ከቀሩትና ከሬሳው ጋር ከተገኙት ጋር አንድ በአንድ በዝ
ርዝር አወዳድሮአቸዋል ። ገዳዩ ሳይወስዳቸው የተገኙት
ጌጣጌጦች በግራ እጅዋ ላይ የመዳብ ብራስሌት ፡ የአንገት
ሀብል ከነመስቀሉ ፡ በቀኝ እጅዋ ላይ የታይሜክስ ሰዓት ፡
ከግራ እጅዋ በ3ኛና 4ኛ ጣቶቿ ላይ አንድ ባለሁለት
ልብ የአልማዝ ቀለበትና ከውድ ድንጋይ የተሰራ ቀለበት
ነበሩ ። በዚያው በዌብ አውራ ጐዳና ቁጥቋጦዎች ሬሳው
ከወደቀበት 7 ጫማ ያህል ራቅ ብሎ ሁለቱን ቁርጥራጭ
ቢጫ የመዋኛ ልብሶች ፡ ከ5 ጫማ በኋላ ደግሞ አንድ ሰማ
ያዊ የነርስ ዩኒፎርምና ነጭ ማላበሻውን አግኝተዋል ።

በመሆኑም በአሰቃቂ ሁኔታ የተገደለችው ወጣት ባሏታ
ሰበ ሁኔታ የተሰወረችው ውብ ነርስ አዴል ኮሀር ነበረች ።

በዘመኑ የአዴል ኮርሀ ጉዳይ በመላው የኒውዮርክ ከተ
ማና በአካባቢው ልዩ ስሜትንና ሁኔታን ቀሰቀሰ ። እነዚያ
ም ሁኔታዎች በአንድ በኩል ሴቶች በማህበራዊ ሕይወት
ሊኖራቸው የሚገባው ደረጃ ከወንድ ወንድሞቻቸው ጋር
እኩል መሆን ይኖርበታል እየተባለ ስለሴቶች ነፃነት ከፍ
ተኛ እንቅስቃሴ የሚደረግበት ዘመን ሆኖ በአዴል ላይ ከሰ
ባዊ ርኅራሄ ውጭ ድርጊት መፈጸሙና በሌላ በኩል ደግሞ
አዴል ኮሀር ወደሞት እፋፍ በፍጥነት እየተንዘችያንን ማስ
ታወሻ ለመጻፍ የመብቃቷ ወኔና ቆራጥነት ነበሩ ።

መርማሪው በፖሊስነት ከተቀጠረበት ጊዜያት አን
ስቶ ከ300 ያላነሱ የነፍስ ግድያ ወንጀል ምርመራዎች
እንዲያጣራ የታዘዘ ቢሆንም ይኸኛው ግን በጣም ለየ
ት ያለና ፈታኝ ወንጀል ሆኖ ማግኘቱን አጥብቆ ተናግ
ሯል ። መርማሪው ሪከሞንድ ግዙፍና ፀጉሩ ጥቁር ፣
ቁመቱ 6 ጫማ ከ2 ኢንች ፣ 225 ፓውንድ ክብደት
ና 50 ዓመት ዕድሜ የነበረው ሲሆን አቋሙ የእግር ኳስ
ተጫዋችን ይመስል ነበር ። በፀባዩ ቀልደኛና ደስተኛም
ነበር ። ተወላጅነቱ ከብሩክሊን ሲሆን በትምህርት ረገ
ድም ከፋርሚንግዴል ኒውዮርክ የብሔራዊ ዩንቨርሲቲ በሕ
ግና በክሪሚኖዎሎጂ ዲግሪውን ተጎናጽፏል ፣ እንዲሁም
በሬሳ ምርመራ ሳይንስ ከአሜሪካን የሬሳ ምርመራ ሳይንስ
አካዳሚ ሌላ ዲግሪ አግኝቷል ። በሁለተኛው የዓለም ጦር
ነት ወቅትም በአሜሪካ በኩል በተባበሩት መንግሥታት
ባሕር ኃይል ውስጥ ግልጋሎት ሰጥቷል ፣ በኮርያም ጦር
ነት በዩናይትድ እስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ውትድርና በኩል
በመሰለፍ አገልግሏል ። ሪከሞንድ ባለትዳርና የሁ
ለት ልጆች አባት ሲሆን ሥራውን የጀመረው የሬሳ



መርማሪ በመሆን ሆኖ ወደኋላ ግን ሙያውን ወደ ፖሊስ
ነት ለውጦታል ።

ከአሜሪካን የሬሳ ምርመራ ሳይንስ አካዳሚ መመረቁ
ለሪከሞንድ ሕይወት ድርብ ጥቅሞችን አስገኝቶለታል ።
በዚህም በሙያው በትርፍ ጊዜ በመሥራት በሎንግ አይ
ላንድ የሠራውን የብድር ቤት ዕዳ ለመክፈል ከመቻሉም
በላይ የኑሮ ጫናውን በማቃለል ከነቤተሰቡ በተሻለ
ሁኔታ እንዲኖር ሆኗል ።

ሪከሞንድ ስለሞት ጠለቅ ያለ ዕውቀትና የዳበረ ግን
ዛቤም ነበረው ። በ1963 አዲስ በተቋቋመው የሱፎልክ
የነፍስ ግድያ ቡድን ተመድቦ መሥራት እንደጀመረ
በመጀመሪያ የተሰጠው ሥራ አንድ ከመጠን በላይ
መድኃኒት በመውሰድ የመመረዝ ጉዳት ያጋጠማቸውን
ሰው ጉዳይ መመርመር ነበር ። እኒያው የ62 ዓመት
ባልተቤታቸው የሞቱባቸው ባልቴት በመድኃኒቱ ብረዛ
በቤታቸው በራፍ ላይ ተዘርረው ተገኙ ። እኒያው አሮ
ጊት ኅሊናቸውን ከመሳታቸው በፊት በሹክሹክታ ከመ
ጠን በላይ የማደንዘዣ መድኃኒት መውሰዳቸውን ተና
ግረዋል ።

አሮጊቷ እንደወደቁ ሐኪም ተጠርቶ ዋና ዋናዎቹን
የሕይወት ምልክቶች ከመረመረና ከተመለከተ በኋላ መሞ
ታቸውን አረጋግጦ ሬሳው ወደ ሬሳ ማስቀመጫ እንዲ
ሄድ አዞ ወደቢሮው ተመለሰ ። ሐኪሞችም አሮጊቷ የተ
ፈጥሮ ሞት ስላልሞቱ የግድ የነፍስ ግድያ ክፍሉንማሳወቅ
ነበረባቸው። በዚሁም መሰረት መርማሪ ሪከሞንድ ተመድቦ
ከባልደረባው ጃክ ሺሊንግ ጋር አሮጊቷ ቤት ሲሄዱ በሐ
ዛን የተቆራመዱና ስቅቅ ብለው የሚያለቅሱ መካከለኛ




መርማሪ ቶም ሪከሞንድ “ ታላቁ መርማሪ ” በመባል ሊታወቅ የቻለው የ18 ቀለመ ስስ የሆኑትን ቲ.37 ፖንቲያክ ቴምፐስት መኪናዎችን ማጣራት በማድረጉና ማየርን በማግባባት ሳያስበው የፈጸመውን ወንጀል በፈቃዱ እንዲያስረዳ በማድረጉ ነው ።



ዕድሜ ያላቸው ሴት ያገኛሉ ። ሴትየዋም የሚች የአክስት ልጅ መሆናቸውን አስተዋወቁ ።

ቪሊንግ ከሚች የአክስት ልጅ ጋር ሲያወጋ ሪክሞንድ ሞቱ ከተባሉት ፊት ላይ የተደረገውን ጨርቅ በማንሳት አትኩሮ ከተመለከተ በኋላ “ ጃክ ! በፈጠራችሁ ጌታ ! ዶክተርና ዓየር የሚሰጥ በአስቸኳይ ጥሩ ! ይቺ ሴት አልሞተችም! ” ብሎ ጮኸ። ባቅራቢያው ያለው ሐኪምም በመጣደፍ ወደተባለው ቦታ በመምጣት መድኃኒት በሴትየዋ ልብ ውስጥ በመውጋት ወደ ሆስፒታል እንዲሄዱ ያደርጋል ፤ ሴትየዋም ሆስፒታል በአልጋቸው ላይ ተጋድመው በፈገግታ “ አንተ ወጣት ! እንዴት እንዳልሞትኩ ልታውቅ ቻልክ ? ” በማለት ሪክሞንድን ጠየቁት ። ሪክሞንድም “ አንዳንድ ትንሽ ጥበብ በማድረግ ነው ” በማለት ከቀለደ ብኋላ “ ፊትዎን አትኩሬ ስመለከተው በማቀዝቀዣ ቀዝ ለማስቀመጥ የተዘጋጀ ሆኖ አልተሰማኝም ፤ በተጨማሪ በሰውነትዎ አንድ እንቅስቃሴ እንዳለ ስለተሰማኝ ነው ” ብሎ አስረድቶአቸዋል ።

ሪክሞንድ በአንድ ሁለተኛ መለስተኛ ትምህርት ቤት በ150 ተማሪዎች ፊት ሆኖ ስለ ነፍስ ግድያ ፍልስፍና ሲናገር “ ማንኛውም መርማሪ የነፍስ ግድያ ወንጀል ሥራ አዋቂ ነው ለማለት አይቻልም ፤ በዚህ ላይ ብዙ መርማሪዎች ጉዳዩን አይተው መፍትሔ ሊሰጡት ይገባል ።” ብሎ ነበር ። ያን ትምህርታዊ ገለጻ ያደረገው ለሁለተኛ መለስተኛ ት/ቤት ተማሪዎች በአገር አቀፍ ደረጃ ስለ ሕግ አጠባበቅና አጠቃቀም የሚሰጠውን ፕሮግራም መሠረት በማድረግ ነበር ።

ሪከሞንድ በወንጀል ምርመራ ሥራ እንደረዳት ፕሮፌሰር በመሆን ሎንግ አይላንድ ሱፎልክ ማህበረሰብ ኮሌጅ ውስጥ ያስተምር ነበር ።

የሪከሞንድ የወንጀል ምርመራ ፍልስፍና በእያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት ላይ የተለያዩ ጠበብት ከሚያካሂዱት የሥራ ውጤት የሚመነጭ ነበር ፣ በአንድ የነፍስ ግድያ ወንጀል ምርመራ በየደረጃው የተለያዩ ጠበበት (አዋቂዎች) ይሰማራሉ ፡ ለምሳሌ የአሻራ መርማሪዎች ፣ የፖሊስ ላቦራቶር ጠበብት፣የዱካ ፈላጊዎች፣ ቢፖሊስ ውሻ አሳሽ ፡ ሲሆኑ በመጨረሻም ወንጀለኛው ከታሰረ በኋላ በፍርድ ቤት ለሚኖረው ክርክርና ብይን በእያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት ላይ ራሱን የቻለ የመፍትሔ ሐሳብ ያፈልቃሉ ማለት ነው ።

ሪከሞንድ በዚህ ረገድ እንዲህ ብሎ ነበር “ አንድ ተጠርጣሪ እስር በፍርድ ቤት የጦፈ ክርክር ካልተካሄደ የፖሊስ ሥራ ምን ዋጋ አለው?፡ ስለሆነም የነፍስ ግድያ ወንጀል ምርመራ ሥራ የአንድ ግለሰብ ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱን ሁኔታ የሚመረምሩትም ሙያተኞች የሥራ ልምድና የሙያ እገዛ መሆን አለበት ። ”

ያም ሆነ ይህ በጣም በተራቀቀና ዘመናዊ የሕግ ዕውቀት በስፋት ባለበት ኅብረተሰብ ውስጥ እንደነሪከሞንድ ችሎታው ያደላቸው መርማሪዎች ከፍተኛ ሚና ለመጫወት ቦታ አላቸው ። ሪከሞንድ በጣም ከሚያስቸግሩ ወንጀል ፈጻሚዎች ወይም ምስክር ሰጪዎች መረጃዎችን ሳያስቡት የማገኘት ከፍተኛ ችሎታ ስላለው በሎንግ አይላንድ ፖሊሶች “ ታላቁ አግባቢ ” በመባል ታዋቂነትን አትርፏል ።



ከእንግዲህ ወደ አዶል ኮር ጉዳይ እንገባና አዶል በተገደለች ማግሥት ሌላ ተመሳሳይ የግድያ ወንጀል በአካባቢው እንተከሰተ እናያለን።

በዕለተ ማክሰኞ ነሐሴ 28 ከረፋዱ ላይ አንዲት በፍርሃትና በድንጋጤ የተዋጠች ቀጫጫ ሴት በሱፎልክ ፖሊስ መምሪያ በድንገት ለአቤቱታ ብቅ አለች ። ያቺው እጆቿ እንደጉድ ይንቀጠቀጡ የነበሩት አቤት ባይ ወ/ሮ ጃናይስ ሬንች ነበረች ። ለአቤቱታም ወደ ፖሊስ ጉራ ያለችው አንድ ሰው ለሕይወቷ አስጊ በሆነ ሁኔታ ስለአስፈራራት ለፖሊስ ለማሳወቅና ለማስመዝገብ ነበር ።

የ28 ዓመት ወጣት የነበረችው ወይዘሮ ለፖሊስ ስታስረዳ “ አብሬው እዝናና ነበር። ነገር ግን ከተውኩት ጊዜ ጀምሮ እቤቴ በተደጋጋሚ በመምጣት እንደድሮው እንድሆንለት ተለማመጠኝ ፡ ዛሬም እንደልማዱ መጥቶ ከሌላ ወንድ ጋር መዝናናት መጀመሬን መስማቱን ከነገረኝ በኋላ እውነቱን ካልተናገርሽ እገልሻለሁ ብሎኛል ። እኔም ዕውነት የሚገለኝ ስለመሰለኝና መንፈሴም ስለተረበሸ ለማመልከት መጥቻለሁ ።” ብላለች ። የወይዘሮዋ ከንፈሮች ይንቀጠቀጡና ዓይኖቿም እንዲሁ የእንባ ዘላላ አዝለው እንባ ያጉርፉ ነበር ። የፖሊሶቹንም ሁኔታ በማየት “ እባካችሁ አንድ ነገር አታደርጉም እንዴ ” በማለት መወትወቷን አላቆመችም ።

የወንጀል ዕለት ሁኔታ መዝገቡም ሲመረመር ያችው ሴት ቀደም ሲል ሶስት ጊዜ ያው ሰው ለሕይወቷ የሚያሰጋት መሆኑን ያስመዘገበችበት ሰፍሯል ። ከዚያም ሌላ ጎረቤቶቿ ካቀረቡት የጸጥታ መንሳት ሪፖርት በመነሳት ሁለት ጊዜ ሮንዶች ከመኖሪያ ቤቷ ድረስ በመሄድ የገላገሏት መሆኑ ተመዝግቧል ። ያው 42 ዓመት የነበ

የደረሰበትን ችግር ከጠየቁት በኋላ በጥይት መመታቱን ሲገልጽላቸው ወደ አካባቢው የፖሊስ ጣቢያ ወሰዱት ። ከዚያም አንድ ተረኛ መኰንን ወደ ሆስፒታል ያስገባዋል ።

ቶም ሪከሞንድ ወጣቱ ቁስለኛ ወደ ሀውፖውጌ የነፍስ ግድያ ወንጀል ምርመራ ለጥያቄ ቢሄድ በሕክምና ረገድ ምን ችግር እንደሚያስከትል ሀኪሙን ጠይቆ ችግር አለመኖሩ በመረጋገጡ ወጣቱን በአንድ መርማሪ የግል ቢሮ ወስዶ ቤተሰባዊና ወዳጃዊ በሆነ አጠራር “ ሩዲ ! ” በማለት ማናገር ይጀምራል “ ለምን እንደባቢቃለን ፣ ነገሩን ቁርጥ አርገህ አውጣው ፣ እናትህን ማን ተኩሶ እንደገደላት በደንብ ታውቃለህ ፣ እናትህን የገደለው አንተንም እንደማይለቅህ ስላወቅህ ፈርተህ ነው የእናትህን ገዳይ ማንነት የደበቅኸውን ዕውነቱን ተናገር ።” ይለዋል።

ክሎይበር ያም ቢሆን መልስ ለመስጠት ፈራ ተባ ማለቱን አልተወም ፣ መልስ ለመስጠት ክፉኛ ጥርጣሬ አደረበት ። በመጨረሻም “ እሺ በቃ ! ሩዲ እኔ እናትህን ማን እንደገደላት ልንገርህ ፣ ሳልቫቶሪ ላውጌት ነው ፣ ክፉኛ ከናትህ ጋር ተጣልተው ነበር ። አይደለም እንዴ ? ” ብሎ በፈካ ፈገግታ ጠየቀው ። የሳልቫቶሬ ላውጌት ስም መጠቀስ የምስጥሩን ቁልፍ እንዳገኘሁ ሪከሞንድ ከወጣቱ ፊት አነበበው ። ልጁም ሁኔታውን ለማረጋገጥ ራሱን ነቅንቆ “አዎ ርሱ ነበር” አለ ፣ ሪከሞንድም በመቀጠል የተሟላ አስተያየትና ሀተታውን ለማስመዝገብ ይፈልግ እንደሆነ ጠይቆት ስምምነቱን ገለጸለት ።

ክሎይበር ባቀረበውም ሀተታ በሁለቱ መካከል የነበረውን ግጭት ተረከለት ። በተጨማሪ “ እኔ የምኖረው ከሳልቫቶሬ ጋር ሲሆን እኔን ጥሩ አድርጎ ይይዘኝ



ነበር ። የፈለኩትንም ሁሉ ገንዘብ ስለሚሰጠኝ ያንቀባርረኝ ነበር ፣ ለኔ እርሱ እንደአባቴ ነው ።” ብሏል ።

በመንገዱ ላይ ለተፈጸመውም ድርጊት እንዲህ በማለት ተርኳል “ ሲከተለኝ ነበር መሰለኝ ፣ መኪናውን እኛ ጉን ለጉን በመንዳት እናቴን ከመንገድ እንድትወጣ አደረጋት በትክክለኛው የሆነው ነገር ሳይገባኝ ሳለ በናቴ በኩል ባለው መስኮት በመምጣት “ ጃን ! ለምንድነው አዲስ ከያዝሽው ሰው ጋር አንድዬ እንድንገናኝ የማታደርጊው ይላታል ” እናቴ ስሙን ልትነግረው ያልፈለገችውን የሰው ስም ለማወቅ ስለፈለገ ደጋግሞ ጠየቃት ፣ ትዝ የሚለኝ እናቴ ዝም ብላ ስትመለከተው ቆይታ ሳላስበው “ ምን ይዘሃል ሽጉጥ !” የሚል የናቴ ድምጽ ተሰማኝ ። ቀጥሎም በጥይት የመመታት ስሜት ስለተሰማኝ ተመታሁ ብዬ ጮኩኝ ። ሳል በኔ በኩል ዞሮ በሩን ከፈተልኝና እጄን በመያዝ “ አይዞህ አንተን ለመጉዳት አይደለም ባንተ ላይ ምን ጊዜም ጥቃት አላደርስብህም ብሎ ከርሱ ጋር እንደሚወስደኝ በመንገር ከመኪናችን ውስጥ ተሸክሞ አውጥቶ በራሱ መኪና ውስጥ አስገባኝ ። ከዚያም እስከ ማቋረጫው መንገድ ድረስ ካደረሰኝ በኋላ በጣም አልተጐዳሁ እንደሆን ጠይቆኝ ለማምለጥ ጊዜ እንድሰጠው የተገኘሁበት ቦታ ትቶኝ ከመሄዱ በፊት ዕርዳታ እንድጠይቅ መከረኝ ጥሎኝ ሄደ ። ” ብሏል ።

ክሎይበር በግምት 3 ሰዓት ያህል እርዳታ ከጠበቀ በኋላ ለሞተር ብስክሌት ተወዳዳሪዎቹ እጁን ማወዛወዙን ተናግሯል ። ሪከሞንድ ላውጌት ወዴት እንደበረረ ቢጠይቀው “ የትም ሊሆን ይችላል ምናልባትም ቤቱ ሄዶ ይሆናል ። ግን እዚያ ሄዳችሁ ብትፈልጉት ልታገኙት መቻላችሁን እርግጠኛ አይደለሁም ” በማለት መልሶለታል ።

ረው ወዳጅዋ ከሚያሳየው አዝማሚያ በመነሳትም ወይዘ
ሮዋ በሕግ እንድትጠይቀው ምክር ሁሉ ተሰጥቷት ነበር፡፡
ሆኖም ምክሩ ተቀባይነት ባለማግኘቱ በዚያው መሰረት
አልተፈጸመም ። ነሐሴ 28 ለአቤቱታም ስትቀርብ ከመጀ
መሪያው ቡድን መርማሪ አንዱ ” ሰውየው እንዳያስቸ
ግርሽ ከፈለግሽ በእስር እንዲቀርብ ማስደረግ እንችላለን ፤
ሆኖም በመጀመሪያ ራስሽ ክሱን መመሥረት አለብሽ ።
ይህን እኛ በአንቺ ቦታ ተተክተን የምንፈጽመው አይ
ደለም ” በማለት ነግሯት ነበር ። ሆኖም ሬንች አሁንም
ለሰውየው የእሥር ማዘዣውን ወረቀት ከማስቆረጥ ተቆጠ
በች። ይህ ከሆነ ከ5 ሰዓታት በኋላ በሎንግ አይላንድ አውራ
ጎዳና ላይ ከመኪናዋ ውስጥ እንዳለች ባቷ ላይ በጥይት
ተመታች ። ወሬው ግልጽ ያልሆነና አጠራጣሪም ነበር ።
በዚያ ወንጀል ላውጌት የመጀመሪያ ተጠርጣሪ ሆኖ ቀረ
በ ። ያም ከክሬንችና አብራት ከነበረችው የ14 ዓመት
ዕድሜ ከነበራት ዴቮራ ቃል በመነሳትም ጭምር ነበር።
ዴቮራ “ እናቴ ከወንድሜ ጋር ከቤት የወጡት ከምሽቱ
12 ሰዓት ላይ ነበር ። የወጡትም ወደ ብሮንክስ በመኪና
ልትወስደው ነበር ” በማለት ተናግራለች ።

የተጐጂዋ ልጅ ለመርማሪው እንደተናገረችው እና
ትዋ ከመጀመሪያው ጋብቻዋ የተወለደውን ወንድሟን
ሩዲ ክሎይበርን ወደላጉዌት አፓርታማ 21 ምሥራቅ
233ኛ መንገድ ወደሚገኘው ልትወስደው እንደነበርና
ሩዲ ከሳልቫቶሬ ጋር ይኖር እንደነበር ገልጻ፡ “ ሁለ
ቱም እናቴን ለማዬት በምሳ ሰዓት ወጥተው ነበር ፡
ሆኖም እናቴና ሳልቫቶሬ ከፉኛ ስለተጣሉ እናቴ ወደ ፖሊስ
ጣቢያ ልታሳስረው ሄዳ ነበር ። እሷ ስትመጣ ግን ወጥቶ
ቆያት ” በማለት አብራርታለች ።



የሚገርመው እናቱ በሽጉጥ በተመታችበት መኪና
ውስጥ ልክ እንደ አደጋ ከባድ ጉዳይ ሩዲ አልተገኘም ።
ያም ሆነ ይህ ሪክሞንድ ይህንንም ምርመራ እንዲከታ
ተለው ትዕዛዝ ተሰጠው ። የዛኑ ዕለትም አቅራቢያው
ከሚገኘው ከናስዋ ፖሊስ መምሪያ ስልክ ተደውሎ መ
ልዕክት ይደርሰዋል ። መልዕክቱም “ አንድ ሩዲ
ክሎይበር የተባለ ወጣት በሁለት ጥይት በመመታት
ቆስሎ በመካከለኛው አጠቃላይ ሆስፒታል ውስጥ ስለሚ
ገኝ ምናልባት ትፈልጉት እንደሆን ነው የደወልንላችሁ ”
የሚል ጥሪ ነበር ። የተገኘው ልጅ የወ/ሮ ሬንች ነበር ።
በጥሪውም መሰረት ሪክሞንድና ረዳቶቹ ከተኛበት ሆስፒ
ታል ድረስ በመሄድ ክሎይበርን በጥሩ ሁኔታ አገኙት፤ በር
ግጥ ሁለት ጥይቶች ጭኑን ጭረውታል። ጥይቶቹም ሲመረ
መሩ በናቱ ሰውነት ያለፉት ዓይነት መሆናቸው ተረጋገጠ።
ወጣቱም በወቅቱ የሆነውን እንዲገልጽ ተጠይቆ በሚከ
ተለው ሁኔታ አብራራ። “እናቴ መኪናዋን እየነዳች ሳለች
በድንገት ከሌላ መኪና ጋር ተጋጨን ፡ ጉዳቱ እንኳን ያን
ያህል ባይሆንም የዛችኛዋ መኪና ሾፌር ከመጠን በላይ
ተናዶ እናቴን በማስገደድ መኪናዋን ከመንገድ እንድ
ታወጣ ያደርጋታል ። ከዚያም ከመኪናዋ ዘሎ በመውጣት
ሽጉጡን ወደ እናቴ በማነጣጠር መጣባት ፡ ወዲያው ወደ
እናቴ ላይ ከተኮሰ በኋላ እኔን ከመኪናችን ጐትቶ አውጥቶ
ራሱ መኪና ውስጥ ከተተኝ ። ” የክሎይበር ማብራሪያ
መርማሪዎቹ ካገኙት ዝርዝር መረጃ ጋር ይገናኝ ነበር ።

በሎንግ አይላንድ አቋራጭ መንገድ መውጫ ላይ
በሚገኘው ረግረግ ጐዳና የሞተር ብስክሌት ውድ
ድር ሲያካሂዱ የነበሩ ጥቂት ወጣቶች በአንዲት
ጉብታ ቁጭ ብሎ በኃይል ሲወዛወዝ በድንገት ተመለከ
ቱት ፡ ወጣቶቹም ሞተር ብስክሌቶቻቸውን አቁመው

ከጥቂት ሰዓት የዚህ አደጋ ጉዳይ እንደተላለፈ ለሱፎልክ የነፍስ ግድያ ቡድን የብሮንስ የነፍስ ግድያ ቡድን መርማሪዎች ላውጌትን በመኖሪያ ቤቱ እንዳገኙት ሪፖርት አድርገውላቸው ነበር ።

ሪክሞንድም ለክሎይበር በቃል ጥያቄ ያቀረበለትን በማስፈረም ወደ ሱፎልክ አውራጃ ጠቢቃ ወደ ጀርጅ አስፕላንድ ሂዷል ። አስፕላንድ የኒውዮርክ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኛ ሪክሞንድን በማስታወስ “ ከቶሚ ሪክሞንድ የሚቀርቡልኝ ማናቸውም ዓይነት የወንጀል ጉዳይዎች ችግር የለባቸውም ። በጣም በጥንቃቄና ሳይሰለቸው በዝርዝር አጥንቶና አጽድቶ ነው የሚያቀርበው ። በኔ ግምት እስካሁን አሉ ከሚባሉት የመጠቀ መርማሪ መሆኑን እመሰክርለታለሁ ። “ ብሏል ።

የሪክሞንድ መረጃዎች ለታዋቂው ዳኛ ከቀረቡ በኋላ ለውሳኔ ለማቅረብ የወሰደው ጊዜ በጣም አጭር ቢሆንም ላውጌት እስከዚያ የት እንዳለ አልታወቀም ነበር ። በተደረገው የማያቋርጥ ክትትልም የአድራሻው ፍንጭ እንኳን ሊታወቅ አልቻለም ። ሪክሞንድ ግን ያለበት ቦታ ድረስ ጭስ በመላክ በአንድ ዘዴ ካለበት እንዲወጣ ያደረገው ሙከራ ተሳካለት ። ዘዴውም እንዲህ ነበር ፤ ወደሩዲ ክሎይበር ስልክ በመደወል ፖሊስ ጣቢያ ሪፖርት እንዲያደርግ ያዘዋል ፤ ክሎይበርም በታዘዘው መሠረት በጣቢያው እንደደረሰ ሪክሞንድ በቀጥታ ላውጌትን ከግድያው በኋላ አይቶት እንደሆን ይጠይቀዋል ፤ ሩዲም “ ያላየሁት መሆኔን እምላለሁ ፤ ከግድያው በኋላ ፈጽሞ አላየሁትም ፤ ከርሱም ጋር አልተነጋገርንም ፤ የት እንዳለም አላውቅም ።” በማለት ይመልስለታል ።



“ እሺ ! ድንገት ልትነግረው ከቻልክ በነፍስ ገዳዩነት ወንጀል እንደምንፈልገው ንገረው ። እናትህን ለመግደል ሽጉጥ ተጠቅሟልና እንደታጠቀም እናውቃለን ። ስለዚህ ከተገናኘን የተኩስ ልውውጥ እንደሚኖርና እኛም እንደማንለቀው እንዲያውቅ አድርግ ” በማለት ሪክሞንድ ከነገረው በኋላ እንደገና ድምጹን ሳብ በማድረግ “ታውቃለህ ! በተኩሱ ጊዜ ሊገደል እኮ ይችላል ” ይለዋል ።

ጭሱ በዚህ ዓይነት ከተላከ በኋላ ውሎ ሳያድር ነሐሴ 28 ከግድያው ልክ ከአንድ ወር በኋላ የኒውዮርክ ከተማ ጠበቃ የሆነው ዊልያም ኢርልባውም “ ሳልቫቶሬ ላውጌት ጠበቃው እንድሆን ስለጠየቀኝ እጁን ለመስጠት መወሰኑን ነግሮኛል ” በማለት ደወለ ። ላውጌት በሚፈረድበት ጊዜ ጠበቃው በቅጣት ቅነሳ ላይ ብቻ ለመከራከር ይስማማል ። በዚያም መሰረት ከ25 ዓመት እስር በመዳን ላውጌት በ7 ዓመታት እስር እንዲቀጣ ተደርጓል ።

የሪክሞንድ ችሎታ “ ወደር የለሽ ማግባባት ” ሲሆን በዚህም መሰረት የአዴልን ኮህር የግድያ ወንጀል ምስጢር በማውጣጣት ረገድ ታላቅና ወሳኝ ሚና ተጫውቷል ። በአዴል ጉዳይ በመጀመሪያ ጸጉር የሚሰነጠቅበት የምርመራ ሥራ መካሄድ ስለነበረበት ሪክሞንድና ረዳት መርመሪዎቹ ያተኮሩት በገማው አሻራ ላይ ነበር ።

ነፍስ ገዳዩ በሬሳው ላይ በተመላለሰበት ጊዜ የጉማውን ቅርጽ በአሸዋው ላይ ቁልጭ አድርጎ አትሞ ትቶታል ። ምርመራው ከዚህ ፍንጭ በመነሳት በዝርዝር ሲካሄድ ሊደረስበት እንደተቻለው ወጣቷን ነርስ በዚያ አሸዋማ ቦታ ያመጣቻት መኪና ከቆመችና ከተጠመዘዘች በኋላ በከፍተኛ ፍጥነት መነዳትዋ ነበር ። ይህ መደምደሚያ ሊደርስበት የተቻለው የላቦራቶሪ ጠበ

ብት በአሸዋ ጉብታዎች ላይ የጉማውን እንሽርት በማጥናት ከሰጡት ሐሳብ በመነሳት ነበር ። እንደኛው መርማሪ “የመኪናው ነጂ በሬሳው ላይ ወጥቶ ከሄደበት በኋላ ተጠመዘዘ ። ከዚያም በችኮላ ከዚያ ቦታ በሯል ። ስለዚህ ዱካዎችን በጥራት በማጥናትና በመከታተል የተከናወኑ ድርጊቶችን ለማወቅ ይቻላል ።” ብሏል ።

በዚህም መሰረት ሪክሞንድና ረዳት መርማሪዎቹ የጉማው ቅርጽ ምልክት በፎቶግራፍ እንዲነሳና በእምሳያው ሰው ሰራሽ ቅርጽ እንዲሠራለት አዘዙ ። ባጭሩ የጉማው “የእጅ አሻራ” መሆኑ ነው። የገዳዩ መኪና ከተገኘች የጉማው የፎቶግራፍ ምስል ዋጋ ቢስ ሊሆን ይችላል ። ሆኖም ለመርማሪዎች ዋና የማወዳደሪያ መረጃ በአሸዋው የተተወው ቅርጽ በመሆኑ የገዳዩን መኪና ለማግኘት እንደሚያዳግታቸው ተማምነው ነበር ።

የሪክሞንድ ተከታይ ግብ (ዓላማ) ተጠርጣሪውን መኪና ማግኘት ነበር ። በፖንትያክ የተሠራ አረንጓዴው ቲ. 37 ሞዴል ቴምፐስት መኪና ያለበት ቢደረስበት ገዳዩን ለማግኘትና ለማብሰር አንድ ከፍተኛ እርምጃ መሆኑም ተረጋገጠ ።

ሪክሞንድ በዚህ ረገድ ያለውን ጉዳይ ለመከታተል ያመቸው ዘንድ ጀራርድ ጉዛሎፍን ወደ ሪቨርሄድ ጣቢያ በመላክ የመኪናው የመጨረሻ ሞዴል ባለቤት የሆኑትን ከመመዝገቢያው ማህደሮች አገላብጦ እንዲያቀርብ መመሪያ ሰጠው ።

ፍሊጋው በአረንጓዴ ቅብ ብቻ ሳይወሰን አመዳማና የሰማያዊ ቀለም ባለንብረት የሆኑትን ሁሉ እንዲያጠቃልልም ተጨማሪ መመሪያ ሰጥቶታል ። ወይዘሪትዋ ስለመኪናዋ ቀለም ስትገልጽ ደማቅ ቀለም አለመሆኑን አመልክታ



ስለነበር ጥቁር ና ቀይ የመሳሰሉትን የደማቅ ቀለሞች ቤተሰብ ከዝርዝሩ ውስጥ ሰረዛቸው ፣ የሆኖ ሆኖ በሳግቲስኮ መናፈሻ ጉዳና ፈካ ያሉ ቀለሞችን የሚቀይሩ የጋዝ ትናንሽ መብራቶች ስላሉ ሟችዋ አረንጓዴ የመሰላት በስህተት ሊሆን ይችላል የሚልም ግምት ተወስዷል ። በመሆኑም ሪክሞንድ ደማቅ ቀለም ያልሆኑትን ቴምፐስት በሙሉ እንደገና እንዲያያቸው ወሰነ ።

ጉዛሎፍ በሪቨርሄድ ዙሪያ ከ70 ማይልስ ጉዞ በኋላ ሪክሞንድ ባወጣለት ዋና ዋና የመኪናው መለያና ምልክቶች ቀለም ፣ ቅርጽ ወዘተ 80 የተመዘገቡ የቴምፐስት ሞዴል መኪናዎች ዝርዝር ይዞ ከተፍ አለ ።

ዝርዝሮቹምእንደሚከተለው ተከፋፍለው ተደላደሉ ። ለመርማሪ ቶማስ ማንሴልና ለመርማሪ ሪቻርድ ዲን ዘጠኝ ስሞች ፣ ለመርማሪ ጉዛሎፍና ለኮንራድ አልት የቀሩት ስሞች ከዚያም የያንዳንዳቸውን ተሽከርካሪ ባለቤት ማንነትና ምንነት የማወቅ ዘመቻ በሰፊው ተካሄደ ። ጉዛሎፍና አልት ከእያንዳንዱ የቴምፐስት ባለቤት ምርመራ በኋላ እየደወሉ የተገኙትን ውጤቶች ያሳውቁት ነበር ። የአንዳቸውም ሪፖርት ለገዳዩ ከተሰጠው መለያ ጋር ተመሳስሎ ሊገኝ አልቻለም ። አንዳንድ በዕድሜ የገፉ አዛውንት ነበሩበት ፣ አንዳንዶቹም ሴቶች ነበሩ ፣ ከነዚህ ሌላ ግን አንድ ጸጉረ በራ ሰው ባለቤቱን ከመኖሪያ ቤታቸው ካደረሰ በኋላ ከሌላ ኮረዳ ጋር ወደ ሆቴል ሄዶ ኖሮ በጉዳዩ ተደናግጦ ኃጢአቱን ተናዘዘ ።

በሌላ በኩል ደግሞ ማንሴልና ዲን በቴሌፎን ሊያስተላልፉለት የፈለጉት ሪፖርት ከጓደኞቻቸው ሁሉ ለዩትያለ ሆኖ ተገኘ ።በዕለቱ ክትትሉን ልክ እንደጀመሩ ያልጠበቁት እክል አጋጥሟቸው ነበር ። ስለሆነም የአይዴል ኮህር የምሥ

ራቅ ስሊፐን መንደር የሚያካልለውን መካከለኛውን ስሊ
ፐን ለመጎብኘት ሄዱ ፣ የመካከለኛው ስሊፐ ትክክለኛው
አድራሻም 185 ሃውቶርን አውራ ጐዳና ነበር ። ሊያገኙት
የፈለጉት የቴምፐስት ባለቤት ሲታይ ደግሞ ሴት ከመሆ
ኗም በላይ ስሟ ሊንዳ ሚየር ሆና ተገኘች ።

መርመሪዎቹ ባገኙት አድራሻ በመመራት ከቦታው
ሲደርሱ ያገኙት በአትክልት ያጌጠ አፓርታማ ሲሆን
የመውጫና መግቢያውን እንደገና በመመልከት የያዙት
አድራሻ ትክክለኛ መሆኑን አረጋገጡ ፣ ከዚያ በኋላ
ወደ ቤቱ በመጠጋት ደወል ደወሉ ። የደወሉን ድምጽ
ስምታ የመጣችው ወ/ሮ ሊንዳ ሚየር በማለት ራሷን ያስተ
ዋወቀች ቀጠን ያለች መልከ መልካም ባለጥቁር ጸጉር
ነበረች። ማንሴልም " የ1970 ቴምፐስት ቲ.37 ሞዴል
በስስ አረንጓዴ የተቀባች መኪና ባለቤት ነሽን?" በማለት
ጠየቃት ርሷም " አዎን ነኝ " በማለት መለሰች ።
ከዚህ በኋላ ጥያቄና መልሱ ቀጠለ ።

ጥያቄ " ካንቺ በስተቀር ሌላ የሚነዳት ሰው አለን ? "
መልስ " አዎን ! ባለቤቴ ይነዳታል "
ጥያቄ " ባለቤትሽ የት ይገኛል ? "
መልስ " ቤት ውስጥ ይገኛል "

" እንግዲያውስ ወደውጭ እንደዩ ብቅ እንዲልልን
ብታደርጊ " ሲልዋት ወጣትዋ ወ/ሮ ወደቤቱ ዘወር በማ
ለት " ቦብ ! እባክህን እንደዩ ብቅ ብትል " ትለዋለች ።

ወዲያውኑ አንድ ዘለግ ያለ ወጣት ጐርምሳ ሲመጣ
ታዩ ። ማንሴልና ዲን ጐረምሳውን ሲያዩት ርስ በርሳቸው
ተጐሻሸመው ጐርምሳውን ገና እንደተመለከቱት የአዴል
ኮሀር ገዳይ ፍለጋ ጉዳይ የተጠናቀቀለት መሰላቸው ።



ጐረምሳው ማም ፣ ረጅም ጸጉር ያለውና መነጽር
ያደረገ ነበር ። እነኝህም ቢሆኑ አዴል ኮሀር በማስታ
ወሻ ደብተሯ የጠቀሰቻቸው ቁልፍ ምልክቶች ነበሩ ።
ዲንም " ከኛ ጋር ወደ ፖሊስ ጣቢያ ለጥያቄ እንድትሄድ
እንፈልግሃለን " በማለት አሳወቀው ። ሮበርት ማየር ያለ
ምንም ማወላወል እንዳሉት አደረገላቸው ። በዚያም መሰ
ረት ወደ ነፍሰ ግድያ ወንጀል ምርመራ ቡድን ቢሮ በመ
ውሰድ ሪከሞንድ ፊት አቀረቡት ። ሪከሞንድም ከመቅጽፈ
ት ማንነቱን ሊደርስበት ቻለ ። በፊቱ ላይ ይታይ የነበረው
ፈገግታ ጠቆረ። ወደ መርማሪዎቹም ዘወር በማለት " ኑዛ
ዜውን በበጐ ፈቃድ እንዲሰጥ ለማድረግ ከአሥር ደቂቃ
የበለጠ የሚወስድባችሁ ከሆነ መከላከያችሁን እንድታቀር
ቡ አሳስባችኋለሁ " በማለት አሾፈባቸው ።

ሪከሞንድ በማሾፍ መልክ እንደተናገረው ኑዛዜውን
ለማግኘት 10 ደቂቃ አልፈጀባቸውም ። የ23 ዓመቱ ወጣት
ራሱን በትንሽዋ ቢሮ ካመቻቸ በኋላ በንዴት የታፈኑ
እሮሮዎችን ማንቆርቆር ጀመረ ። " በሽተኛ ነኝ . . . በጣም
በሽተኛ በመሆኔ ዕርዳታ ያስፈልገኛል " በማለት ያመ
ካኝ ጀመር ። መርማሪዎቹም " ጉዳዩ ስለምን እንደ
ሆን ታውቀው የለምን ? ለአንተ የሚደረገው ነገር ከመደ
ረጉ በፊት የተደረገውን በሙሉ እንድትነግረን እንፈልጋ
ለን " በማለት ጠየቁት ። ማየርም ባዶ አየር የሚመለከት
መስሎ በፈዘዘ አስተያየት መርማሪዎቹን ተመለከተ ።
ለመርማሪዎቹም ጊዜም ቁልፍና ወሳኝ በመሆኑ በት
ክክል ይናዘዝ ይሆን ? ወይስ ጉዳዩን ያዳፍንብን ?
በትክክል አልያዝነው ይሆን ? ወይም ይዘነጋዋል ? በማ
ለት ሲጨነቁ ፣ ሲያወጡና ሲያወርዱ ከቆዩ በኋላ "የምት
ነግረን እኮ መቼ እንደፈጸምከው ? . . . . እንዴት እንደፈጸ
ምከው . . . ብቻ ነው ? . . . " በማለት ማግባባት ቀጠሉ።



ሮበርት ማየር (ቀኝ) በቁጥጥር ሥር በሱፎልክ ካውንቲ ፖሊስ ዋና መምሪያ በቁጥጥር ስር ከዋለበት ወደ እስር ቤቱ ሲወሰድ። ማየር የተፈረደበት ባደረገው አሰቃቂ ግድያ ለ25 ዓመት ዕድሜ ይፍታህ ነበር። /ኒውዮርክ ደይሊኒውስ ፎቶ/



ሪክሞንድም የሚካሄደውን የጥያቄና መልስ ልውውጥ ሚዛን ከበር መልስ ይቆጣጠረው ስለነበር በጣም በተኮሳተረ ፊቱ ወደሪክሞንድ በድንገት ዞረ። ሪክሞንድም ወደ ማየር በማምራት እጁን በማየር ጀርባ ላይ በማስቀመጥ በለሰለሰና ቁርጥ ባለድምጽ "ነገሩ የሆነው ትላንት ማታ አይደለምን?" አለው። ማየርም የአዎንታ አንገቱን ነቀነቀ። ሪክሞንድ አሁንም የተጠርጣሪውን ጀርባ መታ መታ በማድረግ "ልጅ! አሁን ከሁለቱ ጓደኞቼ ጋር ራስህን አስተካክልና ሁሉን ነገር በዝርዝር ንገራቸው ፣ እኛም የሚያስፈልግህን ዕርዳታ በሙሉ እናደርግልሃለን።" ይለዋል ፣ ማየርም ይህን ሲሰማ "ሁሉንም ነገር እነግራችኋለሁ" በማለት ኑዛዜውን ጀመረ። ሪክሞንድ ለማየር ያለውን ሕጋዊ መብት አንድ በአንድ ካነበበለት በኋላ ማየር እንደጉድ ኑዛዜውን ይዘከዝከው ጀመር። በዚህም መሰረት "ያቺ! ወጣት ልጅ" ብሎ በመጠቆም ብቻዋን በሳግቲኮስ የስቴት መናፈሻ ጉዳና የምትነዳ የነበረችውን ሲያገኝ መኪናዋን ከመንገዱ አውጥታ እንድትሄድ ካስገደደ በኋላ በአንድ ወና ለማቆሚያ የተሰራ መጠለያ እንድታቆም ማድረጉንና መኪና ዋን ለመክፈት ቢሞክር ቆልፋው ስለ ነበር ወደመኪናው ሄዶ ብረት ካመጣ በኋላ ወደ መኪናዋ ተመልሶ መስኮቱን እንደሰበረ ፣ ከዚያም በርዋን በክፍት እንደተዋት በጣም ብትጮህም አስገድዶ ጉትቶ እንዳወጣት ፣ ከዚያም ከመኪናው ውስጥ አስገብቶ ወደ ቄብ ጉዳና ጫፍ ላይ ወስዶ ስላስቸገራት ትግል እንደገጠሙና ዩኑፎርሟን ፣ መዋኛዋንና የውስጥ ልብሶቿን ለማውለቅ በሚሞክርበት ሰዓት ትታገለው ስለነበር በቡጤ ደህና አድርጐ እንደደበደባት ፣ በዚያም ድብደባ ስለተዳከመች ያለፍላጐቷ የፍትወተ ሥጋ እንደፈጸመና ከዚያም እንቆ ከመኪናው ውስጥ ከጣላት በኋላ መኪናውን በማስነሳት በላይዋ ላይ እንደሄደባት ተናገረ።

ከዚህ የሚቀረው የምርመራ ሥራ ተራ የመደበኛን
የምርመራ ሥርዓት ማጠናቀቅ ሆነ ። ማየር ወንጀሉን
ለመፈጸሙ በሰጠው የእምነት ቃል ላይ ፊርማውን
አሰፈረ ። የጣቶቹን አሻራና ገጽታውን ለፖሊስ ሪኮርድ
ከአስነሳ በኋላ በነፍስ ገዳይነት ተመዘገበ ። ወደ እሥር
ከመወሰዱም በፊት ከባለቤቱ ፣ ጋር ለጥቂት ደቂቃዎች
ቆይታ እንዲያደርግ ተፈቀደለት ። ባለቤቱ የባለቤቱ
እናትና ወላጅ እናቱ ከፖሊስ ምርመራ ቢሮ ድረስ ተከ
ትለውት መጥተው ስለነበረ ለ30 ደቂቃዎች ያህል አነጋ
ገሩት ፣ የተፈቀደላቸውን ጊዜ አጠናቀው ከመሄዳቸው
በፊትም ሪክሞንድን ሲሰናበቱ በተለይ ባለቤቱ “ ለወሰዱት
ርምጃ ላመሰግንዎት እፈልጋለሁ ። ባለቤቴ በጣም በሽተኛ
ሰውነው ። ከዚህ እስር ውጭ ቢሆን ኑሮ ለማንም እንደማ
ይበጅ ይታወቃል ግዳጅዎን በሚገባ ተወጥተዋል “ በማ
ለት አሞግሳለች ። ሪክሞንድም ስለማየር ባለቤት “ የአ
ንድ የተወንጃይ ዘመድ በዘመዱ ላይ ለተፈጸመው ምስ
ጋና ሲያቀርብ ስሰማ የመጀመሪያዬ ጊዜ ነው ” በማለት
ተደንቋል ። በሌላም በኩል አዴል ኮሀር የራስዋን ገዳይ
እንዲጋለጥ ከሞት አፋፍ ላይ ሆና ያደረገችው ጥረት አቻ
የሌለው ነው በማለት አድንቋል ።

የሪክሞንድ መርማሪዎችም በማየር ሪኮርድ በሴቶች
ላይ ባደረሰው አደጋ ከአንድዬ ሁለትና ሶስት ጊዜ ታስሮ
መፈታቱን ተመዝግቦ አገኙ ። የማየር ምስል ሃንቲንግቶን
ውስጥ በሚገኘው በዋልት ዊትማን የገበያ ማዕከል አን
ዱን ሴት በቅርቡ የጠለፈውን ጐረምሳ መልክ እንደሚመስ
ልም ተገነዘቡ . . . በዚያ አደጋ የተጐዳችው የ23 ዓመት
ዕድሜ የነበራት ሴት ማየር ከታሰረበት ድርስ አምጥተ
ዋት አጥቂዋ ራሱ መሆኑን ከፊቱ መሰከረችበት ፣ በመሆ



ኑም ማየር የተወነጀለው በተለያዩ የወንጀል ዓይነቶች
ነበር ።

ጠበቃውም የክርክሩን መንገድና ሁኔታ ለማስቀየርና
ለማሻሻል ጥረት ቢያደርግም የጉዳዩ ክባድነት ማየርን
በቀላሉ ሊገላግለው አልቻለም ። ከሁለተኛ ደረጃ የወንጀል
ግድያ ፍርድ የተሰየመውን በኩዊንስ ካወንቲ ነበር ። ያል
ተረጋጋ ጤና እንደሌለው እንኳን በሚከራከርለት ጠበቃ
በኩል ቢቀርብለትም አዴልን በመግደሉ የ25 ዓመት ጽኑ
እሥራት ተፈረደበት ።

## በተርጓሚው የታተሙ

- ፖለቲካ ኢኮኖሚ ቀላል ቀንብር
- ኮምሶሞል ምንድነው ?
- ፩ቱ ወንጀለኞች—ሲሆኑ በተከታታይ
  የአሁኑ ተከታይ . . .

በ... ድ እጅግ ቀፋፊና ጭጋግ ባዘለ ዕለት በቶኪዮ ከተማ እንደ
የመንግሥት ጤና ጥበቃ መኮንን ነኝ ባይ በሰለቱ የባንኩን መዝገ
ብዓት ለማስከበር በመዘጋጀት ላይ የነበረውን ያልጠረጠረ ዘበኛ
ትህትና በተሞላበትና በተቻኮለ ሁኔታ ገፍትሮ ገባ ፤ ይሁንና ይ...
ሰው በያዘው ዘመናዊ የቆዳ ቦርሣ ውስጥ ያጨቀው ፈዋሽ መ...
ኃኒት ሳይሆን በቅጽበት የሚገድለውን የሳይናይድ መርዝ ነበር ።
በሺዎች በአንድ የኦፔራ አዳራሽ መድረክ በስተጀርባ በሚገኝ የተዋ
ንያን ልብስ መቀየሪያ ክፍል አንዲት የ10 ዓመት ድንቡሽቡሽ የባሌ
ዳንስ ተጨዋች እጅግ በሚዘገንንና በሚያስቀቅ ሁኔታ ተገድላ ተገ
ኘች ። . . . ሎንግ አይላንድ ተብሎ በሚታወቀው ስውራ ጉዳና ማለትም
በኒውዮርክ አንዲት መኪና ከእኩለሌሊት ላይ ባልታወቀ ሰው ተጥላ
ተገኘች ፤ የሆነ ሆኖ የመኪናዋ የፊተኛው ወንበር ሲታይ ሞቶ በተ
ቻኮለ ሁኔታ በማስታወሻ ደብተሯ የፃፈቸው ተገኘ ። . . .

እነዚህና ሌሎቹም ዕውነተኛ የወንጀል ታሪኮች የዐውቁ መርማሪ
ዎችን መድረክ ቁልጭ አድርገው በማሳየት ሕይወታቸውን ለአደባር
ቀዋል ። ያብቁ መርማሪን ችሎታ የሚጠይቁት ተውኔት መሰል ...
ቸውና አ... ቂ ውጤቶቻቸውም "በዓለም የታወቁ የወንጀል መርማ
ሪዎችና ዝነኛ ውጤቶቻቸው" በሚል ርዕስ የሚታ... ...
ታዋቂ መጽሐፍ ወልዷል ፤ ደራሲዎቹ አቀራረብ ስለት ... ...
ያንጠለጥሉና ልብ-ወለድ መሰል ዓይነት ... ... ...
ዝባ የሚያቀርቡና የጋዜጠኛነትንም ሙያ የሚያከብሩ በ... ...
ቸው የምርምር ፖሊሶች የምርመራ ውጤቶችም ... ... ...
ወለድ ታሪኮችን ለሚከታተሉ ሁሉ ለማንፈስ የሚማርኩና ...
የሚያስደስቱ እንዲሁም በሙያ ለተሰማሩ ትምህርታዊ ለ...
ቸው ሙሉ ቀስቶች ለለው ።

ዋጋው ብር